# ቃና ዘገሊላ



ዲ/ን ሄኖክ ኃይሌ

፳፻፲ ዓ.ም

Scanned by CamScanner

ቃና ዘገሊላ

2010 ዓ.ም.
ስምንተኛ ኅትም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!!
© All Rights Reserved

<u>የሽፋን ሥዕል ትርጉም</u>

የሽፋን ሥዕሉ በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል ላይ ተገልጾ የምናገኘውን በዕለተ አርብ የተፈጸመውን የሙሽራው ክርስቶስና የሙሽራይቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ጋብቻ የሚያስረዳ ነው፡፡ ቀዩ ባለ መስቀል አክሊል ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያን የደፋችውን የክብር አክሊል የሚያሳይ ሲሆን የእሾህ አክሊሉ ደግሞ ሙሽራው መድኃኔዓለም ክርስቶስ በሰርጉ ዕለት የደፋውን የእሾህ አክሊል ያሳያል፡፡

<u>የሽፋን ዲዛይን ቅንብር</u>

ሠዓሊ ዘሪሁን ገብረ ወልድ

<u>የጸሐፊው አድራሻ</u>

251 091 2 08 18 29

henoktsehafi@gmail.com



Scanned by CamScanner

## ጦታሰቢያነቱ

በቅዱሳት መጻሕፍት ባሕር እየዋኘ ፣ በምሥጢር ማዕበል እየተማታ
በእመቤታችን ፍቅር ተሞልቶ በውብ ቋንቋ በጥልቅ ምሥጢር ምስጋናዋን ለጻፈ ፤
የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በሚያስደንቁ ድርሰቶቹ ላስጌጠ፣
‹እንዲህ ስትሉ ዋሉ ፤ እንዲህ ስትሉ ደግሞ እደሩ› ብሎ እንደቃና ዘገሊላዎቹ ጋኖች
ኢትጵያውያንን በቃለ እግዚአብሔር ውኃ ለሞላን ፣
የድርሰቶቹን ምሥጢር ስናስተውል እንደ ቃና ወይን ጠጅ ለሚያስክረን
ለኢትዮጵያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ፤ ለኢትዮጵያዊው ያዕቆብ ዘሥሩግ
ለኢትዮጵያዊው ቄርሎስ ፤ ለኢትዮጵያዊው ዮሐንስ አፈወርቅ

**ለቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይሁንልኝ!**

## ምስጋና

ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነ ፤በምሕረቱና በቸርነቱ ለመጻፍ አነሣሥቶ ላስጀመረኝና በረድኤቱ ላስፈጸመኝ ለልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ፤ ስለ እርስዋ አማላጅነትና ስለተወደደ ልጅዋ ሥራ መጻፍን አስጀምራ ላስፈጸመችኝ አክሊለ ርእስየ ለሆነች ለወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ክብር ምስጋና ይሁን!! የቃና ዘገሊላ በዓል ከበዓሉ ጋር ለተባበረለት ‹ከልጅነቴ ጀምሮ ላሳደገኝና ከክፉ ነገር ላዳነኝ መልአክ› ለሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤልም ምስጋና ይሁን!
‹‹ለወገኖቹ በጎ ነገር ያደረገ ማን ነው? እስኪ እናድንቀው›› ሲራ.፴፩፥፱
በየደረስኩበት በማንበብ በጥያቄዎቻቸው ፣ በሃሳቦቻቸው ፣ በበጎ ምኞታቸውና ጸሎታቸው እንድፈጽመው ላበረቱኝ ለሣምራዊት ደመቀ ፤ ለወንድሞቼ ለዲያቆን ዮናስ ገ/እግዚአብሔር (ካፒቴን) ፣ ለዲያቆን ሄኖክ ወ/አገኝ ፣ ለዲያቆን ተስፋ ሚካኤል አሰፋ (ኢ/ር) ፣ ለዲ/ን አቤል ካሣሁን ፤ ለመጽሐፉ መታተም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ ለመንፈሳዊት እኅቴ ለሰላማዊት ተከስተ ፤ ለተወደዱ ወንድሞቼ ለሊቀ ዲያቆናት ጸጋዬ ፣ ለዲያቆን ስምዐ ጽድቅ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ይህ መጽሐፍ ከመታተሙ በፊትና በኋላ ጊዜያቸውን ሠውተው አስተያየታቸውንና የመጻሕፍት ዳሰሳዎችን ላደረጉልኝ መምህራን ቤተ ክርስቲያን ለመልአከ ሰላም ቆሞስ አባ ሰይፈ ገብርኤል ኡብሰን ፣ ለቀሲስ ኅብረት የሺጥላ ፣ ለመምህር አያሌው ዘኢየሱስ ፣ ለዲያቆን ብርሃኑ አድማስ ፣ ለዲያቆን ያረጋል አበጋዝ ፣ ለዲያቆን ማለደ ዋስይሁን  አስበ መምህራንን ያድልልኝ።

## ማውጫ

ገጽ
ርእስ
መግቢያ ..............................................................................................7-10

ክፍል አንድ
የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክ

ምዕራፍ አንድ
ወደ ቃና ዘገሊላ የሚጋብዝ የሰርግ መጥሪያ (ጠማሪ ጽዋዔ) ..........................11-19
ምዕራፍ ሁለት
ሰርግ ቤቱ
፩. በሦስተኛው ቀን.....................................................................21-23
፪. በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ
- የድሆችና የአሕዛብ ሀገር................................................................ 26-29
- የቃና ዘገሊላ ሙሽሮች ................................................................. 29-31
፫. የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች ............................................................ 31-34
- ወንጌላዊው ድንግል ማርያምን የጠራበት አጠራር ...................... 34-35
- የድንግል ማርያም ትሕትና ............................................. 35-38
- የቅዱስ ዮሴፍ በቃና ሰርግ ቤት አለመገኘት ............................ 38-39
፬. ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም በሰርጉ ታደሙ
- ኢየሱስም ደግሞ....................................................... 40-42
- ምሥጢረ ተዋሕዶ ....................................................... 42-44
- ያለ ጋብቻ የተወለደው ጌታ በሰርግ ላይ የመታደሙ ትርጉም... 44-48
- ደቀ መዛሙርቱ ....................................................... 48-49
ምዕራፍ ሦስት
ምልጃና መልስ
፩. የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ
- የሙሽሮቹ ዕጣ ፈንታ ................................................................... 50-51
- ለድንግል ማርያም ማን ነገራት? ............................................... 52-53
፪. የኢየሱስ እናት የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው
- በመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የድንግል ማርያም ልመና ....................... 54-55
- ትእዛዝና ማሳሰቢያ የሌለበት ልመና ............................................ 55-56
- «እናቱ ሳትነግረው በፊት አያውቅም ነበርን?» ............................ 56-57



Scanned by CamScanner

- የልጅዋን ችሎታ የምታውቅ እናት ........................................ 57-63
- ድንግል ማርያም ራስዋ ተአምሩን መፈጸም አትችልም ነበር? .......... 64-67

፫. አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም

- አንቺ ሴት ........................................................................ 67-71
- ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ........................................................ 71-76
- ጌታችን እናቱን ተቆጥቷት ይሆን? ............................................ 76-81
- ጊዜዬ ገና አልደረሰም ........................................................... 81-83

፬. እናቱም ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው

- ትእዛዘ ማርያም /The Command of Mary/ ................................ 83-84
- ጌታ ለእናቱ አገልጋዮቹን እዘዢልኝ አላላትም ................................ 85-86
- ምልጃ የእኛን እርዳታ ይፈልጋል .................................................. 87-88
- በከፊል ብቻ አትታዘዙ ............................................................ 89-90
- ‹እኔን አትስሙኝ› ማለትዋ ይሆን? ............................................. 90-91
- እግዚአብሔር አብ እና ድንግል ማርያም ......................................... 91-94

ምዕራፍ አራት

<u>የቃናው ተአምር</u>

፩. ለአይሁድ የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች ............................ 95-97

፪. ጋኖቹን ውኃ ሙሏቸው ... ቀድታችሁ ሥጡት አላቸው ፤ ሠጡትም

- ረዳት የማይሻው አምላክ ረዳቶች .............................................. 98-101
- በዝምታ የተፈጸመው ተአምር ..................................................... 101-102
- በምልዐት የተፈጸመ ተአምር ..................................................... 102-103
- መልካም የወይን ጠጅ ............................................................ 104-105
- ክርስቶስ እና ሙሴ .................................................................. 105-108
- ዝምተኞቹ አስተናጋጆች ............................................................ 108-110
- የአስተናጋጆቹ ሽልማት ............................................................. 111-112
- መልስ ያልተገኘላቸው ሁለቱ ጥያቄዎች .......................................... 112-114
- ጌታችን ውኃን ወይን የማድረጉ ዓላማ .......................................... 114-116
- ጌታችን የወይን ጠጅን ጠጥቶ ያውቅ ይሆን? ..................................... 116-118
- የወይን ጠጅ ወይንስ የወይን ጭማቂ? ........................................... 118-122

ምዕራፍ አምስት




Scanned by CamScanner

**ከተአምር በኋላ**

፩. የአሳዳሪው ምላሽ

- አሳዳሪ ማለት ምን ማለት ነው? ........................................ 123-125
- ወይኑ መጀመሪያ ለምን ለእንግዶች አልቀረበም? .................. 125-127
- በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም ............................ 127-128
- መልካሙን እስካሁን አቆይተህ መናኛውን ለምን አስቀደምህ?.. 128-131

፪. የተአምራት መጀመሪያ

- ጌታችን ለምን ተአምራትን አደረገ? ....................................... 131-135
- ተአምራቱ አምላክ መሆኑን ሊያሳዩ ይችላሉ? ......................... 135-137
- ጌታችን ከቃና በፊት ተአምር አላደረገም? .......................... 138-139
- በእኛ ዘንድ ብቻ ድንቅ የሆነ ተአምር .................................. 140-141
- ደቀመዛሙርቱ አስቀድመው የተከተሉት ሳያምኑበት ነበር? .... 142-144
- የቃናው ወይን ጠጅ እና የባለ ትዳሮች ሕይወት ................ 144-149

ክፍል ሁለት

**ሰማያዊው ሰርግ**

ምዕራፍ ስድስት

**ሰርግ በሐዲስ ኪዳን**

፩. የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ እንደ ጋብቻ

- ሦስተኛው ቀን ................................................................ 151-153
- ሰርግ ቤት ውስጥ የተገኘችው ሰርግ ቤት ......................... 153-157
- ንስጥሮሳዊና አውጤኪያዊ ጋብቻ ....................................... 157-159
- ወይን እኮ የላቸውም ... ጊዜዬ ገና አልደረሰም.................... 159-165
- ሁለቱ የቃና ሰርግ ቤት ወይን ጠጆች ............................. 165-167

፪. የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደ ጋብቻ

- የአዳምና ሔዋን ጋብቻ ......................................................... 167-171
- ክርስቶስ እንደ አዳም ቤተ ክርስቲያን እንደ ሔዋን ......... 172-178

ዋቢ መጻሕፍት ................................................................ 179-180



Scanned by CamScanner

## መግቢያ

ውድ አንባቢያን ፤ ከዚህ ቀደም ‹ክብረ ክህነት› ፣ ‹ቅዱስ ገብርኤል› ፣ ‹ታቦት በሐዲስ ኪዳን› የሚሉ መጻሕፍትንና ‹ሊቀ ዲያቆናት ሐቢብ ጊዮርጊስ› እና ‹ተግባራዊ ክርስትና› የሚሉ የትርጉም ሥራዎችን በንባብ ገበታችሁ ላይ ማቅረቤ ይታወሳል። አሁን ደግሞ በእናንተ ጸሎትና በእግዚአብሔር ረድኤት ይህችን ‹ቃና ዘገሊላ› የተሰኘች መጽሐፍ ለአፍታ እንድትጎነጩ አቅርቤአለሁ።

የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለትን የመጀመሪያ አንቀጽ መነሻ ያደረገችውና በሰርግ ቤቱ ስም ‹ቃና ዘገሊላ› በማለት የጠራኋት ይህች መጽሐፍ እንደ ሰርግ ቤቱ ስድስት ጋኖች በስድስት ምእራፎች የተከፈለች ስትሆን ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ እንደነበሩት የቃና ጋኖች እነዚህም ምእራፎች እያንዳንዳቸው ሦስት ወይም አራት የንዑስ ርዕስ እንስራን የያዙ ናቸው። ሰይጣን ሲቀባው የኖረውን የክህደት ጥላሸት ጠርገን ካነበብነው እና ካስተዋልነው የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክ እጅግ ብዙ ጉዳዮችን የሚዳስስ ድንቅ የወንጌል ምንባብ ነው። በዚህች መጽሐፍ ላይም በስድስቱ ጋኖች /ምዕራፎች/ ውስጥ በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ትርጓሜ መነሻነት በሰርግ ቤቱ ውስጥ ጥቂት እንድትቆዩ ለማድረግ እተጋለሁ። ምናልባት እስከ አፉ ድረስ ያልተሞላ ጋን ቢኖር ከእኔ የመሙላት ችሎታ ማነስ እንጂ ቤተ ክርስቲያኒቱ የጎደላት መስሏችሁ እንዳታዝኑ ፤ የጠጣችሁት ወይን መናኛ ቢሆንባችሁ ፣ አለዚያም ጣዕሙ ከወይን ይልቅ ‹ውኃ ውኃ› ቢልባችሁ

አሁንም የጸሐፊው ድክመት መሆኑን ተረድታችሁ አቃንታችሁ በመንፈሳዊ ዓይን እንድታነቡ እማጸናለሁ፡፡

የሳባችሁ የጣማችሁ የምሥጢር ወይን ሲኖር ደግሞ ሊቃውንቱ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ልማዱ እንደዚህ ነው ፤ በብዙ ቃላት ያይደለ በጥቂት ብቻ ብዙ ትርጓሜን /ምሥጢርን/ ያመጣል›› (‹እስመ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘከመዝ አምሳሊሁ ያመጽእ ብዙኀ ፍካሬ አኮ በብዝኃ ንባብ አላ በኀዳጥ›) እንደሚሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን የወንጌል ትምህርት ውበት እና ሀገረ ክርስቶስ በሆነችው ኢትዮጵያ እንደ አራቱ ወንዞች አራቱ ወንጌላት እንዴት እንደሚፈስሱ አስባችሁ እንድታደንቁ እጋብዛለሁ፡፡

በዚህ መጽሐፍ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከኒቅያ ጉባኤ በፊት ፣ በኒቅያ ጉባኤ ጊዜና ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ የነበሩ ብዙ አባቶችን በሃሳብ ምንጭነት ተጠቅሰው የምናገኛቸው ሲሆን በትምህርቶቻቸው የተነሣ እንደ ማጣቀሻነት የቀረቡት እነዚህ አባቶች በሁለት ዓይነት መደብ ያሉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ አባቶች ቤተ ክርስቲያናችን የቅድስና ማዕረግ የሠጠቻቸው ቀደምት ክቡራን አበው ናቸው፡፡ እነዚህም እንደ ቅዱስ ሳዊሮስ ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣ ቅዱስ ኤፍሬም ወዘተ የመሳሰሉ ያለ ስጋት የምናነባቸው ጸሐፍት /Safe Fathers List/ ውስጥ የሚመደቡ አበው ናቸው፡፡ የእነዚህ አባቶች ዝርዝር በቅዳሴያችን /ቅዳ. ባስል. ፸፮/ ፣ በስንክሳርና በሃይማኖተ አበው ላይ የተቀመጠ ነው፡፡

ሁለተኞቹ አባቶች በቅዱሳን ዝርዝር ያልተመደቡ እና አንዳንዶቹም በዘመናቸው አወዛጋቢ ሃሳቦችን ያነሡ ሆኖም በነገረ መለኮት መጻሕፍት ላይ

በብዛት እንደ ሊቅ ብቻ /as a Scholar/ የሚጠቀሱት ናቸው። እነዚህን አባቶች በአንዳንድ አስፈላጊ ጉዳይ ስንጠቅስ በጥንቃቄና የቅዱሳን አበውን ትምህርት እንደ መመዘኛ በመጠቀም ነው። ቅዱሳን ከተባሉት አባቶች መካከል ደግሞ ወጣ ያለ ሃሳብ ብናገኝ የምንዳኘው የአበው ስምምነት /Consensus patrum or Consensus of Fathers/ በሚባለው መመዘኛ ነው። ይህም የተለየውን ሃሳብ አበው በተስማሙበት የጋራ ሃሳብ መመዘኛነት ማየት ነው። የአባቶች ስምምነት የምንለው ደግሞ በልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትቀበላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ላይ የተወሰኑ የተረቀቁ ውሳኔዎችን እና በሃይማኖተ አበው የምናነበውን ነገረ ሃይማኖታዊ ድንጋጌን ነው። (PAROUSIA VOLUME XVII ; On THE NICENE AND POST NICENE FATHERS! The Mistery of Death ; Fr. Peter A. Chamberas : The orthodox Brotherhood of Theologians)

ከዚህ ባሻገር በዚህ መጽሐፍ ላይ ከላይ ያየናቸው በሁለት ወገን የተቀመጡ አባቶች እንደ ማጣቀሻ የተጠቀሱት እጅግ ውብ የሆነውን የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ትርጓሜ መነሻ በማድረግም ነው። የእኛን ሊቃውንት ትርጓሜያት አክብሮ ለሚያነባቸው ሰው ‹ወደ ጥልቁ ብወርድ አንተ በዚያ አለህ› የሚለውን ጥቅስ ያስታውሳሉ። በተለያዩ ርዕሶች የሌሎች ሀገራትን ትርጓሜና የቀደምት አበውን ጽሑፎች በየትኛውም ጥልቀት ብናነብ የእኛን ሊቃውንት በዚያ ጥልቅ ጉዳይ ላይም አንዳች ነገር ብለው እናገኛቸዋለን። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ ሌሎች አባቶችን ስንጠቅስ ሀገር በቀል የነገረ መለኮት ሊቃውንትን /Indigenous scholars of theology/ ሃሳብና ትርጓሜ እንደ ዋና መለኪያ በመጠቀም ነው።



Scanned by CamScanner

ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ያነበብኳቸውን እና እንደ ምንጭ የተጠቀምኳቸውን መጻሕፍት በየሥፍራው የጠቀስሁ ሲሆን ለማመሳከር አስፈላጊ ይሆናሉ ባልኳቸው ቦታዎች ላይ የእንግሊዝኛውን ንባብም በግርጌ ማስታወሻ አስቀምጩአለሁ፡፡ ከዚህ ባሻገር በቃና ዘገሊላ ዙሪያ ያነበብኳቸውን በሌላ ወገኖች የተጻፉ ተቃራኒ ወይም አሻሚ ይዘት ያላቸውን ጽሑፎች አንባቢን ወደ ግራ ላለመምራት ምንጫቸውን ሳልጠቅስ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ አካሔድ አስፈላጊ ምላሽ ይሆናል የምለውን በመጻፍ ላይ ብቻ አትኩሬአለሁ፡፡

(ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው በኤፌሶን የነበሩ ሊቃነ ጳጳሳት በዘመኑ ለተነሡ እንደ ግኖስቲኮች ላሉ መናፍቃን መልስ እንዲሠጥላቸው ስለለመኑት ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ለሁሉም ኑፋቄ መልስ የሚሆን ወንጌልን ሲጽፍ አንድ የኑፋቄ ሃሳብም ሆነ የአንድ መናፍቅ ስም አላነሣም፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ‹ሥራን መንቀፍ በሥራ ነው› እንደሚሉት የመናፍቃንን ሃሳብ መልሶ ከማስተጋባት የራሳችንን ትምህርት ብቻ ማስተማር ይጠቅመናል፡፡)

የቃና ዘገሊላ በዓል የሚከበረው ከጥምቀት በዓል ማግሥት በመሆኑና ከበዓለ ከንግሥ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እንደሌሎች በዓላት በጉዳዩ ላይ ሰፊ ትምህርት ሳይሠጥበት በዝማሬ ብቻ ያልፋል፡፡ ቀደምት አባቶቻችን ሲያደርጉት እንደኖሩት በዓላት በየጊዜው ከባሕል ጋር ትስስር እንዲኖራቸው የሚያደርጉ እሴቶች ቢጨመሩባቸው የበለጠ ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህም የቃና ዘገሊላ በዓል አሁን ከሚከበርበት ድምቀት ጋር ‹መጋባት እየቻሉ ሰርግ

የማድረግ አቅም ለሚያጥራቸው፣ ምእመናን የቅድመ ጋብቻ ትምህርት ተሠጥቷቸው በጋራ ሰርግ የሚያደርጉበትና ቤተ ክርስቲያን ልጆችዋን በጋራ የምትድርበት በዓል እንዲሆንና በጉዳዩ ላይ ጥናት ተደርጎ እንዲሠራበት የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ምኞትና ጥቆማ ነው።

በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሪ አድርገን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ውስጥ እንመላለሳለን። ከጌታችንና ከሐዋርያቱ ጋር ወደ ሰርግ ቤቱ እንገባለን። ወደ ጓዳ ዘልቀን የወይኑን ማለቅ አስበን እንጨነቃለን ፣ እመቤታችን ስታማልድ ልጇም ሲማለድ እናያለን ፣ ከአገልጋዮቹ ጋር ውኃ ልንቀዳ ወንዝ እንወርዳለን። አብረን ውኃውን እስከአፉ ሞልተን ጌታችን የሚያደርገውን እንጠብቃለን። ከታዳሚዎች ጋር ወይን የሆነውን ውኃ ቀምሰን እናደንቃለን። መልካሙ የወይን ጠጅ ምነው እስካሁን ቆየ? ብለን ከአሳዳሪው ጋር አብረን እንቆጫለን። ከዚያም ከሐዋርያቱ ጋር በስሙ አምነን ከሰርግ ቤቱ እንወጣለን። ከምድራዊው ሰርግ ቤት ወጥተንም ወደ የቤታችን ሳንገባ ወደ ሌላ ሰማያዊ ሰርግ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ እንታደማለን።

መልካም ንባብ
ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ አንድ

## ለቃና ዘገሊላ የተዘጋጀ የሰርግ መጥሪያ

### (ጦማረ ጽዋዔ)

ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የዮሐንስ ወንጌልን ‹‹የሐዲስ ኪዳኑ ኦሪት ዘፍጥረት›› (The book of Genesis in the New Testament) በማለት ይጠሩታል። ለዚህም ሁለቱን መጻሕፍት በንጽጽር የሚያመሳስሉአቸውን ነጥቦች ይዘረዝራሉ። ኦሪት ዘፍጥረት ‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ› በማለት የሚጀምር ሲሆን የዮሐንስ ወንጌል ደግሞ ‹በመጀመሪያ ቃል ነበረ› በማለት ይጀምራል። ሁለቱም መጻሕፍት ‹በመጀመሪያ...› ብለው በመጀመራቸው የሚመሳሰሉ ቢሆኑም በሁለቱ ‹መጀመሪያዎች› መካከል ግን እጅግ ሰፊ የሆነ ልዩነት አለ። ‹ንባብ ቢያሳብራቸውም ምሥጢር አያስተባብራቸውም› ይላል መጽሐፉም። (ትርጓሜ ወንጌል ዘዮሐንስ)

የኦሪት ዘፍጥረቱ ‹መጀመሪያ› የሰማይና የምድር ዕድሜ መቆጠር የጀመረበትን ጊዜ /ዓመተ ዓለምን/ የሚያመለክት ሲሆን መነሻ ያለው መጀመሪያ ወይም መጀመሪያ ያለው መጀመሪያ ነው። በዮሐንስ ወንጌል ላይ ‹ቃል ነበረ› የተባለበት መጀመሪያ ግን መነሻ



Scanned by CamScanner

የሌለው መጀመሪያ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከዚህ ዘመን ጀምሮ ነበረ የማይባልለት በቅድምና የነበረ አምላክ መሆኑን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱ መጻሕፍት ‹መጀመሪያ› በሚለው ቃል በንባብ ብቻ እንጂ በትርጉም አንድ አይደሉም፡፡

ይሁንና የዮሐንስ ወንጌልን የሐዲስ ኪዳን ዘፍጥረት የሚያሰኙ ሌሎች ነጥቦችም አሉ፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት እግዚአብሔር በስድስቱ ቀናት የፈጠራቸውን ፍጥረታት በመዘርዘር የሚያስቀምጥ ሲሆን ‹የሐዲስ ኪዳኑ ኦሪት ዘፍጥረት› የዮሐንስ ወንጌል ደግሞ ሁሉንም የእግዚአብሔር ፍጥረታት በአንድ ዐረፍተ ነገር በመግለጽ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ፤ ከሆነውም አንዳች እንኳን ያለ እርሱ አልሆነም» በማለት ያስቀምጠዋል፡፡ ‹ሁሉ በእርሱ ተፈጠረ ፤ ከተፈጠረውም አንዳች እንኳን ያለ እርሱ አልተፈጠረም› ማለት ነው፡፡

‹ሁሉ በእርሱ ሆነ› የሚለው ቃል ሁሉ በእግዚአብሔር ወልድ ህልውና መፈጠሩን የሚስረዳ መሆኑን ሙሉ አንቀጹን በማንበብ ለመረዳት እንችላለን፡ በዚህም ከዘፍጥረት አንድ ጋር የሚነጻጸር ሌላ ነጥብ እናገኛለን፡፡ ‹በመጀመሪያ..› የሚለውን የዘፍጥረት አገባብ አንዳንድ ሊቃውንት የወልደ እግዚአብሔር ስም ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ‹አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ› (መጀመሪያ እና መጨረሻ እኔ ነኝ) ሲል ‹መጀመሪያ› የሚለው ቃል ስሙ እንደሆነ ጌታችን ተናግሯል፡፡ ስለዚህ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» የሚለው «እግዚአብሔር መጀመሪያ በተባለ በልጁ ዓለምን ፈጠረ» የሚል ትርጓሜን ይሠጣል፡፡ ይህ ማለት አርዮስ እንዳለው ‹ፈጥሮ ፈጠረበት› ማለት ሳይሆን ቅዱስ ጳውሎስ «ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ ተናገረን» እንዳለው በሥላሴ አንድነት ሰማይና ምድር መፈጠራቸውን ያስረዳል፡፡ «ሁሉ



Scanned by CamScanner

በእርሱ ሆነ ፤ ከሆነውም አንዳችስ እንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» የሚለው ቃልም ይህንን የበለጠ ያብራራልናል። (ዕብ. ፩፥፪)

የዮሐንስ ወንጌልን ‹ኦሪት ዘፍጥረት› የሚያሰኘው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ ደግሞ በሁለቱም መጻሕፍት በምዕራፍ ሁለት ስለ ጋብቻ ተጽፎ መገኘቱ ነው። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት ላይ እግዚአብሔር በአዳም ላይ እንቅልፍን ጥሎ ከጎኑ አንዲት ዐፅም ስለመንሣቱና ሴት አድርጎ ስለ መሥራቱ አዳምም ሚስት አድርጎ እንደወሰዳት የተጻፈ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌልም እንዲሁ ጋብቻ የምዕራፍ ሁለት ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም የሚያሳየን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም አዲስ ፍጥረት ሊያደርገን መምጣቱን እና በገነት በሰይጣን ተንኮል የተሰናከለውን ቅዱስ ጋብቻ ሊባርክ መገኘቱን ነው። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ሆኗል» እንዳለ ሐዋርያው። (፪ቆሮ. ፭፥፲፯)

የሁለቱ ጋብቻዎች ቀናት ጉዳይም እንዲሁ አስገራሚ ንጽጽር ያለበት ነው። ከኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ጀምረን ስንቆጥር የተጻፉት ቀናት ስድስት መሆናቸውን እንቆጥራለን። በሰባተኛው ቀን ስለ ጋብቻ ተጽፎ እናገኛለን። በዚህ መነሻነት አይሁድ የ[1]ሰርግ በዓልን [2]ለሰባት ቀናት ያህል ያደርጋሉ። (ታልሙድ ቅጽ 1 ገጽ 45) በዮሐንስ ወንጌልም ከምዕራፍ ፩፥፳፱ ጀምረን በነገውም (፳፱) ፤ በነገውም (፴፭) ፤ በነገውም (፵፫) የሚሉትን ቀናት

[1] ‹ሰርግ› የሚለው ቃል በእሳቱ ‹ሰ› ሲጻፍ የጋብቻ በዓልን የሚያመለክት ሲሆን በንጉሡ ሠ ‹ሠርግ› ተብሎ ሲጻፍ ግን መስዋ ማለት ይሆናል። (ኪ.ወ.ክ. ገጽ ፲፻፳፩ እና ፳፻፹፪ )

[2] ለምሳሌ ያዕቆብ ልያን ያለ ፍላጎቱ ካገባት በኋላ የሚወዳትን ራሔልን ለማግኘት ሌላ ሰባት ዓመት የተገዛው ከልያ ጋር የነበረውን የሰባት ቀናት የጋብቻ በዓል ከፈጸመ በኋላ ነው። በጦቢትም ታሪክ ይህንኑ እናገኛለን። (ዘፍ. ፳፱፥፳፯ ፤ ጦቢ.፲፩፥፳)



Scanned by CamScanner

ስንቆጥር አራት ቀናትን እናገኛለን፡፡ ከዚህ በኋላ እስከ ቃናው ሰርግ ድረስ ያሉት ሦስት ቀናት ሲደመሩ ደግሞ [3]ሰባት ይሆናሉ፡፡ በዚህም በኦሪት ዘፍጥረት በተጻፉት ቀናት ውስጥ በሰባተኛው ቀን የተጻፈውን የጋብቻ ዕለት በዮሐንስ ወንጌልም እናገኘዋለን ማለት ነው፡፡

የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክ በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ከተጻፉ ተአምራት አንዱ ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ከነበሩት ደቀ መዛሙርት አንዱ በመሆኑ በዚያ ለተደረገው ተአምር የዓይን ምስክር ነው፡፡ ከአራቱ ወንጌላውያንም ውስጥ በዚህ ሰርግ ቤት ተገኝቶ የነበረው እርሱ ብቻ ነው፡፡ እናም ይህ ሐዋርያ ‹ያዩትን ከመናገር ዝም ለማለት ከማይችሉ› ሐዋርያት አንዱ በመሆኑና እሱም ደጋግሞ ‹ያየውን እንነግራችኋለን› ሲል የነበረ በመሆኑ የቃናውን ሰርግ ቤት ተአምር መዝግቦልናል፡፡ (ሐዋ. ፬፥፳ ፤ ፩ዮሐ. ፩፥፩፣፫)

ቅዱስ ዮሐንስ ስለዚህ ሰርግ ቤት እንዲጽፍ የሚያስችለው ሌላ ምክንያትም አለ፡፡ በቃና ሰርግ ነበረ ካለ በኋላ አያይዞ ‹የኢየሱስ እናት በዚያ ነበረች› ብሏል፡፡ የዚህ ሰርግ ቤት ተአምር ምክንያት የነበረችውን እመቤታችንን ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ከመስቀል ሥር በአደራ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወስዷት ነበር፡፡ ከእርስዋም ጋር ለዐሥራ አራት ዓመታት ኖሮአል፡፡

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ እመቤታችን ‹በልብዋ ትጠብቀው የነበረውን› ምሥጢር ሁሉ ለዮሐንስ ገልጣ ነግራዋለች፡፡ እመቤታችን ብዙ ስትናገር አልተሰማችም፡፡ ነገር ግን በእርስዋ ልብ ውስጥ ብዙ ምሥጢር ነበር፡፡

[3] በምዕራፍ አንድ የተጻፉትን ቀናት ማለታችን ነው እንጂ የቀናቱን አቆጣጠር በኋላ በዝርዝር እንደምንመለከተው ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ የጾመውን አርባ ቀንና ሌሊትም የሚያካትት ነው፡፡



Scanned by CamScanner

ኤልሳቤጥ ጻድቁ ዮሐንስን ጸንሳ ‹በማኅጸኔ በደስታ ዘለለ› ብላ የልጅዋን መደሰት በጸጋ አውቃ ተናግራለች። እመቤታችን ግን የጻድቃንን አምላክ ፈጣሪዋን ጸንሳ ወልዳዋለች። እርስዋ ስለ ጽንሱ የምትናገረው ብዙ ምሥጢር አለ። ሰማይና ምድር የማይችሉት ያልተነገረ ያልተሰማ ምሥጢር በእመቤታችን ልብ ውስጥ አለ። አባ ሕርያቆስ እንዲህ ሲል ጠይቆአታል «ድንግል ሆይ እሳተ መለኮት በሆድሽ ባደረ ጊዜ ፊቱ እሳት ቀሚሱ እሳት ነው ፤ እንደምን አላቃጠለሽም? ሰባቱ የእሳት መጋረጃ በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተጋረደ ፤ ከጎንሽ በቀኝ ነውን ወይስ ከጎንሽ በግራ ነውን ፤ ትንሽ አካል ስትሆኚ!» እያለ ይመረምራታል።

እመቤታችን ጌታን ጸንሳ ከወለደችውም በኋላ እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስ እንደ ልጅነቱ እያገለገላት ፣ እንደ አምላክነቱ እያገለገለችው አብራው ኖራለች። ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። እመቤታችን ከልጅዋ ጋር ለሠላሳ ዓመታት አብራ በአንድ ቤት ስትኖር የነበራቸው ንግግር ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደመሆኑ ጸሎትም ጭምር ነበር። በእርግጥ እመቤታችን እና ጌታችን በእነዚያ ሁሉ ዓመታት ምን ሲነጋገሩ ነበር? ምን ምን ሲነግራትስ ኖሮ ይሆን? ስለየትኛውስ ምሥጢር ሲገልጥላት ነበር?

ገና የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ቆይቶ በነበረ ጊዜ ያነጋገሩት የአይሁድ መምህራን ‹በማስተዋሉና በመልሱ ሲገረሙ ነበር› እመቤታችን ከሕጻንነቱ ጀምሮ እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስ አብራው ስትኖር በስንቱ ነገር ስትደነቅ ኖራ ይሆን? /ሉቃ. ፪፥፵፯/

የኤማሁስ መንገደኞች ከጌታችን ጋር ተጉዘው ጥቂት ቢወያዩ ‹በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትን ሲተረጉምልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን?› ብለዋል። እመቤታችን

ለሠላሳ ዓመታት ከልጅዋ ጋር ስትነጋገር እንደምን ባለ መንፈሳዊ መቃጠል ልቧ በፍቅሩ እሳት ሲቃጠል ኖሮ ይሆን? የምትነደዋ ዕጸ ጳጦስ ብለን የምንጠራት እመቤታችን የልጅዋ ፍቅር በውስጥዋ ሲነድ እንደምን ችላው ይሆን? /ሉቃ. ፳፬፥፴፪/

ቅዱስ ዮሐንስ ከእርስዋ ጋር በመኖሩ ጥልቅ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ለመጻፍ ችሏል። መላእክት ተገልጸው ‹ተው የማትጨርሰውን አትጀምር›[4] እስኪሉት ድረስ ጥልቅ የሆነ ነገረ መለኮትን የተረዳው የምሥጢር መዝገብ የሆነች እመቤታችን ከእርሱ ጋር ስለነበረች ነው። ከእነዚህ ምሥጢራት በተጨማሪ ስለ ቃናው ሰርግ እሱ ያልሰማው ነገር ቢኖር እንኳን ከእመቤታችን አንደበት ለመስማት እና የእናትና ልጅን ንግግር አጥርቶ ለመጻፍ ከዮሐንስ ወንጌላዊ የተሻለ ሰው የለም።

ሌላው ነገር የቃናውን ሰርግ በወንጌል ፤ ከወንጌልም ጥልቅ ነገረ መለኮት በተጻፈበት በዮሐንስ ወንጌል እንዲጻፍ ያደረገውስ ምንድር ነው? የሚለው ነው። ወንጌላዊው ዮሐንስ ከታሪኮች ይልቅ ነገረ መለኮት ላይ የሚያተኩር ጸሐፊ ሆኖ እያለ በሌሎች ወንጌላት ስላልተጻፈው ስለዚህ የሰርግ ቤት ተአምር መጻፉ ለምንድር ነው? ሙሽሮቹ ስማቸው የገነነ ስለሆነ ነው እንዳንል በታሪኩ ላይ ስማቸው እንኳን አልተጻፈም። ባለጸጎች ናቸው እንዳንል የጠሩትን እንግዳ እንኳን የሚሸኝ የወይን ጠጅ ያላዘጋጁ ድሆች ነበሩ። ይህ ጋብቻ እንዲህ ትኩረት የሳበው የምድር የሰማይ ፈጣሪ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከቅድስት እናቱ እና ከደቀመዛሙርቱ ጋር ስለተገኘበት

[4] ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ መቅድም



Scanned by CamScanner

ነው። ስርግን ስርግ የሚያሰኘው የሙሽሮቹ ማንነት ፣ ሀብት ፣ የድግሱ ስፋት ሳይሆን ጋብቻው እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጋር ያለበት ሲሆን እንደሆነ በዚህ እንረዳለን።

በቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ የቃናው ተአምር ትልቅ ትኩረት የሚሠጠው ነው። በሮም ‹ካታኮምብ› /ግበ ምድር/ ከተገኙ ሃምሳ ሁለት ጥንታዊያን የዋሻ ውስጥ የግድግዳ ሥዕላት ከዐሥራ ስድስት የሚበልጡት የቃና ዘገሊላን ተአምር የሚያሳዩ መሆናቸው በዚያ የጭንቅ ዘመን የነበሩ የጥንት ክርስቲያኖች ስለዚህ ስርግ ቤት ተአምር የነበራቸውን ትኩረት የሚያሳይ ነው።[5]

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የቃና ዘገሊላ ተአምር የተፈጸመበት ጥንተ ዕለት የካቲት ፳፫ እንደሆነ ያስረዳሉ።[6] ሆኖም የካቲት ፳፫ ዕለት በጾም ወቅት ስለሚውል በዓሉን በደስታ ለማክበር እንዲሁም የውኃን በዓል ከውኃ በዓል ጋር አንድ ለማድረግ ከጌታችን በዓለ ጥምቀት ማግሥት ጥር ፲፪ ዕለት ከ[7]ቅዱስ ሚካኤል በዓል ጋር እንዲከበር አድርገዋል።

የቃና ዘገሊላ በዓል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀብት በሆነው በቅኔ ታሪክ ውስጥም የሚታወስ ዕለት ነው። በዚህም ምክንያት ከቅኔ መንገዶች አንዱ ‹ጉባኤ ቃና› ተብሎ ይጠራል። ታሪኩ እንዲህ ነው። እንደሚታወቀው የቅኔ ጀማሪ ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ነው። ይህን የቅዱስ ያሬድ የቅኔ

---

5 H. Macmillan, LL. D.: Bible Illistrator / Article "The popularity of the Cana Miracle"

6 የካቲት ፳፫ በኢትዮጵያ የአድዋ ድል በዓል የሚከበርበት ቀን መሆኑን ልብ ይሏል።

7 አንዳንድ ጸሐፍት በዚህ ሰርግ ቤት ቅዱስ ሚካኤል እንዳልተለየ ጽፈዋል። (ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ገጽ. 383) በእርግጥም ስለማይበሉና ስለማይጠጡ አይጠቀሱ እንጂ ጌታችን ባለበት መላእክቱ አይለዩም።



Scanned by CamScanner

መንገድ እግዚአብሔር እንዲገልጥለት በ፲፬፻፰ ዓ.ም. ዮሐንስ ገብላዊ የተባለ ሊቅ ደብረ ታቦር በሚባል ተራራ ሱባኤ ይገባል፡፡ በዚህም ሱባኤ ምሥጢሩ ከነቤቱ ተገልጾለት ከቅዱስ ያሬድ አያይዞ ደርሶታል፡፡ ይህንን ቅኔውንም ለአባ ወልደ ገብርኤል አስተማረ፡፡ አባ ወልደ ገብርኤል ለሠምረ አብ ያስተምራሉ፡፡ ሠምረ አብ ቅኔን ሲያስተምር በወቅቱ (በ፲፬፻፳ዓ.ም.) የነበረው ንጉሥ በዕደ ማርያም ነበር፡፡ ንጉሡ ቅኔውን በሰማ ጊዜ ሠምረ አብን «አንተ ከነአባትህ ትለፈልፉለህ እንጂ ቅኔን ከየት አገኘኸው» ይለዋል፡፡ መምህሩ ሠምረ አብም በትሕትና ቃል «ይህንን ካልህስ እንዲገለጽልን ስለምን ሱባኤ አንገባም?» አለው፡፡ ንጉሡም እሺ ብሎ ተያይዘው ሱባኤ ገቡ፡፡ እግዚአብሔርም ነገሩ ከእርሱ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ በሱባኤው ወቅት የንጉሡን ልብ ብሩሕ አደረገለትና እንዲህ ሲል ቅኔ ተናገረ፡፡

ድኅረ ተሰብረ አጽንዖ ለሰብእናነ ልሕኵት
ለብሐዊ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት

(ትርጉም)

ሸክላ (ሰብእናችን) ከተሰበረ በኋላ ሸክላ ሠሪው ክርስቶስ
በአዲሲቱ ጥምቀት ውኃ አጸናው (ሠራው)

ይህን ቅኔ የመራበት (የተቀኘበት) ዕለት የቃና ዘገሊላ ዕለት በመሆኑም ስሙ [8]ጉባኤ ቃና ተባለ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችንም ጌታችን ካደረጋቸው እጅግ ብዙ ተአምራት መካከል በዓል አድርጋ የምታከብረው የቃና ዘገሊላውን ተአምር ነው፡፡ መጻጉዕን የፈወሰበትን ፣ አልዓዛርን ከሞት ያስነሣበትን ፣ ዓይን ያበራበትን ፣

---


[8] (መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ፤ መጽሐፈ ቅኔ /ዝከረ ሊቃውንት/ ክፍል 2 ገጽ 11 ፤ ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ መርሐ ልቡና ገጽ. 18)

በአጋንንት እስራት የተያዙትን ነጻ ያወጣበትን ዕለት በክብረ በዓል ደረጃ ሳታከብር የቃናው ተአምር ከጌታችን ንዑሳን በዓላት ውስጥ ተደምሮ እንዲከበር ያደረገችበት ምክንያት ምንድር ነው? አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ባደረገው ጋብቻ ላይ ውኃን ወይን ማድረጉ ብቻ በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን የጌታ በዓል ብላ እንድታከብረው ያደርጋት ይሆን? አይደለም!

ቅዱስ ዮሐንስ ስለዚህ ሰርግ ቤት በስፋት የጻፈው ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም የቃና ዘገሊላን በዓል የምታከብረው «ሁሉን ማድረግ የሚቻለው አምላክ ስድስት ጋን ውኃን የወይን ጠጅ አደረገ!» ብላ ሳይሆን ከዚህ የሰርግ ቤት ታሪክ በስተጀርባ የሰው ልጅን ድኅነትና ሰማያዊ ክብር የሚያስረዳ ጥልቅ ምሥጢርን ስለያዘ ነው። መምህራችን የኔታ ዮሐንስም በምዕራፍ ሁለት የነገረንን ንባብ በምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ አመስጥሮ ተርጉሞ ሰርግ ቤቱም ፣ ሰርጉም ፣ ወይኑም ፣ የእመቤታችንም ጥያቄ ፣ የልጅዋም መልስ ሌላ መሆኑን አስረድቶን እፁብ እፁብ አሰኝቶን ነው የሔደው። ዮሐንስን ያስጻፈ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን አበው እና ተጠቃሽ ሊቃውንት የቃና ዘገሊላን ምሥጢር በሚገባ አብራርተው ጽፈውልናል። በቀጣዩ ምዕራፍ ወደ ሰርግ ቤቱ ዘልቀን ገብተን እያንዳንዱን ነገር እንመለከታለን እዚያው እንገናኝ።



Scanned by CamScanner



## ክፍል አንድ

# የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክ

«ቃና እንዲህ ትላለች ፡-
ወደ ሰርጌ እንድጠራው የተገባሁ ያደረገኝን
ጌታዬን ከእንግዶቼ ጋር ሆኜ አመሰግነዋለሁ፡፡
እርሱ ሁሉን ወደ ራሱ ሊጠራ የመጣው
እኔንም ወደ ንጹሕ የሰርጉ በዓል የጠራኝ ሰማያዊ ሙሽራ ነው፡፡
በምድር ሁሉ (በሚኖሩ) ሰዎች ፊት እርሱ ሙሽራ መሆኑን ልመሰክር ይገባኛል ፤
የሙሽርነቱ አዳራሽ ለዘላለም ተመሥርቷል፡፡
ሰርጉም በባለጠግነት ተዘጋጅቶአል፡፡ አንዳች ነገር አያስፈልገውም፡፡
የእርሱ ሰርግ ጉድለቱ እንደተሞላለት እንደ እኔ ሰርግ ዓይነት አይደለም፡፡»

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ

Scanned by CamScanner

## ምዕራፍ ሁለት

# ሰርግ ቤቱ

‹‹በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ ፤
የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች።
ኢየሱስም ደግሞ ደቀመዛሙርቱም በሰርጉ ታደሙ››

ዮሐ. ፪፥፩-፪

### ፩. በሦስተኛው ቀን

የቅዱስ ዮሐንስ የወንጌል አጻጻፍ ስልት ዋና ዋና መገለጫ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ጌታችን እያንዳንዷን ቀን እና ሰዓት ያለ ሥራ እንዳላባከነ በሚያሳይ መንገድ ቀናትንና ሰዓታትን በጥንቃቄ መዝግቦ ማስቀመጡ ነው። ይህ ወንጌል ሰዓት ላይ ያተኮረው አንድ ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜ ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን የአምላክን ሰው መሆንም ለማሳየት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ዘመናትንና ሰዓትን የሚለካ እንጂ እርሱ በዘመን የሚለካ

አምላክ አይደለም። እርሱ ያልነበረበት ዘመን የሌለ [9]‹በዘመናት የሸመገለ› ብሉየ መዋዕል አምላክ ነው። ሰው በመሆኑ ግን ‹‹[10]ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት ዘመን ተቆጠረለት›› ይህን ለማሳየትም ቅዱስ ዮሐንስ ‹በሦስተኛው ቀን› ብሎ በቀን ሰፍሮ ስለ ጌታችን ጻፈ።

ሦስተኛ ቀን ለእስራኤላውያንም ታሪካዊ ትርጉም ያለው ቀን ነው። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ለእስራኤል ሊገለጥ ሲል ‹‹በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ ሁሉ ሲያዩ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳልና ለሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ።›› ብሎ ነበር። (ዘጸ. ፲፱፥፲፩) በሐዲስ ኪዳንም በቃና ዘገሊላ የመጀመሪያ ተአምሩን አድርጎ ራሱን የገለጠው በሦስተኛው ቀን መሆኑ ‹አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ለዘላለም የሆነ› በቅድምና የነበረው አምላክ እርሱ መሆኑን ያስረዳናል። (ሚክ. ፭፥፪)

በመጽሐፈ ኢያሱም እንዲሁ ሦስተኛ ቀን ታሪካዊ ክስተት ተፈጽሞበታል። ራሳቸውን ሰውረው ወደ እስራኤላውያን የተጠጉት አሕዛብ /የገባዖን ሰዎች/ ማንነታቸው ታውቆ ከእስራኤል ጋር ተቀላቅለው መኖር የጀመሩት በሦስተኛው ቀን ነበር። (ኢያ.፱፥፩-፲፯) እስራኤል የሚያርቋቸውን አሕዛብ በሦስተኛው ቀን አቅርበው ማኖር እንደጀመሩ ጌታችንም በሦስተኛው ቀን አሕዛብ በሚኖሩበት የገሊላ ከተማ ተአምራቱን በማድረግ አሕዛብን ወደ እርሱ ሳባቸው።

ቅዱስ ዮሐንስ ‹በሦስተኛው ቀን› በማለት የጻፈውን ዕለት የተለያዩ ሊቃውንት በሦስት ዓይነት አተረጓጎም ይቆጥሩታል። አንደኛው በዮሐ. ፩፥፵፩

[9] ዳን. ፯፥፱ ፣ ፳፪
[10] ‹‹ወለዘአልቦ መዋዕል ኮነ ሎቱ መዋዕል›› (ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ)

‹ጌታችን ፊልጶስን› አግኝቶ ‹ተከተለኝ› ካለበትና ፊልጶስም ጓደኛውን ናትናኤልን ከጠራበት ዕለት ሦስት ቀን በኋላ ተአምሩን አደረገ የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው አቆጣጠር ደግሞ ‹‹በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ቆመው ነበር፥›› (ቁ. ፴፭) ላይ ያለውን እሑድ ፤«በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ፥ ፊልጶስንም አገኘና። ተከተለኝ አለው።» (ቁ.፵፫) ያለውን ሰኞ ብሎ በመተርጎም ማክሰኞ ተአምሩን በቃና አደረገ የሚል ነው፡፡

ሦስተኛው እና የእኛ ቤተ ክርስቲያን የበለጠ የምታስተምረው አገባብ ደግሞ ጌታችን በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሔዶ ያሳለፈውን አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደ አንድ ቀን በመቁጠር ከዚያ መልስ ተአምራቱን አደረገ የሚል ነው፡፡ ‹አርባ ቀንና ሌሊት እንደ አንድ ቀን እንዴት ይቆጠራል?› ቢባል ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ልማድ ስለሆነ ነው፡፡

ለምሳሌ ቅዱስ ማቴዎስ ጌታችን ከግብፅ ስደት መልስ «ወደ ናዝሬት መጥቶ ኖረ» ብሎ ከጻፈ በኋላ ቀጥሎ ‹‹በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።›› ብሎ ጽፎአል። (ማቴ.፪፥፳፫፤፫፥፩) በሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች መካከል የሃያ አምስት ዓመታት ልዩነት አለ፡፡ ብዙውን እንደ አንድ መቁጠር የመጻሕፍት ልማድ ስለሆነ ግን «በዚያ ወራት» ብሎ ጻፈ፡፡ ይህ የትርጓሜ አገባብ የበለጠ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡ ፡ ምክንያቱም ‹ጌታችን ከመጾሙ በፊት በአደባባይ ተአምራት አደረገ› የሚለው ሃሳብ ለመቀበል የሚከብድና ጌታችን የመጣው ለአርአያ ከመሆኑ ጋር የሚሔድ አይደለም፡፡ ከማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎትና ተአምራት በፊት መጾምና

መጸለይ እንደሚቀድም ያስተማረንም ከቃናው ተአምር በፊት በገዳመ ቆሮንቶስ በመቆየቱ ነው።

## ፪. በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ

የገሊላዋ ቃና የሚለው አነጋገር የሚያሳየው ሌላ ቃና በሚል ስም የሚጠራ ሥፍራ እንዳለና ከዛ ለመለየት መሞከሩን ነው። ቃና በሚል ስም የታወቀው ሌላ ሥፍራ የኤፍሬም ልጆች ርስት ያለበት አካባቢ ሲሆን በዛ ሥፍራ ቃና የሚባል ወንዝ አለ። (ኢያ.፲፮፥፰፤፲፯፥፱) ወንጌላዊው ከዚህ ቃና ለመለየት ‹በገሊላ ቃና› ብሎ ጀመረ።

በዘመነ ኢያሱ በተደረገው የእስራኤላውያን የርስት ድልድል የገሊላዋ ቃና ለአሴር ልጆች ነገድ ከተሠጡ ቦታዎች ውስጥ ትመደብ ነበር። (ኢያ.፲፱፥ ፳፰) የሕይወት እንጀራና እውነተኛ መብል የሆነው ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር ስላደረገበት ስለዚህ ሥፍራ ሕዝብ «የአሴር እንጀራው ወፍራም ነው፥ ለነገሥታቱም ደስ የሚያሰኝ መብልን ይሰጣል።» የሚል ትንቢት አስቀድሞ ተነግሮም ነበር። (ዘፍ. ፵፱፥፳)

በሐዲስ ኪዳን የገሊላዋ ቃና የሰርጉን ክስተት ጨምሮ የተጠቀሰችው ለሦስት ጊዜ ነው። አንደኛው በሰርግ ቤቱ ታሪክ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በሥፍራዋ የተወለደውን ሐዋርያ «ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤል» ብሎ ሲያነሣው

ነበር። (ዮሐ. ፳፩፥፪) ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቀሰችው ደግሞ «ኢየሱስም ውኃውን የወይን ጠጅ ወዳደረገባት ወደ ገሊላ ቃና ዳግመኛ መጣ» ሲል ነው። (ዮሐ. ፬፥፮)

ባለንበት ዘመን «ሰርግ የተደረገባት የገሊላዋ ቃና እኔ ነኝ» የሚሉ ሁለት ሥፍራዎች አሉ። አንደኛዋ ሥፍራ ቤት በደቡባዊ ሊባኖስ የምትገኘው ዓይን ቃና (Ain Qana) የተባለች መንደር ስትሆን የሊባኖስ ክርስቲያኖች ይህች ሥፍራ ጌታችን ተአምሩን የፈጸመባት ቃና እንደሆነች ያምናሉ።

ሁለተኛዋና የበለጠ ተቀባይነት ያገኘችው ቃና የተባለችው ሥፍራ ደግሞ ከእስራኤል ናዝሬት በስተሰሜን ሰባት ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኘው ካፍር ቃና (Kafr Kanna) ቃና በመባል የምትታወቀው ሥፍራ ናት። በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ቁጥር የምትጎበኝ ሲሆን ሙሽሮች የጋብቻ ቃልኪዳናቸውን የሚያድሱባትና የወይን ጠጅ የሚቀመስባት ሥፍራ ሆናለች።

- **<u>የድሆችና የአሕዛብ ሀገር</u>**

ጌታችን ይህንን የመጀመሪያ ተአምሩን በኢየሩሳሌም ወይም በይሁዳ በቤተ መንግሥት ወይም በታላላቅ ሰዎች ቤት ሊያደርገው ይችል ነበር። በቃሉ ‹ከሰው ክብርን አልቀበልም› ብሎ እንደተናገረው ጌታችን አፈር ትቢያ ከሆነው ሰው የሚገኘውን ክብር አልፈለገም። (ዮሐ. ፭፥፵፩) አባ ጊዮርጊስ ስለ ጌታችን ልደት በተናገረበት ሥፍራ «ከሔሮድስ ሴት ልጅ ቢወለድ ኖሮ አይሰደድም ነበር ፤ እርሱ ግን ወላጆችዋ የሞቱባትን የድሆች ልጅ ድንግል ማርያምን መረጠ» ሲል

እንደተናገረው ጌታችን የአንድ ባለጸጋ ልጅ ሲዳር ተገኝቶ ይህን ተአምሩን ቢያደርግ ኖሮ የበለጠ ተቀባይነትን ያገኝ ነበር፡፡ እንኳን ሰርገኞቹን ከነዘን አድኖ ይቅርና በሰርግ ላይ ታድሞ ያጀበ ሰው እንኳን በባለጸጎች ዘንድ ውለታ ሆኖ ይወሳለታል፡፡ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ካህናቱን ሰብስቦ የታደመው በድሆች ሰርግ ላይ መሆኑ በራሱ በየዘመኑ ለሚነሡ ለካህናትና ለደቀመዛሙርት ትልቅ ምሳሌና ትምህርት ነው፡፡

ይህን ተአምር በአይሁድ መካከል ተአምርን አጥብቀው በሚሹ መካከል ቢያደርገው ኖሮ ትልቅ ቦታና ማዕረግ ይሠጡት ነበር፡፡ የእነሱ ጠባይ መቼም የታወቀ ነው፡፡ ከቤተ ሳይዳ ከተማ አጠገብ ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ አበርክቶ ሲመግባቸው ደስ ብሏቸው ሊያነግሡት አስበው አልነበር? ‹‹በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ።›› ተብሎ ተጽፏልና፡፡ (ዮሐ.፮÷፲፭ ፤ ሉቃ. ፱÷፲)

ልብ አድርጉ እንጀራና ዓሣ ብቻ ስለመገባቸው እናንግሥህ ያሉት ሰዎች ልብን የሚያስደስተውን የወይን ጠጅ ቢሠጣቸው ኖሮ ደግሞ እናምልክህ ሳይሉ አይቀሩም፡፡ (አካሔዳቸውን ለመተቸት እንጂ ቢያመልኩትስ መልካም ነበር፡፡) ጌታችን ግን ወደ ዓለም የመጣው በምግብ መጠጥ እየደለለ ተከታዮችን ለማፍራት ስላልነበር ይህንን አላደረገም፡፡ ተአምራቱን ያደረገውም ያጡ የነጡ ድሆች በሚበዙበት ፣ ውለው አድረው ብድር ሊመልሱለት የማይችሉ ምስኪኖች ባሉበት በቃና መንደር ነው፡፡ ‹ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ ልኮኛል› ተብሎ ስለ እርሱ እንደተነገረ፡፡ (ኢሳ. ፷፩÷፩) ይህ ሲባል ደግሞ ጌታችን ባለጸጎችና ሹማምንት ባሉበት ጨርሶ ተአምር አያደርግም ማለት



Scanned by CamScanner

አይደለም። ጌታ ለድሆች ያለውን ፍቅር መናገር ትሕትናውን ከማድነቅ ነው እንጂ ባለጠጎችን ይጠላል ማለት አይደለም። ለዚህም ማሳያ የሚሆነን በዚሁ ቃና ዘገሊላ የሚኖር የንጉሥ ቤት ሹምን ልጅ ፈውሶለታል። (ዮሐ. ፬፥፵፯)

ጌታችን በገሊላ ካደረጋቸው እጅግ ብዙ ተአምራት ሦስቱ ብቻ በዮሐንስ ወንጌል ተመዝግበዋል። የመጀመሪያው የቃናው ሰርግ ቤት ተአምር ነው ፤ ሁለተኛው የንጉሥ ቤት ሹምን ልጅ ከሞት ያስነሣበት ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ እንጀራና ዓሣ አበርክቶ የመገበበትና በባሕር ውኃ ላይ የተራመደበት ተአምር ነው። (ዮሐ. ፬ እና ፮)

በቃና ዘገሊላ ተአምር ማድረጉ ትኩረት የሚስብበት ሌላ ጉዳይ ቃና አሕዛብ በብዛት የሚኖሩባት ከተማ በመሆንዋ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስም በትንቢቱ ‹‹ነገር ግን ተጨንቃ ለነበረች ጨለማ አይሆንም። በመጀመሪያው ዘመን የዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር አቃለለ በኋለኛው ዘመን ግን በዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ ያለውን <u>የአሕዛብን ገሊላ</u> ያከብራል።›› ብሎ ተናግሯል። (ኢሳ. ፱፥፩) ይህ ትንቢቱ መፈጸሙንም ቅዱስ ማቴዎስ እንዲህ ሲል ጠቅሶ ጽፏል። ‹‹በነቢዩም በኢሳይያስ። የዛብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር፥ የባሕር መንገድ፥ በዮርዳኖስ ማዶ፥ <u>የአሕዛብ ገሊላ</u> በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው›› (ማቴ.፬፥፲፬) በሁለቱም ሥፍራ ገሊላ የተጠራችው ‹የአሕዛብ ገሊላ› ተብላ ነው።

የዚህ ተአምር ተመልካቾች አብዛኞቹ አሕዛብ መሆናቸው የላቀ ትርጉም አለው። «በጥንቃቄ የሚሰማ ሰው ይህ ሰርግ የተካሔደው በኢየሩሳሌም አለመሆኑንና ከይሁዳ ውጪ በሆነችው አሕዛብ /በሚበዙባት/ ሀገር መሆኑን ያስተውላል።

ለማያዊው ሙሽራ በአይሁድ ሸንጎ መናቁና በአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ግን በደስተኛ ልብ አቀባበል እንደተደረገለት በጣም ግልፅ ነው፡፡»[11] ብሏል ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፡ ፡ ቅዱስ ያሬድም በድጓው ‹የማይታይ ታየ ፤ በአሕዛብ ዘንድ ፍጹም ተአምራትን ሲያደርግ መታየቱ የታመነ ሆነ ፤ ውኃውንም ወይን አደረገው› ብሏል፡፡ «አስተርአየ ዘኢያስተርኢ ኮነ እሙነ አስተርእዮቱ ለመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ይገብር ተአምረ ወመንክረ በውስተ አሕዛብ ወለማይኒ ረሰዮ ወይነ» (ዋዜማ ዘቃና ድጓ)

## ○ <u>የቃና ዘገሊላ ሙሽሮች እነማን ነበሩ?</u>

የቃና ዘገሊላ ሙሽሮች ስማቸው አልተጻፈም፡፡ ወይም ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ አጠራር በሌላ ቅጽልም ፣ በማዕረግ ስም ‹አንድ ባለ ጸጋ ፤ አንድ በሽተኛ ፣ አንድ የአይሁድ ሰው ፣ አንድ የጦር አለቃ› በሚለው መንገድ አልተጠሩም፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በሙሉ ታሪኩ ውስጥ የሙሽራውና ሙሽሪቱን ማንነት የሚመለከት ምንም ነገር አልተጻፈም፡፡ አንድ አንቀጽ ላይ ብቻ «አሳዳሪው <u>ሙሽራውን ጠርቶ</u> ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው፡፡» የሚል ዐረፍተ ነገር እናገኛለን፡፡ ሙሽራውን ማን ብሎ እንደጠራውም ሆነ ከነገረው በኋላ ምን ብሎ እንደመለሰለት አልተጻፈም፡፡

[11] «The careful listner will notice that the celebration of the wedding feast was not held in Jerusalem, but outside Judea in the country of the Gentiles. For it is very clear that the Synagogue of the Jews had rejected the heavenly Bridegroom, but by the Church of the gentiles He was recived with joyful heart.» **St .Cyril Archbishop of Alexandria Commentary on the Gospel according to Jhon/**



Scanned by CamScanner

በእርግጥም በማያውቀው የወይን ጠጅ ‹ምነው አቆየኸው?› ተብሎ የተደነቀው ይህ ሙሽራ ምን ብሎ መልሶ ይሆን? ግራ ተጋብቶ ይሆን? ምስጋና ከሆነ ምን ችገረኝ ብሎ ባልጠመቀው ወይን መወደሱ ደስ ብሎት ተቀብሎ ይሆን? ይህ ሁሉ ግን አልተጻፈም።

አንዳንድ ጸሐፍት የቃናው ሙሽራ ማንነት ላይ የተለያዩ (ከመላ ምትነት እስከ አደገኛ ከህደትነት የሚደርሱ) ሐሳቦችን ጽፈዋል። አንዳንድ መጻሕፍት ደግሞ የቃናው ሙሽራ ሐዋርያው ቀናተኛው ስምዖን ነው ብለው ጽፈዋል። የእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ግን የሙሽራው አባት ‹ከገሊላ ቃና የሆነ› /ማቴ.፳፩፥፪/ የናትናኤል ዘመድ እንደሆነ እና ስሙ ባቲለስ እንደሚባል ፤ የሙሽራውም ስም ደግሞ ዶኪማስ እንደሚባል ጽፈዋል። (ትርጓሜ ወንጌል ፤ ተአምረ ኢየሱስ)

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ደግሞ የቃና ተጋባዥ እንግዶች ከሙሽራው ይልቅ ትኩረታቸውን ምን እንደሳበው እንዲህ ሲል ይናገራል። ‹‹‹‹ጋኖችን በወይን ለሞላው ለእርሱ ሰርግ ቤቱ ምስጋናን ያቅርብለት! ... ስድስት ጋን አስደናቂ ወይን ከውሃ ተለወጠ። (እንግዳ ብለው) የጠሩት ንጉሥ ራሱ (ተነሥቶ) ወይን ጠጅ አቀረበላቸው። በዚያ በእንግድነት የተገኘ ሰው እንዴት ይደሰት ይሆን? ዓይኑን የሙሽራዋን ውበት ከመመልከት ላይ አንሥቶ ወደ አንተ ይመለከታል። ጌታችን ሆይ ምንኛ ቸር እንደሆንከም ያያል››[12] /ቅዱስ ኤፍሬም ፤ መዝሙር በእንተ ድንግልና/

---

12 «Let the wedding feast thank Him who multiplied its wine jars ... The King whom they had invited Himself pour out the wine for them! How happy he who was a guest there, who could turn away from the bride's beauty and gaze at You, our Lord, and see how fair You are.» /Hymns on Virginity, no. 33 THE HARP OF THE SPIRIT *Eighteen Poems of Saint Ephrem*/



Scanned by CamScanner

ስማቸውን ባናውቀውም የቃና ዘገሊላ ሙሽሮችን እስቲ እናድንቃቸው! እነዚህ ሙሽሮች የሰርጋቸው ታሪክ የተጻፈው እንደ ሌሎች ሙሽሮች በጋብቻ ውል ሰነድ ላይ ሳይሆን ሁላችንም በአክብሮት በምንሳለመው በቅዱስ ወንጌል ላይ ነው። የሰርጋቸውን ታሪክም የምናዳምጠው እንደሌላ የሰርግ ዜና ሳይሆን ‹ቆማችሁ ስሙ› ተብለን በምንሰማው በወንጌል ንባብ ላይ ነው። ከተጋቡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ እንኳን ‹በቃና ዘገሊላ› እየተባለ የሚዘመርላቸው እነዚህ ሙሽሮች ምንኛ የታደሉ ናቸው? ድንግል ማርያም በጓዳቸው የተመላለሰችላቸው ፤ ወልደ እግዚአብሔር የወይን ጠጅን የጠመቀላቸው ፤ ሐዋርያት አጃቢ የሆኗቸው ፤ ከፈጣሪያቸው የማይለዩ መላእክት በእሳት ሠረገላ የሰርግ ቤታቸውን የከበቡላቸው እነዚህ ሙሽሮች ምንኛ የታደሉ ናቸው? ሰው የሀገር መሪ ወይም ዝነኛ ሰው እንኳን ከሰርጉ ሲገኝ እጅግ ይደሰታል ፤ ክብር ይሰማዋል ፤ ውለታ አድርጎም ይቆጥረዋል። እግዚአብሔር እንግዳ የሆነላቸው ፤ ወላዲተ አምላክ የተገኘችላቸው ሙሽሮች በእውነት ምንኛ ክቡራን ናቸው!?

## ፫. የኢየሱስ እናት በዚያ ነበረች

አንድ ታሪክ ሲጀምር ‹እንዲህ በሚባል ቦታ አገሌ ነበረ› ብሎ ከጀመረ የታሪኩ ዋነኛ ገጸ ባሕርይ ‹አገሌ› መሆኑን ለማወቅ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያ መሆን አይጠይቅም። ከሕጻንነታችን ጀምሮ ስንሰማቸው ባደግናቸው ተረቶችና ምሳሌያዊ ታሪኮች ብቻ እንኳን ይህንን መረዳት አያቅተንም። የቃና ዘገሊላው

ሰርግ ቤት ታሪክ በዋነኛነት ርዕሰ ጉዳይ እመቤታችንን መሆኑንም አስቀድሞ ‹የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች› ብሎ በመጻፉ ለመረዳት እንችላለን፡፡

ይህ አነጋገር እመቤታችን ከጌታችን አስቀድማ በዚያ መገኘትዋን የሚያስረዳ ቢሆንም እንኳን ታሪኩ በተጻፈበት ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ ተከታታይ ዐረፍተ ነገሮች ባለቤት /subject/ መሆኗ ቅዱስ ዮሐንስ የእመቤታችንን መኖር አስቀድሞ የጠቀሰው ያለ ምክንያት እንዳልሆነ ያስረዳናል፡፡ በአራቱም ወንጌላት ከተጻፉ በርካታ ተአምራት ውስጥ ከቃና ዘገሊላው ተአምር በስተቀር ‹የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች› ብሎ የሚጀምር ተአምር የለም፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ለዝርዝር ጉዳዮች ትኩረት የሚሠጥ ጸሐፊ እንደመሆኑ የእመቤታችንን ስም ያስቀደመው በዚህ ሰርግ ቤት እመቤታችን እጅግ ወሳኝ ሚና የነበራት ስለሆነች ነው፡፡ አንድ ሰው የእመቤታችንን ስም እና ሚና አውጥቶ የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክን ለማንበብ ቢሞክርም ትርጉም ሊሠጠው አይችልም፡፡

አንዳንዶች ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በወንጌል ላይ አልተጻፈም ይላሉ፡፡ በመሠረቱ በወንጌል ስለ እመቤታችን በሚገባ ተጽፏል፡፡ ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ቅዱስ ሉቃስ ‹ልብንና ኩላሊትን የሚመረምረው› የእግዚአብሔር መንፈስ ገልጦለት የእመቤታችንን የልብዋን ሃሳብ ሳይቀር ሦስት ጊዜ ጽፎአል፡፡ (መዝ. ፯÷፱) ‹ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ብላ <u>አሰበች</u>› (ሉቃ. ፩÷፳፱) ‹‹ ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ <u>በልብዋ</u> <u>እያሰበች</u> ትጠብቀው ነበር›› (ሉቃ.፪÷፲፱) «ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፥ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን ነገር ሁሉ <u>በልብዋ</u> ትጠብቀው ነበር» (ሉቃ. ፪÷፶፩) በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ቅዱስ ሉቃስ ስለ



Scanned by CamScanner

እመቤታችን ሃሳብ ሦስት ጊዜ ሲጽፍ በሁለቱ ሥፍራዎች እመቤታችን በውጪ የሚደረገውን እያየች ምንም ሳትናገር ‹በልብዋ ትጠብቀው ነበር› ብሎ በልብዋ ማሰቧን ብቻ የጻፈ ሲሆን ፣ በአንደኛው ግን በውስጥዋ ምን ብላ እንዳሰበች ሳይቀር ገልጾ ጽፎልናል፡፡

ከዚያም በፊትም ሆነ በኋላ እመቤታችንን የሚመለከቱ ብዙ ምዕራፎች በምሥጢርም በግልጥም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈዋል፡፡ ነገሩን አልን እንጂ ስለ እርስዋ በወንጌል አልተጻፈም ብሎ መከራከር የእርስዋን ማንነት አለመረዳት ነው፡፡ ወንጌል ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስቶስ ደግሞ የተወለደው ከእመቤታችን ነው፡፡ እርስዋ ክርስቶስን ስትወልድ የወለደችው ወንጌልንም ጭምር ነው፡፡ «ትመስሊ ፊደለ ወትወልዲ ወንጌለ» (ፊደልን ትመስዪአለሽ ፤ ወንጌልን ትወልጂአለሽ) እንዳለ ደራሲው እመቤታችን የወንጌል መጻፍ ምክንያት ናት፡፡ ከእርስዋ ሰው ሆኖ ባይገለጥ ኖሮ ወንጌልም አይጻፍም ነበርና፡፡

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስና የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክ ስለ እመቤታችን ከተጻፉ የወንጌል ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ መቼም የዮሐንስ ወንጌል ‹ወንጌል አይደለም› ካልተባለ በስተቀር ይህ ሁሉም ሰው የሚያየው እውነታ ነው፡፡ የቃና ዘገሊላ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈው እንደ ተአምረ ማርያም ባሉ በአዋልድ መጻሕፍት ላይ ቢሆን ኖሮ ብዙዎች *‹የፈጠራ ታሪክ ነው›* እንደሚሉ ጥርጥር የለውም፡፡ *‹ለተጠማ ውሻ ውኃ አጠጣች›* ስንል የማያምኑ ሰዎች ‹ውኃውን ወይን አስደረገች› ስንል ያምኑናል ማለት ዘበት ነው፡፡ ሆኖም ይህን

ታሪክ በወንጌል ከወንጌልም በዮሐንስ ወንጌል ያስጻፈልን አምላካችን ክብር ምስጋና ይድረሰው!

## ○ ወንጌላዊው ዮሐንስ እመቤታችንን የጠራበት መንገድ

ቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን በዚህ ታሪክ መግቢያ ላይ ‹የኢየሱስ እናት› ብሎ ጠርቶአታል። ይኼ ሐዋርያ በጻፈው ወንጌል ላይ የራሱንም ስም እንኳን አንድ ጊዜም ያልጠራ ትሑት ሰው ቢሆንም የእመቤታችንን ስም የጠራበት መንገድም እንዲሁ የምናልፈው አይደለም። በወንጌሉ እመቤታችንን ስምንት ጊዜ አንሥቶአታል። (ዮሐ. ፪፥፩፡፫፡፭፡፲፪ ፤ ፮፥፵፪ ፤ ፲፱፥፳፭፡ ፳፮ /፪ጊዜ/ ፤ ፳፯) ስምንት ጊዜም ሲጠራት ግን አንድም ቦታ ‹ማርያም› ብሎ በስምዋ አልጠራትም። የጠራት ‹የኢየሱስ እናት› ፤ ‹እናቱ› ብቻ ብሎ ነው። ቅርበት ባይኖረው ነው እንዳንል ወንጌሉ ድንግል ማርያም በመስቀል ሥር ለዮሐንስ ተሠጥታው ‹ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ወደ ቤቱ ወሰዳት› ይላል። (ዮሐ.፲፱፥፳፯) ሥጋዋን መላእክት ነጥቀው ወደ ሰማይ ሲወስዱትም አብሯት ተነጥቋል። ይህ ሐዋርያ በወንጌሉ ዐሥራ አራት ጊዜ ‹ማርያም› የሚባሉ ሴቶችን ስም ቢጽፍም አንድም ቦታ እመቤታችንን በስምዋ አልጠራትም።

ነገሩን አልን እንጂ እሱማ መጽሐፍ ቅዱስን ስንመረምር አምላክን ከወለደች ጀምሮ ከመላእክትም ወገን ሆነ ከሰዎች ወገን እስዋን የጠሩበትን መንገድ ሲቀይሩ አይተናል። አምላክን ከመጽነስዋ በፊት «ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ» ሲሉ የነበሩት መላእክት ከወለደችው

በኋላ ግን «ሕጻኑን እና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ» ሲሉ እናገኛለን፡፡ (ሉቃ. ፩፥፴ ፤ ማቴ. ፪፥፲፫) አክስትዋ ኤልሳቤጥን ልትጠይቅ በሔደችበት ጊዜ ኤልሳቤጥ ‹የጌታዬ እናት› አለቻት እንጂ እንደ ዝምድናዋ ‹ማርያም› ብላ አልጠራቻትም፡፡ (ሉቃ. ፩፥፵፫)

ይህ የሆነበት ምክንያት ለድንግል ማርያም እጅግ ታላቅ የክብር ስምዋ ‹እናቱ ፣ የኢየሱስ እናት› ‹የጌታ እናት› ‹የአምላክ እናት› የሚለው ስም ስለሆነ ነው፡፡ አንዲት እናት የታወቀ የከበረ ዝነኛ ልጅ ካላት ከስሟ ይልቅ ‹የእገሌ እናት› ተብላ መጠራትዋ የተለመደና ተገቢ ነው፡፡ እመቤታችን ሰማይና ምድርን በእጁ ለሠራው ለገናናው አምላክ ለእግዚአብሔር እናቱ ሆናለች፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው በስሟ ከመጥራት ይልቅ በክብር ስሟ ‹የኢየሱስ እናት› ብሎ ሊጠራት ወደደ፡፡ ይህን የቅዱስ ዮሐንስን ፣ የመላእክቱን ፣ የቅዱሳኑን ትውፊትና የጉባኤ ኤፌሶንን ውሳኔ ይዘን ዛሬ እኛም ማርያም ከማለት ይልቅ ‹ወላዲተ አምላክ› ፣ ‹እመ አምላክ› ፣ ‹እመቤታችን› ፣ ‹እመብርሃን› እንላታለን፡፡

- **የማያቋርጠው የእመቤታችን ትሕትና**

እመቤታችን በቃናው ሰርግ ቤት የተገኘችበት ምክንያት የገሊላ አውራጃ ሰው በመሆንዋ ነው፡፡ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እርስዋ የተላከውም ‹ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ› መሆኑ ይታወሳል፡፡ (ሉቃ. ፩፥፳፮) እርስዋም የሀገር ሰው በመሆንዋና በደግነትዋ በዚህ ሰርግ ቤት ተገኝታለች፡፡ ወደ ሰርግ ቤት በመምጣትዋ የምናስተውለው ትልቅ ቁምነገር የእመቤታችንን ትሕትና

ነው። እመቤታችን ከፍጥረት ሁሉ ተለይታ ፈጣሪዋን ለመውለድ የተመረጠችበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ትሕትናዋ ነው። «ወደ ትሑትና መንፈሱም ወደተሰበረ ሰው አመለከታለሁ» በማለት የተናገረው ልዑል እግዚአብሔር እመቤታችንን ከሌሎች በላይ ሆና ያገኘበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ትሕትናዋ ነበር። እርስዋም ስትጸልይ «የባርያዪቱን መዋረድ አይቷልና» ብላ ከአንስተ ዓለም ለይቶ የመረጣት አምላክ በእርስዋ ላይ ምን እንዳየ ነግራናለች። (ኢሳ. ፶፯፥፲፭ ፤ ሉቃ. ፩፥፵፰) ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግም የእመቤታችንን ትሕትና ከሌሎች እንደ አብርሃም ፣ እንደ ሙሴ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያሉ ትሑታን አበው ጋር ካስተያየ በኋላ «ነገር ግን በምድር ላይ እንደ ማርያም ራሱን ዝቅ ያደረገ ሰው የለም ፤ በዚህም ምክንያት እንደ እርስዋ የከበረ ማንም አለመኖሩ በግልጥ የሚታይ ነገር ነው» ብሏል። (On The Mother of God ; Homily 1 St. Jacob of Serug)

እመቤታችን የአምላክ እናት ሆና ፈጽሞ ያልተለወጠና የማያቋርጥ ትሕትና ነበራት። ከሰው ልጆች ሁሉ እንደ እመቤታችን ያለ ትሕትና ያለውም የለም። ከፍጥረታት ሁሉ በላይ የሚያደርጋትን አምላክን የመውለድን ክብር መሸከም የቻለችበት ታላቅ ትሕትና ነበራት። ትዕቢት ብዙ ፍጹማንን ሳይቀር የጣለ እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ የማይለቅ ፈተና ነው። ወደ ሰማይ በቅድስና መሰላል የወጡ ብዙ ቅዱሳን ጥቂት ሲቀራቸው የወደቁት በትዕቢት ነው። ክብሩና ጸጋው ሲጨምር ጠባዩ የማይለወጥ ሰው የለም። አንድ አባት እንዲያውም ‹ጸጋንና ክብርን አትሥጠኝ ፤ ጸጋና ክብርን ከሠጠኸኝ ደግሞ መሸከም የምችልበት ትሕትና ሥጠኝ› ብሎ እስከመለመን ደርሷል።

እመቤታችን ግን ማንም ያልደረሰበትና [13]ሊደርስበትም የማይቻለውን የእናትነት ክብርን ይዛ ፣ በመላእክት አንደበት ተመስግና ለቅጽበት እንኳን አልተመካችም፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም ‹በትሕትና የተናገርሽ ተራራ ሆይ› ብሎ ያመሰገናት ይህች ድንግል እንደ ተራራ ከፍ ያለች ስትሆን ራስዋን እንደ ሸለቆ ዝቅ አድርጋ «እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን ይደረግልኛል?» ብላ በልብዋ አሰበች፡፡ በዚህ የእናታችን ትሕትና እጅግ እንደነቃለን ፤ ‹ድንግል ሆይ እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን አይደረግልሽም? የተመረጥሽው የሰማይና ምድርን ፈጣሪ ልትወልጂ አይደለም ወይ? እሳተ መለኮትን ተሸከመሽ ፣ ሰማይና ምድር የማይችሉትን ቻልሽ እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን አይደረግልሽም?› እያልንም እናመሰግናታለን፡፡

አምላክን ከጸነሰችበት ሰዓት ጀምሮ እመቤታችን ከፍጥረት ሁሉ በላይ የሚያደርጋትን ክብር ተጎናጽፋ እያለ ለቅጽበት አልታበየችም፡፡ በሦስት መንገድ ማለትም በሃሳብዋም ፣ በንግግርዋም ፣ በሥራዋም ትሕትናን አሳይታናለች፡ ፡ ሰማያዊ መልአክ አደግድጎ እያመሰገናት ‹እንዲህ ያለውን የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን ይቀበሉታል?› ብላ በልብዋ በማሰብ በሃሳብዋ ትሑት እንደሆነች አሳይታናለች፡፡ በንግግርዋ ደግሞ ከመጽነስዋ በፊትም ከጸነሰች በኋላም ራስዋን ‹እነሆኝ የጌታ ባሪያ› ‹የባሪያዪቱን መዋረድ አይቶአልና› በማለት በትሕትና ጠርታለች፡፡ ቅዱስ ያሬድ ‹እንዘ አመቱ እሞ ረሰያ› እንዳለ እግዚአብሔር

[13] ሰው በተጋድሎ እንደ ሰማዕታት ፣ እንደ ጻድቃን ፣ እንደ ቅዱሳን መሆንና ከደረሱበት ክብር መድረስ ይችላል፡፡ የድንግል ማርያምን ክብር ግን ሊደርስበት የሚቻለው የለም፡፡ ይህም ክብር አምላክን ጸንሶ የመውለድ ክብር ነው፡፡ የአምላክ ሰው መሆን ደግሞ አንዴ የተፈጸመ ነውና ሊደረስበት አይቻልም፡፡

ባሪያው ስትሆን እናቱ አደረጋት ፣ እርስዋ ደግሞ እናቱ ስትሆን ራስዋን ባሪያ አደረገች።

በተግባር ደግሞ ትሕትናዋን ያሳየችን ከመልአኩ ብሥራት በኋላ ባደረገችው ጉዞ ነው። እንደጸነሰች በእመቤት ደንብ ልቀመጥ ሳትል ወደ ተራራማው ወደ ኤፍሬም ሀገር ኤልሳቤጥን ለመጠየቅ ተፋጥናለች። የአምላክ እናት ሆና እያለ የነቢዩን እናት ኤልሳቤጥን ተሳልማለች። በስተርጅና የጸነሰችውን ኤልሳቤጥን ስትንከባከብ ሦስት ወራት ቆይታለች። (ሉቃ.፩፥፶፮)

አሁን ደግሞ በታላቅ ትሕትናዋ በሰርግ ቤት አስቀድማ ተገኘች። መገኘትዋ ብቻ ሳይሆን ሰርግ እንደተጠራ እንግዳ በክብር ወንበር ተቀምጣ መደሰትን አልመረጠችም። የሰርግ ቤቱ ወይን ጠጅ ማለቅ ከደጋሾቹ ቀድሞ ያስጨነቀው እርስዋን ነበር። በማያቆም ትሕትናዋ የምትደነቀው እመቤታችን በቃና ሰርግ ቤትም ውሎዋ ከክብር እንግዶች ጋር ሳይሆን ከአገልጋዮቹ ጋር ነበረ።

## ○ ቅዱስ ዮሴፍ በቃና ሰርግ ቤት ስምን አልተገኘም?

ሰርግ እና ለቅሶ የማይቀርበት የሰዎች መገናኛ እንደመሆኑ ከአንድ የምናውቀው ቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው ቢቀር ‹አገሌስ ምነው አልመጣም?› ብለን መጠየቃችን የማይቀር ነው። በዚህ ሰርግ ቤትም እመቤታችን ከነልጅዋ ተገኘች የሚለውን ሐረግ ስናነብ በሌሎች ወንጌላት ላይ ከጌታችን እና ከእናቱ ጋር እንዳልተለየ የምናውቀውን ፣ ከቤተልሔም ግርግም እስከ ግብፅ በረሃ

አብሮ ሲንከራተት የነበረውን ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍን ሳንጠይቅ ከቀረን የማይረሳው ረስተናል፡፡ ቅዱስ ዮሴፍን እዚህ ሰርግ ቤት ያላገኘነው ለምን ይሆን?

ወንጌላውያኑ ቅዱስ ዮሴፍ በተገኘበት ሥፍራ መገኘቱን ሳይጠቅሱ አያልፉም ነበር፡፡ ጌታችን በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ጠፍቶ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በተገኘ ጊዜ በፍለጋ ወቅት ቅዱስ ዮሴፍ መኖሩም በጥንቃቄ ተመዝግቧል፡፡ (ሉቃ.፪፥፵፫) ቅዱስ ዮሴፍ የናዝሬት ገሊላ ሰው እንደመሆኑና የቤተሰቡ አባት እንደመሆኑ በዚህ ሰርግ ቤት ታላቅ የክብር እንግዳ መሆን ይገባዋል፡፡ ቢኖር ደግሞ ዮሐንስ ‹ዮሴፍና እናቱም በሰርጉ ቤት ነበሩ› ብሎ ይጽፍ ነበር፡፡ ተገኝቶ ስሙን ስላልጠቀሰው ነው እንዳንል ደግሞ የደቀ መዛሙርቱን መገኘት ጽፎ እንዴት ቅዱስ ዮሴፍን ይተወዋል? ነገሩ ግን ወዲህ ነው በቃና ዘገሊላ ሰርግ በተደረገበት ጊዜ ቅዱስ ዮሴፍ ከሞተ ልክ ዐሥራ አንደኛ ዓመቱን ይዞአል፡፡ ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌል ጻድቅነቱን የመሰከረለት (ማቴ.፩፥፲፱) በአሳዳጊነቱ የጌታ አባት ተብሎ ይጠራ ዘንድ የተገባው (ሉቃ.፪፥፵፰) ለዘመናት በእንጨት ሥራ ሲደክም በዛለው የአረጋዊ ጉልበቱ አዝሎ ጌታን ያሳደገው ይህ ጻድቅ ሰው ለአንድ መቶ ዐሥራ አራት ዓመታት ኖሮ ጌታችን የዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለ በክብር ዐርፎአል፡፡ እኛንም በጸሎቱ ይማረን! (ስንክሳር ሐምሌ ፳፮)

## ፬. ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም በሰርጉ ታደሙ

○ ኢየሱስም ደግሞ...

ጌታችን ከልደቱ ጀምሮ በፍጹም ትሕትና በምድር ላይ ተመላልሷል፡፡ አሁን ደግሞ የአሕዛብ በሚበዙባት በሆነችው በትንሽዋ የቃና መንደር በድሆች ሰርግ ላይ ታዳሚ ሆኖ ተገኘ፡፡ ፈጣሪ ሆኖ ሳለ በፍጡራኑ ሰርግ ላይ ታደመ፡፡ አባ ሕርያቆስ «እኛ ግን ከእርሱ ጋር በላን ጠጣን» እንዳለው ከፍጡራኑ ጋር በሰርግ ቤት ማዕድ ተቀመጠ፡፡ ጻድቃንና ኃጢአተኞች ባሉበት የሰርግ ቤት ማዕድ ንጹሑ አምላክ ተገኘ፡፡ አይሁድ እሱን ለማሳጣት ካቀረቡአቸው ክሶች አንዱም «ኃጢአተኞችን ይቀበላል ፤ ከእነርሱም ጋር ይበላል» የሚል ነበር፡፡ (ሉቃ. ፲፭፥፩)

ጌታችን በቃና ዘገሊላ እንደ ልዩ የክብር እንግዳ ሆኖ አልተጠራም ነበር፡፡ «እንደማንኛውም እንደሚያውቁት ሰው ጠሩት እንጂ ፤ እንደ ታላቅ ሰው አልጠሩትም» /ቅዱ.ዮሐ.አፈ./ ‹ኢየሱስም ደግሞ በሰርጉ ታደመ› የሚለው አነጋገር ይህንን ያሳያል፡፡ የተቀመጠውም በተለየ የክብር ሥፍራ ሳይሆን ከእንግዶች እንደ አንዱ ነበር፡፡

በአንድ ወቅት ራሱ ጌታችን ሰርግ ቤት ገብቶ እንዴት መቀመጥ እንደሚገባ ሲያስተምር እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ «ማንም ለሰርግ ቢጠራህ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና አንተን እርሱንም የጠራ መጥቶ ለዚህ ስፍራ ተውለት ይልሃል፥ በዚያን ጊዜም እያፈርህ በዝቅተኛው ስፍራ ልትሆን ትጀምራለህ። ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ፥ የጠራህ መጥቶ ወዳጄ ሆይ፥ ወደ ላይ ውጣ



Scanned by CamScanner

እንዲልህ፥ ሄደህ በዝቅተኛው ስፍራ ተቀመጥ፤ ያን ጊዜም ከአንተ ጋር በተቀመጡት ሁሉ ፊት ከብር ይሆንልሃል» (ሉቃ. ፲፬፥፯)

ጌታችን ‹በሥራና በቃል› የሚያስተምር መምህር እንደመሆኑም (ሉቃ. ፳፬፥፲፱) በቃናው ሰርግ ቤትም ከእሱ የከበረ እንግዳ ሊጠራ እንደማይችል እያወቀ እንኳን በከበሬታ ስፍራ አልተቀመጠም፡፡ ክብሩንም የገለጠው በከበሬታ ስፍራ በመቀመጥ ሳይሆን በድንቅ ሥራው ነበር፡፡ ‹ኢየሱስም ደግሞ በሰርጉ ታደመ› ብሎ የጀመረው ታሪክ ‹ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ ፤ ክብሩንም ገለጠ› በማለት ይጠናቀቃል፡፡ በዚህ ሥራውም ‹በእኛ መካከል ተሰውሮ እያለ አሁን ግን ግልጥ ሆነ!› (እንዘ ሥውር እምኔነ ይእዜሰ ከሡተ ኮነ) ብለው እንግዶች ሁሉ አደነቁ፡፡ ይህ የአምላካችን መንገድም ‹ከሥራዬ ክብሬ ይቅደም› የሚለው ሰው ለበዛበት ዓለም ተግባራዊ ትምህርት ነው፡፡

ጌታችን ከእንግዶች ጋር ወንበር ተጋርቶ መቀመጡን ስናስብ ስለ ታላቅ ትሕትናው እንደነቃለን፡፡ የፈጣሪ ትሕትና ከፍጡራን ትሕትና የበለጠ የሚያስደንቅ ነው፡፡ ሰዎች ትሑታን ቢሆኑ እንኳን ፍጡር በመሆናቸው ዝቅ ማለት የሚገባቸው ነው፡፡ ሰው በትሕትና ‹አፈር ነኝ ትቢያ ነኝ› ሊል ይችላል ፤ ሊልም ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም እንደ እውነታው ሰው አፈርና ትቢያ ነው፡፡ ለዚህም ነው አባቶች ‹የሰው ትሕትናው ራሱን ማወቁ ነው› የሚሉት፡፡ ልዑል ለሆነው አምላክ ግን ራሱን በፈቃዱ ዝቅ ማድረጉ ፍጹም ትሕትናው ነው፡፡

‹እኔ የዋሕ በልቤም ትሑት ነኝ› ያለው ጌታችን በቃና ዘገሊላ ያሳየውም ይህን ትሕትናውን ነበር፡፡ (ማቴ.፲፩፥፳፱) ሰማይና ምድርን የሞላው አምላክ በአንድ ሰርግ ቤት ድንኳን ውስጥ ጥሪ አክብሮ ተገኘ፡፡ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጠው



Scanned by CamScanner

አምላክ በሰርግ ቤት ወንበር ላይ ተቀመጠ። ቅዱሳን መላእክት በፍርሃት በፊቱ የሚቆሙለት አምላክ ከሰርግ ቤት እንግዶች እንደ አንዱ ሆነ። ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ የጌታችንን ፍጹም ትሕትና እንዲህ ያደንቃል። «ጌታ ሆይ! ታላቅ ሲሆን ታናሽ የሆነ ፣ ንቁ ሲሆን የተኛ ፣ ንጹሕ ሲሆን የተጠመቀ ፣ ሕያው ሲሆን የሞተ ፣ ንጉሥ ሲሆን ራሱን ያዋረደ እንደ አንተ ያለ ማን አለ?» (Harp of Sprit ; Hymns On The Resurrection 22)

## ○ የተዋሕዶን ምሥጢር በሰርግ ቤት

ጌታችን ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ፣ በተዋሕዶ የአምላክነቱ ሥራ ከሰውነቱ ሥራ ተለይቶ እንደማይነገር ለማስረዳት ከምንጠቀምባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች አንዱ በዚህ ሰርግ ቤት መገኘቱ ነው። ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ የሆነውን የሁለት ባሕርይን ትምህርት ለመቃወም እና በመለኮትና በሥጋ ፍጹም ተዋሕዶ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ መሆኑን ለማስረዳት የተጠቀመበት ማሳያ ይህን ሰርግ ቤት እንደሆነ አንዳንድ መጻሕፍት መዝግበዋል።

ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የልዮንን ወገኖች «ክርስቶስን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት የጠሩት እንደ ሰው ነው ወይስ እንደ አምላክ?» ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም «እንደ ሰው ነው እንጂ አምላክስ ወደ ሰርግ ቤት አይጠራም» አሉት። ደግሞም «ውኃውን ወይን ያደረገው አምላክ ነው ወይስ ሰው?» ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም «አምላክ ነው እንጂ ሰውስ ውኃውን ወይን ሊያደርግ አይችልም» አሉት።



Scanned by CamScanner

ዲዮስቆሮስም ሲመልስ ፡-

«ወደ ሰርግ ቤትም የተጠራው ፣ ውኃውንም ወይን ያደረገው አንድ እርሱ ነው እንጂ ከእርሱ ጋራ ሌላ የለም፡፡ ወደ ሰርግ ቤት የተጠራው እርሱ ውኃውን ወይን እንዳደረገው ታወቀ ተረዳ፡፡ የተጠራው እርሱ ውኃውን ወይን አደረገ ካላችሁ ኹለት ባሕርይ ኹለት ፈቃድ ብላችሁ ለኹለት ልትከፍሉት አትችሉም፡፡ ... ትንሽ ቆይታችሁ ‹ወደ ሰርግ የተጠራው ሥጋ ነው ውኃውን ወይን ያደረገ መለኮት ነው› አትበሉ እንጂ ‹ወደ ሰርግ ቤት የተጠራው ውኃውን ወይን አደረገ› የምትሉ ከሆነ መልካም ነው፡፡ ከዚህ አልፋችሁ ‹ወደ ሰርግ ቤት የተጠራ ሥጋ ነው ፤ ውኃውን ወይን ያደረገው መለኮት ነው› የምትሉ ከሆነ ግን ይህ ንግግር ንስጥሮስ ‹ከእግዚአብሔር የተወለደው ተአምራት ያደርጋል ከማርያም የተወለደው መከራን ይቀበላል› ብሎ ያስተማረውን ትምህርት የመሰለ ነው፡፡ ... እንዲህ ከሆነ እስቲ ንገሩኝ ተዋሕዶ ወዴት አለ? ለትስብእትስ (ለሥጋስ) ወደ ሰርግ ቤት መጠራት ልማዱ ነውና ይገባዋል ኸረ መለኮት ሰርግ ቤት መግባት የማይገባው ሲሆን ለምን ተጠራ? ትስብእት ነው እንጂ መለኮት አልተጠራም አልሔደም እንዳትሉም ትስብእት ብቻውን ውኃን ወይን ሊያደርግ አይችልም፡፡ መለኮት የትስብእትን ሥራ ካልሠራ ፣ ትስብእት ደግሞ የመለኮትን ሥራ ካልሠራ እርስ በእርሱ ከተለያየ ተዋሕዶ ወዴት አለ? ጌታችን ራሱ ‹እርስ በእርስዋ የምትለያይ መንግሥት አትፀናም› (ማቴ. ፲፪፥፳፭) እያለ ሲያስተምረን እንዴት ራሱን እንከፍለዋለን?› ስለዚህ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት አንዱ ተጠሪ ሌላው አድራጊ ነው ሊባል አይገባም፡፡»

በማለት ጌታችን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት መገኘቱን ለሥጋና ለመለኮት ተዋሕዶ ማስረጃ አድርጎ አቅርቦታል፡፡ (መድሎተ አሚን ገጽ 303-305 ፤ መዝገበ ሃይማኖት - ነገረ ጉባኤ ራብኣዊ ቁ.10)

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊም ስለ ደብረ ታቦር በጻፈው ክታቡ ይህን ጉዳይ ሲያነሣ «ሰው ካልሆነ ወደ ቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት የተጠራው ማን ነው? ደግሞስ አምላክ ካልሆነ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠው ማን ነው?»[14] ብሏል፡፡ «የከበሩ መጻሕፍት

[14] "If He was not flesh, who was invited to the wedding in Cana of Galilee? And if He was not God, who turned the water into wine" (St. Ephraim : On The Transfiguration)

ክርስቶስ ሰው እንደሆነ እንደሚነግሩን አምላክ እንደሆነም ይነግሩናል፡፡ ግዙፍ እንደሆነ እንደሚነግሩን ረቂቅም እንደሆነ ይነግሩናል፡፡» ያለው ቅዱስ ሄሬኔዎስ ደግሞ «ወበከመ ጸምዐ ከማሁ አስተዮሙ ለሰብአ ከብካብ ረሰዮ ማየ ወይነ» «(ሰው በመሆኑ) እንደተጠማ እንዲሁ (አምላክ በመሆኑ) በሰርግ ቤት ለነበሩ ሰዎች ውኃውን ወይን አድርጎ አጠጣቸው» ብሏል፡፡ (ሃይ.አበ.ዘሄሬኔዎስ ምዕራፍ 7)

- ያለ ጋብቻ የተወለደው በጋብቻ በዓል ላይ

ጌታችን በሰርግ ቤት ታዳሚ መሆኑ የጋብቻን ቅድስናም ያስረዳናል፡፡ «ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንደሌለበት» ለምንናገር ለእኛ የጌታችን በሰርግ ቤት መታደም ታላቅ አብነት ሆኖናል፡፡ ራሳቸው ከጋብቻ የተገኙ ፍሬዎች ሆነው እያለ ጋብቻን እንደ ርኩስ ነገር ይቆጥሩ ለነበሩ መናፍቃንም ዘለፋ ሆኖአቸዋል፡፡

አንዳንድ ሰዎች እነርሱ ሊፈጽሙት ስላልተቻላቸው ብቻ የምንኩስናን ሕይወት እንደማያስፈልግ አድርገው ይናገራሉ፡፡ ‹ከምንኩስና ጋብቻ የተሻለ እንደሆነና በዓለም ላይ ከሰው ጋር ኖሮ ፈተናን መቋቋም የተሻለ ተጋድሎ እንደሆነ› አድርገው ሊሰብኩም ይጥራሉ፡፡ ይህ ፈጽሞ የተሳሳተ እና *‹የማትደርስበትን ፍሬ አይጣፍጥም አንዳለችው ጦጣ›* ያለ አካሔድ ነው፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ግን ስለ ድንግልና ሕይወት በጻፈው ጽሑፍ ላይ «ይኼን ሕይወት መኖር ቢያቅተን እንኳን እንዴት ማድነቅ ያቅተናል?» ብሏል፡፡ አክሎም በዓለም የምንኖረውን ሰዎች በድንግልና ሕይወት ከሚኖሩት ሰዎች ጋር በአንድ ሰርግ ቤት ውስጥ አስቀምጦ ያነጻጽረናል፡፡ በሰማያዊው ሰርግ ቤት ውስጥ አለ ‹ሐኛ ምግብ

ለመብላት የተጠጋን ነዳያን› ስንሆን በድንግልና ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ግን ‹ሙሽራውን (ክርስቶስን) የከበቡ ሚዜዎች› ይመስላሉ ብሏል፡፡ ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን ሁሉን ትቶ በመከተል በምናኔ ማገልገል ቢቻለው እጅግ ታላቅ ክብር ያገኛል፡፡ ጌታችንም «ፍጹም ልትሆን ብትወድ ያለህን ትተህ ተከተለኝ» ብሎ አስተምሯል፡፡ (ማቴ. ፲፱፥፳፩) መነኮሳት የመንግሥተ ሰማያትን ኑሮ ሳይሞቱ የጀመሩ ምድራውያን መላእክት ሰማያውያን ሰዎች ናቸው፡፡ የሚቻለን የእነሱን የሕይወት መንገድ እንከተላለን ፤ ካልተቻለን ደግሞ ጸሎታቸውንና በረከታቸውን እንማጸናለን፡፡

አንዲት ግብፃዊት ወጣት በአንድ መካነ ድር ላይ እንዲህ ብላ ለአንድ አባት ጥያቄ ላከች «እኔ ሕይወቴን ለክርስቶስ መሥጠት እፈልጋለሁ፡፡ በገዳም መኖር ግን አልፈልግም፡፡ ምን ይመክሩኛል?» እኚህ አባት ከገዳማዊ ሕይወት ውጪ በዓለም እየኖሩ እግዚአብሔርን እንዴት ማገልገል እንደሚቻል ከማስረዳታቸው በፊት የተናገሩት ነገር የበለጠ ትምህርት የሚሠጥ ነው፡፡ «የእኔ ልጅ ገዳማዊ ሕይወትና ምንኩስና አያስፈልግም ብለሽ ሳታቃልዪ ይህን ጥያቄ በትሕትና በመጠየቅሽ እግዚአብሔር ይባርክሽ!»

በሌላ በኩል የድንግልና ሕይወትን ከማድነቅ የተነሣ ጋብቻን እንደረከሰ ነገር መቁጠርም የተሳሳተ መንገድ ነው፡፡ መረሳት የሌለበት ነገር መነኮሳትም በጋብቻ የተወለዱ ልጆች መሆናቸው ነው፡፡ ጌታችን ያለ ጋብቻና ያለ ሩካቤ ተወልዶ እንኳን ጋብቻን አልነቀፈም፡፡ ይልቁንም በሰርግ ቤት በመገኘት የጋብቻን ቅድስና አረጋገጠ፡፡ አምላክን እንደምትወልድ ሲነገራት እንኳን ‹ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆንልኛል?› ብላ ስለ ድንግልናዋ የጠየቀችው

እመቤታችን በዘላለማዊ ድንግልናዋ ተመክታ ጋብቻን አልናቀችም፡፡ ይልቁንም በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ከነልጅዋ ታደመች፡፡ መታደምዋም ሳይበቃ ወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ ከልጅዋ አማልዳ ከተጋባዥነት ባለፈ ወደ ደጋሽነትም ገብታለች፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት እንዲህ ሲል ምእመናንን አስተምሮአል፡፡ ‹‹እስካሁን አላገባችሁም እንዴ? ከጋብቻም በኋላ ንጽሕናችሁን ይዛችሁ ስለምትኖሩ ይህንን የተቀደሰ ምሥጢር ለመፈጸም አትፍሩ፡፡ እኔ ሓላፊነቱን እወስዳለሁ፡፡ በሰርጋችሁም ላይ እገኛለሁ፡፡ ሙሽራዬቱንም መጥቼ አለብሳታለሁ፡፡ ለድንግልና ከፍ ያለ ክብር ስለምንሠጥ ጋብቻን አናቃልለውም፡፡ በዚህ ንጹሑን ሙሽራና የሙሽራዪቱ ራስ የሆነውን ክርስቶስን አመስለዋለሁ፡፡ እርሱ በሰርግ ላይ ተአምርን እንደፈጸመ ሁሉ በሰርጉ ላይ በመታደሙም ጋብቻንም አከብሮታል››[15] (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ትምህርት በአንተ ጥምቀት ቅድስት)

ጌታችን በሰርግ ቤት ይዞአቸው ከታደመው ደቀ መዛሙርት መካከል ወይን ጠጅ የማይቀምሰው የመናኙ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የነበሩት ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ እንድርያስ ይገኙበታል፡፡ የዮሐንስ ትሕርምትና ቅድስና የተደነቀ ፤ ‹ከሴት ከተወለዱት ሁሉ እንደ መጥምቁ ያለ የለም› ብሎ ጌታችን የመሰከረለት ነበር፡፡ ሆኖም እንደ ዮሐንስ በድንግልና መኖር እንዳለ ሁሉ በጋብቻ መኖርም ርኩሰት እንዳልሆነ አብረውት በሰርግ ቤት እንዲታደሙ በማድረግ አስተማራቸው፡፡ ወይንን አለመጠጣት የተሻለ ምናኔ ቢሆንም ወይንን የቀመሱ ሁሉ የረከሱ እንዳልሆኑ ሲያስረዳም የመጥምቁ ደቀመዛሙርትን ይዞ በቃና ዘገሊላ ስድስት ጋን ውኃን የወይን ጠጅ አደረገ፡፡

---

15 St. Gregory the Theologian, Oration on Holy Baptism, 18



Scanned by CamScanner

የጌታችን በቃና መታደም ‹በመከራህ ቀን ጥራኝ› ያለው አምላክ በደስታም ቀን ከእኛ ጋር እንዳለ አሳይቶናል፡፡ አንዳንድ ሰው ለሰው በኀዘን ጊዜ ፈጥኖ ደራሽ ይሆንና በደስታ ቀን ግን ወደ ኋላ ይላል፡፡ «እኔ ለሰው በክፉ ቀን ደራሽ ነኝ» እያሉ በዚያ በሰው የደስታ ቀን ግን መምጣት የማይወዱ ፣ ጨርሰው ድርሽ የማይሉ ሰዎች አሉ፡፡ በኀዘን ላይ መድረስ መልካም ቢሆንም ደስታ ሲሆን ሆን ብሎ መሸሽ ግን እንደ ድክመትና እንደ ምቀኝነትም ሊቆጠር የሚችል ነገር ነው፡፡ እንደ መጽሐፉ ከሆነ «ከሚያለቅሱ ጋር ማልቀስ እንደሚገባ ሁሉ ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ መሰኘትም» ተገቢ ነው፡፡ (ሮሜ.፲፪፥፲፭) ክርስቲያን ማለት ‹የደስታ ሕይወት የተለየውና ኀዘንተኞችን ከማጽናናት በቀር ደስታቸውን የማይካፈል› እንዳልሆነ አምላካችን በቃናው ሰርግ ቤት በተግባር አስረዳን፡፡ አንድ ግሪካዊ ጸሐፊ «ለመጾም ጊዜ እንዳለው ሁሉ በዓል ለማድረግም ጊዜ አለው» ብሎ እንደተናገረው ነው፡፡ (እንግሊዝኛው የበለጠ ይገልጸዋል፤ "There is a time to feast as well as a time to fast.)

ጌታችን በቃና ዘገሊላ ሥራውን መጀመሩ አንደኛ የጋብቻ መሥራች መሆኑን የሚያስታውስ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ለካሳ መምጣቱን እና «የዲያቢሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ መገለጡን» ያስረዳናል፡፡ (፩ዮሐ. ፫፥፱) ቅዱስ አውግስጢኖስ ጌታችን በሰርግ ቤት ለምን እንደተገኘ ሲያስረዳ ‹‹በገነት ጋብቻን የመሠረተው እርሱ ራሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው››[16] ብሏል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለካሳ ነው፡፡ ዲያቢሎስ የሰውን ልጅ ለውድቀትና ለሞት የዳረገው በመጀመሪያዎቹ

16 "...to confirm that He Himself established marriage (in Paradise)" St. Augustine, *On John*, 9.2)

ሙሽሮች በአዳም እና ሔዋን መካከል ገብቶ ነበር:: አምላካችን ይህን የዲያቢሎስን ተንኮል ያፈርስ ዘንድ ሰው በሆነ ጊዜ ምልክቱን ማድረግ የጀመረው በቃና ዘገሊላ የጋብቻ በዓል ላይ መሆኑ ካሳ ያደርገዋል::

- ደቀ መዛሙርቱ

በቃናው ጋብቻ ላይ ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ታድሟል:: ደቀ መዛሙርት የሚለው ስያሜ በወንጌል ሁለት ዓይነት ትርጉምን ይሠጣል:: አንደኛው ትርጉም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጌታችንን እየተከተሉ የሚማሩትን ሕዝብ ሁሉ የሚያጠቃልል ስም ነው:: ለዚህ ማሳያ የሚሆነንን አንቀጽ በዮሐ. ፮፥፷፮-፷፯ ያለው ነው:: «ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ ፤ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም። ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ። እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? አለ።» በቃና ዘገሊላ ግን ይህ ስያሜ የሚመለከተው ሐዋርያቱን ብቻ ነው::

በቃና ዘገሊላ ተአምር ያደረገበት ጊዜ ዐሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት መርጦ የጨረሰበት ጊዜ እንደነበረ የሚያሳይ ጽሑፍ በወንጌል አናገኝም:: እንደ ዮሐንስ ወንጌል ብቻ ከሆነ ደግሞ ጌታችን እስከ ቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ድረስ የጠራቸው ሐዋርያት ዮሐንስ ፣ እንድርያስ ፣ ያዕቆብ /ከዮሐንስ ጋር አብረው እንደተጠሩ በማሰብ ሉቃ. ፭፥፲/ ፣ ጴጥሮስ ፣ ፊልጶስ ፣ ናትናኤል ናቸው::

በትርጓሜ ወንጌል ላይ ጌታችን ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ያለበትን ምክንያት ሊቃውንቱ ሲያብራሩ ‹ይሁዳ አልነበረምና› የሚል ማብራሪያን ጽፈዋል፡፡ ይህ እንዴት ነው ቢባል ይሁዳም ሆነ የቀሩት ሐዋርያት በቃና ዘገሊላ ተአምር ወቅት ስለመመረጣቸው የሚያስረዳ ነገር ባናገኝም እንደ ሌላ እንግዳ በሰርግ ቤቱ አልነበሩም የሚል ነገርም ስለማናገኝ የትርጓሜውን ሃሳብ አናቃልለውም፡ ፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› የሚለውን በተረጎመበት አንቀጽ (ያለበት አገባብ ለሌላ ሃሳብ ቢሆንም) «ጊዜዬ ገና አልደረሰም ያለው ይህን ተአምር ይረዱ ዘንድ የተገባቸው ሰዎች ቁጥር ገና ስለነበር ነው» ማለቱ ይሁዳንም ሆነ የቀሩትን ሐዋርያት ሊያካትት የሚችል ሃሳብ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

## ምዕራፍ ሦስት

# ምልጃና ጠለስ

‹‹የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት
የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው።
ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?
ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት።
እናቱም ለአገልጋዮቹ። የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው።››
ዮሐ. ፪፥፫-፭

## ፩. የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ

### ○ የወይኑ ማለቅ ለሙሽሮቹ ምን ያስከትል ነበር?

[17]ድህነት በራሱ በዚህች ቁሳዊነት በሰፈነባት ዓለም ዝቅ ያልን ሆነን እንድንታይ የሚያደርገን ነው። ሰዎች በማጣታቸው ስለሚሰቀቁ በተቻለ ዓቅም እንደተቸገረ ሆኖ ላለመታየት እና ደስተኞች ለመምሰል ይጥራሉ። በቃናው ሰርግ ቤት የታየው የደስታ ቀን ጉድለት ግን እጅግ የከፋ ነው። አንድ ሰው ድህነቱ ምንም ቢያስጨንቀው ቆሎ እየቆረጠመ እና ውኃ እየጠጣ

[17] ድህነት የሚለው ቃል በሃሌታው ሀ ሲጻፍ ማጣትን ችግርን የሚያሳይ ሲሆን በብዙኃኑ ኀ ድኅነት ተብሎ ሲጻፍ ግን መዳንን ያሳያል።



Scanned by CamScanner

ችግሩን ተቋቁሞ ክብሩን ሊያስጠብቅ ይችላል፡፡ ደሃም ይሁን ሀብታም ሰው ብሉ ጠጡ ብሎ ጠርቶ እንግዶችን መሸኘት ሲያቅተው የማይቋቋመው ማኅበራዊ ቀውስና ውርደት ይሆንበታል፡፡ የቃናው ሙሽሮች ሊደርስባቸው የነበረው ይኼ እፍረት ነበር፡፡ ያለቀው ደግሞ ‹ድህነትን ያስረሳል› ተብሎ የተነገረለት የወይን ጠጅ ነው፡፡ (ምሳ. ፴፩፥፯)

ሰርግ የተጠራ ሕዝብ ‹ሙሽሮቹ ለመስተንግዶ ዓቅም አነሳቸው› ሲባል ድሆች ከሆኑ «ማን ደግሱ አላቸው? ሰው ሲያደርግ አይተው ነው! ዓቅማቸውን አያውቁም ነበር!» ብሎ ያፌዝባቸዋል እንጂ አያዝንላቸውም፡፡ ባለጠጎች ከሆኑ ደግሞ «ሲሰገበገቡ ለዚህ ቀን መሆን አቃታቸው... ለካ ያላቸው ባዶ ጉራ ብቻ ነው እንጂ» ብሎ ይሳለቅባቸዋል፡፡ ካለፈም በኋላ ‹እንደነ እገሌ ሰርግ...› እየተባለ መተረቻ ይሆናሉ፡፡ ውርደቱ ለቤተሰብ እና ለዘመድ አዝማድ ጭምር የሚተርፍ ይሆናል፡፡ ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ሰርግ በድጋሚ ተደግሶ ሰው ተጠርቶ የሚካስበት አለመሆኑ ሲሆን በድጋሚ መደገስ ቢቻልም እንኳን ያለፈው ታሪክ ፈጽሞ ሊፋቅ የሚችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የቃናዎቹ ሙሽሮች ሊደርስባቸው የነበረው የዕድሜ ልክ ዘመን እፍረት ነበር፡፡ እንደ ሌሎች ሙሽሮች የሰርጋቸውን ዕለታት በትዝታ ከማውራት ይልቅ ባስታወሱ ቁጥር የሚሸማቀቁበት እና እንዳይነሣ የሚፈልጉት ርዕስ ይሆን ነበር፡፡ በሰው እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻላልና ሙሽሮቹ በእሱ እጅ መውደቃቸው የተሻለ ሆነላቸው፡፡



Scanned by CamScanner

- ስድንግል ማርያም የወይኑን ማለቅ ማን ነገራት?

እመቤታችን ለልጅዋ የተናገረችው ሰዎች መጥተው ፣ ከእግርዋ ሥር ወድቀው ‹ከጉድ አውጪን› ብለው ለምነዋት አልነበረም፡፡ ‹[18]ሳንለምነው የምንሻውን አውቆ የሚሠጠን› የአምላካችን እናት ናትና እስዋም ሳይለምኗት የሚያስፈልጋቸውን በተሠጣት ጸጋ አውቃ አማለደቻቸው፡፡

የወይን ጠጁን ማለቅ ለእርስዋ ማንም አልነገራትም፡፡ መጽሐፉም የሚለው «የወይን ጠጁ ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት...» እንጂ ወይን አምጡልን ብለው ተጋባዦቹ ደጋግመው በተጣሩ ጊዜ አይደለም፡፡ ይህ የሚያሳየው ለዓይን ከሽፋሽፍቱ ቀድማ የምትደርሰው እመቤታችን ፣ ነቢዩ ኢሳይያስ ‹ፈጣን ደመና› ብሎ የጠራትና ወደ ዘመድዋ ኤልሳቤጥም ‹ፈጥና ወጣች› ተብሎ የተነገረላት እመቤታችን ለቃናዎቹ ሙሽሮችም የደረሰችላቸው ፈጥና መሆኑን ነው፡፡ (ኢሳ. ፲፱፥፩ ፤ ሉቃ. ፩፥፴፱) ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስም ስለዚህ ሰርግ ቤት በጻፉበት አንቀጽ «እመቤታችን ድንግል ማርያም ከሰው ወገን የሰው ችግር ቶሎ የሚገባት ቶሎ የሚታያትና የሚሰማት ርኅርኅት ናት፡፡ የሰዎቹ ችግር ገብቷት ለልጅዋ ነገረችው»[19] ብለዋል፡፡

ፈጥና አማለደች ስንል ደግሞ እመቤታችን ለጌታ የተናገረችው ያለ ጊዜው በችኮላ ነው ለማለትም አይደለም፡፡ ልመናዋ በወሳኝ ሰዓት /critical time/ የተደረገ ነው፡፡ ብትዘገይ ችግሩ ይፋ ይሆን ነበር፡፡ ሙሽሮቹም ስማቸው ይጠፋ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ተአምር ቢደረግም ከጉዳት በኋላ የተደረገ እርዳታ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ወይን ጠጁ እንዳለቀ ያማለደችው ማንም ሰው ሳይሰማ ፣

[18] ‹ዘእንበለ ንስአሎ ይሁብ ፍትወተነ› መጽሐፈ ኪዳን
[19] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ. 156

በሰርጋቸው ላይ ገመናቸው ሳይወጣ ነበር። ተአምረ ኢየሱስም «ከእመቤታችን ፣ ከደቀ መዛሙርቱ ፣ ከጠጅ አሳላፊዎች በስተቀር ሕዝብ ሁሉ ፈጽሞ አያውቅም ነበር» ይላል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም «ስለተደረገው ነገር ትኩረት ሠጥተው የተረዱት) አገልጋዮቹ ፣ አሳዳሪውና ሙሽራው ነበሩ»[20] ብሏል። አሳዳሪውም ስለ ወይኑ ያደነቀው ሙሽራውን ለብቻው ጠርቶ እንጂ ሰው ሁሉ ፊት አለመሆኑን ከዚያ ጥቅስ ልብ እንላለን።

እዚህ ላይ ውኃው ወይን ተደርጎ የመሠጠቱ ዜና በዕለቱ ቢደበቅም ቆይቶ ሰው ጆሮ ሲደርስ ገመናቸው መውጣቱ መቼ ቀረ? ሲባል ይችላል። ነገር ግን የተፈታን ችግር ያን ያህል ትኩረት ሠጥቶ የሚያወራበት የለም። የውኃው ወይን መሆን ዜና የወይኑን ማለቅ ሐሜት የሚያሸንፍ ዜና ስለሆነ ሙሽሮቹ ነጻ ይወጣሉ። በእኛ ዘመን እንኳን በሰርግ ላይ አንድ ወሳኝ ነገር ድንገት ቢጎድልና ቢሞላ ካለፈ በኋላ አንድ ሰው መጥቶ «እንዳትደነግጡ ብዬ እንጂ እንዲህ ዓይነት ጎድሎ ነበር እኮ ነገር ግን እንደምንም ብለን በምሥጢር ሞላነው» ብሎ ቢነገረን ‹እንኳንም በሰላም አለፈ› ብለን ከማመስገንና ከማድነቅ አልፈን «እንዲህ ያለ ነገር ጎድሎ ነበር» ብለን እንዳዲስ ገመና እንዳይወጣ የሚል ስጋት አይኖርብንም።

## ፪. <u>የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም</u>

[20] " For only the servants, the ruler of the feast, and the bridegroom, not the greater number of those present, gave heed to what was done" Homily XXIII. John ii. 11 /St. Jhon Chrysostom/

○ **በመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የድንግል ማርያም ልመና**

ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡና ሲያነጋግሩት የሚለምኑት ስለራሳቸው አይደለም። የትኛውም ጻድቅ ‹እግዚአብሔር ሆይ ርስት ጉልት ሥጠኝ› ሲል አናገኝም። እንዲያውም ያየናቸው ከራሳቸው ጥቅም አስበልጠው ‹ሕዝቡ ከሚጠፉስ እኔ ልጥፋና ሕዝቡ ይዳን› ሲሉ ነው። ስለ እስራኤል የለመነው ሙሴና ስለ ሰዶም የተማጸነው አብርሃም ለዚህ ምሳሌዎች ናቸው። አልፎ ተርፎ በሰማይ ክብር አግኝተው በዙፋኑ ፊት ሲቆሙ እንኳን «ስለወገኖቻችን ስለምን አትፈርድም?» ሲሉ ታይተዋል። (ዘጸ. ፴፪፥፴፪ ፤ ዘፍ. ፲፰፥፳፬ ፤ ራእ. ፮፥፲)

ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችንም በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ወደ ልጅዋ ያቀረበችው ብቸኛ ልመና ‹ወይን እኮ የላቸውም› የሚለው ነው። «አንተን መውለዴ ለመቼ ሊሆነኝ ነው? እንዲህ አድርግልኝ እንጂ» ስትል አልሰማናትም። ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳን ትቶት የመጣውን አንድ በሬ ፣ አንድ አህያ ከጀልባና መረቡ ጋር አስቦ (ሠርቼ እከብራለሁ የሚል ሃሳቡን መተዉን አስቦ) «ጌታ ሆይ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ፤ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን?» ብሎ ነበር። የዘብዴዎስ ልጆች ዮሐንስና ያዕቆብም ‹‹በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝ አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ሥጠን›› ብለውት ነበር። (ማቴ. ፲፱፥፳፯ ፤ ማር. ፲፥፴፯)

ዘጠኝ ወር በማኅጸንዋ የተሸከመችው ፣ ጡትዋን አጥብታ ያሳደገችው ፣ ይዛው በረሃ ለበረሃ የተንከራተተችው እመቤታችን ግን ለራስዋ ስትለምን አልተገኘችም። በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበው ብቸኛውና የመጨረሻው ልመናዋ ‹ወይን እኮ የላቸውም› የሚል ነበር። በአዋልድ መጻሕፍትም ላይ



Scanned by CamScanner

እመቤታችን ‹ማርልኝ› ስትል እንጂ ስለ ራስዋ ስትጠይቅ አናገኝም፡፡ «እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ» የሚለውን ቃል እመቤታችን በተግባር አሳይታናለች፡፡ (፩ቆሮ. ፲፥፳፬)

እመቤታችን በቃና ሰርግ ቤት የለመነችው ስለራስዋ ሳይሆን ወይን ስለሌላቸው ስለ ሌሎች ነው፡፡ ጌታችን ሌሎች እንደሚሉት የእውነት ተቆጥቶም ቢሆን ኖሮ እንኳን የጠየቀችውን አድርጓል፡፡ በታሪኩ መጨረሻም ‹የላቸውምኮ› ያለችው ወይን ለሰርገኞቹ ተሠጥቶአል፡፡ አንድ ሰው ‹በፍጹም ዓይኔን ግንባር ያድርገው› ካላለ በስተቀር በዚህ ሰርግ ቤት የአማላጅነት ሥራ መሥራትዋ በግልጽ የተቀመጠ ነገር ነው፡፡

- ትእዛዝ እና ማሳሰቢያ የሌለበት ልመና

‹ወይን እኮ የላቸውም› የሚለው አነጋገር ፍጹም ትሕትና ያለበት ልመና ነው፡፡ እንዲህ አድርግ የሚል ትእዛዝ /አገብሮ/ የለበትም፡፡ በልጅዋ እምነት ነበራትና ሌሎች እንዳደረጉት እሺ በለኝ የሚል አደራንም አላስቀደመችም፡፡

የሰሎሞን እናት ቤርሳቤህ ወደ ልጅዋ ሰሎሞን ለልመና ስትመጣ ልጅዋ ተነሥቶ በክብር ተቀበላት ፤ ወንበር አስመጥቶም በቀኙ አስቀመጣት እስዋም ‹አንዲት ታናሽ ልመና እለምንሃለሁ አታሳፍረኝ› ብላ ከልመናዋ በፊት እሺ እንዲላት አሳሰባው ነበር፡፡ ከሰሎሞን የሚበልጠው የክርስቶስ እናት እመቤታችን ግን በቃና ዘገሊላ ልጅዋን ስትጠይቅ አስቀድማ ማሳሰቢያ



Scanned by CamScanner

አልተናገረችም፡፡ (፩ ነገሥ.፲፱፥፳) እንደ ዮሐንስና ያዕቆብ መምህር ሆይ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንወዳለን›› ብላ ማሳሰቢያ አልሠጠችም፡፡ (ማር. ፲፥፴፭)

«በሰርግ ቤቱ ያለውን ችግር እንዲህ አድርገህ ፍታ» ብላ ለማይነገረው አምላክ አልተናገረችም፡፡ የትሕትና ጸሎት ችግርን በእግዚአብሔር ፊት ማስቀመጥ ነውና ለልጅዋ ‹ወይን እኮ የላቸውም› አለችው፡፡ ይህ ትሑት ልመናዋ አንዳንዴ ሁሉን ነገር በእኛ ምክረ ሃሳብ ለማስፈጸም ለምንጸልይ ሰዎች ወይም ደግሞ እግዚአብሔርን የቀረብን መስሎን ‹እንዲህ ካላደረግህልኝ በዙፋንህ የለህም› ብለን ፈጣሪን ለምንፈታተን ደካሞች ተግሣፅ ነው፡፡

ይህንን ስንል ደግሞ «ወይን እኮ የላቸውም» ያለችው ለመለመን ሳይሆን ምልከታዋን /observation/ ለመናገር ያህል ብቻ ነው» ብለው አንዳንድ መናፍቃን እንደጻፉት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ምንም ዓይነት ልመና ሳይቀርብለት ምንም የተጠየቀው ነገር ሳይኖር መቼም ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› አይልም፡፡ ምንም ካልለመነችው ‹የምኑ ጊዜ ነው ያልደረሰው?› ያሰኛል፡፡ ለምሳሌ አንዲት እናት ‹ይቺ ልጅ እኮ ጫማ የለውም› ብላ ለአባቱ ብትናገር የተናገረችው ምልከታዋን /observation/ እንዳልሆነ ወይም የመረጃ ልውውጥ ብቻ አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡

- ጌታችን የወይኑን ማለቅ እናቱ ሳትነግረው አያውቅም ነበርን?

ጌታችን ‹በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ወይን ጠጅ ማለቁን እመቤታችን እስከምትነግረው ድረስ አያውቅም ነበር ወይ?› ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር የቃናው ወይን ጠጅ

እንደሚያልቅ ‹ከማለቁ አስቀድሞ ብቻ ሳይሆን ሰማይና ምድር ሳይፈጠሩም ያውቅ ነበር› ብለን እንመልሳለን፡፡ ይሁንና የእርሱ ተአምራት በእናቱ አማላጅነት ይገለጥ ዘንድ ዝም አለ፡፡ ከነናዊትዋ ሴት ‹ልጄን ማርልኝ› ብላ ስትጮኽ የሐዋርያቱ አማላጅነት ይታወቅ ዘንድ እየሰማ ዝም እንዳለ በዚህ ሰርግ ቤትም የወይን ጠጁን ማለቅ እያወቀ የእናቱ አማላጅነት ይታወቅ ዘንድ ዝም አለ፡፡ (ማቴ. ፲፭፥ ፳፫)

ጌታችን ሁሉን ሲያውቅ እንዳላዋቂ በትሕትና ዝም ማለት ልማዱ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ እንዳደነቀው ሁሉን አዋቂ ሲሆን ሊማር ከአይሁድ እግር ሥር ተቀምጦ ነበር፡፡ ዐሥርቱ ቃላትን በጣቶቹ የጻፈው እርሱ ሆኖ ሳለ ከትምህርት ገበታ በትሕትና ተቀምጧል፡፡ በሰናዖር ሜዳ ሰው ልጆችን ቋንቋ የደባለቀው እና ሁሉንም ቋንቋዎች የፈጠረ እርሱ ነበር፡፡ ሆኖም በምድር ላይ ሲኖር የአሕዛብን ቋንቋ እንደማያውቅ ሆኖ የዕብራውያንን ቋንቋ (አራማይክ) ብቻ ሲናገር ኖረ፡፡ (አርጋኖን ዘሐሙስ) አሁንም በቃና ዘገሊላ እንዳላወቀ ዝም ብሎ የእናቱን ምልጃ ሰማ፡፡

አንዳንዶች እመቤታችን የወይን ጠጁን ማለቅ ስለነገረችው እንደተቆጣ አድርገው ይናገራሉ፡፡ ጌታችን ‹የማውቀውን ነገር ስለምን ነገርሽኝ?› ብሎ ይቆጣል ብሎ ማሰብ የጌታችንን ትሑት ኅሊና ያለመረዳትና መጽሐፍ ቅዱስንም ያለ ማወቅ ውጤት ነው፡፡ እግዚአብሔር መቼም ቢሆን የማውቀውን አትንገሩኝ ብሎ የለመኑትን ሲቆጣ አናገኝም፡፡ ገና ከኦሪቱ ብንጀምር እንኳን በትሕትና «አዳም ሆይ ወዴት ነህ?» ‹ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?› እያለ ሲጠይቅ እናገኘዋለን፡፡ በአስረጂነት ለማሳየት ያህል እንጂ ዛሬስ ቢሆን ጸሎት የምንጸልየው

ለእግዚአብሔር የማያውቀውን ለመናገር ብለን ነው? እሱስ ‹ትገና ጸልዩ› ሲል የማላውቀውን ንገሩኝ ማለቱ ነውን? አይደለም፡፡

### ○ እመቤታችንና ሐዋርያት

ጌታችን እንኳንስ አትንገሩኝ ሲል ቀርቶ በወንጌል ተአምራቱን ለማድረግ ሲፈልግ አስቀድሞ ሰዎች ይለምኑት እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ሲፈትን ተመልክተናል፡፡ በጥብርያዶስ ባሕር ማዶ ሲያስተምር ብዙ ሕዝብ ተከትለውት ነበር፡፡ አብረውት የዋሉት ሕዝብ ምግብ ሳይመገቡ ሰዓቱ መሸ፡፡ ሐዋርያቱ እንደ ቃናዋ እንግዳ እንደ እመቤታችን ‹የሚበሉት እኮ የላቸውም› ብለው ለጌታችን አልተናገሩም፡፡ ወደ እርሱ ቀርበው «ቦታው ምድረ በዳ ነው ፤ አሁንም ሰዓቱ አልፎአል ፤ ወደ መንደሮች ሔደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት» አሉት፡፡ ይህን ጊዜ ጌታችን ፊልጶስን ‹‹እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው። ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ። ፊልጶስ። እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ። አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለው።›› ከዚህ በኋላ ሕዝቡ እንዲቀመጡ አዝዞ አምስቱን እንጀራ እና ሁለቱን ዓሣ ባርኮ መገባቸው፡፡ (ማቴ.፲፬÷፲፭-፳፩ ፤ ዮሐ. ፮÷፭-፱)

«ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ»[21] የሚለው ቃል ምንኛ ድንቅ ነው፡፡ ለፊልጶስ የጠየቀው ተአምሩን ከመሥራቱ በፊት በፊልጶስ

---

[21] ሙሴንም ‹በእጅህ የያዝኸው ምንድርን ነው?› ብሎ ጠይቆት ነበር፡፡ የጠየቀው በሙሴ እጅ ምን እንዳለ ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን በትሩን እባብ ከማድረጉ በፊት በሙሴ እንደበት በትር መሆኑን ለማስመስከር ነበር፡፡ ዘጸ. ፬÷፪



Scanned by CamScanner

አንደበት ያለውን የምግብ እጥረት እንዲነገር እና በኋላ ለሚያደርገው ተአምራት ምስክር እንዲሆን ለማድረግ ነው። ስለዚህ ጌታችን እንኳንስ ‹የማውቀውን ነገር ለምን ነገራችሁኝ?› ብሎ ሊቆጣ ይቅርና ሳይነግሩት ሲቀሩም ራሱ የሚጠይቅ እና ተአምሩን የሚሠራ አምላክ ነው።

እዚህ ላይ የሚያስገርመን በእመቤታችንና በሐዋርያቱ መካከል ያለ ታላቅ ልዩነት አለ። ሐዋርያቱ ጌታ ለዚያ ሁሉ ሕዝብ ምግብ ሊያበላ ይችላል የሚል እምነት ስላልነበራቸው ‹የሚበሉት የላቸውምና በዙሪያ ወዳሉ ገጠሮችና መንደሮች ሄደው እንጀራ ለራሳቸው እንዲገዙ አሰናብታቸው› ብለው ራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ሞከሩ።

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት የወይን ጠጁን ማለቅ ቀድመው ያወቁት ደቀ መዛሙርቱ ቢሆኑ ኖሮ ምን ይሉ ይሆን? እመቤታችን ግን ሐዋርያቱ ሲያደርጉት እንደምናየው የወይኑን ማለቅ ስትረዳ ‹ልጄ ሆይ በጊዜ ከሰርግ ቤቱ ተሰናብተን እንውጣ› ብላ ራስዋን ከጉዳዩ ለማውጣትና ለመሸሽ አላሰበችም። ጌታችን ነገሩን ካነሣባቸው በኋላም እንኳን ከሐዋርያት መካከል ጌታን ቀርቦ የለመነው አንድም ሰው አልነበረም። እመቤታችን ግን እሱ ነገሩን ሳያነሣው ቀድማ ‹ወይን እኮ የላቸውም› ስትል አማለደች። ከሁሉ የሚገርመው ሐዋርያቱ በጥብርያዶስ ‹የሚበላ ስለሌለ ሕዝቡን አሰናብታቸው› ብለው በተስፋ መቁረጥ የተናገሩት ጌታ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ያደረገውን ድንቅ ተአምር ካዩ በኋላ መሆኑ ነው። ከዚህ የምንረዳውም እመቤታችን ከቃናው ተአምር በፊት በልጅዋ ላይ የነበራት የእምነት ደረጃ ፤ ሐዋርያት ከቃናው ተአምር በኋላም እንኳን እንዳልነበራቸው ነው። በእውነት ጌታችን መቆጣት ቢያስፈልገው እንኳን ይቆጣ የነበረው



Scanned by CamScanner

ለመለመን እምነት የጎደላቸውን ሐዋርያቱን እንጂ ‹ያመነችውን ብፅዕት› እመቤታችንን አልነበረም፡፡

ሐዋርያት በቃና ዘገሊላ ተአምር ማድረግ መቻሉን አይተው ለሕዝቡ ምግብ እንዲሠጥ ያልለመኑት ምናልባት ‹ውኃን ወይን ሲያደርግ› እንጂ ‹ምግብ ሲያበረክት› ስላላዩ ነው እንበል፡፡ የሚገርመው ግን ሐዋርያቱ ምግብ ሲያበረክት ካዩ በኋላም ‹ምግብ አበርክቶ ይመግባል› የሚል ሙሉ እምነት አልነበራቸውም፡፡ በግልጽ የገሠጻቸው ስለ ዝንጋዔያቸው ብቻ ሳይሆን ስለ እምነታቸው መጉደል ነበር፡፡

ጌታችን ዓሣና እንጀራን አበርክቶ ሕዝብ የመገበው ለሁለት ጊዜ ነበር፡፡[22] አንደኛው በአይሁድ ዘንድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአሕዛብ ዘንድ በገሊላ ነው፡፡ ይህን ያደረገው ለሕዝብም ለአሕዛብም እንደመጣ ለማስረዳት ነበር፡፡ በእነዚህ በሁለቱም ጊዜያት ሐዋርያቱ አብረውት ነበሩ፡፡

የመጀመሪያውን ተአምር ሲያደርግ ቆመው ያዩትና አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ አቅርበው ባርኮ ሲመግብ ያዩት ደቀመዛሙርት ለሁለተኛ ጊዜ ሕዝብ በተራበበት ወቅት ያደረጉትን እስቲ እንመልከት፡፡

‹‹ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ። ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለ ሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፤ በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም አላቸው።

[22] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጌታችን ሌሎች ተአምራትንና ፈውሰን ለማይቆጠሩ ጊዜያት ደጋግሞ ሲያደርግ ሕዝብ የመገበው ግን ሁለት ጊዜ ብቻ የነበረው የሚከተሉት ሁሉ ከትምህርት በኋላ ምግብ ፈልገው እንዳይከተሉት ሲል ነው ብሏል፡፡ በእርግጥም ጌታችን በየዕለቱ ተአምር እየሠራ ከመገበ ብዙ ሥራ ጠል ሰነፎችም እየተማሩ ለመጠር ሲሉ ይከተሉት ነበር፡፡

ደቀ መዛሙርቱም፡፡ ይህን ያህል ሕዝብ የሚያጠግብ ይህን ያህል እንጀራ በምድረ በዳ ከወዴት እናገኛለን? አሉት።

ኢየሱስም፡- ስንት እንጀራ አላችሁ? አላቸው። እርሱም፡- ሰባት፥ ጥቂትም ትንሽ ዓሣ አሉት። ሕዝቡም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤ ሰባቱንም እንጀራ ዓሣውንም ይዞ አመሰገነ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ። ሁሉም በሉና ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሡ።›› (ማር.፰፥፴፰፤ማር.፳፥፪) በዚህ ታሪክ ላይ እንደምናየው አምስት እንጀራ አበርክቶ የመገበ ጌታ በቁጥር የሚበልጠውን ሰባት እንጀራን ሊያበረክት እንደሚችል አለማመናቸው እጅግ ያስደንቃል፡፡

በዚህ ቢያበቃ ጥሩ ነበር፡፡ ሆኖም ሐዋርያት ለሁለተኛ ጊዜ እንጀራና ዓሣ አበርክቶ ሕዝቡን ከመገበ በኋላም ‹እንጀራ አበርክቶ ይመግባል› የሚል እምነት አልነበራቸውም፡፡ ለማመን ይከብድ ይሆናል ፤ ሆኖም ሐዋርያቱ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ አበርክቶ ዐሥራ ሁለት መሶብ ትርፍራፊ ካነሡ በኋላም ፤ ሰባት እንጀራና ጥቂት ዓሣ አበርክቶ ሰባት ቅርጫት ሙሉ ትርፍራፊ ካነሡ በኋላም እምነት አልነበራቸውም፡፡

ከሁለቱ ታሪኮች በኋላ በአንድ ዕለት ወደ ጌታችን ወንዝ ተሻግረው ሲመጡ እንጀራ መያዝን ረስተው ነበር፡፡ ጌታችን በዚያ ሰዓት ከፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ጋር ሲነጋገር ቆይቶ ነበር፡፡ ሐዋርያቱ ወደ እርሱ ሲደርሱም «ከፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ» አላቸው፡፡ ‹ከከፉ ትምህርታቸው ተጠንቀቁ› ለማለት ነበር፡፡ እንጀራ ሳይይዙ ወደ ጌታ የመጡት ደቀመዛሙርት ግን ይህን ንግግሩን ሲሰሙ «እንጀራ ስላልያዝን ነው እንዲህ ያለን» ብለው

ተረጎሙት:: ስለሚበሉት ተጨንቀው ምን እናድርግ እያሉ ቀስ ብለው መነጋገርም ጀመሩ:: ጌታችን ይህን ጊዜ ‹ስለ እምነታቸው መጉደል› እንዲህ አላቸው::

‹‹እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ እንጀራ ስለ ሌላችሁ ስለ ምን እርስ በርሳችሁ ትነጋገራላችሁ? ገና አታስተውሉምን? ለአምስቱ ሺህ አምስቱ እንጀራ፥ ስንት መሶብም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? ወይስ ለአራቱ ሺህ ሰባቱ እንጀራ፥ ስንት ቅርጫትም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንድትጠበቁ ብዬ (እንጂ) ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኋችሁ እንዴት አታስተውሉምን?›› /ማቴ. ፲፮፥፰-፲፩/

ከቤተ ክርስቲያናችን ምሰሶዎች ከቅዱሳን ሐዋርያት ሁሉ በእምነቷ የምትልቀውን ፤ ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ እንኳን ሲያደርገው ስላላየችው የወይን ጠጅ በእምነት የለመነችውንና ስለ ችሎታው ሳትጠራጠር አገልጋዮቹን ጠርታ ‹የሚላችሁን አድርጉ› ያለችውን ይህችን ቅድስት ድንግል በምን እንደበታችን ፤ በምንስ ዓይነት ቃል እናመስግናት ይሆን?

እስቲ በደንብ እናስተውለው! ጌታችን በቃና ዘገሊላ ያደረገው ተአምር በአደባባይ በሰው ሁሉ ፊት ያደረገው የመጀመሪያ ተአምር መሆኑን በቃናው ታሪክ መጨረሻ ላይ እናነባለን:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለዚህ ጉዳይ ሲያብራራ «በልጅነት ዕድሜው በሕዝብ ሁሉ ፊት ተአምራትን አድርጎ ቢሆን ኖሮ ሰው መሆኑ የምትሐት ይመስላቸው ነበር ፤ ከጊዜውም በፊት አስቀድመው በሰቀሉት ነበር»[23] ብሏል::

---

[23] "It was fitting that He should not begin to work wonders from His early years; for men would have deemed the Incarnation to be imaginery and would have crucified Him before the proper time" St. Jhon Chrysostom /Jhon Hom. xxi/



Scanned by CamScanner

እንዲህ ከሆነ ታዲያ እመቤታችን ልጅዋ ውኃን ወይን ማድረግ እንደሚቻለው በምን አወቀች? የሚለውን አባታችን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይመልስልናል። ‹‹ወባሕቱ አእመረት ከመ በጽላሎተ አብ ጸነሰቶ ወበኃይለ ልዑል ወለደቶ ወሰአለቶ በእንተ ወይን» «ነገር ግን በአብ ጥላ እንደጸነሰችው በልዑል ኃይልም እንደወለደችው ታውቃለችና ስለ ወይን ማለደችው» (መጽሐፈ ምሥጢር)

በእርግጥም ያለ ወንድ ዘርዕ በማኅጸንዋ ማደሩ ፣ የድንግልናዋን ማኅተም ሳይፈታ ተጸንሶ ከመወለዱ የሚበልጥ ምን ምልክትና ተአምር ሊፈጸም ይችላል። መጽሐፉም «ጌታ ራሱ ምልክትን ይሠጣችኋል ፤ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች። ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» አይደለም የሚለው? (ኢሳ. ፯፥፲፬) ስለዚህም እመቤታችን ስለ ልጅዋ አምላክነት እና ሁሉን ቻይነት «በልብዋ ትጠብቀው ነበር» የተባለውን ምሥጢር በቃና ዘገሊላ ይፋ አወጣችው። (ሉቃ.፩፥፱) እርስዋ ልጅዋን ታውቀዋለች አሁን ደግሞ ለእኛ እንድናውቀው አደረገችን።

ቅዱሳን ሐዋርያት የፍጹም እምነት ደረጃ ላይ የደረሱት እስከ ጰራቅሊጦስ ድረስ በቀጠለ ረዥም የእምነት ጎዳና ላይ ተጉዘው ነበር። እመቤታችን ግን እነርሱ ገና ጉዞውን ሳይጀምሩ የእምነት ጉዞዋን ጨርሳ በፍጻሜው ስፍራ ደርሳ ቆማ ስትጠብቃቸው ነበር። የዮሐንስ ወንጌል ሐዋርያት ‹የቃና ዘገሊላን ተአምር አይተው በስሙ አመኑ› ይላል። እመቤታችን ግን ከተአምራቱ አስቀድሞ በልጅዋ ሁሉን ቻይነት እምነት ነበራት። እነርሱ ጀማሪ ክርስቲያኖች በነበሩበት ጊዜ እስዋ በእምነት ፍጽምት ነበረች። የመጀመሪያዎቹ የሐዲስ ኪዳን ፓትርያርኮች ፣ የመጀመሪያው ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ቅዱሳን



Scanned by CamScanner

ሐዋርያት የእምነታቸው መሠረት የተጣለው እመቤታችን አምና ባስፈጸመችው ተአምር ላይ መሆኑ ምንኛ ይደንቃል!? «አንቲ ተዐብዪ እምሊቃነ ጳጳሳት» ብሎ መጥቀስ ይህን ጊዜ ነው፡፡ «አንቺ ከሊቃነ ጳጳሳት ትበልጪአለሽ» (ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስቲያን)

## ○ እመቤታችን ራስዋ ውኃውን ወይን ማድረግ አትችልም ነበር?

የእመቤታችንን ልመና የትሕትና ነው የምንልበት ሌላ ወሳኝ ነጥብም አለ፡፡ «እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው» እንደሚል በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብዙ ድንቅ ነገርን በቅዱሳኑ እጅ አድርጓል፡፡ ‹እንደ እኛ የሆኑ ሰዎች ነበሩ› የተባሉት ቅዱሳን እግዚአብሔር በሠጣቸው ሥልጣን ሰው ሊያደርጋቸው የማይቻሉ ታላላቅ ተአምራትን አድርገዋል፡፡ (መዝ. ፷፯፥፴፭ ፤ ያዕ. ፭፥፲፯)

ሙሴ በግብፅ የአባይን ውኃ ከእግዚአብሔር በተሠጠው ሥልጣን ወደ ደምነት ለውጦታል፡፡ (ዘጸ. ፯፥፳) በምድረ በዳም እጅግ መራራ የነበረውን የማራ ውኃ እንጨት ነክሮ አጣፍጦታል፡፡ (ዘጸ.፲፭፥፳፫) ኤልያስ በማሰሮ ውስጥ የነበረን ጥቂት ዘይት አበርክቶ ለመንፈቅ እንዲቆይ አድርጓል፡፡ (፩ነገሥ.፲፯፥፲፮) ደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕም የኢያሪኮን የተመረዘ ውኃ በማሰሮ ጨው ጨምሮ ፈውሶታል፡፡ (፪ነገሥ.፪፥፳፪) ወደ አንዲት ባልቴት ሔዶም ከጎረቤት ሳይቀር

ማሰሮ እንድትዋስ አድርጎ በዘይት ሞልቶላታል። (፪ነገሥ.፬፥፯) የእኛ መምህር ኢትዮጵያዊው ፀሐይ አባ ተክለ ሃይማኖትም ገና አፉን ባልፈታበት የሕጻንነት ዕድሜው እናቱን ወደ ጓዳ እንድትወስደው አመልክቶ በረሃብ ዘመን ቤትዋን ሙሉ አድርጎላታል። (ገድለ ተክለ ሃይማኖት)

እነዚህ ሁሉ ቅዱሳን ውኃን የለወጡት ፣ መራራውን ያጣፈጡት፣ የተመረዘውን የፈወሱት ፣ ማድጋዎችን የሞሉት በእግዚአብሔር ፊት ሞገስና ክብርን ስላገኙ ነው። እኛም ብንሆን ኃጢአታችን ከልክሎን ፣ እምነታችን ጎድሎብን ነው እንጂ ብዙ ድንቅ ነገር ማድረግ እንችላለን። ይህንን ጌታችንም ‹‹የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ሾላ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል ብትሉት፥ ይታዘዝላችሁ ነበር።›› ፤ «በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» ፤ ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል» ብሎ ነግሮናል። (ሉቃ .፲፯፥፮ ፤ ዮሐ. ፲፬፥፲፪ ፤ ማር .፱፥፳፫)

እመቤታችን በደብረ ታቦር ሙሴን ከመቃብር ፣ ኤልያስን ፣ ከብሔረ ሕያዋን እንደ ሎሌ ጠርቶ ያከበራቸው የአምላክ እናት ናት። እነዚህ ሁሉ ቅዱሳን ያላገኙትን ክብር አግኝታለች። ንጉሥ እግዚአብሔር በነቢያቱ በቅዱሳኑ ላይ ያላገኘውን ቅድስናና ውበት ያገኘው በእርስዋ ላይ ነው። ቅድስት የሆነችውም አምላክን ስለወለደች ሳይሆን ፤ አምላክን የወለደችው ቅድስት ስለሆነች ነው። በእግዚአብሔር ፊት ሞገስና ክብርን እንዳገኘችም በቅዱስ ገብርኤል አንደበት ተነግሮናል። የየሰው ‹የጸጋ ሥጦታ ልዩ ልዩ› ቢሆንም እመቤታችን ግን ‹ጸጋን የተሞላች› መሆንዋን በመልአኩ ሰላምታ ተረድተናል። እንዲህ ከሆነ ታዲያ የዚህ ሁሉ ሀብት ባለቤት እመቤታችን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ያለቀውን



Scanned by CamScanner

የወይን ጠጅ ራስዋ ያልሞላችው ነቢያቱ ቅዱሳኑ የቻሉትን ሳትችል ቀርታ ነው ሊባል አይችልም። (ዮሐ. ፫፥፪) ኒቆዲሞስ «እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት ሊያደርግ የሚቻለው የለም።» ብሎ መስክሮ ነበር። /ዮሐ. ፫፥፩/ እመቤታችን ደግሞ «እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው» ተብላ የተመሰገነች ናትና እግዚአብሔር ከእርስዋ ጋር ከሆነ ከእመቤታችን በቀር ጌታ የሚያደርገውን ተአምራት ሊያደርግ የሚቻለው ማን ነው?

የአምላክ እናት መሆንዋን ትተነው ‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል› በሚለው መሥፈርት እንኳን ብናየው እንደ እመቤታችን ያለ እምነት ያለው ሰው የለም። ዘካርያስ ‹ከሚስትህ ትወልዳለህ› ተብሎ ሳያምን ‹ያለ ባል ትወልጂያለሽ› ተብላ ያመነችውን እመቤታችንን በእምነት ማን ይተካከላታል? ፍጡር ሆኖ አምላክን ትወልዳለህ ሲባል አምኖ የሚቀበል ከቶ ማን ነው? የአብርሃም ሚስት ሣራ ራሱ እግዚአብሔር በስተርጅና እንደምትወልድ ሲነግራት በዚያ ዕድሜዋ በልቧ ስቃ ነበር ታናሽዋ ብላቴና እመቤታችን ግን ያለ ወንድ ዘር ስለመውለድዋ ሲነገራት አልሳቀችም ፤ አምና ተቀበለች እንጂ። እመቤታችን እንዲያውም ለቅጽበት ያልተናወጠ ፤ ጥርጥር የሌለበት በመከራ የተፈተነ ጽኑዕ እምነት አላት።

በቤተልሔም ልጅዋን ስትወልደው እያየች ቅድመ ዓለም የነበረ አምላክ መሆኑን አምናለች። በግርግም እያስተኛችው በዓለም ሁሉ የሞላ አምላክ መሆኑን ግን አምናለች። ከንጉሥ ሔሮድስ ሰይፍ ለማዳን ይዛ እንድትሸሽ ሲነገራት እርሱ የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ መሆኑን አልተጠራጠረችም። በኤፍራታ በሕጻንነቱ ሲያለቅስ ስትሰማው ዕንባን

የሚያብስ ፈጣሪ መሆኑን አልተጠራጠረችም፡፡ የመስቀል ስቃዩን ባየች ጊዜ አሸናፊ እግዚአብሔር መሆኑን አልጠራጠረችም፡፡

ተአምር ለማድረግ ‹የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል› እምነት ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ እምነት የተባለው በራስ ችሎታ መተማመን ሳይሆን ‹ለፈጣሪዬ ሁሉን ማድረግ ይቻለዋል› ብሎ ማመን ነው፡፡ የአምላኩን ሁሉን አድራጊነት በሙሉ ልብ ያመነ ሰው በእምነቱ ብቻ የሚሻውን ማድረግ ይችላል፡፡ እመቤታችን ሌላውን እምነቷን ትተነው በቃና ሰርግ ቤት በልጅዋ ችሎታ ላይ የነበራት እምነት ብቻ በራሱ ተአምር ለመሥራት የሚያስችላት ታላቅ እምነት ነበር፡፡ ምክንያቱም ‹ወይንኮ የላቸውም› ‹የሚላችሁን አድርጉ› ብላ ስትገናር በልጅዋና በአምላክዋ አምና ስለነበርና ይህም ከበቂ በላይ ስለሆነ ነው፡፡

ሆኖም በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት እመቤታችን ከልጅዋ በተሠጣት ሥልጣን ተአምራት አላደረገችም፡፡ ምክንያቱም ሥልጣንንና ክብርን የሠጣት የአምላክዋ የልጅዋ ክብር እንዲገለጥ ስለፈለገች ነው፡፡ እርሱ የእናቱ አማላጅነት እንዲገለጥ ዝም እንዳለ እርስዋም የልጅዋ አምላክነት እንዲገለጥ እንደ ቅዱሳኑ ተአምራትን ከማድረግ ይልቅ አማለደች፡፡

የቃናው ሰርግ ቤት የጌታችን አምላክነት የተገለጠበት የመጀመሪያ ተአምር ነው እንጂ ያደረገው ብቸኛ ተአምር አይደለም፡፡ ጌታችን ከዚያ በኋላ አምላክነቱን የሚያስረዱ ሙት ከማስነሣት ፣ ራሱ ከሙታን እስከመነሣት የሚደርሱ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና በቃና ብቻ ተአምር ማድረግ መቻሉን አሳየ አንልም፡፡ ስለዚህ የቃናው ተአምር ብቸኛ ማሳያ የሚሆነው ለእመቤታችን አማላጅነት ነው፡፡

## ፫. አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት

### ○ አንቺ ሴት

ልጅ እናቱን ‹አንቺ ሴት› ብሎ መጥራት በእኛ ሀገር ባሕልና በብዙ ቋንቋዎች ባሕል ፈጽሞ ያልተለመደ ነገር ነው። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ የሚዳኘው በተጻፈበት ቋንቋ (Source language) እንጂ በተተረጎመበት ቋንቋ ባሕል አይደለም። ይህ አነጋገር በአይሁድ ዘንድ እና የዮሐንስ ወንጌል በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ የሚሠጠው ትርጉም በእኛ ዘንድ ካለው ትርጉም የተለየ ነው። በግሪኩ «አንቺ ሴት» (gune = woman") ተብሎ የሚጻፍ ሲሆን ጌታችን እመቤታችንን «አንቺ ሴት» ብሎ በጠራበት ሥፍራ ግን በግሪኩ ‹አንቺ ሴት› የሚለው ንባብ የተጻፈው ‹አንቺ ሴት ሆይ› (gynai "Dear woman") በሚል [24]የአክብሮት አጻጻፍ ነው። ይህ ዓይነቱ አነጋገር ደግሞ ነገሥታት ለንግሥቶቻቸው በሚጽፉአቸው ደብዳቤዎችም ላይ ጭምር ይጻፍ የነበረ እንደሆነ የቋንቋው ባለቤቶች የሆኑት ግሪካውያን አገናዝበው ጽፈዋል። ለምሳሌ አውግስጦስ የተባለው ንጉሥ ለግብፃዊቷ ንግሥት ለክሊዮፓትራ በጻፈው ደብዳቤ ላይ የተጠቀመው ቃል የግሪኩን ‹gynai› /ጋይናይ /አንቺ ሴት ሆይ/ የሚለውን የአክብሮት አጠራር እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።

---

[24] Dr. Panagopoulos : Evangalists against the Gospel (ወንጌልን የሚቃረኑ ወንጌላውያን) /article www.oodegr.com/

ጌታችን በቃና ሰርግ ቤት ‹አንቺ ሴት› ብሎ የተናገረው ንግግር የቁጣ አነጋገር ነው የሚሉ ሰዎችን ሃሳብ እንዳንቀበል የሚያደርገን ሌላው ምክንያት ደግሞ ጌታችን ‹አንቺ ሴት› የሚለውን አጠራር ለእናቱ የተናገረው በቃና ሰርግ ቤት ብቻ አለመሆኑ ነው። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ በመጨረሻው ሰዓት ከመስቀሉ ሥር ቆማ መከራውን እያየች በጽኑ ኀዘን ላይ እያለች «አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ» በማለት ዮሐንስን ለእርስዋ እርስዋን ለዮሐንስ ሠጥቷል።

በልጅና በእናት መካከል ባለው ሥነ ልቡናዊ ትስስር ምክንያት ለእናት የልጅዋን ስቃይ ቆሞ መመልከት እጅግ ከባድ ስቃይን ያስከትልባታል። እመቤታችን እያንዳንዱ ችንካር በተወደደ ልጅዋ እጅ ውስጥ ሲቸነከር ልብዋ በኀዘን ይቸነከር ነበር። ታዲያ ‹አንቺ ሴት› የሚለው አነጋገር የቁጣ አነጋገር ከሆነ ጌታችን በመስቀል ላይ ሆኖ ‹በነፍስዋ የኀዘን ሰይፍ እያለፈባት› ያለችውን እናቱን እንዴት ይቆጣል? በሰርግ ቤት ውስጥስ ስለጠየቀችው ተቆጣ ይባል ፤ በመስቀል ሥር የልጅዋን ስቃይ በዝምታ ስትመለከት የነበረችን እናት ልጅዋ በስቃዩ መካከል ትንፋሹን ሰብስቦ «ተቆጣት» ብሎ ሊነገር እንዴት ይችላል? በስተግራው የተሰቀለው ወንበዴ ‹አንተስ ክርስቶስ አይደለህም› ብሎ ሲሰድበው መልስ ያልሠጠ ‹ከቁጣ የራቀ›[25] አምላክ በእርሱ ስቃይ እየተሰቃየች ያለችውን እናቱን እንዴት ይቆጣል? (ሉቃ. ፳፫፥፴፱) ይህ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ከእናቱ ጋር በተነጋገረበት ስፍራ ‹እናቴ› ብሎ በመጥራት ወይም ‹ማርያም› በማለት

---

25 ‹ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት» (ትርጓሜውን ተመልከት)

ፈንታ ‹አንቺ ሴት› የሚለውን አጠራር መጠቀሙ እመቤታችን በኦሪት ዘፍጥረት በተጠራችበት ስም ለመጥራት እና እርስዋ ትንቢት የተነገረላት ዳግሚት ሔዋን ፣ ጌታችንም የዕባቡን ራስ የሚቀጠቅጠው ዘርዋ መሆኑን የሚያስረዳን ነው።

በሊቃውንት ዘንድ የወንጌል መቅድም (Protevangelium / Protogospel) ወይም ‹የመጀመሪያው የነገረ ሥጋዌ ትንቢት› በመባል የሚታወቀው ‹‹በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።» የሚለው ትንቢት በእርስዋ መፈጸሙን ከምንረዳበት መንገድ አንዱ ጌታችን ‹አንቺ ሴት› ብሎ በመጥራቱ ነው። (ዘፍ. ፫፥፲፩) በዕለተ አርብ በዕባብ የተመሰለው ዲያቢሎስ የጌታችንን ‹ሰኰና› በአይሁድ አድሮ ሲቀጠቅጥ ዋለ። ‹ዘርዋ› የተባለው ጌታም የዕባቡን ራስ እንዲሁ በመስቀሉ ቀጠቀጠው። በዚህ ወቅት እናቱን ደግሞ ‹አንቺ ሴት› ብሎ ጠራትና በትንቢቱ ላይ ያለችው ‹ሴቲቱ› እርስዋ መሆንዋን አስረዳን።

የጻፈውን መተርጎም ልማዱ የሆነው ዮሐንስም ይህንን ጉዳይ የበለጠ ግልጽ በሚያደርግ ሁኔታ የሴቲቱን ፣ የልጅዋን እና የቀደመውን ዕባብ ማንነት በአንድ ምእራፍ ላይ አብራርቶ በራእዩ ጽፎልናል። ‹‹ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። ... ዘንዶውም (እርሱም የቀደመው ዕባብ) በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ›› በማለት የዘፍጥረቱን ትንቢት በመተርጎም ሴቲቱ በእርግጥም ‹አሕዛብን በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ የወለደችው›



Scanned by CamScanner

እመቤታችን መሆንዋን አስረድቶአል፡፡ (መዝ. ፵፬፥፱) ስለዚህ ጌታ ‹አንቺ ሴት› ማለቱ ጾታን ለማመልከት ብቻ ሳይሆን እመቤታችን የትንቢቱ ፍጻሜ መሆንዋን የሚያስረዳ የክብር አነጋገር ነው፡፡ (ራእ. ፲፪፥፩-፲፯)

እንዲሁም ለአዳም ሔዋን በተሠጠችው ጊዜ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና [26]ሴት ትባል።» ማለቱ (ዘፍ. ፪፥፳፫) ሴት የሚለውን ቃል ትርጉም ጾታን ከመግለጽ በላይ ‹ሥጋሽ ከሥጋዬ አጥንትሽም ከአጥንቴ› የሚል የእኔነት ትርጉም ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ልዩነቱ የመጀመሪያው አዳም ከጎኑ ሔዋንን ያስገኘ ሲሆን ሁለተኛው አዳም ግን ከሁለተኛዋ ሔዋን የተገኘ ነው፡፡ ሆኖም ሁለተኛው አዳምም ከጎኑ በፈሰሰው ውኃ የሁላችንን እናት ጥምቀትን (ቤተ ክርስቲያንን) አስገኝቷል፡፡ (በዚህ መጽሐፍ ክፍል ሁለት ላይ በዝርዝር እንመለስበታለን፡፡)

## ○ [27]ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?

«ከአንተ / ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?› የሚለው አነጋገር በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ስድስት ቦታ ፣ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በአምስት ቦታዎች ተጽፎ የምናገኘው አነጋገር ነው፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር በየተጻፈባቸው አገባቦች

---

[26] በአንዳንድ መጻሕፍት ‹አዳም ደግሞ ሚስቱን አወቀ ወንድ ልጅንም ወለደች። ስሙንም፡- ቃየን በገደለው በአቤል ፋንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተከቶልኛል ስትል ሴት አለችው።› (ዘፍ.፬፥፳፭) የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ ሴት የሚለው ቃል ‹ምትክ› የሚል ትርጉም እንደሚሰጥ ተጽፏል፡፡ ሆኖም ‹ሴት› የሚለው የአዳም ልጅ ስም ‹ሴት› ከሚለው ‹የጾታ ስም› ጋር የሚመሳሰለው በአማርኛ ቋንቋ ብቻ በመሆኑ ይህን ትርጉም ብዙ ርቀት ላያስኬድ ይችላል በሚል አላካተትሁትም፡፡
[27] ወንጌሉ በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ይህ ንግግር የተጻፈው ‹tee emee ke see, gynai› ‹ይህ ለእኔና ለአንቺ ምንድር ነው?› /What is it to you and thee/ መሆኑን ግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡



Scanned by CamScanner

(contexts) ሁለት ዓይነት ትርጉም የሚሠጥ ሆኖ ይገኛል። የመጀመሪያው አገባብ አለመግባባትን የሚገልጽ አነጋገር ሲሆን ፤ ሁለተኛው አገባብ ደግሞ አክብሮትን ወይም ሰላም ጠያቂነትን የሚያሳይ አነጋገር ነው።

አለመስማማትን የሚያሳይ የተግሣጽ ንግግር ሆኖ የምናገኘው በነቢዩ ኤልሳዕ ታሪክ ነው። የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮሳፍጥ ጋር ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ መፍትሔ ለመጠየቅ መጥቶ ነበር። ኢዮራም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን አድርጎ ስለነበር ኤልሳዕ ‹‹እኔ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ወደ አባትህና ወደ እናትህ ነቢያት ሂድ›› ብሎ መልሶለት ነበር። ኢዮራም ኤልሳዕን ለማነጋገር ሲሞክርም ኤልሳዕ በቁጣው ጸንቶ «አብሮህ ያለውን የይሁዳን ንጉሥ ባላፍር ኖሮ አንተን ባልተመለከትሁና ባላየሁ ነበር።» ብሎታል። (፪ነገሥ. ፫፥፲፫)

በዚህ ታሪክ ውስጥ በግልጽ ‹ከአንተ ጋር ምን አለኝ?› የሚለው ቃል ‹ከአንተ ጋር ምን ኅብረት አለኝ?› በሚል አገባብ ተቀምጧል። በተመሳሳይም እግዚአብሔር የጢሮስ ፣ የሲዶናና የፍልስጤም ግዛትን በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ ስላደረሱት በደል እንደሚፋረዳቸው በተናገረበት አንቀጽ «ከእናንተ ጋር ለእኔ ምን አለኝ? በውኑ ብድራትን ትመልሱልኛላችሁን? ፈጥኜ ብድራታችሁን በእናንተው ላይ እመልሳለሁ» በማለት ተናግሯል። በዚህም ስፍራ እንዲሁ ይህ አነጋገር ከቁጣ ጋር ተነግሮ ይገኛል። (ኢዮ. ፫፥፬)

ሁለተኛው አገባብ ደግሞ ‹ከአንተ ጋር ምን ጠብ አለኝ?› የሚል ትርጉም የሚሠጠው አገባብ ነው። ንጉሥ ዳዊት ለእርሱ የተቆረቆሩ የጽሩያ ልጆች የሰደበውን ሳሚን ‹እንምታው ፤ እንግደለው› ሲሉ «እናንተ የጽሩያ ልጆች፥ እኔ ከእናንተ



Scanned by CamScanner

ጋር ምን አለኝ? እግዚአብሔር፡- ዳዊትን ሰደበው ብሎ አዝዞታልና ይርገመኝ ለምንስ እንዲህ ታደርጋለህ? የሚለው ማን ነው?» ብሎ ከልክሎአቸዋል። (፪ሳሙ. ፲፮፥፲) ተሳዳቢው ሳሚ መጥቶ ከእግሩ ሥር ተደፍቶ ይቅርታ ሲጠይቅም ዳግመኛ ‹‹እግዚአብሔር የቀባውን ሰድቦአልና ሞት ይገባዋል» አሉ። ይህን ጊዜ ዳዊት ‹እናንተ የጽሩያ ልጆች፥ እኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝ? ዛሬ ስለ ምን ጠላቶች ትሆኑብኛላችሁ? ዛሬስ በእስራኤል ዘንድ ሰው ሊሞት ይገባልን? ዛሬስ በእስራኤል ላይ እንደ ነገሥሁ አላወቅሁምን?» (፪ሳሙ. ፲፱፥፳፪)

በእነዚህ የንጉሡ ንግግሮች ውስጥ ‹ከእናንተ ጋር ምን አለኝ?› የሚለው ቃል በአክብሮት የተነገረ ባይሆንም መልእክቱ ግን ‹ምን ጠብ አለኝ› ማለት መሆኑን ከአገባቡ መረዳት ይቻላል። ምናልባት የመጨረሻው አገባብ ቁጣ ያዘለ ቢመስልም እንኳን እየተናገረ ያለው ለእርሱ ከእርሱ በላይ ለተቆረቆሩት ታማኝ ወታደሮቹ ጋር መሆኑን መርሳት የለብንም። እርሱም ‹ከእናንተ ጋር ምን አለኝ?› ያለውን ‹ለምን ጠላቶች ትሆኑብኛላችሁ?› ብሎ በማብራራት የንግግሩ ፍሬ ሃሳብ ‹ከእናንተ ጋር ምን ጠብ አለኝ› እንደሆነ አሳይቶአል።

ሌላው ማሳያ ደግሞ የግብፅ ንጉሥ ኒካው ንግግር ነው። ኒካው ካልተዋጋሁህ ብሎ ለመጣበት ለኢዮስያስ ፡- ‹‹የይሁዳ ንጉሥ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? በምዋጋበት በሌላ ቤት ላይ ነው እንጂ በአንተ ላይ ዛሬ አልመጣሁም እግዚአብሔርም እንድቸኵል አዝዞኛል ከእኔ ጋር ያለው እግዚአብሔር እንዳያጠፋህ ይህን በእርሱ ላይ ከማድረግ ተመለስ ብሎ መልእክተኞችን ላከበት።›› (፪ዜና ፴፭፥፳፩) ይህ አነጋገር በትሕትና እና ‹ሆይ› በሚል የአክብሮት አጠራር የቀረበ ነው። በግልጽ ‹ልዋጋ የተነሣሁት ከሌላ ጋር ነው ፤ ከአንተ ጋር ምን ጠብ አለኝና ነው የምዋጋው!› ነው ያለው።



Scanned by CamScanner

በእውነቱ ‹ከአንተ ጋር ምን አለኝ?› ማለት ‹ከአንተ ጋር ምን ጠብ አለኝ?› ማለት መሆኑን ለማስረዳት ከዚህም የተሻለና ግልጽ ታሪክ የለም፡፡ ምክንያቱም ኢዮስያስ የተነሣው ለጠብ ነው፡፡ ኒካዑም በአክብሮት የነገረው ‹ከአንተ ጋር ምን ጠብ አለኝ?› ብሎ ነው፡፡

እንደተጨማሪ ማሳያ የምናገኘው ደግሞ የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስን በቤትዋ የተቀበለችው የሰራፕታዋ መበለት የተናገረችው ነው፡፡ ይህች ሴት ኤልያስ በቤትዋ በመገኘቱ በቤትዋ ያለው ምግብ ተባርኮ በረሃብ ዘመን እየተመገቡ ከከረሙ በኋላ ልጅዋ በጠና ታመመ፡፡[28] ይህን ጊዜ ሴቲቱ ወደ ኤልያስ ቀርባ ፡- ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ፥ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን? አለችው፡፡›› (፩ነገሥ.፲፯፥፲፰)

ይህች ሴት ለነቢዩ በአክብሮት ያለችው ‹ከአንተ ጋር ምን ጠብ አለኝ?› ነው፡፡ የቁጣና የተግሣፅ ንግግር ነው እንዳይባል መቼም «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ...» ብሎ የሚጀምር ቁጣ የለም፡፡ እንዲያውም በአንድ ሰው ስንቆጣ ማዕረጉን ትተን እንናገራለን እንጂ ማዕረግ ጠብቆ ቁጣ የለም፡፡

ወደ ሐዲስ ኪዳን ስንመጣ ‹ከአንተ ጋር ምን አለኝ?› የሚለውን ቃል የተናገሩት ዛሬ በወዳጆቻቸው አድረው ‹ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ማለት ስድብ ነው› እያሉ የሚበጠብጡን አጋንንት ናቸው፡፡ ከአዋቂ ጋር እንደ አዋቂ ፤ ካላዋቂ ጋር እንደ አላዋቂ ሆኖ ማደናቆር የአጋንንት ልማድ ነውና እነሱ በሚገባ ትርጉሙን ተረድተው እየተንቀጠቀጡ ለጌታ የተናገሩትን የአክብሮት አነጋገር ለእመቤታችን ሲሆን ትርጉሙ ሌላ ነው እያሉ ያውካሉ፡፡

---

[28] ይህ ልጅ ነቢዩ ዮናስ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

«አነሆም። ኢየሱስ ሆይ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን? እያሉ ጮኹ።» (ማቴ. ፰፥፳፱)

«እርሱም፡- የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ።» (ማር. ፩፥፳፬)

«የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ አለ፤» (ማር. ፭፥፯)

« ተው፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄሃለሁ፥ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱሱ አለ።» (ሉቃ. ፬፥፴፬)

«ኢየሱስንም ባየ ጊዜ ጮኾ በፊቱ ተደፋ በታላቅ ድምፅም። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳትሣቀየኝ እለምንሃለሁ አለ» (ሉቃ. ፰፥፳፰)

ምንም እንኳን አጋንንትን እንደ ማስረጃ በመጥቀስ ክብር ባንሠጣቸውም ‹የጠላት ምስክርነት የታመነ ነው› እንዲል (ትምህርተ ኅቡዓት/ትር.) የአጋንንቱ ንግግር ‹ከአንተ ጋር ምን አለኝ› የሚለው ቃል በአክብሮት ሊነገር የሚችል ‹ምን ጠብ አለኝ› የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑን በግልጽ ያስረዳል። ምክንያቱም ‹ከአንተ ጋር ምን አለን› ከማለታቸው ጋር ‹ኢየሱስ ሆይ ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ ፣ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ ፣ የእግዚአብሔር ቅዱሱ› የሚል የአክብሮት ንግግር ተናግረዋል። ከዚያም ‹እንዳታሠቃየኝ እለምንሃለሁ› የሚል ልመና ተከተለ። ልመናውም ከእግሩ ሥር እስከ መደፋት ድረስ የደረሰ ነበር። መቼም ከእግር ሥር ተደፍቶ የቁጣ ንግግር መናገር የማይታሰብ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ባየነው የአገባብ ዝርዝር ‹ከአንተ ጋር ምን አለኝ?› ለሚለው ንግግር የሚያመዝነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም ‹ከአንተ ጋር ምን ጠብ አለኝ› የሚል ነው። በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ጌታችን ለእናቱ የተናገረው

‹ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?› የሚለው አነጋገርም ከአገባቡ እንደምንረዳው ሌሎች ስለ እርሱ በፍርሃት የተናገሩትን የአክብሮት የተነገረ ሲሆን ትርጉሙም ‹የጠየቅሽኝን እንዳላደርግልሽ የሚከለክለኝ ከአንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ?› የሚል ነው:: ይህን የሚያስረዳን መልሱ የእምቢታ ቢሆን ኖሮ አንደኛ እመቤታችን ልመናዋን ቀጥላ ‹አባክህን ልጄ ሆይ› ብላ ለማሳመን ትሞክር ይሆናል እንጂ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› ብላ ለአገልጋዮቹ በልበ ሙሉነትና በእርግጠኝነት ትእዛዝ ልትሠጥ አትችልም ነበር::

ሁለተኛ ደግሞ ጌታችን ከዚያ በኋላ ጋኖቹን ሙሉ ብሎ ተአምራቱን አያደርግም ነበር:: እንዲያውም ጌታችን ‹ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ያላት በቁጣና በእንቢታ ከሆነ ለአገልጋዮቹ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› ብላ መናገርዋ የበለጠ ቁጣውን የሚያነድ ነበር የሚሆነው:: ለእርስዋ እንቢ እያላት ቁጣውን ከምንም ሳትቆጥር ሌሎች ሰዎችን ማዘዝዋ የበለጠ አያስቆጣም ወይ ሊባል ይችላል? ይህ ሁሉ የሚያሳየን ጌታችን አንዳች የቁጣ ንግግር አለመናገሩን ነው::

አባ ጊዮርጊስም የጌታችን መልስ የጠብ ሳይሆን እንዲያውም የጥልቅ ፍቅር መሆኑን ሲገልጽ «በልቡ ውስጥ ለተከማቸ ፍቅሯ በሚሻል /በሚመጥን/ ነገር መለሰላት» «ወአውስአ ዘከመ ይኄይስ ለዘዝጉብ ፍቅረ ዚአሃ ውስተ ልቡ» ብሏል:: (መጽሐፈ ምሥጢር) ስለዚህ ‹ከአንቺ ጋር ምን አለኝ› የሚለውን ንግግር የቁጣ ንግግር አድርጎ መተርጎም ጥቅሱን ከአገባቡ የወጣ ጥቅስ (Text out of context) ያደርገዋል::



Scanned by CamScanner

○ ጌታችን እናቱን ተቆጥቷት ይሆንን?

የቃና ሰርግ ቤት ታሪክ ለጊዜው እናቶየውና አንድ ልጅ በአደባባይ በሰዎች ፊት እናቱን በምንም ምክንያት ቢቆጣ እንኳን ከሃይማኖት አንጻር ከሥነ ምግባርም አንጻር የሚደገፍ ሥራ አይደለም፡፡ ክብር ይግባውና ጌታችን ‹እናቱን በቁጣ ተናገራት› የሚለው አስተሳሰብም እንዲሁ ብዙ የሚያመጣው ጣጣ አለ፡፡ «እናትና አባትህን አክብር» «እናቱን የሰደበ ይሙት» የሚለውን ሕግ የሠራ አምላክ ‹እኔን ምሰሉ› እያለ ለሰው ልጆች አርኣያ ሊሆን በመጣበት በዚህ ዓለም ራሱ እናቱን በአደባባይ በሰው ፊት ያቃልላታል ብሎ ማሰብ እጅግ ከባድና ለብዙ ሰዎች የኃጢአትን በር ወለል አድርጎ ከፍቶ መረን የሚለቅ ነው፡፡ (ዘጸ. ፳፥፲፪ ፣ ፳፩፥ )

እመቤታችንን የጎዱ መስሏቸው ‹ጌታ እናቱን ተቆጣ› ብለው የሚሰብኩ ሰዎችም ሳያውቁት እየተናገሩ ያሉት በእመቤታችን ላይ ሳይሆን በራሱ በጌታችን ላይ ነው፡፡ ጌታችን ‹‹ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?›› ብሎ የተናገረ ንጹሐ ባሕርይ ነው፡፡ (ዮሐ. ፰፥፵፮) ‹የሚጤስን የጧፍ ክር የማያጠፋ ፣ የተቀጠቀጠ ሸንበቆን የማይሰብር› በአነጋገሩ ጭምት ነው፡፡ ስንክሳሩም «ወንድሜ ምእመን ሆይ ጌታችን ለንጽሕት እናቱ ለድንግል ማርያም ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም በማለቱ የክብርት እናቱን ቃል እንዳቃለለ አታስብ» ይላል፡፡ (ስንክ. ጥር ፲፪ ቁ. ፵)

በማስከተልም «ጌታችን የሰማያዊውና የመለኮታዊ አባቱን ክብር እንደጠበቀ ይታወቅ ዘንድ እንዲሁ ከእርስዋ ፍጹም ሥጋንና ፍጽምት ነፍስን ነሥቶ ከመለኮቱ ጋር

ያዋሐደውን የእናቱን ክብር ጠበቀ፡፡ በወንጌል ይታዘዛትና ይላላካት ነበር ተብሎ እንደተጻፈ»[29] ይላል፡፡ (ስንክ.ጥር ፲፪ ቁ. ፵፪)

በእርግጥም ጌታችን የባሕርይ አባቱን አብን ክብር እንደጠበቀ በራሱ አንደበት «አባቴን አከብራለሁ»[30] ሲል ተናግሯል፡፡ (ዮሐ. ፰፥፵፱) ለእመቤታችንና ለአሳዳጊው ዮሴፍም እንዲሁ ‹‹ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፥ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር።›› ተብሎ ተጽፎአል፡፡ (ሉቃ. ፪፥፶፩) እመቤታችን በቃና ዘገሊላ ስለ ወይኑ የነገረችውም የልጅዋን መታዘዝ በልብዋ ትጠብቀው ስለነበር እና እንደሚታዘዛት ታስብ ስለነበር ነው፡፡

እስቲ ነገሩን ሌሎች ከሚያዩበት ማዕዘን ለመመልከት እንሞክር፡፡ እውነት ግን ጌታችን እናቱን ሊቆጣ የሚችልበት ምን ምክንያት ነበረው? ከላይ እንደተመለከትነው የለመነችው ስለ ራስዋ ጥቅም አይደለም፡፡ በዚያ ላይ ልመናዋ ከሚያስፈልግ ነገር ውጪ ይደረግ የተባለ አላስፈላጊ የቅንጦት ልመና አይደለም፡፡ በሰርግ ቤት ሙሽሮችን ለዕድሜ ልክ ውርደት ሊዳርግ የሚችል የወይን ጠጅ እጥረት በተከሰተበት ሰዓት ‹ወይን እኮ የላቸውም› ብሎ

29 «ወበከመ ዓቀበ እግዚእነ ክብረ አቡሁ ሰማያዊ ወመለኮታዊ ይትዐወቅ ከማሁ ዐቀበ ክብረ ወላዲቱ ዘበሥጋ እንተ እምኔሃ ነሥአ ሥጋ ፍጹመ ወነፍሰ ፍጽምተ ወረሰየ ምስለ መለኮቱ አሐደ በከመ ጽሑፍ ውስተ ወንጌል ከመ ይትኤዘዝ ላቲ ለእሙ ወይትለአካ»

30 ‹አብን አከብራለሁ› የሚለውን ቃል ክብር ይግባውና ወልድ ከአብ ያንሳል ለማለት የሚጠቅሱት አሉ፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር አብም በተመሳሳይ ጌታችን ‹አባት ሆይ ስምህን አክብረው› ብሎ በተናገረ ጊዜ ‹አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ› ሲል ከደብረ ታቦር በኋላ ከደመና ድምፅ አሰምቶ ተናግሯል፡፡ (ዮሐ. ፲፥፳፰) በአንጻሩ ለእናቱ መታዘዙን አይተው ‹ምንን አምላክ ነው ለሰው እየታዘዘ አይደል?› ለሚሉ ደግሞ ‹በአምላክነቱ ተአዝዞ አገብሮ› እንደሌለበት ለማሳየት ጊዜዬ አልደረሰም› አለ፡፡

ማመልከት እንኳን በሩኅሩኅ አምላክ ፊት ይቅርና በእኛ በጨካኞቹ የሰው ልጆች ፊት እንኳን ሊያስቆጣ የሚችል ነገር አይደለም።

የለመነችው እንደ አይሁድ ምልክት ለማየት ጓጉታ አይደለም። እንደ ፈሪሳዊያንና ሰዱቃውያን ‹አይተን እንድናምንህ ምን ምልክት ትሠራለህ?› ‹ከሰማይ ምልክት ልናይ እንወዳለን› የሚል የፈተና ጥያቄ አልጠየቀችም። (ማቴ. ፲፮፥፩ ፤ዮሐ. ፮፥፴) ተአምር የማየት ምኞት አድሮበት እንደጠየቀው እንደ ሄሮድስም በአጋጣሚው ልጠቀምና ተአምር ልይ ብላም አይደለም። (ሉቃ. ፳፫፥፰) ደግሞስ ያለ ወንድ ዘር በማኅጸንዋ አድሮ በታተመ ድንግልና ሲወለድ ያየች እናት ሌላ ምን ተአምር ሊያስደንቃት ይችላል?

የሰርጋቸው ቀን የኀዘናቸው ቀን ሊሆን ስለተቃረበ ሙሽሮች ተጨንቃ መለመንዋ እንዴት የሚያስቆጣ ሊሆን ይችላል? ያለጊዜው ስለለመነችውና ስለቸኮለች ተቆጣት እንዳንል ልመናዋን ትንሽ ብታዘገየው ኖሮ ነገሩ ይፋ እየሆነ ፣ ሙሽሮቹ መዋረዳቸው ነው። ስለዚህ የደረሰችው በሰዓቱ ነው።

የጌታችን አሠራር እንዲህ አልነበረም። የቅዱስ ጴጥሮስ አማት በንዳድ በታመመች ጊዜ እንዲፈውሳት ሲለምኑት እሺ ብሎ ንዳዱን ገሥፆ አሳቀቃት። (ሉቃ.፬፥፴፱) የአንድ መቶ አለቃ ልጅ በታመመ ጊዜ የአይሁድ ሽማግሌዎች ሊያማልዱ በመቶ አለቃው ተልከው መጡ። ጌታችን ከይሁዳ ነገድ መሆኑን በማሰብም ‹‹ይህን ልታደርግለት ይገባዋል፤ ሕዝባችንን ይወዳልና ምኩራብም ራሱ ሠርቶልናል ብለው አጽንተው ለመኑት። ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሄደ።›› የመቶ አለቃውንም ልጅ በመጨረሻ ፈወሰው። (ሉቃ. ፯፥፪-፲) እነዚህ ሰዎች ተአምር እንዲያደርግ ሲጠይቁት እሺ ያለ ጌታ እናቱ ስትለምነው ይቆጣል ብለን



Scanned by CamScanner

እንዴት እንቀበል? የአይሁድን ሽማግሌዎች እንኳን ያልተቆጣውን ጌታ በምን አንደበታችን እናቱን ተቆጣ ልንለው ይቻለናል?

ከሁሉ በላይ ቅዱስ ዳዊት «ጸሎቴን ያልከለከለኝ ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ እግዚአብሔር ይመስገን» እንዳለው በረከሰ አንደበታችን ፣ በሚወላውል ልባችን ፣ በሚባክን ሃሳባችን ወደ እርሱ የምንጸልየውን የእኛን የኃጢአተኞቹን ጸሎት ለምን ጸለያችሁ ብሎ ያልከለከለ አምላክ ንጽሕት እናቱ በፍጹም ትሕትና ለለመነችው ልመና የቁጣ ምላሽ ሠጠ ማለት እንዴት እንደፍራለን? ዳዊት ‹‹በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰማኝ የልመናዬን ድምፅ አደመጠ›› ብሏል፡፡ እርሱ በልቡ በደል ስለሌለ ጌታ ከሰማው በሃሳብዋ ድንግል የሆነች እናቱን እንዴት አልሰማትም እንላለን? (መዝ. ፷፮፥፲፱-፳)

እመቤታችን የጠየቀችው ይህን ያህል የማይጠየቅ ነገር ነው እንዴ? የመንግሥትህን እኩሌታ ፣ የሥልጣንህን ፈንታ ሥጠኝ አላለችውም፡፡ የጠየቀችው ስለ ድሆቹ ሙሽሮች ነው፡፡ እኛ በረባ ባልረባው ስንዘበዝበው የምንውለውና የምናድረው ታጋሽ አምላክ ለእናቱ ለእኛ የሠጠውን ነገር ይነሣል ማለት ፈጽሞ አይታሰብም፡፡ ‹አብን አሳየንና ይበቃናል› ፤ ‹እሳት ከሰማይ ወርዶ ሕዝቡን ያጥፋቸው› ፤ ‹በግራ ቀኝህ አስቀምጠን› የሚሉ ደቀ መዛሙርትን ታግሶ ለሦስት ዓመት ከሦስት ወራት ያስከተለ ጌታ ቅድስት እናቱ ተገቢ ልመና በተገቢ ሰዓት ስትለምነው ሊቆጣ አይችልም፡፡

እንደ ወንጌሉ ብቻ ከሔድን ደግሞ እመቤታችን ከዚህ በፊትና በኋላ ምንም ነገር ስትለምነው አልተጻፈም፡፡ በወንጌል ለተጻፈው ለዚህ ብቸኛ ልመናዋም መልሱ ቁጣ ነው ብለን አምነን መቀመጥ ለእኛ ለኦርቶዶክሳውያን

ፈጽሞ የሚዋጥልን ሃሳብ አይደለም፡፡ በልጅነትዋ ወልዳው ለተሰደደችው ፣ በነፍስዋ የኀዘን ሰይፍ ሳለፈባት እናቱ አንዴ ብትለምነው ተቆጣ ብለን እንዴት እንናገራለን?

ጌታችን በዚህ ሰርግ ቤት እንኳንስ እንዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የሚተረጉመው ‹ከአንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ› የሚል የአክብሮት ንግግር ተናግሮ ቀርቶ ፤ ለእናቱ የተናገረው በቀጥታና በግልፅ የቁጣ ንግግር ቢሆን ኖሮ እንኳን ጾመን ጸልየን ፣ ወድቀን ተነሥተን ምሥጢራዊ ትርጉሙን እንፈልጋለን እንጂ ሰማይና ምድር ቢነዋወጥ ‹ጌታ እናቱን ተቆጣ› ብለን አናምንም!!!

## ○ ጊዜዬ ገና አልደረሰም

ቅዱስ ዳዊት አንድን ወቅት ለይቶ «ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ነው /አለው/» (‹ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር›) በማለት እንደተናገረ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በጊዜው ይፈጽማል፡፡ (መዝ. ፻፲፰፥፻፳፮) ጠቢቡ ሰሎሞንም ‹ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው› በማለት እግዚአብሔር በጊዜው ሁሉን የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳናል፡፡ አንዳንድ ጸሐፍትም ኦሪት ዘፍጥረት ገና ሲጀምር ‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ› ብሎ መሆኑ ‹መጀመሪያ› የሚለው ቃል እግዚአብሔር አስቀድሞ ጊዜን መፍጠሩን የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡[31]

[31] እግዚአብሔር የጊዜ ፈጣሪ እንጂ የጊዜ ተገዥ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከዘመናት በፊት የነበረ ዘመናትንም አሳልፎ የሚኖር በመሆኑ እግዚአብሔር ከጊዜ መለኪያ ውጪ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

እግዚአብሔር ለጸሎት የሚሠጠው ምላሽ ሦስት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው ይሁን ብሎ የሚያደርገው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አይሆንም ብሎ የሚከለክለው ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ‹ጊዜዬ እስኪደርስ ታገሡ› የሚለው መልስ ነው፡፡ ለሦስተኛው ምላሽ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን ለአዳም የተሠጠው የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት ቀጠሮ ነው፡፡ ብዙ ነቢያት ‹ውረድ ተወለድ› ሲሉ ኖረዋል ፤ እግዚአብሔር ያለ ጊዜው የፈጸመው ነገር አልነበረም፡፡ «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» (ገላ. ፬፥፬)

ከተወለደም በኋላ ሁሉን ነገር ያከናወነው ለሕግ ጠባያዊ /ለተፈጥሮ ሕግ/ በመገዛት ቀስ በቀስ አድጎ ነው፡፡ ጌታችን በተጸነሰበት ዕለት ተወልዶ አድጎ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ዓለምን ማዳን ይቻለው ነበር፡፡ ሆኖም ሁሉን በጊዜው አደረገው፡፡ «ሁሉንም ሥራ ተገቢ በሚሆንበት ወቅት ሠራ እንጂ ሁሉንም በአንዴ አልሠራም፡፡ ምክንያቱም ይህን ቢያደርግ አንዳች ግራ መጋባት እና መቃወስ ይከሰት ነበር፡፡ እስከዚህም ሰዓት ድረስ ለብዙዎች ሌላው ቀርቶ ለሁሉም ደቀመዛሙርቱ እንኳን አልተገለጠም ነበር፡፡»[32] (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

ጌታችን በዚህ ሰርግ ቤት ውስጥ ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ያለበት ሰፊ ምሥጢራዊ ትርጓሜ ቢኖረውም ከሰርግ ቤቱ ታሪክ አንጻር ግን ለጊዜው ደግሞ ምክንያቶች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት በሰርግ ቤቱ ያለቀው ወይን ጠጅ ከማድጋው ፈጽሞ ተንጠፍጥፎ አለመድረቁ ነበር፡፡ እስኪያልቅ

---

[32] "He works all things at their due season, not doing everything at once, because a kind of confusion and disorder would have ensued, as yet He was not manifest to the many, not had even his whole choir of disciples" /St. Jhon Chrysostom/

መጠበቁ ሰዎች ያደረገውን ተአምር እንዳያቃልሉ እና «የነበረውን አንጥፍጣፊ ወይን አበረከተ እንጂ አዲስ የወይን ጠጅ መቼ ሠጠ» እንዳይሉ መንገድ ሲዘጋ ነበር፡፡ ሰዎች ጥቂት ነገር አለን ብለው ሲያስቡ የእግዚአብሔርን ሥራ ይዘነጋሉ፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ፡- «ፈጣሪዬ ይኼን ፈተና ብቻ ከጉድ አውጣኝ በደንብ አላጠናሁም» ብሎ ተስሎ ፈተና ተፈትኖ ጥሩ ውጤት ሲያመጣ ፈጣሪን ሳለማመስገን ‹‹ፈተናውም ቀላል ነበር ፣ እኔም እኮ ብሆን ጥሩ መሠረት (base) አለኝ›› ብሎ የሚያወራርድ ተማሪ ነው፡፡

## ፩. እናቱም ለአገልጋዮቹ ፡- የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው

- **ትእዛዘ ማርያም** /The Command of Mary/

«የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» የሚለው ዐረፍተ ነገር ትእዛዘ ማርያም ነው፡፡ ትሑትዋና ዝምተኛዋ እናታችን በቀጥታ «እንዲህ አድርጉ» ብላ በማዘዝ ስትናገር ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያዋም የመጨረሻዋም ነበር፡፡ ይሁንና በአንድ ዐረፍተ ነገር ዐሥርቱ ትእዛዛትን እና ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ጠቅልላ «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ብላናለች፡፡

«ሰው ከመናገር የዘገየ ይሁን» እንደተባለ ለንግግር የማትፈጥነው እመቤታችን የተናገረችው ጥቂት ቃል ከሁሉም ስብከት የበለጠ ነው፡፡ (ያዕ. ፩፥ ፲፱ ) «በማብዛት አይደለም በማሳነስ ነው እንጂ» የሚለው የቅዳሴዋ ንባብ አስቀድሞ በእርስዋም ሕይወት የተተረጎመ ነበር፡፡ እርስዋ ምንም የምሥጢር መዝገብ



Scanned by CamScanner

ብትሆንም በአደባባይ ጉባኤ ዘርግታ አላስተማረችም ፤ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ዐሥራ አራት መልእክታትን ፣ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አምስት መጻሕፍትን አልጻፈችም። ሆኖም የሁሉንም መልእክትና ስብከት በሦስት ቃላት ደመደመችው። «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ!!»

የሔዋን መመኪያ የሆነችው እመቤታችን በዚህ ንግግርዋ በሐዲስ ኪዳን ወለል ብሎ ለተከፈተውና ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ አከታትሎ ለመዘገበው ለሴቶች የመንፈሳዊ አገልጋይነት በር የመጀመሪያዪቱ ደጅ ከፋች ሆናለች። ሳምራዊቷ ሴት ብርስፌንያ /St. Photini/ ለሰማርያ ሰዎች ሔዳ ስለ ክርስቶስ መመስከሯንና እንዲያምኑ መንገድ መጥረጓን (ዮሐ. ፬፥፩) ፤ የቢታንያዋ ማርታ ወንድሟ አልዓዛር በሞተ ጊዜ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ› ብላ መመስከሯን (ዮሐ. ፲፩፥፳፯) ፤ ባለ ሽቱዋ ማርያም በራሱ ላይ ሽቱ አፍስሳ ታላቅ ንስሐን ማሳየቷን (ዮሐ. ፲፪፥፫)፤ መግደላዊት ማርያም ‹ጌታዬን አየሁት ፤ ዐርጋለሁ ብሏል› ብላ ሐዋርያት ለሐዋሪታቸው /apostle of the apostles/ መሆኗን መዝግቦልናል። (ዮሐ. ፳፥፲፰) ቅዱስ ዮሐንስ እነዚህን ሁሉ የጻፈው ግን እመቤታችን በቃና ሰርግ ቤት የነበራትን ሚና ካስቀደመ በኋላ ነበር።

የሚያስደንቀው ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› የሚለው የእመቤታችን ንግግር በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፉት ንግግሮችዋ ለመጨረሻ ጊዜ የተናገረችው ዐረፍተ ነገር መሆኑ ነው። ይህ ቃልዋ ጌታችን በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚለንንና የሚያዝዘንን ሁሉ እንድናደርግ የሚያሳስብ ነው። በእውነት ይህንን የእመቤታችንን ትእዛዝ ለመፈጸም ያብቃን!!



Scanned by CamScanner

○ ጌታችን ለእናቱ ‹አገልጋዮቹን እዘዢልኝ› አሳሳትም

‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› በሚለው ንግግር ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ሁለት ነጥቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ትኩረት የሚስብ ነጥብ እመቤታችን ከላይ በዝርዝር እንዳየነው ‹ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ብሎ የመለሰላት መልስ ‹እሺ› ማለት መሆኑን ነው፡፡ በእሱ እሺ ማለት እርግጠኛ ባትሆን ኖሮ ለአገልጋዮቹ በሙሉ ልብ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› ለማለት ድፍረቱ ሊኖራት አይችልም ነበር፡፡ እንቢ እንዳላት ብታስብ ኖሮ ለአገልጋዮቹ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› በማለት ፈንታ ሌላ አማራጭ ፈልጉ ባለቻቸው ነበር፡፡

ሁለተኛው ትኩረት የሚስብ ነጥብ ደግሞ ቀጥሎ የሚሠራው ሥራ የአገልጋዮቹን ተሳትፎ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ማወቋ ነው፡፡ ጌታችን «ጋኖቹን ውኃ አስሞዪልኝ» አላላትም ፤ በሠጣት መልስም ውስጥ አገልጋዮቹን እንድታዝዝለት የሚያሳስብ ምንም ነገር አልተናገረም፡፡ ዓሣና እንጀራ ባበረከተበት ተአምር ወቅት አስቀድሞ ለሐዋርያቱ ‹ሰዎቹ እንዲቀመጡ አድርጉ› ብሎ ሐዋርያት ሳይለምኑት በራሱ ለሚፈጽመው ተአምር መንገድ እንዲጠርጉለት አዝዞአቸው ነበር፡፡(ዮሐ.፮፥፲) ለእመቤታችን ግን እርሱ

ሳይነግራት የሚሠራው ተአምር የአገልጋዮችን ተሳትፎ እንደሚጨምር ጭምር በተሠጣት ጸጋ አውቃ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› አለች፡፡

ልጅዋ በአንደበቱ ቀጥሎ ለሚሠራው የአገልጋዮቹን ታዛዥነት እንደሚፈልግ ባይነግራትም እናትና ልጅ ያለ ንግግር የተግባቡበት አንዳች መንፈሳዊ መገናኛ ግን ነበረ፡፡ ስንክሳሩም «ወእግዝእትነሰ እእሚራ ዘይገብር በጊዜሁ ትቤሎሙ ለእለ ይትለአኩ ግበሩ ዘይቤለክሙ» «እመቤታችንስ በጊዜው የሚሠራውን አውቃ ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን አድርጉ አለቻቸው» ይላል፡፡ (ስንክሳር ጥር ፲፪ ቁ. ፷፰)

ተአምራት እንዲፈጽም የለመነችውና ልጅዋን ይሁን ያሰኘችው ድንግል ማርያም በሰርግ ቤቱ የነበራት ሚና በዚህ ላይ አላበቃም፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ «አገልጋዮቹንም (ለእርሱ) እንዲታዘዙ ዝግጁ በማድረግ ለተአምሩ መንገድ ጠረገችለት»[33] ብሏል፡፡ ይህን ማድረጓም እመቤታችንን ለቃናው ተአምር አማላጅ ብቻ ሳትሆን ጸያሒተ ፍኖት (መንገድ ጠራጊ) ያደርጋታል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የድርሻውን ካስተማረና ለክርስቶስ መንገድን ከጠረገ በኋላ ‹እርሱ ሊልቅ እኔ ላንስ ይገባኛል› ብሎ ለጌታው ሥፍራ እንደለቀቀ ፤ እመቤታችንም በምልጃዋ መንገድ ጠርጋ አገልጋዮቹን ወደ እርሱ አቅርባ ለልጅዋ ሥፍራውን ለቀቀች፡፡

እንዲሁም እመቤታችን በዚህ አነጋገርዋ ጸሎትን እንዴት በእምነት ማቅረብ እንደሚገባ አስተማረችን፡፡ ልጅዋን ከለመነች በኋላ እንደሚያደርግላት ቅንጣት እንኳ ጥርጥር አልነበራትም፡፡ የሚያደርገውን በመጠባበቅ ፈንታ ሌሎችን ዝግጁ ለማድረግ ተፋጠነች፡፡ በእውነቱ ይህ ዓይነቱ እምነት ወደ እኛ

---

33 /St. Cyril of Alexandria ፤ commentary on Jhon 2:5/ pg 93/

ዘመን ስናመጣው የማይታሰብ እየሆነ ነው። እኛ አንድ ነገር ወደ እግዚአብሔር ከለመንን በኋላ ያደርግልናል ብለን ስለማናምን ሌሎች አማራጮችን በአእምሮአችን ማመላለሳችን የማይቀር ነው። እመቤታችን ግን ለልጅዋ ከነገረች በኋላ እንደሚያደርገው አምና ያለምንም ማመንታት ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› አለቻቸው።

## ○ የቅዱሳን ምልጃ የእኛን እርዳታም ይፈልጋል

‹ቅዱሳን ስለ እኛ ያማልዳሉ› ማለት ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው እኛ ‹ከበጎ ምግባር ከመሥራት እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ ይገባናል› ማለት አይደለም። የቅዱሳን አማላጅነት የሚያስፈልገው እኛ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ተከልክለን ቅዱሳኑ ብቻ በእኛ ፈንታ እንዲጸልዩ የሚል የመንፈሳዊ ሥራ ፈትነት መንሥኤ አይደለም። ይልቁንም የቅዱሳኑ አማላጅነት እኛ በመንፈሳዊ ሕይወት ከቅዱሳኑ ጋር እንድንበረታ የሚያደርገን ሲሆን ምልጃ ያስፈለገበትም[34]በቂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ስላለ ነው።

---

[34] ‹እኛ መጸለይ ከቻልን የቅዱሳን አማላጅነት ያስፈለገው ለምንድን ነው?› ፤ ፩. እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች ጸሎት የበለጠ የጻድቃንን ጸሎት ስለሚሰማና ምልጃን መፈለግ ኃጢአተኛ ነኝ ብሎ ማመን ስለሆነ ነው (፩ጴጥ. ፫፥፲፪ ፤ ምሳ. ፲፭፥፳፱ ፤ ዮሐ.፱፥፴፫ ፤ ፩ዮሐ. ፩፥፰) ፪.እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ወደ ጻድቃን ሔደው ምልጃ እንዲጠይቁ ሲልክ ስላየን ነው (ዘፍ.፳፥፯ ፤ ኢዮ.፵፪፥፰) ፤ ፫. ከመቅጣቱ በፊት ጻድቃን እንዲያማልዱ ዕድል ሲሠጥ ስላየን ነው (አሞ. ፫፥፯፤ዘጸ. ፴፪፥፱ ፤ ዘዳ. ፱፥፲፰) ፬. ሕዝቡን ሊያጠፋ ከወሰነ ደግሞ አስቀድሞ ጻድቃንን ምልጃ ያስቆማል በከንቱ ይጮኹ ብሎ አይተዋቸውም። ምልጃን ቢተዉም እንደ በደል አድርጎ ይቆጥርባቸዋል። (፩ሳሙ.፲፪፥፩፤ኤር.፯፥፲፯) ፭. ጻድቃን ባያማልዱም እንኳን የሚኖሩበትን ሀገር በእነሱ መኖር ምክንያት ይምራል። /ኢሳ. ፳፭፥፰ ፤ ሕዝ. ፳፪፥፴፩/ ቢያንስ እስከ ፲ ጻድቃን ድረስ ካሉ ሀገር ያስምራሉ። (ዘፍ. ፲፰፥፳-፴፪) ስምንት ወይም ሦስት ቢሆኑ ራሳቸውን ያስምራሉ

ቅዱሳን ፍቅርና ርኅራኄን የተሞሉ በመሆናቸው ስለ እኛ ያማልዳሉ፡፡ ይህ አማላጅነታቸው ውጤት እንዲያመጣ በእኛ ዘንድ ጥቂትም ቢሆን አስተዋጽኦን ማድረግ ይገባናል፡፡ በእኛ ጥቂት መልካም ሥራ ላይ የቅዱሳኑ አማላጅነትና የእግዚአብሔር ቸርነት ተጨምሮ ምሕረትን እናገኛለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ኤልሳዕ ማሰሮዎችዋን በዘይት ለሞላላት መበለት «አደርግልሽ ዘንድ ምን ትሻለሽ? በቤትሽ ያለውን ንገሪኝ» ብሎ ጠይቋት ነበር፡፡ ይህም አንድን ጻድቅ አማልደኝ ስንል «በቤትህ ያለው ምንድር ነው?» ብሎ የእኛንም ድርሻ እንደሚፈልግ ያሳያል፡፡ አንድ  ቅዱስ አትናቴዎስ የተረከው የቅዱስ ሚካኤል ተአምርም ይህን ያሳያል፡፡ አንድ ሰው ከቤቱ እጅ እግሩን አጣጥፎ ተቀምጦ ‹ቅዱስ ሚካኤል ሆይ እርዳኝ› ሲል «በምን ሥራህ ልርዳህ ፤ ከቤትህ ውጣና [35]ከአንድ ባለጠጋ ሔደህ ገንዘብ አበድረኝ በለው፡፡ ዋስ አምጣ ካለህ ቅዱስ ሚካኤል ዋስ ይሆነኛል በለው› አለው፡፡ ይህ ሰው እንደተባለው አድርጎ ነግዶ ባለጠጋ ሆነ የተበደረውን ገንዘብም ለአበዳሪው ሊከፍል ሲል አበዳሪው በሌላ ሀገር ነበር፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን በሳጥን አድርጎ ቅዱስ ሚካኤል ያድርስለት ብሎ ወደ ባሕር ወረወረው ፤ መልአኩም ዓሣን አዝዞ ገንዘቡ ወደ አበዳሪው ደርሶአል፡፡ ይህ ታሪክ እንኳን በነፍስ በሥጋ እንኳን ሳይሠሩ ‹አማልደኝ› ማለት እንደማይገባ የሚያሳይ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ (ድርሳነ ሚካኤል)

---

/፩ጴጥ ፫፥፳! ዘፍ. ፲፱፥፴/ ! የመጨረሻው ጣሪያ ሦስት ነው፡፡ (ሕዝ. ፲፬፥፲፬) ከሦስት ሲያንሱ ደግሞ ለኃጥአን የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል፡፡

[35] "Go in the city to a certain man and ask him to lend you some gold for a period of one year. If he says that he needs a guaranty, tell him the Archangel Michael is your guarantor." /The miracle of the Archangel told by St. Athanasius /

እመቤታችን ምንም እንኳን በዚህ ሰርግ ቤት ለነበሩት ሰዎች በምልጃዋ የጎደለውን ብትሞላላቸውም እነሱ ግን እጃቸውን አጣጥፈው እንዲቀመጡ አልተወቻቸውም፡፡ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› በማለት በምልጃ ሒደት ውስጥ የሚማለድላቸው አካላትም ድርሻ እንዳላቸው አስተምራናለች፡፡

## ○ የሚላችሁን ‹ሁሉ› /በከፊል ብቻ አትታዘዙ/

‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የምናየው የመጨረሻው ነጥብ ‹ሁሉ› የሚለውን ቃል ነው፡፡ እመቤታችን ‹የሚላችሁን አድርጉ› ብቻ ሳይሆን ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› ነው ያለችው፡፡ ይህም ማለት ማድረግ ያለብን የሚለንን ብቻ ሳይሆን <u>የሚለንን ሁሉ</u> ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን በብዙ ነገር ለእግዚአብሔር እየታዘዘ «ብቻ ይቺ አይንካብኝ እንጂ በማንኛውም ነገር እታዘዛለሁ» ቢል ‹የሚለውን ሁሉ› አደረገ ሊባል አይችልም፡፡ አብርሃም ልጁን እንዲሠዋ ሲታዘዝ ‹ልጄን አትንካብኝ በሌላው ሁሉ እታዘዝሃለሁ› አላለም፡፡ የሚለውን ሁሉ ሊያደርግ ተነሣ እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ለእርሱ መታዘዛችንን የሚያውቀው የሚለንን ‹ሁሉ› ስናደርግ ነው፡፡ ታዛዥነታችን የሚለካውም ከእኛ ፍላጎት ጋር በሚቃረን ቁርጠኝነት ስንታዘዝ ነው፡፡ ቅዱስ ዳዊት «ከፈቃዴ እሠዋልሃለሁ» እንዳለ ለፈጣሪ ብለን የምንወደውን ካልተውን ወይም የማንወደውን ካልተቀበልን ታዘዝን ሊባል አይችልም፡፡ (መዝ. ፶፫፥፮)

አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር የምንታዘዘው እርሱን ከመፍራትና ከማክበር ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ የእርሱ ትእዛዝ ከእኛ ፍላጎት ጋር ሲጣጣም ወይ ደስ የሚለን ነገር ሲሆን ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ብዙ ሰው አርብ

ረቡዕን ሰዓት ጠንቅቆ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ላይጾም ይችላል። ሆኖም ሰንበት ሲሆን ግን «ሸረ ሰንበት ነው» ብሎ ይበላል። ይህ የሚያሳየን በሰንበት መብላትም ፣ አርብ ረቡዕ እስከ ዘጠኝ መጾምም እኩል የተደነገጉ ሕግጋት ሆነው እያለ ሰዎች ግን የሚያከብሩት ከእነርሱ ጋር የተስማማውን ሕግ መሆኑ ነው።

ይህን ትንሽ ምሳሌ እንደ ማሳያ አነሣን እንጂ ብዙ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የማንታዘዝ መሆናችንን የሚያሳዩ እጅግ ብዙ ነገሮች አሉ። እመቤታችን ግን ‹ደስ የሚለንን› እየመረጥን ሳይሆን የሚለንን ሁሉ እንድናደርግ አዝዛናለች።

## ○ ‹የሚላችሁን አድርጉ› ስትል ‹እኔን አትስሙኝ› ማለትዋ ይሆን?

መናፍቃን እመቤታችንን አማልጅን ማለታችንን በመቃወም ሲናገሩ «እርስዋም እኮ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ ነው ያለችው» እያሉ ሰብከዋል ፣ ጽፈዋል። ይህን የሚሰሙ አንዳንድ የዋሃንም እመቤታችን ይህን ያለችው «እኔን አትስሙኝ» ለማለት መስሎአቸው ይደናገራሉ።

ወደ ምላሹ ከመግባታችን በፊት በዚህ በመናፍቃኑ አካሔድ ላይ ትንሽ ነገር እንመልከት። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስን እነሱ እንደሚሹት ብቻ የሚተረጉሙ መሆናቸውን ማየት ነው።

ሁላችንም እንደምናውቀው ጌታችን በመስቀል ላይ ለሚወደው ሐዋርያ ለቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ «እነኋት እናትህ» ብሎ ሠጥቶታል። እኛም

በዮሐንስ በኩል እመቤታችንን እናታችን ብለን ተቀብለናል፡፡ ይህንን ስንል መናፍቃኑ «ጌታ እናትህ ብሎ የተናገረው ለዮሐንስ ብቻ ነው እንጂ ለሌሎች አይደለም» ብለው ይሟገታሉ፡፡ አሁን ደግሞ እመቤታችን ለቃና አገልጋዮች የተናገረችውን «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» የሚል ንግግር ለሁላችንም ነው ብለው ይጠቅሱታል፡፡ አወንታዊ የሆነውን ለእኛ አይደለም ብለው አሉታዊ መስሎ የታያቸውን ግን ለእኛ ነው ማለታቸው መጽሐፉን እንደ ገዛ ፍላጎታቸው እንደሚተረጉሙት የሚሳይ ነው፡፡

«የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» የሚለው ንግግሯ እመቤታችንን ከመስማት ከማክበር ጋር የሚጣላ አይደለም፡፡ እስኪ ከእዚያው ሰርግ ቤት ሳንወጣ እንመልከተው፡፡ የሰርግ ቤቱ አገልጋዮች ‹ጋኖቹን ሲሞሉ› የታዘዙትና ያከበሩት ማንን ነበር? ጌታችንን ብቻ ነው? እንዲህ ካልን ምላሻችን ሙሉ በሙሉ የተፈጸመውን ሁኔታ አያሳይም፡፡ ምክንያቱም አገልጋዮቹ ጌታችን የሚለውን ያደረጉት ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› የሚለውን የእመቤታችንን ትእዛዝ ሰምተው ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህ ራስዋ የተናገረችውን ንግግር እርስዋን ለመቃወም መጥቀስ ከሰይጣን ብቻ እንጂ ከሥጋና ደም ብቻ የሚመነጭ ሃሳብ አይደለም፡፡ በቀላል ምሳሌ እንኳን ብንመለከተው አንዲት እናት ለልጆችዋ «አባታችሁ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ብላ ብትናገር «እኔን ኣታከብሩኝ ፤ አትስሙኝ ማለትዋ ነው» ብሎ የሚተረጉም ሰው ጤነኛ ሊባል አይችልም፡፡

## ○ እግዚአብሔር አብ እና እመቤታችን

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ጊዜ መወለዱን ታምናለች፡፡ የመጀመሪያው ልደት ከዓለም አስቀድሞ ባሕርይ ዘእም ባሕርይ አካል ዘእም አካል ከአብ የተወለደው ልደት ነው፡፡ ራሱ እግዚአብሔር አብ ‹አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ› ‹ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ› ብሏል፡፡ (መዝ.፪፥፯ ፤ ፻፱፥፫) ሁለተኛው ልደት ደግሞ የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ከእመቤታችን የተወለደው ልደት ነው፡፡ ስለእነዚህ ነው እንግዲህ ‹ነአምን ክልዔተ ልደታተ› ‹በሁለት ልደታት እናምናለን› ብለን የምንመሰክረው፡፡

የወልደ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ልደቱን ስናነሣ አስቀድመን እግዚአብሔር አብን ማንሣት የግድ ነው፡፡ ደኃራዊ ልደቱን /ሁለተኛውን ልደቱን/ ለማንሣት ደግሞ እመቤታችንን ማንሣት የግድ ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ‹ያ ቃል ሥጋ ሆነ› ብሎ ለመናገር አስቀድሞ ‹ቃልም በእግዚአብሔር (አብ) ዘንድ ነበረ› ብሎ መጻፍ እንዳስፈለገው ሁሉ ‹ክርስቶስ ተሰቅሎ ሞቶ አዳነን› ብሎ ለመናገርም መጀመሪያ ‹በማርያም ዘንድ ነበረ› ብሎ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ወልድን በባሕርየ መለኮቱ የወለደው እግዚአብሔር አብ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ባሕርየ ትስብእቱን ከእርስዋ ከነሣው ከወላዲተ አምላክ ማርያም ጋር ያነጻጽሩታል፡፡ የቃና ዘገሊላውን ሰርግ ቤት የሚያካትተው ይህ ንጽጽር እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

ቅዱስ ያሬድም በድጓው ለዘመኑ መነሻ የሌለውን ከዓለም አስቀድሞ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደውን ወልድ ድንግል ማርያም በመውለድዋ እግዚአብሔር አብን መሰለች የሚለውን ምሥጢር ሲያስረዳ በመንፈስ ቅዱስ

ተቃኝቶ እግዚአብሔር አብ ለድንግል ማርያም «አዝማንየ አዝማንኪ» /ዘመንሽ ዘመኔ ሆኑ/ ማለቱን ተናግሯል፡፡

ራስዋ እመቤታችንም ቅዱሳን ሐዋርያት ‹ጌታን ስትጸንሽው እንዴት ነበር?› ብለው ጠይቀዋት ነበር፡-

ሲናገሩት የማይቻለውን ይህንን ምሥጢር በጠየቋት ጊዜ «ጭንቅ ጭንቅ ይለኛል እጅ እግሬን ያዙኝ» አለቻቸው፡፡ «ለወትሮ የማውቀው መልአክ ቀርቶ ለወትሮ የማላውቀው መልአክ መጣ፡፡ ጊዜው ካፊያ ነበረ ፤ ግራ አጽፉን ቢባርከው ኅብስተ ሕይወት ሆነ በልቶ አበላኝ ፤ ቀኝ አጽፉን ቢባርከው ጽዋ ሕይወት ሆነ ጠጥቶ አጠጣኝ» ብላ ነገር ጀምራላቸው ሳለ መልአከ እግዚአብሔር ወርዶ ድምፅ አሰማቸው፡፡ እንደ ቅጠል ረገፉ፡፡ እርስዋ ለበቃችው ምሥጢር አልበቃችሁም ሲል ነው፡፡ ዓይነ ስውሩ ልበ ብሩሑ ኢትዮጵያዊው ሊቅ መምህር ኤስድሮስ ግን ይህን የእመቤታችን ንግግር ተርጉመውታል፡፡ «ብቻ መውለድን ቀምሶ አቀመሰኝ ፤ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ተወልዶ ድኅረ ዓለም ያለ አባት እንድወልደው አደረገኝ» ማለትዋ ነው ብለዋል፡፡[36]

ቅዱስ ኤፍሬምም በዚህ ጉዳይ አብንና እመቤታችንን አነጻጽሮ ሲናገር «እምኀበ አብ ወጽአ ቃል ዘእንበለ ድካም ፤ ወእም ድንግል ተወልደ ዘእንበለ ሕማም» «ከአብ አካል ዘእም አካል ባሕርይ ዘእም ባሕርይ ድካም ሳይሰማው ተወለደ ፤ ከእመቤታችንም እርስዋን ሕማም ሳያሰማት እርሱም ሕጻናትን የሚሰማ ሳይሰማው ተወለደ፡፡» ብሏል፡፡ (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ)

እመቤታችን የአብ ምሳሌ መሆንዋን ሊቃውንት ስለ ዘላለማዊ ድንግልናዋም ሲያስረዱ እንደ ማስረጃ ያቀርቡታል፡፡ እግዚአብሔር አብ ከወልድ በቀር ሌላ ልጅ እንደሌለው በባሕርይውም ሌላ እንደማይወልድ ሁሉ የአብ ምሳሌ የሆነች እመቤታችንም ከሥግው ቃል በቀር ለዕሩቅ ብእሲ (አምላክነት ለሌለው ለተራ ሰው) እናት መሆን አይቻላትምና ለዘላለም ድንግል ሆና ኖራለች፡፡ (ሕዝ. ፵፬፥፩ ትርጓሜ)

[36] ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

ሌላው እመቤታችንን ከእግዚአብሔር አብ ጋር የሚያነጻጽረው ምሥጢር የሚገኘው ደግሞ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ነው። ጌታችን ሦስቱን የምሥጢር ሐዋርያት ይዞ ወደ ታቦር ተራራ በወጣበት ጊዜ የባሕርይ አባቱ አብ «የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት» ብሎ ከደመና ተናግሮ ነበር። በተመሳሳይም የሥጋን ባሕርይ ከእርስዋ ነስቶ የተወለደባት ድንግልም እንደ እግዚአብሔር አብ «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» በማለት ተናግራለች። የቃናውን ንግግርዋን ‹አትስሙኝ ማለትዋ ነው› የሚሉ ሰዎች እግዚአብሔር አብ በደብረ ታቦር የተናገረውንም በዚህ መንገድ ይተረጉሙት ይሆን? ክብር ይግባውና እግዚአብሔር አብ ‹እኔን አትስሙኝ አለ› ሊባል ይሆን?



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ አራት

## የቃናው ተአምር

ኢየሱስም፦ ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው፡፡
እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው፡፡ እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው፡፡
አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ሥጡት አላቸው ፤ ሠጡትም፡፡
አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ
ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር
ዮሐ. ፪፥፯-፱

### ፩. ስለአይሁድ የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች

እጅን በመታጠብ የሚፈጸም የማንጻት ልማድ በአይሁድ ዘንድ በጣም የሚከበር ልማድ ነው፡፡ አይሁዳውያኑ እጅ አለመታጠብን የሚያዩት እንደ ንጽሕና ጉድለት ሳይሆን እንደ መርከስ ነው፡፡ ከእንቅልፍ ሲነሱ ፣ ከገበያ ሲመለሱ ይታጠባሉ ፣ ማድጋቸውን ፣ ጽዋቸውን ሌላው ቀርቶ አልጋቸውን ሳይቀር እየደጋገሙ ያጥባሉ፡፡ በህገራቸውም ‹‹በብዙ ውኃ የሚታጠብ በብዙ ሀብት

ይታጠባል»[37] እንደማለት ያለ አባባል አላቸው። ወደ ደብተራ ኦሪት ሲገባ ከመሠዊያው ቀጥሎ መጀመሪያ የሚገኘው የተቀደሰ ዕቃ ካህናቱ የማንጻት ሥርዓት የሚፈጽሙበት ትልቅ የመታጠቢያ ሰን ነው።

ንጽሕና እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የአይሁዳዊያኑ ጥፋት ግን እጅ መታጠብን ከዐሥርቱ ትእዛዛት በላይ ማክበራቸውና እንደ ወሳኝ የቅድስና ሥራ መቁጠራቸው ነበር። ጌታችን ባስተማረበት ወቅት የተፈጠረውን ነገር ቅዱስ ማርቆስ እንዲህ ይተርከዋል ፦

«ፈሪሳውያንና ከጻፎች ወገን ከኢየሩሳሌም የመጡትም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንድ በርኩስ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ። ፈሪሳውያንና አይሁድም ሁሉ የሽማግሎችን ወግ ሲጠብቁ እጃቸውን ደኅና አድርገው ሳይታጠቡ አይበሉምና፥ ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም፥ ጽዋንም ማድጋንም የናስ ዕቃንም አልጋንም እንደ ማጠብ ሌላ ነገር ሊጠብቁት የተቀበሉት ብዙ አለ።»

«ፈሪሳውያንም ጻፎችም። ደቀ መዛሙርትህ እንደ ሽማግሌዎች ወግ ስለ ምን አይሄዱም? ነገር ግን እጃቸውን ሳይታጠቡ እንጀራ ይበላሉ ብለው ጠየቁት።

«እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፦ ኢሳይያስ ስለ እናንተ ስለ ግብዞች። ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ በእውነት ትንቢት ተናገረ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ጽዋን ማድጋንም እንደ ማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፥ ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ እንዲህም አላቸው፦ ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል።» (ማር. ፯፥፩-፱)

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት የተቀመጡት ስድስት የድንጋይ ጋኖች እንደ

37 ‹‹He who uses much water in washing will gain much wealth in this world›› /የአማርኛውን ትርጉም የአባባል ለዛ እንዲኖረው በሚል በቀጥታ ቃል በቃል አልተረጎምሁትም/

ማንኛውም አይሁዳዊ ቤት ይህንን የመናጻት ወግ ለመፈጸም የተዘጋጁ እጅ መታጠቢያ ውኃ የሚሞላባቸው ነበሩ። ስድስቱ ጋኖች የሚቀመጡት ከሰንበት ውጪ ላሉት ስድስት ቀናት የተዘጋጁ ሲሆን በሰባተኛይቱ ቀን ቅዳሜን ግን አይሁድ ከአምልኮና ከዕረፍት ውጪ ያረክሰናል የሚሉትን ሥራ ስለማይሠሩ ለዚያ ቀን ጋን ማዘጋጀት [38]አስፈላጊ አልነበረም።

የቃናዎቹ የድንጋይ ጋኖች የውኃ ማስቀመጫ መሆናቸው እና ከድንጋይ መሠራታቸው የጌታችንን ተአምር የበለጠ እንከን የለሽ ያደርገዋል። የውኃ ማስቀመጫ እንደመሆናቸው ጋኖቹ በምንም ምክንያት የወይን ጠጅ ተጠምቆባቸው አያውቅም። ተጠምቆባቸው ቢሆን እንኳን የድንጋይ ጋን እንደ ሸክላ ጋን መጥጦ የማስቀረት ጠባይ የለውም። ስለዚህ ጌታችን ምንም የወይን ጠጅ ጣዕም ሊኖረው በማይችል የድንጋይ ጋን ውስጥ ተአምር ማድረጉ ተአምሩን ሊያጣጥሉ ለሚሹ ሰዎች ምክንያት የሚያሳጣ ነው።

[38] «Six pots were used to correspond to the days of the week from Sunday to Friday, each pot consecrated for a specific day for purification. As for Saturday, it was a day for worship and rest- no one did any work that required purification.» /A PATRISTIC COMMENTARY THE GOSPEL ACCORDING TO ST. JOHN / Fr. Tadros Y. Malaty/



Scanned by CamScanner

## ፪. ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው

◦ ረዳት የማይሻው አምላክ ረዳቶች

ጌታችን የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት አስተናጋጆችን ውኃ እንዲሞሉ አዘዛቸው:: «የባሕርን ውኃ እንደ ረዋት የሚሰበስበው» ፣ «ውኆችን እንደ ክምር አቁሞ ሕዝቡን ያሻገረ» ፣ «እልፍኙን በውኃ የሚሠራ» ፣ «ውኆችን በእፍኙ የሰፈረ » ‹ውኃና ነፋስ የሚታዘዙለት አምላክ ሁሉን ማድረግ ሲቻለው ለሰርግ ቤቱ አገልጋዮች ‹ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው› አላቸው:: (መዝ. ፴፫፥፯ ፣ ፩፻፬፥፲፫፣ ፻፯፥፫ ኢሳ. ፵፥፲፪) ይህ እጅግ የሚደንቅ ትሕትና ነው:: አባ ጊዮርጊስ በሰዓታቱ ‹በረቂቅ ጉም ትነት ውኃውን የሚቋጥረው ፤ ከወንዝም ወደ ላይ የሚያወጣው ፤ ከሩቅ ሰማይ የሚያወርደው› (በተነ ጊሜ ረቂቅ ዘየዓቁሮ ለማይ ያዐርጎ እም ቀላይ ወያወርዶ እም ኑኅ ሰማይ) (ሰዓታት/ ቅዱስ ) እንዳለ ዝናምን በምድር ላይ የሚያዘንም ፣ ውቅያኖስንና ባሕርን በውኃ የሞላ አምላክ ‹ውኃ ሙሉ› ያለው ስድስት ጋኖችን ውኃ መሙላት አቅቶት አይደለም:: በዚህ አሠራሩ እጅግ ትልቅ ትሕትናን እና ቸርነቱን ሊያስረዳን ነው::

አገልጋዮቹ በተአምራቱ እንዲሳተፉ ማድረጉ ትሕትናውን ያሳየናል። ቅዱስ ዳዊት ‹ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ› ‹ብቻውን ታላላቅ ተአምራትን ያደረገ ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና› በማለት እንደተናገረ እርሱ የሰውን ረዳትነት የሚሻ አምላክ አይደለም:: (መዝ. ፻፴፮፥፬) ‹ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው› ሲል ስንሰማ የጌታችንን ትሕትናውን እናደንቃለን:: ‹አምላካችን ሆይ ውቅያኖስን በውኃ ስትሞላ ማን ሞልቶልህ ነበር? የሰማዩን እልፍኝ በውኃ ስትሠራ ማንን ረዳት አደረግህ? ውኃን ለሦስት ስትከፍለው ፤ ሐኖስ ጠፈር ውቅያኖስን ስትሠራ ማንን ረዳት አደረግህ?› እያልንም እናደንቃለን::

አፈር ትቢያ የሆነውን የሰው ልጅ አክብሮ እሱ በሚያደርገው ተአምራት ላይ ድርሻ እንዲኖረው ማድረጉ ታላቅ ትሕትና ነው:: ንዋይ ኅሩይ

ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነን» እንዳለ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር በትሕትና የሚሠራ አምላክ ነው። (፩ቆሮ. ፫፥፱)

በዮሐንስ ወንጌል በተጻፉ ሌሎች ተአምራቱም ውስጥ ሰዎች ድርሻ ነበራቸው። አልዓዛርን ከሞት ባስነሣው ጊዜ ለሕዝቡ ‹ድንጋዩን አንሡ› ለደቀ መዛሙርቱም «ፍቱትና ይሒድ» ብሎ ድንጋይ የማንሣትና መግነዝ የመፍታትን የሥራ ድርሻ ለሰዎች ሠጥቶአቸው ነበር። (ዮሐ. ፲፩፥፵፬) ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ዓይኑን በጭቃ ከሠራለት በኋላ ‹በሰሊሆም ተጠመቅ› ብሎ በፈውሱ ሒደት ውስጥ ለራሱም ድርሻ ሠጥቶት ነበር። (ዮሐ. ፱፥፯) እነዚህን ነገሮች ያደረገው ሙት ያስነሣ አምላክ ድንጋይ ማንሣትና መግነዝ መፍታት አቅቶት ፤ ዓይንን በጭቃ የሠራ አምላክ ወዲያው ማብራት ተስኖት ሳይሆን ከፍጥረቱ ጋር የሚሠራ ትሑት አምላክ ስለሆነ ነው።

ጌታችን ውኃውን ያለ ሰው እርዳታ በጋኖቹ ውስጥ መሙላት ይችላል። ለእስራኤላውያን ከዓለት ላይ ውኃ እንዳፈለቀላቸው ከእነዚህ ጋን ሆነው ከተሠሩት ድንጋዮች (ዓለቶች) ላይም ውኃ አፍልቆ ጋኖቹ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲሞሉ ማድረግም ይቻለዋል። ጭራሽም ውኃ ማስሞላት ሳያስፈልገው ድንገት ጋኖቹን እስከ አፋቸው በወይን ጠጅ መሙላትም ይችላል። ወይን ጠጁም ቀርቶ ደግሞ በሰው ልጅ ዓይን ታይቶ የማያውቅ አዲስ ነገር መፍጠር ፤ ሰርግ ቤቱን በመላእክት ዝማሬ መሙላት ፤ ሙሽሮችን በብርሃን ልብስ ማጎናጸፍ ፤ የሚጠጣውን እንደ ዝናም ማዝነም ፤ ማዕዱን እንደ መና ማውረድ ይቻለዋል። ነገር ግን በሰርግ ቤቱ በትሕትና

ሁሉም በሚያውቁት ውኃና ጋን ውስጥ በቀላልና ግልጽ መንገድ ተአምሩን በማድረግ የሙሽሮቹን ችግር ሊፈታ ወደደ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ተአምሩ በዚህ መንገድ ባይፈጸም ኖሮ በብዙዎች ዘንድ ተአማኒነት አይኖረውም ነበር ብሏል።[39]

የቃና አገልጋዮች በጌታችን ተአምር ላይ ተሳትፎ ማድረጋቸው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በዚያች ሰርግ ቤት በተደረገው ተአምር ዙሪያ ዋነኛ ምስክሮች አድርጓቸዋል። እነዚህ አገልጋዮች የወይን ጠጁን ማለቅ ማንም ሳይሰማ ያወቁ አስተናጋጆች ናቸው። ከዐሥራ ሁለት እስከ ዐሥራ ስምንት እንስራ ሊደርስ የሚችል ውኃ ቀድተው እስከ አፉ ድረስ ሞልተዋል። ውኃው ወይን ከሆነ በኋላም ማንም ሳያውቅ እነሱ ‹ከወዴት እንደመጣ ያውቁ ነበር› ተብሎ ተጽፏል። ከወዴት እንደመጣ ማወቅ የቻሉት ውኃ የቀዱት እነርሱ ስለሆኑ ነው።

ውኃው የወይን ጠጅ ሲሆን እና በታዳሚው ሲጠጣ ከእነዚህ አገልጋዮች በላይ ማን ምስክር ሊሆን ይችላል? የተአምሩ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች እንደመሆናቸውም ከዚያች ዕለት ጀምሮ በሔዱበት ስለዚህ ተአምር ዋነኛ ማብራሪያ ሠጪዎች እነሱ ይሆናሉ። «ውኃውን ቅዱት አለን .. ቀዳነው ... ጋኖቹን ሙሉአቸው አለን ... ሞላናቸው ... እስከ አፋቸው ሙሉአቸው አለን...[40]እንደ ቅቤ

---

[39] "And why was it, that He did not the miracle before they filled them, which would have been more marvelous by far? for it is one thing to change given matter to a different quality, and another to create matter out of nothing." The latter would indeed have been more wonderful, but would not have seemed so credible to the many." (St. Jhon Chrysostom , Commentary on the Gospel of Jhon ver. 6,7)

[40] ይህ አገላለጽ በትርጓሜ ወንጌል የተጻፈው አገላለጽ ነው።

፣ እንደ ማር ቁልል አድርገን ሞላነው... ከዚያ በኋላ ...!!!» እያሉ እንደሚተርኩ ጥርጥር የለውም። ጌታችን አብረውት የመጡትን ሐዋርያት በአስተናጋጆቹ ፈንታ ውኃ እንዲያቀርቡ ማዘዝ ይችል ነበር። ነገር ግን አስተናጋጆቹን የተአምሩ ምስክሮች ማድረግ ፈለገ። በእርግጥም ሐዋርያቱን አስተናጋጆች ከማድረግ ይልቅ አስተናጋጆቹን ሐዋርያት ማድረግ ይሻላል።

## ○ በዝምታ የተፈጸመ ተአምር

በቃና ዘገሊላ ጌታችን የሠራው ተአምር አምላካዊ ኃይሉን የሚያስረዳ ድንቅ ሥራ ነው እንጂ ምትሐት አይደለም። ብዙ ምትሐት የሚሠሩ ሰዎች በዓለም ላይ አሉ። እነዚህ ምትሐተኞች አስማታቸውን ሲሠሩ ብዙ ድግምት እየደገሙ ፣ በዕቃ ላይ ወይም በሰው ላይ እጃቸውን እያዞሩ ፣ እነሱም ብዙ ፍዳ እያዩ ፣ ከተለመደው ነገር ውጪ ሰዎችን እንዲህ አድርጉ ፣ እንዲህ አታድርጉ ብለው መከራ እያሳዩ ነው። ካሉት ቃል ወይም አካሔድ አንዳች ነገር ዝንፍ ቢል አስማቱ ሊከሽፍ ፣ ጨዋታው ሊፈርስ ይችላል። እንዲህ አድርገው የሚሠሩትን ምትሐት «የአባቶች አብነት ነው ፣ ጥበብ ነው ፣ አርት ነው ፣ ሳይንስ ነው፣ በሰለጠኑት ዓለማት የተለመደ ነው» እያሉ ሊያሳምኑንም ይሞክራሉ። መቼም ዲያቢሎስ ለኃጢአት የማያወጣው ‹የክርስትና ስም› የለም።

ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና ጌታችን የቃናውን ተአምር ሲሠራ እንኳን ውኃውን ጋኖቹንም በእጁ አልነካቸውም ፣ ጨርሶም አልተጠጋም። ለአገልጋዮቹም ‹እስከ አፋቸው ውኃ ሙሉአቸው› ከማለት በቀር «በዚህ መንገድ ሒዱ ፣ ከዚህኛው ወንዝ ቅዱ ፣ ሰው እንዳታናግሩ ፣ በዚህ ጋር እንዳትዞሩ....» የሚል ዝርዝር

አልተናገረም:: አገልጋዮቹም ውኃውን የቀዱት በማንኛውም ጊዜ እንደሚቀዱት ነው:: ውኃውንም የተለየ ነገር እንዳልተጨመረበት በሚያረጋግጥና ሁሉም በግልጥ ሊያዩ በሚችሉበት ሁኔታ እስከ አፉ ድረስ እንዲሞላ ነው ያደረገው:: በአንደበቱ ‹አንተ ውኃ የወይን ጠጅ ሁን› ብሎም አልተናገረም:: [41]ዓለማትን በዝምታ (በአርምሞና በኃልዮ) የፈጠረ አምላክ መሆኑን ሲያስረዳ ውኃውን ወይን ያደረገውም በዝምታ ብቻ ነበረ:: አይሁድ ወይን ጠጅ ሲጠምቁ የማስከር ኃይሉን ለመቀነስና ለብዙ ሰው ለማዳረስ አንድ እጁን ወይን በሦስት እጅ ውኃ ይበርዙት ነበር:: አምላካችን ወይን የሚበረዝበትንና ጣዕም የሚጠፋበትን ውኃ የወይን ጠጅ አደረገው::

## ○ በምልዐት የተፈጸመ ተአምር

የቃናው ተአምር አፈጻጸም ከዚህ ቀደም እርሱ በሠጣቸው ኃይል ተመሳሳይ ተአምራትን ካደረጉት ነቢያት ከነ ኤልያስና ከነኤልሳዕ ተአምራት እና ራሱም በሕዝቡ መካከል ከዚያ በኋላ ምግብ ሲያበረክት ካደረገው ሌላ ተአምር የተለየና የላቀ ነው::

[41] ጌታችን በተአምሩ አፈጻጸም እርሱ ሰማይና ምድርን የፈጠረው ፣ አስቀድሞ የነበረው አምላክ እንደሆነ አሳይቶናል:: ለምሳሌ ሰውን ከአፈር ለውሶ የፈጠረው እርሱ መሆኑን ለማስረዳት ዕውር ሆኖ ለተወለደው ሰው በቅዱስ ምራቁ ዓይንን ሲፈጥር እንደ ሸክላ ሠሪ በእጆቹ ጭቃን ለውሶ በደረቅ ግንባር ላይ ዓይን ሠራ:: (ዮሐ. ፱፥፮) አዳምን በገነት ‹ወዴት ነህ?› ብሎ የጠራው እርሱ መኖሩን ሲያስረዳን ‹አልዓዛርን ወዴት ቀበራችሁት?› አለ:: (ዮሐ. ፲፩፥፴፬)

ኤልያስ በሰራፕታዋ መበለት ቤት የነበረውን እፍኝ ዱቄትና ጥቂት ዘይት አበርክቶ ለብዙ ቀን በልተዋል፡፡ (፩ነገሥ. ፲፯፥፲፬-፲፭) ይሁንና በማድጋውና በማሰሮው የነበረው ዱቄት ቀስ በቀስ እየበረከተ ሔደ እንጂ ለብዙ ቀን በሚበሉት መጠን ወዲያውኑ አልበዛም፡፡

የኤልያስ መንፈስ እጥፍ ሆኖ ያደረበት ኤልሳዕም በአንዲት መበለት ቤት ያሏትን ባዶ የዘይት ማሰሮዎች እንድታመጣ እና ከጎረቤትም እንድትዋስ ከነገራት በኋላ ዘይቱ ቀስ በቀስ እየተቀዳ ዘይቱ እየፈሰሰ እንዲሞላ አድርጎላታል፡፡ (፪ነገሥ. ፬፥፩-፯) ይሁንና ዘይቱ ከማድጋ ማድጋ እየተቀዳ እየተቀዳ ሲሔድ እየበረከተ ሔደ እንጂ በአንድ ጊዜ የበዛ አይደለም፡፡

እንዲሁም ራሱ ጌታችን በዮሐ.፮ ላይ ዓሣውንና እንጀራውን አበርክቶ አምስት ሺህ ወንዶችንና ያልተቆጠሩትን ሕጻናትና ሴቶች ሲመግብ ዓሣውና እንጀራው በአንድ ጊዜ እንደተከመረ አልተጻፈም፡፡ ይልቁንም አንዱ ከአንዱ ጋር ሲቀባበል እየበረከተ ሔደ፡፡ ታሪኩ ሲነገር ‹አበረከተ› የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

በቃና ዘገሊላ ያደረገው ተአምር ግን የማበርከት ሥራ ሳይሆን በምልዐት የተፈጸመ ተአምር ነው፡፡ «አንዱን ጋን ውኃ ሞልታችሁ ወደሌላው ቅዱት» ብሎ አንዱን ጋን ውኃ ወይን አድርጎም አላበረከተውም፡፡ ይልቁንም ቸርነቱን ሲገልጥ ስድስቱንም ጋን እስከ አፉ ድረስ ውኃ አስሞልቶ የወይን ጠጅ አደረገው፡፡



Scanned by CamScanner

### ○ መልካም ወይን ጠጅ

የቃናው የወይን ጠጅ ተራ የወይን ጠጅ አልነበረም:: በጥራቱ እጅግ ከፍተኛ የሆነ (super quality) ነበር:: ለዚህም የመጀመሪያው ምስክር ‹ጥዒም አንከረ ሊቀ ምርፋቅ› እያልን የምናዜምለት ‹በቀመሰ ጊዜ› ያደነቀው አሳዳሪው ነው:: ጌታችን በሚያደርጋቸው ድንቅ ሥራዎች ሁሉ ላይ ከተለመደው የበለጠ ነገርን ሲያደርግ እናያለን:: ሕሙማንን ሲፈውስ ከበሽታቸውና ከስቃያቸው ማዳን ብቻ ሳይሆን ከጤነኛ ሰው የበለጠ ብርታትን ይሠጣቸው ነበር:: ለዚህም ምስክራችን ከሠላሳ ስምንት ዓመት የአልጋ ቁራኛነት አድኖ ያለምንም የማገገሚያ ጊዜ ወዲያው አልጋውን አሸክሞ የላከው መጻጉዕ ነው:: (ዮሐ.፩+፭) በዚህ ሰርግ ቤትም ውኃን ወይን ባደረገ ጊዜ ሲጠጣ የዋለውን ዓይነት የወይን ጠጅ አልሠጣቸውም:: ያለቀውን ዓይነት ወይን ጠጅም ቢሠጣቸው አመስግነው ይጠጡ ነበር:: ምክንያቱም የለመዱትና የወደዱት ጣዕም ስለሆነ ነው:: ከዚህም አልፎ ደግሞ የባሰ መናኛ ወይን ጠጅ ቢሠጣቸው ኖሮ በሰው ደንብ ‹ከሰከሩ በኋላ መናኛ› ስለሚቀርብ አመስግነው ያቀርቡት ነበር:: እርሱ ግን ‹ድሆች ናቸው ይህን ከቀመሱ ይበቃቸዋል› ሳይልና ሳያቃልል እንኳን በድሆች መንደር በቤተ መንግሥትም ከሚቀርበው እጅግ የላቀ የወይን ጠጅን ሠጣቸው::

ወይንን መልካም ለማድረግ ሙያና ሀብት ብቻ አይበቃም:: ጊዜም ይፈልጋል:: በአንዳንድ ሀገራት በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት የቆየ የወይን ጠጅ አንዱ መለኪያ ብቻ ብዙ ጎጆ ሊቀልስ በሚችል ዋጋ እንደሚሸጥ ይሰማል:: ምዕራባውያኑም ማስቶቻቸውን ሲያደንቁ ‹She's like wine!› (እንደ

ወይን ናት!) ይላሉ። በዕድሜ ብዛት የማትሰለች የማትጠገብ ናት ለማለት ነው። ቅዱስ ዳዊት ‹ብእሲትከ ከመ ወይን ሥሙር ውስተ ጽርሐ ቤትከ› ያለው ዓይነት ነው። ‹‹ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ እንደ ወይን ናት›› መዝ. ፻፳፰፥፫/ በአጠቃላይ የወይንን ጣዕም አስደናቂ ለማድረግ እጅግ ብዙ ዓመታትን ይጠይቃል። የጊዜ ባለቤት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የዓመታቱን ሒደት መጠበቅ ሳያስፈልገው በአንዲት ቅጽበት ውኃውን አስደናቂ ወይን አደረገው። በቃናው ወይን ጠጅ ጣዕም ውስጥ በተአምር የተጨመቀ /compressed/ የወይን ዕድሜም አለ ማለት ነው።

## ○ ክርስቶስ እና ሙሴ

እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣ ዘንድ የተመረጠውና በኋላም ነጻ ያወጣው ታላቁ ነቢይ ሙሴ በብሉይ ኪዳን ከነበሩ የጌታችን ምሳሌ የሆኑ ሰዎች (Prototypes of Christ) አንዱ ነበር። ወላጆቹ ‹ምልከአም› /Melchi/ ብለው ስም ያወጡለት ሙሴ ከአስተዳደጉ ጀምሮ እስራኤልን ነጻ እስካወጣበት ጊዜ ያለው ታሪክ ነገረ ድኅነትን የሚያስረዳ ነበረ። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ሙሴስ በኋላ ስለሚነገረው ነገር ምስክር ሲሆን በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ፥ ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው›› በማለት ሙሴ አሁን ለምንናገረው ለሚበልጠው ነገረ ክርስቶስ ምስክር የሚሆን መሆኑን በንጽጽር አስቀምጧል። (ዕብ.፫፥፭) ይህን የሚሳዩ ብዙ ነጥቦች አሉ።

ሙሴ ባልወለደው ፈርዖን የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ ይጠራ እንደነበር ፤ ጌታችንም በሥጋ አባት የሌለው ሲሆን የዮሴፍ ልጅ ተብሎ ተጠርቶአል። (ዕብ. ፲፩፥፳፬ ፤ ሉቃ. ፫፥፳፫) ሙሴ የተወለደው ጨካኝ ንጉሥ ፈርዖን ተነሥቶ ብዙ ሕጻናትን ባስጨፈጨፈበት ዘመን ሲሆን ፤ የጌታችንም የሕጻንነት ዕድሜ በጨካኙ ሔሮድስ ዘመን ነበረ። (ዘጸ.፩፥፳፪ ፤ ማቴ. ፪፥፲፮)

ሙሴ ከሞቱት ሕጻናት መካከል ወደ ወንዝ አብራው በወረደችው በእኅቱ በማርያም አማካይነት ተርፎ እንዳደገ ፤ ጌታችንም በእናቱ በማርያም እቅፍ ተሰድዶ ከሔሮድስ ሰይፍ ተርፎአል። (ዘጸ. ፪፥፬ ፤ ማቴ. ፪፥፲፬) ሙሴም ጌታችንም አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾመዋል። (ዘጸ. ፳፬፥፲፰ ፤ ማቴ. ፬፥፪) ሙሴ ግብጻዊውን ገድሎ በአሸዋ ቀብሮ እስራኤላዊውን ነጻ እንዳደረገ ጌታችን በመስቀሉ ዲያቢሎስን ገድሎ ነጻ አድርጎናል። (ዘጸ. ፪፥፲፪፤ ኤፌ. ፪፥፲፮) ሙሴ እስራኤልን መርቶ ከግብፅ እንዳወጣቸውና ግብፅን ባዶ እንዳደረጋት ጌታችንም እኛን ከሲኦል ባርነት ነጻ አድርጎ ሲኦልን ባዶ አድርጓታል።

የሙሴ እኅት ማርያም ‹ንሴብሖ› ብላ እንደዘመረች በልደተ ነፍስ እኅቱ[42] የምትባል እመቤታችንም ‹ታዐብዮ› ብላ ዘምራለች። (ዘጸ.፲፭፥፳፩፤ ሉቃ. ፩፥፵፮ ፤ ኪ.ወ.ክ ፮፻፲ ) የሙሴ እናት ዮካብድ ለሙሴ እናቱ ስትሆን ከፈርዖን ልጅ

[42] በሥጋ የዳዊት ልጅ በመሆኗም እመቤታችን የጌታ እኅቱ ትባላለች። ጌታ ‹የዳዊት ልጅ› እንደተባለ እንዲሁ ለእመቤታችን ‹ልጄ ሆይ ስሚ እዪም› አባትዋ ዳዊት ተናግሯል። (መዝ. ፵፬፥፲ ) እርሱም ‹እኅቴ ሙሽራዬ› ብሎ መጥራቱ እንዲሁ ሌላው ማስረጃ ነው። (መኃ. ፬፥፲፪ ፤ Who is Christ to me? ; Hegomen Matta Morgan of Alexandria ppg 87)እንዲሁም ሊቃውንት በሥጋ እናቱ ስትሆን በመንፈስ ቅዱስ እኅቱ ትባላለች ብለዋል። የጎንደሩ ሊቅም በቅኔአቸው ለልጆቻቸው እናትም እኅትም ከሆኑት ከሎጥ ልጆች ጋር አነጻጽረው ተቀኝተዋል። «በዘርዐ አቡሆን ኮና እኃተ ውሉዶን እኃት ፡ አመ ወርኃ ሕጸጽ ወንትጋ ። ለከሰ አምላከ ክርስቶስ ቀዳሚ ጸጋ። ወለተ ሐና ጠባብ በመንፈስ ቅዱስ እኅትከ እንዘ እምከ በሥጋ» «በችግርና በማጣት ወራት እኅትማማቾቹ በአባታቸው ዘር የልጆቻቸው እኅቶች ሆኑ። ቀዳሜ ጸጋ የሆንህ አምላከ ክርስቶስ ለአንተ ግን አስተዋይዋ የሐና ልጅ በሥጋ እናትህ ስትሆን በመንፈስ ቅዱስ እኅትህ ሆነች»



Scanned by CamScanner

እየተከፈላት ምግዚቱም ሆና እንደነበር ፤ እመቤታችንም ለሙሴ አምላክ ለክርስቶስ እናቱም አገልጋዩም ሆናለች። በዚህ ጉዳይ ቅዱስ ያሬድ ‹እንዘ አመቱ እሞ ረሰያ› ‹አገልጋዩ ስትሆን እናቱ አደረጋት› ሲል ቅዱስ ኤፍሬም ደግሞ ‹እናትና ገረድ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ› ብሏል።

ከዚህ ሁሉ ጋር ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌ ነው የሚያሰኘንን ምሥጢር በቃና ዘገሊላም እናገኘዋለን። ሙሴ ከእግዚአብሔር በተሠጠው ጸጋ ሕዝቡን ነጻ ያወጣ ዘንድ የመጀመሪያ ተአምሩን ያደረገው [43]የአባይን ውኃ ወደ ደምነት በመለወጥ ሲሆን የመጨረሻው ተአምር ደግሞ በፋሲካ የተደረገው ሞተ በኩር ነበር። አምላከ ሙሴ ክርስቶስም የመጀመሪያ ተአምሩን [44]ውኃን ወይን በማድረግ ጀምሮ የመጨረሻውን የማዳን ሥራውን በራሱ ፋሲካነት ፈጽሞልናል። «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» እንዳለ ሐዋርያው። (፩ቆሮ. ፭፥፯) በቃና ዘገሊላ ውኃውን ወይን እንዳደረገው በምሴተ ሐሙስ ደግሞ ወይኑን ደሙ አድርጎ ለሐዋርያቱ አጠጥቷቸዋል።

የጌታችን ተአምር ከሙሴ ተአምር ጋር ሲነጻጸር ግን ልዩነት እንዳለውም መዘንጋት የለብንም። ሙሴ ተአምርን ያደረገው ከእግዚአብሔር ባገኘው ሥልጣን ሲሆን የሙሴ አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ይህን

[43] እግዚአብሔር በባሪያው በሙሴ እጅ ያደረጋቸው ዐሥሩ መቅሠፍቶች ግብፃውያን በእያንዳንዱ ፍጥረት ላይ ሥልጣን አላቸው ብለው የሰየሟቸው ጣዖታት ኃይል እንደሌላቸው ለማስረዳት ነበር። የአባይን ውኃ ደም ባደረገ ጊዜም ኩኑም (የዐባይ ጠባቂ) እና ሆፒ (የአባይ መንፈስ) ብለው ያመልኳቸው የነበሩት ሁለት ጣዖታት ኃይል እንደሌላቸው አሳየ። (Myth buster /The read sea crossing / CYCtv Series)

[44] ጌታችን በውኃ ላይ ተአምራት ያደረገው በቃና ብቻ አይደለም። ሲጠመቅ የዮርዳኖስ ውኃ እንዲናወጥና እንዲሸሽ አድርጎታል (መዝ.፻፲፫፥፫) ከዚህ በኋላ ውኃውን እንደ የብስ ተራምዶ ሔዶበታል ፤ ጴጥሮስንም እንዲሔድ አስችሎታል (ማቴ. ፲፬፥፳፱) ፤ የሚናወጠውን የውኃ ማዕበል ጸጥ አድርጎታል (ሉቃ. ፰፥፳፬) ሁለት ጊዜ ከባሕር ውኃ እጅግ ብዙ አሣዎች እንዲያዙ አድርጓል (ሉቃ.፭፥፮፤ዮሐ.፳፩፥፮) ፤ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ከጎኑ ከደም ጋር ውኃ ፈስሶአል (ዮሐ. ፲፱፥፴፬)



Scanned by CamScanner

ያደረገው ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ በራሱ ሥልጣን ነው። የተአምሩን አፈጻጸምም ስንመለከት ሙሴም ጌታችንም ውኃውን የለወጡት በሚመሳሰል መንገድ ነበር። «ሙሴኒ ሜጠ ለማይ እምከዊነ ማይ ኅበ ከዊነ ደም እንዘ ኢይትናገር በአፉሁ ዳዕሙ በህሊናሁ» (ሙሴስ ውኃውን በሃሳቡ እንጂ በአፉ ሳይናገር ውኃ ከመሆን ደም ወደ መሆን ለወጠው።) እንዲል ሙሴ ያለ ንግግር ውኃን ደም አድርጎት ነበር። ጌታችንም ውኃውን ወይን ሲያደርግ ከላይ እንደተመለከትነው በዝምታ ነበር። ሆኖም ሙሴ ውኃውን ደም ለማድረግ ባይናገርም ውኃውን ተአምር እንዲያደርግባት በተሠጠችው በትር መምታት አስፈልጎት ነበር። ጌታችን ግን ውኃን ለሦስት በከፈለበት በዕለተ ሰኞ ሰማይን በሃሳቡ ብቻ በውኃ የሣለ አምላክ ነውና ይህን ውኃ ለመለወጥ በትር አላስፈለገውም።[45]

## ○ ዝምተኞቹ አስተናጋጆች

የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት አገልጋዮች እጅግ አስደናቂ የሆነ ታዛዥነትና ትሕትና ያላቸው ነበሩ። እነዚህ ሰዎች የገሊላ ሰዎች እንደመሆናቸው ጌታችንን ሊያውቁት ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን ጌታችን ከቃናው ሰርግ ቤት በፊት በአደባባይ ተአምራትን አደረገ የሚል ነገር ተሰምቶ አይታወቅም። ከዚህ በፊት በሌላ ሥፍራ ተአምር አደረገ የሚል ዝና ቢሰሙ ኖሮ መታዘዛቸው አያስደንቅም ነበር። ሆኖም በእነርሱ ዓይን ጌታችን የሚታየው

[45] ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ‹ሰማይ› ማለት ‹ሥዕለ ማይ› /የውኃ ሥዕል/ ማለት ነው፣ ሲሉ በዕብራይስጡም שָׁמַיִם /shamayim/ ሺማይም ‹ከውኃ የተገኘ› ማለት ነው።

ዓለምን ለማዳን ሰው እንደሆነ ወልደ እግዚአብሔር ሳይሆን የጠራቢው የዮሴፍና የማርያም ልጅ ሆኖ ነው:: ቅዱስ ሉቃስ «እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ...» በማለት እንደተናገረ (ሉቃ. ፫፥፳፫)

እነዚህ አገልጋዮች እመቤታችን «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ስትላቸው ጌታችንም :- ጋኖቹን እስከ አፋቸው ውኃ ሙሉአቸው» ሲላቸው ‹እነዚህ ገሊላውያን እናትና ልጅ የሚያዞን ምን ነክቷቸው ነው? እናቲቱ ‹ልጄ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› የምትለን ፤ ልጅዋስ መስተንግዶ ትታችሁ ውኃ ቅዱ› የሚለን ለምንድር ነው?» ብለው አልተበሳጩም፣ ጭራሽም አልጠየቁም:: የሰርግ ቤት መስተንግዶአቸውን አቋርጠው ቃል ሳይተነፍሱ ከ፪/ሥራ ሁለት እስከ ዐ/ሥራ ስምንት ጊዜ እንስራ አመላልሰው ጋኖቹን ውኃ ሞሉባቸው::

ያ ዘመን መቼም ውኃ በየቤቱ በቧንቧ እየመጣ የሚቀዳበት ዘመን አልነበረም:: ውኃ የሚቀዳው ከጉድጓድ ነበር:: ጉድጓዱ ከሰርግ ቤቱ አጠገብ ለመሆኑ እርግጠኞች መሆን እንችላለን? ምናልባትም የሰዓታት መንገድም ሊያስኬድ ይችላል:: የውኃ ጉድጓዱም ጠላት መርዝ እንዳይጨምርበት በመሥጋት በትልቅ ድንጋይ ይዘጋ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናልና እሱን ማንሣትም ሌላ ሥራ ነው:: (ዮሐ.፬፥፪ ፤ ዘፍ. ፳፱፥፫)

ጌታችን ውኃውን እንዲሞሉ ብቻ ነግሯቸው አላቆመም:: ወንጌሉ ቃል በቃል እንዲህ ነው የሚለው «ኢየሱስም:- ጋኖቹን ውኃ <u>ሙሉአቸው</u> አላቸው። እስከ <u>አፋቸውም ሙሉአቸው</u> አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው።» አገልጋዮቹ «ይኸው ሞላነው አይደል ፤ እስከ አፉ ድረስ መሙላት ምን ያስፈልጋል?» ብለው አልተከራከሩም ፤ አላጉረመረሙም:: የሚገርመው ደግሞ ከመካከላቸው ጌታችንን «ምን ልታደርግ

አቅደህ ነው?» ብሎ እንኳን የጠየቀው የለም፡፡ ሙሉ ተባሉ ሞሉ ፣ እስከ አፉ ድረስ ሙሉ ተባሉ እስከ አፉ ድረስ ሞሉ፡፡

መንፈሳዊ ሥራ ገና ሳይጀመር ‹ያስኬዳል አያስኬድም› በሚል ውዝግብ በሚከሸፍበት በእኛ ዘመን የቃናዎቹን አገልጋዮች ስናያቸው እጅግ እንደነቃለን፡፡ ሁሉን የሚያከናውነው እግዚአብሔር መሆኑ ተዘንግቶ አገልጋዮች አንድ አገልግሎት ‹ሊሳካ አይችልም› የሚል ሥጋት ላይ ብቻ ሲያጠነጥኑ ፣ መረጃ ሲያሰባስቡ ጊዜ በሚያጠፉበት በእኛ ዘመን እንደ ቃና ዘገሊላ አገልጋዮች ያለ ሳይጠይቅ የሚሠማራ አገልጋይ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ታዛዥነታቸው ጋር የበለጠ አስደናቂው ነገር ለአሳዳሪው ወስደው መሥጠታቸውም ነው፡፡ እስቲ ልብ ብለን እናስበው፡፡ እነዚህ አገልጋዮች ውኃ ሙሉ ተብለው ሞሉ፡፡ በጋኑ የሞሉትን ውኃ ሳይነካው ፣ ሳይጸልይበት ፣ ሳይባርከው ባለበት ሆኖ «አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ሥጡት» ሲላቸው ምን ይሰማቸው ይሆን? ውኃውን የሞሉት በድንጋይ ጋን እንጂ በጠርሙስ ባለመሆኑ /እስከ አፉ በመሞላቱ ሊያዩ ይችሉ ካልሆነ በቀር/ የውኃውን ወደ ወይን መለወጥ አይተው የሚያረጋግጡበት ዕድል የላቸውም፡፡ ለአሳዳሪው ከመሥጠታቸው በፊት ለመቅመስ እንኳን አልሞከሩም፡፡ «ሥጡት አላቸው ሠጡትም» ይህ እጅግ አስደናቂ የሆነ ታዛዥነት ነው፡፡ አገልጋዮቹ የዛሬ ቢሆኑ ኖሮ ‹ቀድታችሁ ሥጡት› ሲባሉ የመጀመሪያ ጥያቄያቸው «ምኑን? ውኃውን?...ምን አድርግ ብለን እንሥጠው?» የሚል ሳይሆን አይቀርም፡፡



Scanned by CamScanner

## ○ ለአገልጋዮቹ ብቻ የተሠጠ ሽልማት

የቃና ዘገሊላ አገልጋዮች ከላይ የተመለከትነው እጅግ ብዙ በጎ ነገር የተገኘባቸው ታዛዦች ነበሩ። ቅዱስ ጳውሎስ ‹ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ እግዚአብሔር አመፀኛ አይደለም› በማለት እንደተናገረ ጌታ ውለታቸውን አይዘነጋም። (ዕብ.፮፥፲) እናም እነዚህ አገልጋዮች በዚህ ሰርግ ቤት ላሳዩት ቅንነትና ታዛዥነት ምን ተደረገላቸው ቢባል ለማንም ያልተሠጠ ሽልማትን እዚያው ሰርግ ቤት ውስጥ እንዳገኙ በታሪኩ መጨረሻ ላይ እንረዳለን። ይህም ሽልማት ፣ ለተሰበሰቡት ተጋባዦች ፣ ለአሳዳሪውና ለሙሽሮቹ እንኳን ያልተሠጠ ትልቅ ሽልማት ነበር።

ልብ ብለን ታሪኩን ስናነብ ‹አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር› ይላል። ማንኛውም መገለጥ /revelation/ የሚታየው ወይም የሚገኘው በተጋድሎና በሥራ ነው። እነዚህ አገልጋዮች በዚህ ሰርግ ቤት በሠሩት በጎ ሥራ ለማንም ያልተገለጠ የተአምሩ ምሥጢር ለእነርሱ ተገለጠላቸው። ሙሽራውና ሙሽሪቱ አሳዳሪውን ጨምሮ ሁሉም ያደነቁት ወይኑን ቀምሰው አጣጥመው እንጂ ወይን ከመሆኑ በፊት ውኃ እንደነበር አላዩም።

ሙሽሮቹ እንኳን ‹በሰርጋችን ከውኃ የተለወጠውን ወይን ጠጅ ጠጥተን ነበር› ከማለት በላይ ምንም ሊናገሩ አይችሉም። አሳዳሪውም ‹ወደ ወይን ጠጅ እንደተለወጠ መጀመሪያ አምጥተው ለእኔ ሠጡኝ› ከማለት ውጪ በዚያ ሰርግ ቤት ውስጥ እያለ ይህ የወይን ጠጅ ከየት እንደመጣ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም።

ልብ አድርጉ ከወይን ጠጁ ከመቅመሳቸው በስተቀር የዕለቱ ሙሽሮች በሰርጋቸው ላይ ስለተደረገው ተአምር ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እያነበብን ካለነው ሰዎች በምንም አይለዩም። የመረጃ ቅብብሎሽ ሰንሰለቱ ርዝመት ቢለያይም እነሱም እንደኛ ‹ወይኑ ውኃ እንደነበር› ሰምተው ነው እንጂ አላዩም። እዚያው ሰርግ ቤት ቁጭ ብለው ይህን ለዘመናት የሚወራ የአምላክን ድንቅ ሥራ ሳያዩ ቀርተዋል።

በዚያ ሰርግ ቤት ውኃውንም ወይኑንም አይተው የ‹ከተአምር በፊትና በኋላ› ምስክርነት መሥጠት የሚችሉት ውስጥ አዋቂ የጌታ ምሥጢረኞች በትሕትና ተመላልሰው ውኃ የቀዱት ታዛዥ አገልጋዮች ናቸው። እነዚህ የቃና ዘገሊላ አስተናጋጆች ቀሪ ዘመናቸውን እንዴት እንዳሳለፉና የሰማይ ዋጋቸው ምን እንደሆነ ባናውቅም ፍጹም ታዛዥነታቸው ግን በቃና ቤተልሔም ምሥጢር ያዩ ዲያቆናት አደረጋቸው።[46]

○ <u>መልስ ያልተገኘላቸው ሁለቱ ጥያቄዎች</u>

የሰርግ ቤቱ አገልጋዮች ውኃውን ከሞሉ በኂላ ‹ውኃው ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠው መቼ ነው?› እና ‹እንዴት ሆኖ ተለወጠ?› የሚሉት ሁለት ጥያቄዎች በዚህ ሰርግ ቤት ታሪክ ላይ ያልተጻፉ መልስ ያልተገኘላቸው ነገር ግን ሊስተዋሉ የሚገባቸው ሁለት ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች በተናጠል እንመልከታቸው።

---

[46] የዮሐንስ ወንጌል በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ‹አገልጋዮች› የሚለው ዲያቆናት διάκονος (diakonos) ይላል።



Scanned by CamScanner

የመጀመሪያው ተአምሩ መቼ ተከናወነ የሚለው ነው፡፡ ታሪኩን ስናነብ ጌታችን ውኃ ሙሉ ካላቸው በኋላ ‹አሳዳሪውም ወይን የሆነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ› ብሎ በሓላፊ ግሥ ትረካውን ይቀጥላል እንጂ ‹የሞሉት ውኃም ወይን ሆነ› ብሎ አይናገርም፡፡ ውኃ ሞሉ ካለ በኋላ የውኃውን ወይን መሆን ሳይናገር ‹ወይን የሆነውን ውኃ› የቀመሰውን አሳዳሪ መደነቅ ይናገራል፡፡ መጽሐፉ ያተኮረው ከተአምሩ አፈጻጸም ይልቅ ወደ ተአምሩ ውጤት ነበረ፡፡ ‹አሁን ቀድታችሁ ሥጡት› የሚለው ትእዛዝ ግን ጌታችን ውኃውን ወይን ለማድረግ ጊዜ እንዳልፈጀበት ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ያልተገለጠ ምሥጢር ውኃው በምን መልኩ ወደ ወይንነት እንደተለወጠ ነው፡፡ በውኃ ላይ እንደ መሔድ ፣ ማዕበልን እንደ መገሠፅ ወዘተ ባሉ በጌታችን የተፈጸሙ ተአምራት ላይ በየጊዜው የሚነሡ የሳይንስ ሰዎች የ‹እንዴት ሊሆን ቻለ?› ሳይንሳዊ ትንታኔ ለመሥጠትና [47]ማንም ሰው ሊያደርገው የሚቻለው ተራ ነገር እንደሆነ ለማሳመን ይሞክራሉ፡፡ እኛ ግን ‹ከግብር ገብተን› በፈጣሪ ሥራና ተአምራት ላይ እንዳንመራመርና ‹ማሰብ ከሚገባን አልፈን በትዕቢት እንዳናስብ› ፈሪሐ እግዚአብሔር ይከለክለናል፡፡ /ሮሜ ፲፪፥፫/

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ባስተማረበት ስብከቱ እንዲህ ብሏል

[47] አንዳንድ የሳይንስ ሰዎች ‹ውኃን ወደ ወይን እንዴት መለወጥ ይቻላል?› ለሚለው መልስ የሚሠጥ ቀመር አለን ብለው ሲያስተዋውቁ ይታያል፡፡ ይህም Sodium Hydroxide + phenolphthalein + Hydrochloric acid የተሰኙትን ንጥረ ነገሮች ከውኃ ጋር በመጠቀም ነው፡፡ ይህ ሳይንሳዊ ሙከራ ግን ውኃን ወደ ቀይ ቀለም ከመቀየርና ቀይ ቀለምን መልሶ ወደ ውኃ ከመቀየር ውጪ ከወይን ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ በዚህ ሙከራ ሒደት ወደ ቀይነት የሚለወጠው ውኃም እንኳንስ ወይን ሆኖ ሊጠጣ ይቅርና ሙከራው በሚካሔድበት ወቅት እንኳን የእጅ ጓንት በማድረግ ጥንቃቄ ካልተደረገ በስተቀር ቆዳን ሊበጣጥስ የሚችል አደገኛ ፈሳሽ ነው፡፡ /How to Turn Water into Wine. /www.goscience.com/ www.about.com/

«ጌታ ሐዋርያቱ በተሰበሰቡበት ቤት ውስጥ በሮቹ ዝግ ሆነው ሳለ እንደገባ ከቅዱሳት መጻሕፍት ተረድቼአለሁ:: ‹እንዴት ሊድርጎ ገባ?› የሚለውን ግን እስካሁን ድረስ አልተማርሁም:: ያልተቀበልሁትን ነገር ደግሞ ልናገር አልሞክርም:: በተዘጋው ደጅ የገባውን ጌታችንን አወድሰዋለሁ:: ስለ አገባቡ ግን ለማወቅ ጓጉቼ አልመራመርም:: በፈጸማቸው ልዩ ልዩ ተአምራቱ እደነቃለሁ:: እንዴት እንደተፈጸሙ ግን ለማብራራትና ዝርዝር ትንታኔ ለመሥጠት አልሻም:: እኔ የጌታዬን ተአምራት በአድናቆት የምሰማ ባሪያው ነኝ እንጂ የአምላኬን አሠራር የምዳኝ ዳኛ አይደለሁም::» (ቅዱ.ዮሐ.አፈ./በእንተ ቅዱስ ቶማስ ሐዋርያ/ On The Holy Apostle Thomas)

## ○ ጌታችን ውኃን ወይን የማድረጉ ዓላማ ምን ነበር?

ጌታችን በቃና ዘገሊላ ውኃውን የወይን ጠጅ ያደረገው ለምንድር ነው? ብለን ስንጠይቅ በታሪኩ ላይ በግልጽ የሚታዩ ምክንያቶች አሉ:: የተወደደች እናቱን ጥያቄ መመለስ ፣ ሙሽሮቹን ከሚደርስባቸው ውርደት ማዳን ፣ ክብሩን መግለጥና ደቀመዛሙርቱ እንዲያምኑ ማድረግ ናቸው:: ስለዚህ በጌታችን ተአምር ውስጥ የወይን ጠጁ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ የሚያደርስ መሣሪያ ነበር እንጂ ወይን ጠጁ ራሱ ዓላማ አልነበረም::

ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸውም ጌታ ውኃን ወይን ማድረጉ ክብር ይግባውና ስካርን ለሚወዱ ፈቃድ ለመሥጠትም አይደለም::[48] መንፈሳዊ ልቡና ያለው ሰው የሚታየው አምላክ ጣዕም የሌለውን ነገር ጣዕም የሚሠጥ ቸር መሆኑ ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይላል

[48] አንድ ከስካር ዓለም ወደ መንፈሳዊነት ተመልሶ ቤተሰቡን በአግባቡ ማስተዳደር የጀመረ ሰው የቀድሞ የመጠጥ ቤት ወዳጆቹ ‹ክርስቶስ ውኃን ወይን ጠጅ አድርጎ የለ ወይ?› ብለው ሊያሳምኑት ሲሞክሩ ‹አዎን ውኃን ወይን ጠጅ አድርጎ ነበር ፤ አሁን ደግሞ አጠጣ የነበረውን የወይን ጠጅ ወደ ልጆቼ ምግብና ልብስ ለውጦታል› ብሎ እንደረታቸው ይነገራል::

«አንተ የምትፈልግ ከሆነ ጌታችን ያን ጊዜ ያደረገውን ተአምር አሁንም ሊያደርግልህ ይቻለዋል። አሁንም ውኃን ወይን ማድረግ ይችላል። የበለጠ የሚያስደንቅ ነገር የሚሆነው ግን ይህንን ዕረፍት ያልሠጠህንና ለጥፋት የሚዳርግህን (ጊዜያዊ) ደስታህን ፣ የያዘህን የፍትወት ቆፈን ወደ ጋለ መንፈሳዊነት ሊለውጥልህ መቻሉ ነው። ውኃን ወይን ማድረግ ማለትም ይኼ ነው።» (ቅዱ.ዮሐ. አፈ ፲ Homily 12 On Colossians)

**በሌላ ሥፍራም ይኸው ባለ ወርቅ ልሳን ቅዱስ ዮሐንስ** «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ውኃን ወይን አድርጓል። ያኔም አሁንም ደካማና ያልሰከነ ፈቃዳችንን ለመለወጥ አይታክትም። ከውኃ በምንም የማይለዩ ሰዎች አሉ። የቀዘቀዙ ፣ (በተቀደደላቸው የሚፈስሱ) ደካሞችና ያልተረጋጉ ሰዎች! እነዚህን ሰዎች ይለውጣቸው ዘንድ ወደ ጌታችን እናምጣቸው።» **ብሏል።** (Homily XXII. John ii.4) **ስለዚህ በጌታ ተአምር ላይ የድፍረት ንግግርን ከመናገር ይልቅ** ‹ውኃ የሆነ ሕይወቴን እንደ ወይን የጣፈጠ አድርግልኝ› **ብሎ መጸለይ ይሻላል።**

**ቅዱስ ጳውሎስ** «እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።» **በማለት እንደተናገረው መብልና መጠጥ ለእግዚአብሔር ክብር እስከሆነ ድረስ አይወገዝም።** «ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።» **ከሚለው ዐረፍተ ነገር እንደምንረዳው የቃናው ወይን ጠጅ ለእግዚአብሔር ክብር መገለጫ የዋለ ነበር።** (፩ቆሮ. ፲፥፴፩)

**ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሣው ጥያቄ** «ጌታችን ውኃውን ወይን አድርጎ በሠጠበት ወቅት የሰርግ ቤቱ ታዳሚዎች ሰክረው ነበር። (አሳዳሪው ከሰከሩ በኋላ መናኛ መቅረብ ነበረበት እንዳለ) ታዲያ ለሰከሩ ሰዎች የወይን ጠጅን መሥጠቱ የበለጠ እንዲሰክሩ የሚያደርግ አይሆንም ወይ?» **የሚል ነው። ይህንን ጥያቄ በአጭሩ ስንመልሰው ጌታችን በሰርግ ቤቱ ስድስት ጋን ሙሉ የወይን ጠጅ የሠጠው ጠጥተው የሰከሩ**

ሰዎች በስካር ላይ ጨምረው ይስከሩ ብሎ ሳይሆን በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደተመለከትነው የአይሁድ የጋብቻ በዓል ለሰባት ቀናት የሚቆይ ስለሆነና በዚህ ሰርግ ቤትም የሚቀሩ የግብዣ ቀናት ስላሉ ነው።

### ○ ጌታችን በዚህ ሰርግ ቤትም ሆነ በሌሳ ሥፍራ የወይን ጠጅን ጠጥቶ ያውቅ ይሆን?

ጌታችን በቃና ሰርግ ቤት ከተአምሩ በፊት ወይም በኋላ ወይን ጠጅ እንደጠጣም እንዳልጠጣም የሚያሳይ በግልጽ የተጻፈ ነገር የለም። ሆኖም ወደ ሰርጉ ታደመ ስለሚል ተጋባዥ ሊሆን ከፈቀደ ከምግብና መጠጡ አልታደመም ለማለት ያስቸግራል። ራሱ የለወጠውን የወይን ጠጅ ስለመጠጣቱ በታሪኩ ላይ በግልፅ የተጻፈ ምንም ነገር የለም። ‹ለአሳዳሪው ሥጡት› አለ እንጂ ወደ እኔ አምጡት እንዳለም አልተጻፈም። ሆኖም ‹ለአሳዳሪው ሥጡት› ማለቱ መጀመሪያ ለአሳዳሪው ሥጡት ማለቱ ነው እንጂ ለቀረው ታዳሚ እንዳትሠጡ ማለት ስላልሆነ ለእርሱ እንዳልቀረበለት አያሳይም። ሃይማኖተ አበው በተሰኘው መጽሐፈ ሊቃውንት እንደተመዘገበው ሰኑትዩ የተባለ ሊቅ «ወለህላዌ ማየ ቃናሂ ረሰዮ ወይነ ሠናየ ወጥዑመ ፤ ወሰትየ እምኔሁ በፈቃዱ እንዘ አልቦ ዘይኤዝዞ» «የቃናን ውኃ ባሕርይም ያማረ የጣፈጠ ወይን አደረገው ፤ ግድ ያለው ባይኖርም ከእሱ ጠጣ» ብሏል። (ሃይ.አበ. ዘሰኑትዩ ፻፲፥፵፰)

ጌታችን ወይን ጠጥቶ ያውቅ ይሆንን በሚለው ጉዳይ ላይ የሀሳብ ልዩነት ያላቸው አሉ። በዘኍ ፮፥፩ ፡- ላይ ናዝራዊያን ስእለት ስላለባቸው ወይን

አይጠጡም ተብሏል፡፡ ይህን ይዘው አንዳንዶች ጌታችን [49]ናዝራዊ ነው ወይን አልጠጣም ይላሉ፡፡ ሆኖም ጌታችን እንዲህ ብሏል፡፡ ‹‹ መጥምቁ ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላ የወይን ጠጅም ሳይጠጣ መጥቶ ነበርና። ጋኔን አለበት አላችሁት። የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቶአልና። እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ አላችሁት። ›› (ሉቃ. ፯፥፴፬) በዚህ ጥቅስ ጌታችን ‹ወይን ጠጅ ጠጪ› ያሉት ‹እየበላ እየጠጣ› ስለመጣ መሆኑን መንሥኤና ውጤት /cause & effect/ አድርጎ በግልጥ አስቀምጦታል፡፡

ይህ ሲባል ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹ወይን ጠጅን እንደ ርኩስ ነገር አልቆጠረም› ለማለት ነው እንጂ ክብር ይግባውና አይሁድ በድፍረት ‹በላተኛና ጠጪ» ያሉትን ፅርፈት /ስድብ/ እንደ ማስረጃ ተቀብለን አይደለም፡፡ እንደ ምስክርነት የምንወስደውም የአይሁድን የድፍረት የዘለፋ ንግግር ሳይሆን ጌታችን ‹እየበላ እየጠጣ ስለመጣ› ብሎ የተናገረውን ብቻ ነው፡፡ ‹ይበላ ነበር› በማለትና ‹በላተኛ ነው› በማለት ፣ ‹ይጠጣ ነበር› በማለትና ‹ጠጪ ነው› በማለት መካከል እጅግ ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ ጌታችን እንደ ሰውነቱ በመጠን ይበላ ይጠጣ ነበር እንጂ ክፉዎች አይሁድ በስድብ እንደተናገሩት በላተኛና ጠጪ አልነበረም፡፡ «በስግብግቦች ዘንድ እንደ በላተኛ ተቆጠረ ፤ በሚያውቁት ዘንድ ግን እርሱ

[49] ጌታችን ናዝራዊ የተባለው በናዝሬት ስላደገ ነው እንጂ እሱ የወጣው /የተወለደው/ በትንቢቱ መሠረት ከይሁዳ ቤተልሔም ነበር፡፡ ናትናኤል ‹ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?› ብሎ ግራ የተጋባውም ትንቢቱን ስለሚያውቅ ነበር፡፡ /ዮሐ. ፩፡፵፯/



Scanned by CamScanner

የሁሉ መጋቢ ነው፡፡ በሰካራሞች ዘንድ እንደሚጠጣ ተቆጠረ ፤ በሚያስተውሉት ዘንድ ግን እርሱ የሁሉን ጥም የሚያረካ ነበር፡፡›[50] እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም፡፡

## ○ የወይን ጠጅ ወይስ የወይን ጭማቂ

አንዳንድ የፕሮቴስታንት ጸሐፊዎች ‹መጠጥ አያስፈልግም› ለማለት ጌታችን በቃና ዘገሊላ *‹ውኃውን የለወጠው አልኮልነት ወዳለው ወይን ሳይሆን ወደ ወይን ጭማቂ ብቻ /Grape Juice or unfermented wine/ ነው›* ብለው ለማስተባበል ይሞክራሉ፡፡ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በማያሻማ ሁኔታ ‹የወይን ጠጅ› ተብሎ ስለተቀመጠ ሌላ ትርጓሜ አያስፈልገውም፡፡ ወንጌሉ በጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ግን ኦይኖስ /oinos/ ተብሎ የተጻፈ ሲሆን ይህ ቃል ለጭማቂም ለጠጅም /unfermented and fermented wine/ የሚሆን ለትርጉም አሻሚ ቃል ነው፡፡ በግእዝና በሌሎች ቋንቋዎችም እንዲሁ «ወይን አደረገው» ብቻ ስለሚል ሌላ ማብራሪያ መሥጠት ያስፈልጋል፡፡ መጠጥ ላይ ሊኖር ስለሚገባ አመለካከት [51]የጠራ ትምህርት ያላት ቤተ ክርስቲያናችን ግን አትስከሩ ትላለች እንጂ ሰዎችን ከመጠጥ ለማሸሽ ብላ በሰርግ ቤት ‹የወይን ጭማቂ ተሠጠ›

---

[50] "By the greedy, He was considered a glutton, but by those who know, The provider of all. By the drunk, He was considered a drinker, but by the discerning, The Giver of drink to all" /Harp of the Sprit /Hymn On The Resurrection 17/

[51] ስለ መጠጥና ተያያዥ ጉዳዮች በዝርዝር ለማንበብ የዲ/ን ኅብረት የሺጥላን /አሁን ቀሲስ/ ‹ሕይወተ ወራዙት› ክፍል ሁለት መጽሐፍ ይመልከቱ፡



Scanned by CamScanner

አትልም:: የወይን ጭማቂ አለመሠጠቱን የሚሳየን እዛው ሰርግ ቤት ውስጥ አሳዳሪው የሠጠው ምስክርነት ነው::

አሳዳሪው ወይኑን ሲያደንቅ «ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።» ይላል:: ይህ አነጋገር የሚያሳየው ሰዎቹ አስቀድሞ የጠጡት ወይን የሚያሰክር እንደነበር ነው:: ሁለተኛው ወይን ደግሞ ከመጀመሪያው የተሻለ «መልካም የወይን ጠጅ ነው» ሌሎች እንደሚሉት ጌታችን የሠጠው የወይን ጭማቂ ቢሆን ኖሮ አሳዳሪው በማድነቅ ፈንታ «ወይን ጠጁ አልቆ ነው እንዴ ጭማቂ የምታቀርቡት?» ብሎ ይጠይቅ ነበር እንጂ ከወይን ጠጁ አስበልጦ ጭማቂ አያደንቅም ነበር:: ስለዚህ ጌታችን በቃና የሠጠው በተአምር ሒደቱን የጨረሰ አልኮልነት ያለው መጠጥ /fermented beverage/ ነው::

ሌሎች ጸሐፊዎች ደግሞ «በሰርግ ቤቱ አስቀድሞ የቀረበውም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ በእስራኤላውያን ታሪክ ወይን ተብሎ የተጻፈው ሁሉ አልኮልነት የሌለው የወይን ጭማቂ ነበር ፤ [52]ሰርጉ ለሰባት ቀን የሚቆይ እንደመሆኑ ወይኑ አንድ ቀን በቆየ ቁጥር እየፈላ ስለሚሔድ የጭማቂ ለዛውን እያጣ ይመጣል:: ጌታችን የሠጠው ወይን አዲስ ጭማቂ ሲሠጥ አሳዳሪው ያነጻጸረው

---

[52] ይህን ሃሳብ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 118ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዋድሮስም ይጋሩታል:: ግንቦት 2014 ‹የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት› በሚል ርዕስ ባስተማሩት ትምህርት ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ወይን የተባለው አልኮልነት የሌለው የወይን ጭማቂ ስለመሆኑ አበክረው ተናግረዋል:: ይሁንና ብዙ ጸሐፊዎች የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይህን አቋም የያዘችው ከጥቂት ከፍለ ዘመናት ዓመታት ወዲህ በገጠማት የአረብ ባሕል ተጽዕኖ አንጻር እንደሆነ ይተቻሉ:: ይህ ‹የወይን ጭማቂ›ን ሕልውና ብቻ የሚያቀነቅን ሃሳብም በግብጽ የተጋደሉ አበው መነኮሳትን ሕይወት በሚያሳዩት እንደ መጻሕፍተ መነኮሳት ባሉ መጻሕፍት ላይ መነኮሳት የወይን ጠጅን ለመሸሽ ያደረጉትን ተጋድሎ የሚመለከቱ ታሪኮችን ሁሉ ዋጋ የሚያሳጣ ነው:: ምክንያቱም ሊያሰክር የማይችልን የወይን ጭማቂ መሸሽ ያን ያህል ሥፍራ ተሠጥቶት የሚነገር ስላልሆነ እና ታሪኮቹ በተመዘገቡባቸው በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ስለ ወይን ጠጁ የሚያሰክር መሆን በግልጽ አብሮ የተመዘገበ በመሆኑ ነው:: (ፊልክ.፱ ፤ ፲፱) የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በተጨማሪ ለምሥጢረ ቁርባን የሚሆነው ወይን ደግሞ እንደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በአዲስ ወይን ፍሬ /ሉቃ. ፳፪፥ ፲፰/ ሳይሆን ተጠምቆ ሒደቱን በጨረሰው መሆን አለበት የሚል ሥርዓት አላት::



Scanned by CamScanner

በመቆየት ምክንያት አዲስ ጭማቂ የመሆን ለዛውን ካጣው ወይን ጋር ነው›› [53] ብለው ይከራከራሉ፡፡ ይህ መከራከሪያ ከላይኛው የተሻለ ቢመስልም ግን ከቃናው አሳዳሪ ንግግር ውስጥ ግን ‹ከሰከሩ በኋላ መናኛውን አቀረባችሁ› የሚለው ንግግር ያከሽፈዋል፡፡ ምክንያቱም በሰርጉ ቤት መጀመሪያ የቀረበውም እንደተባለው ጭማቂ ከሆነ ታዳሚዎቹ መጀመሪያ በምን ሰክረው ነው ጣዕም ለመለየት የሚቸገሩት ያሰኛል፡፡

‹በእስራኤል ዘንድ ወይን የተባለው የማያሰክር ጭማቂ ነው› የሚለውን እና ብዙ የዚህ ሃሳብ ደጋፊዎች በጽሑፎቻቸው ደጋግመው የሚያነሡትን ‹በድሮ ጊዜ የነበረው ወይን በአሁን ዘመን እንደምናውቀው ወይን የማስከር ኃይል አልነበረውም› የሚለውን ሃሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ውድቅ ያደርገዋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወይን የሚለው ቃል የተጻፈው ወይንን ተክሎ ገበሬ መሆን በጀመረው በጻድቁ ኖኅ ታሪክ ላይ ነው፡፡ ‹የድሮ ዘመን› ተብሎ የሚነገረው ዘመን እንግዲህ መቼም ከኖኅ ዘመን ሊቀድም አይችልም፡፡ ይህ [54]ጻድቅ ኖኅ ሰው ከወይን ጠምቆ ጠጥቶ ዕርቃኑን ጥሎ እንደሰከረ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ቅዱስ አንብሮስ የተባለው ሊቅ እንዲያውም ‹የጥፋት ውኃ ያላሰጠመውን ኖኅ ፤ አንዲት ጽዋዕ የወይን ጠጅ አሰጠመችው› ብሎ የስካርን ክፋት ታዝቧል፡፡ ታዲያ ወይን ጠጅ በቀድሞው ዘመን የማስከር ኃይል

---

[53] *Difficulties in the Bible* / R. A. Torrey/ pg 53

[54] በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ውብ ትርጓሜ ጻድቁ ኖኅ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ኖኅ የጠጣው መጠጥ ጌታ ስለሰው ልጆች የጠጣው ‹የሞት ጽዋ› ምሳሌ ነው፡፡ ኖኅ ሰክሮ ዕርቃኑን እንደጣለ ጌታም በሰው ልጆች ፍቅር ‹ሰክሮ› ዕርቃኑን ተሰቅሏል፡፡ በኖኅ ዕርቃን ላይ ካም እንዳፌዘ በጌታችን ላይም አይሁድ ዕርቃኑን ሰቅለው አፌዘውበታል፡፡ ሴምና ያፌት የኖኅን ዕርቃን አናይም ብለው እንደሸፈኑ ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትም ብርሃን ያለበሳቸውን ጌታ ዕርቃኑን ላለማየት ጨልመዋል ፣ ደም ሆነዋል፡፡ ‹‹ፀሐይ ጸልመ ወወርኀ ደመ ኮነ ፤ ወከዋክብት ወድቁ ፍጡነ ፤ ከመ ኢይርአዩ ዕርቃኖ ለዘአልበሰሙ ብርሃነ›› እንዲል (አሴብሕ ጸጋከ)

ያልነበረው ከሆነ ይህ ሐትውልዱ ጻድቅ የነበረ ሰው፣ ዕርቃኑን የጣለው የወይን ጭማቂ ጠጥቶ ነበር ማለት ይቻላል? በወይን ጠጅ ምክንያት ስለሚከሰት ኃጢአትና ስንተትስ መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ የሚናገረው የአልኮልነት ኃይል ስለሌለው ስለማያሰክር መጠጥ ነው? በማያስኬድ ትምህርት ከመድከም መጠጥን ከስካር ለይቶ ማስተማር ይበጃል።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስካርን እንጂ የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆነውን የወይን ጠጅ አያወግዝም። ከርዕሳችን ብዙ ላለመውጣት ከሐዲስ ኪዳን ብቻ አንድ ምሳሌ እንኳን ብንመለከት የተወገዘው ያለ መጠን መጠጣትና ስካር እንጂ የወይን ጠጅ እንዳልሆነ እንገነዘባለን።

ቅዱሳን ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት በበዓለ ጰራቅሊጦስ ሰዎች እያፌዙባቸው «ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል» ሲሏቸው ቅዱስ ጴጥሮስ የመለሰው ‹‹ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤›› ብሎ ነበር። (ሐዋ.፪፥፲፭) በዚህ አነጋገሩ አልሰከሩም ለማለት እንደ ማስረጃ ያቀረበው ሰዓቱ ከቀኑ ሦስት ሰዓት መሆኑን ነበር። ይህ ማለት ሐዋርያቱ በስካር መከሰሳቸውን ተገቢ ነው ብሎ ሳይሆን ሰዓቱ ወይን ጠጅ የማይጠጣበት [55]ማለዳ መሆኑን ለመግለጽ ነበር።

ሌሎች እንደሚሉት ወይን የተባለው የረከሰ ነገር ወይንም ፈጽሞ ሊያሰክር የማይችል ነገር ቢሆን ኖሮ ምላሹ ወይ ‹እንዴት የረከሰን ነገር ይጠጣሉ ትላላችሁ?» የሚል ነው ፤ አለዚያም ደግሞ «እንዴት ያሰክራል ትላላችሁ?› የሚል

[55] ‹ወይን ጠጅ የሌለበት ገበታ ቁርስ ተብሎ ይጠራል› ("A meal without wine is called breakfast") የሚል ታዋቂ አባባልም አለ።



Scanned by CamScanner

ይሆን ነበር። ይኸው ሐዋርያ በመልእክቱ ‹የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም <u>ያለ ልክም በመጠጣት</u> ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና።› በማለትም ጽፏል። በዚህም ሥፍራ ያወገዘው ያለ ልክ መጠጣትን እንጂ መጠጣትን አይደለም። (፩ጴጥ. ፬፥ ፫)

# ምዕራፍ አምስት

## ከተአምር በኋላ

አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ ሰው ሁሉ አስቀድሞ
መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤
አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።
ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤
ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።
ዮሐ.፪፥፲-፲፩

### ፩. የአሳዳሪው ምላሽ

○ **አሳዳሪ ማለት ምን ማለት ነው?**

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ጌታ ውኃውን የወይን ጠጅ ባደረገበት ዕለት ይህንን የወይን ጠጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀመሰው የሰርግ ቤቱ አሳዳሪ /ሊቀ ምርፋቅ/ ነበር።[56] ጌታ በቸርነቱ ያደረገውን የመጀመሪያ ተአምር ቀምሶ ‹ቸር

---

[56] መጽሐፉ በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ባሕልም አሳዳሪን ለግብዣ መመደብ እስከአሁን የተለመደ ሥርዓት ሲሆን አሳዳሪም በግሪኩ ‹Architrivlioncs› ይላል።

እንደሆነ› ለመመስከርና ‹ቅመሱ እዩ› ብሎ ለሌሎች ለመሥጠት በታደለው በዚህ የሰርግ ቤት አሳዳሪ ምንነትና ማንነት ላይ በተለያዩ መጻሕፍት ሁለት ዓይነት ሃሳብ ይስነዘራል፡፡

የመጀመሪያው ሃሳብ የሰርግ ቤት አሳዳሪ የሚሆነው ይህ ሰው ‹ከእንግዶቹ መካከል በራሳቸው በእንግዶቹ የተመረጠ ሰው ነው› የሚል ሲሆን የሥራ ድርሻውም ለእያንዳንዱ ተጋባዥ በአግባቡ ምግብና መጠጥ መቅረቡን መከታተል ነው፡፡ ለወደደውም ዮሴፍ ለብንያም እንዳደረገው የምግቡን ፈንታ ከፍ ሊያደርግለት ይችላል፡፡ (ዘፍ. ፵፫፥፴፬) በአጭሩ አሳዳሪው በተጋባዦቹ ተመርጦ ከተጋባዦቹ ወገን ሆኖ እዚህ ጋር እንዲህ ይቅረብ እያለ የሚያዝ ነው፡፡

በመጽሐፈ ሲራክ ፴፭፥፩ ላይ ፡- ‹‹አለቃም አድርገው ቢሾሙህ ራስህን አታኩራ ከእነርሱ እንዳንዱ ሁን ፤ ተቀምጠህም ፍረድላቸው››[57] የሚለውን ብዙ ጸሐፍት ለድግስ ቤት አሳዳሪም የተነገረ ነው ብለው ይጠቅሱታል፡፡ በእርግጥም ጥቅሱን ወረድ ብለን ስናነበው አሳዳሪው ሽማግሌ ከሆነ በገበታ መካከል ሊኖረው ስለሚገባ ሥርዓት ፣ ጎልማሳም ከሆነ ምን ማድረግ እንዳለበት ፣ ስለ ሰርግ ቤቱ መሰንቆና ዘፈን ፣ ስለ ወይን መቅረብ ይናገራል፡፡ የእንግሊዝኛው ትርጉም ደግሞ በቀጥታ ‹አለቃ አድርገው ቢሾሙህ› ብቻ ሳይሆን ‹የድግስ/ የበዓል አለቃ አድርገው ቢሾሙህ› ይላል፡፡

---

[57] "Did they appoint you as leader of the banquet? Do not exalt yourself. Among them be as one of them. Take care of them and only then be seated" Wisdom of Sirach 32:1 /**Orthodox Bible**; St. Athnasius Acadamy Septuagint, St. Athnasius Academy of Theology/
"If thou be made the master of a feast, lift not thyself up, but be among them as one of the rest; take diligent care for them, and so it down" /Ecclesiasticus 32:1. The king James Version/ Catholic Bible/



Scanned by CamScanner

ከቃናው ሰርግ ታሪክ አንጻር ስናየው አሳዳሪው ራሱ እንግዳ ነው የሚለው ሃሳብ አሳማኝ ነው። ምክንያቱም አሳዳሪው ወይኑን እንደቀመሰ ለሙሽራው ስለ አዲሱ ወይን በሠጠው አስተያየት ላይ «ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል» ብሏል። ይህ አነጋገር ከቤተሰብነት ይልቅ የአሳዳሪውን እንግድነት የሚያጎላ ነው። በእርሱ አስተሳሰብ መጀመሪያ የቀረበውም ወይን ፣ በኋላም የመጣው ወይን ቤት ውስጥ ተጠምቀው የተቀመጡ ነበሩ። አስተያየት የሠጠው መጀመሪያ ለምን መልካሙን አላቀረብህም? ብሎ ነበር። ይህ አነጋገሩም ይህን አሳዳሪ ጓዳውን ጠንቅቆ ከሚያውቅ ቤተኛ ይልቅ አሁን የመጣ እንግዳ ያሰኘዋል። መቼም ራሱ ደጋሽ ሆኖ እንዲህ ዓይነት አስተያየትን ሲሠጥ አይችልም።

ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ ይህ አሳዳሪ የሥራ ድርሻው እንዳለ ሆኖ ለሙሽራው የቀረበና በሙሽራው የተመረጠ አሳላፊ ነው የሚል ሃሳብ ነው። ያም ሆነ ይህ አሳዳሪ ማለት በሰርግ ቤቱ የእንግዶችን መስተናገድ የሚከታተለውና ሥርዓት የሚያስይዘው ሹም ነው።

### ○ የወይኑ ጠጁ መጀመሪያ ለምን ለእንግዶች አልቀረበም?

ጌታችን ውኃውን ወደ ወይን ከለወጠ በኋላ ለአስተናጋጆቹ ‹ቀድታችሁ ሥጡኝ መጀመሪያ እኔ ልቅመሰው› አላለም። ወይም ደግሞ ‹በሉ ውኃውን ወይን አድርጌዋለሁ



Scanned by CamScanner

፤ አሁን ለሙሽሮቹና ለእንግዶቹ አቅርቡላቸው› አላለም:: ጌታችን ይህንን ቢል ኖሮ አስተናጋጆቹ ያለጥርጥር ያደርጉት ነበር:: ምክንያቱም የቃና አገልጋዮች እንኳን ተአምር አድርጎ አይተውት ቀርቶ ተአምር ከማድረጉም በፊትም ጌታ ከእናቱ ጋር ያዘዛቸውን ሁሉ ያለ ጥያቄ የፈጸሙ ትሑታን ነበሩ:: ሆኖም ጌታችን ‹ተአምር ካደረግሁ የሚከለክለኝ ምን አለ?› ብሎ የሰርግ ቤቱን ሥርዓት ሊያፋልስ አልወደደም::[58] ተአምርን ቢያደርግም ሁሉን ነገር በጸጥታ አደረገው፡ ፡ ‹ተአምር ማድረግ እንጂ ሥርዓትን አያውቅም› የሚል ትችት በማያስከትል ጥንቃቄ ሥርዓቱን ጠብቆ ‹ለአሳዳሪው ሥጡት› አለ:: (ትርጓሜ.ወንጌል) በዚህ አካሔድ የአሳዳሪውም ስሜት ከመጎዳት ተጠብቋል:: ምክንያቱም አሳዳሪው እሱ በሚመራው ድግስ ስለቀረበ አዲስ የወይን ጠጅ ከሌሎች አፍ ቢሰማ ኖሮ መከፋቱ አይቀርም ነበር::

ጌታችን ለአሳዳሪው ሥጡት ያለበት ሌላ ምክንያትም አለ:: በዚህ ሰርግ ቤት የታደሙት ተጋባዦች በመካከላቸው ከሚዞረው አሳዳሪ አንደበት እንደምንሰማው ጠጥተው እንዲያልቅ ባደረጉት የወይን ጠጅ ሰክረዋል:: ከሰከሩ በኋላ ደግሞ ጣዕም ሊለዩ አይችሉምና በዚህ ሰዓት የሚቀርብላቸው አስቀድሞ ከቀረበው ደረጃው የወረደ መናኛ ወይን ነበር:: ውኃም ቢጠጡ ላያመዛዝኑ ይችላሉ:: ታዲያ ጌታችን ከውኃ የለወጠውን ድንቅ የወይን ጠጅ ከሰከሩት ሰዎች ለአንዱ ቢያሠጠውና ቀምሶ ‹ግሩም የወይን ጠጅ ነው› ብሎ ቢያደንቅ አገልጋዮቹ ‹ሐይ ሰካር! መቼም የማያናግረው ነገር የለም::›› ብለው ይሳለቃሉ እንጂ ሊያምኑ አይችሉም::

---

[58] አንዳንድ ሰዎች ሥጦታ ሠጠን ብለው የሰውን ሰርግ በተንዛዛ ንግግር ሲያበላሹና በሁሉ ነገር ላይ ካላዘዝን ሲሉ በሚታይበት ዓለም ላይ ሆነን የጌታችንን አሠራር ስንመለከት የእርሱ አርአያነት በሁሉም ዘርፍ መሆኑን እናደንቃለን::



Scanned by CamScanner

ጌታችን ተአምሩን ሲያደርግ ከሰርግ ቤቱ አስተናጋጆቹን ውኃ እንዳስሞላ አሁን ደግሞ ለተአምራቱ ምስክር ይሆን ዘንድ ሁነኛ ሰው መፈለግ ነበረበት። ይህ ሁነኛ ሰው እስካሁን መጠጥ ያልጠጣና ያልሰከረው አሳዳሪው ብቻ ነበር። አሳዳሪው ሥራውን በአግባቡ እንዲሠራ ሲባል መጠጥ አይጠጣም ነበር። አሁንም አምጥተው ሲሠጡት ‹ቀመሰ› እንጂ ግጥም አድርጎ ጠጣ የሚል አናገኝም። ስለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው ለተአምሩ የታመነ ምስክር ያደረገው ይህን አሳዳሪ ነበር።

## ○ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አሳወቀም!

የሰርግ ቤቱ አሳዳሪ ወይን ጠጁን ያደነቀው እንደቀመሰው ነበር። ብዙ ሰዎች የመጠጥን ኃይለኛነት የሚያደንቁት ጨርሰው ጠጥተው ወደ አናታቸው ሲወጣና ናላቸው ሲዞር ነው። የጌታችን ተአምር ግን እጅግ ድንቅ ነበርና አሳዳሪው ገና እንደቀመሰው አደነቀው። ‹ጥዒሞ አንከረ ሊቀ ምርፋቅ› እንዲል

የበለጠ የሚስደንቀው ነገር አሳዳሪው ወይን ጠጁን ከሁሉ ቀድሞ ይቅመስ እንጂ ከወዴት እንደመጣ ግን አላወቀም ነበር። በመልካሙ የወይን ጠጅ ሲደሰትም ለማመስገን የሔደው ወደ ጌታችን ሳይሆን ወደ ሙሽራው ነበር።

ይህ አሳዳሪ ከፈጣሪ የተሠጠንን ነገር ቀምሰን እየተደሰትን ከማን እንዳገኘነው ግን ለማናውቅ ደካሞች ምሳሌ ሆኖ ይኖራል። በሕይወታችን ውስጥ እግዚአብሔር ውኃን ወደ ወይን እንደ መለወጥ የሚመስሉ ብዙ የቸርነት ሥራዎችን ይሠራልናል። እንደዚህ አሳዳሪ የተደረገልንን እያደነቅን



Scanned by CamScanner

ያደረገልንን ግን የማናውቅ ልንሆን አይገባንም። ሠሪውን ሳያውቁ ሥራን ማድነቅ አለማወቅ ነው።

ዓለማችን ዛሬም ድረስ እንደዚህ አሳዳሪ ወይኑን እያደነቁ ወይኑን ከውኃ የለወጠውን በማያውቁ ተሞልታለች። እንዲያውም የተፈጠረውን ድንቅ ነገር በማየት ‹ለተፈጥሮ ምስጋና ይግባውና!› /"Thanks to nature"/ ማለትም የተለመደ ሆኗል። ፈጣሪን ትቶ ፍጥረትን ብቻ ማመስገን አለማወቅ እንጂ ምን ሊባል ይችላል?

## ○ መልካሙን እስካሁን አቆይተህ መናኛው ለምን አስቀደምክ?

የቃና ዘገሊላው አሳዳሪ ወይን ጠጁን በቀመሰ ጊዜ ጠርቶ ያወደሰው ሙሽራውን ነበር። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳስተዋለው ወንጌላዊው ዮሐንስ በማያውቀው ነገር የተመሰገነው ይህ ሙሽራ ለአሳዳሪው አስተያየት ምን ምላሽ እንደሠጠ አልጻፈልንም፦

«ሙሽራው ለዚህ የአሳዳሪው አስተያየት ምላሽ መሥጠቱ የሚጠበቅ ነገር ነው። ወንጌላዊው ግን የተፋጠነው የበለጠ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ነበርና እነዚህን ነገሮች ብቻ ጽፎ አለፈው። እኛ ልንማርበት የሚያስፈልገን ክርስቶስ ውኃን ወይን ማድረጉንና ወይኑም እጅግ መልካም የወይን ጠጅ እንደነበረ ነው። ስለዚህ ሙሽራው የተናገረውን መጨመር (ለወንጌላዊው) አስፈላጊ መስሎ አልታየውም።» (Homily XXII. John ii. 4)

አሳዳሪው ስለወይኑ ሲያደንቅ ‹ሰው አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል ከሰከሩ በኋላ መናኛውን› አለ። በእርግጥም በድግስ ወቅት መጀመሪያ የሚቀርበው መጠጥ በድግሱ አለ የሚባለው ይሆን ነበር። ከዚያ በኋላ ደግሞ ሰዎች



Scanned by CamScanner

ሰክረው ጣዕም ማገናዘብ የማይችሉ በሚሆንበት ሰዓት ደረጃው ዝቅ ያለውን መጠጥ ማቅረብ የተለመደ ነበር፡፡ በተለይም ለሳምንት በሚዘልቀው የአይሁድ ሰርግ ዘንድ ቀን በጨመረ ቁጥር የሰርግ ቤቱ ምግብና መጠጥ ደረጃ እየቀነሰ መምጣቱ የግድ ነው፡፡

ይህ አሳዳሪ ‹ሰው አስቀድሞ መልካሙን በኋላ መናኛውን ያቀርባል› በማለት የተናገረው ቃል በወቅቱ ስለ ሰርግ ቤቱ ክስተት ይናገረው እንጂ ኃይለ ቃሉ ግን በአጠቃላይ ስለ ዓለም ሊነገር የሚችልም ነው፡፡ ‹አስቀድሞ መልካሙን ነገር› ማቅረብ የሰው ልጅና የዚህች ወረተኛ ዓለም መገለጫ ነው፡፡ በማኅበራዊ ኑሮ ብቻ እንኳን ተርጉመን ብናየው ሰው አስቀድሞ በጎ ማንነቱን ያሳያል፡፡

አዲስ ወዳጅ ስናፈራ በወዳጅነታችን የመጀመሪያ ዕለታትና ሳምንታት ስለዚያ ሰው የምናየው ነገር ሁሉ ፍጹም መልካም ነው ፣ አዲስ ጉርብትና ስንጀምር ጎረቤቶቻችን ሁሉ ሰው ወዳድ ናቸው ፣ አዲስ ሥራ ስንቀጠር ባልደረቦቻችን ሁሉ ቀና ናቸው ፣ አዲስ ትውውቅ ስናደርግ የሚገጥመን ነገር ሁሉ መልካም ሆኖ ይታየናል፡፡

ከጊዜ በኋላ ግን ወዳጅ የተባለው ጠላትነትን ፣ ሰው ወዳድ የመሰሉን ጎረቤቶች አትድረሱብኝ ባዮች ፣ ባልደረቦቻችን ተቀናቃኞች ሆነው ይታዩናል እኛም እንታያቸዋለን፡፡ ይህ ሁሉ ለምን ሆነ ስንል የአሳዳሪው ንግግር ምላሽ ሠጥቶናል «ሰው አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል!» ዓለም ወደ እርስዋ የምትስበን አስቀድማ መልካሙን በማሳየት ነው፡፡ በኃጢአት ስለሚገኝ ጊዜያዊ ደስታ እንጂ ከዚያ በኋላ ስላለው ክፉ ነገር አታሳየንም፡፡



Scanned by CamScanner

የሚያስደንቀው ነጥብ ይህ አሳዳሪ በንግግሩ ላይ ‹መናኛ የወይን ጠጅ› ብሎ የጠራው መጠጥ በሰርግ ቤቱ መልካም የወይን ጠጅ ተብሎ ቀርቦ ሰው ሲስተናገድበት የዋለውን ጠጅ መሆኑ ነው። የፀሐይን ብርሃን ካየ በኋላ የጨረቃን ብርሃን የሚያደንቅ እንደሌለ ይህ አሳዳሪ ጌታችን ከውኃ የለወጠውን መልካም የወይን ጠጅ ሲቀምስ ጠጡ እያለ ለሰዎች ሲጋብዘው የዋለውን የወይን ጠጅ ‹መናኛ› አለው። መልካም መስሎት የኮራበትን ወይን ጠጅ አሁን ደግሞ ‹ለምን መጀመሪያ ላይ ቀረበ?› ብሎ ተቆጨ።

የእግዚአብሔርን ሥራ በወይን ጠጅ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም መንገድ ስንቀምሰው የዚህ አሳዳሪ ቁጭት እንዲቆጨን የሚያደርግ ነው። በአምላካዊ ፈቃድ የተከናወነን ነገር ስንቀምስ በሰው ፈቃድ የጠጣነው ነገር ያስቆጨናል። የእግዚአብሔርን ፍቅር የቀመሰ ሰው እስከ ዛሬ የተጋተው የዓለም ነገር ያስቆጨዋል። ቅዱስ አውግስጢኖስ በንስሓ ከተመለሰ በኋላ «ጌታዬ ሆይ እኔ ከአንተ ጋር ያልነበርሁበት ዘመን ብዙ ነው ፤ አንተ ከእኔ ጋር ያልነበርህበት ዘመን ግን የለም» ብሎ እንደተቆጨ ሁሉ ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ልቡ ዘልቆ ሲገባ እንደ መልካም ወይን ቆጥሮት የነበረው ዓለማዊ ደስታ መናኛ እንደሆነ ይረዳል።

የቅድስናን ሕይወት ጣዕም የቀመሰ የረከሰበት ዘመን ይቆጨዋል ፣ የዝማሬን ቃና የተረዳ የዘፈነበት ዘመን ያንገበግበዋል ፣ የጾምና ጸሎትን ጣዕም ሲቀምስ የስካርና የጥጋብ ዘመኑ ያስቆጨዋል። ‹‹ለካ እስከዛሬ ስጋተው የኖርኩት የዓለም ነገር ሁሉ መናኛ ነበረ? እስካሁን ይህ ጣዕም አምልጦኝ ነበር?›› ይላል። መነኮሳትና ባሕታውያኑ ዓለምን ንቀው የሚመንኑት ፣ የከተማ ኑሮን

ሸሽተው በዱር ገደል የሚኖሩት ፣ የዓለም ጌጥና ውበት የማይደንቃቸው እንደዚህ አሳዳሪ እስከዛሬ የጠጡትን ወይን መናኛ ያደረገ የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለቀመሱ ነው። ምንም መከራ ቢገጥማቸው የማይሰማቸውም ይህንን መንፈሳዊ ጣዕም በልጦ ስለማይታያቸው ነው። አባ ጽጌ ድንግል «በአበባሽ (በልጅሽ) በክርስቶስ (በፍቅሩ) መዓዛ የሰከረ ሰው ፤ በሰማዕትነት አደባባይ ቢቆም እንኳን በድንጋይ መወገር ለእርሱ ገለባ ይመስለዋል ፣ እሳትም ለእርሱ እንደ ቀዝቃዛ የባሕር ውኃ ነው»[59] እንዳለ የእግዚአብሔርን ሥራ የቀመሱ ሁሉ እስከሞት ጨክነው ዓለምን ይንቃሉ። ቅዱስ ኤፍሬምም «ሰማዕታት በእውነት የዚህችን ዓለም ጣዕም ናቁ! ስለ መንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሡ» በማለት የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲቀምሱ የዓለም ጣዕም እንደመረራቸው አስረድቷል። ‹‹ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።›› በማለትም ቅዱስ ጳውሎስ የሰማዩ ወይን የምድሩን የሚያስንቅ ዋጋ ቢከፈልለትም የማይቆጭ እንደሆነ ነግሮናል። /ሮሜ. ፰፥፲፰/

## ፪. የተአምራት መጀመሪያ

### ○ ጌታችን ለምን ተአምራትን አደረገ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው የቃና ዘገሊላውን ተአምር ብቻ አልነበረም። በአራቱ ወንጌላት የተመዘገቡ እጅግ ብዙ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓል። አምነን በስሙ ሕይወትን እንድናገኝ የተጻፉት ብቻ

[59] በመዓዛ ጽጌኪ ለዘበዐውደ ስምዕ ሰከረ ፤ ውግረተ አዕባን ይመስሎ ሐሰረ ፤ እሳትኒ ማየ ባሕር ቈሪረ

ተጻፉ እንጂ በተጨማሪ «በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት» አድርጓል። (ዮሐ.፳፥፴) ጌታችን ተአምራትን የሚያደርገው ሰዎች በአድናቆት እንዲከተሉት ለማድረግ አልነበረም። ተአምራትን የሚፈጽምባቸው በቂ ምክንያቶች ነበሩት። የሚያደርጋቸው ተአምራትም አንዳች ነገር ለማስተማር ወይም ለማስረዳት የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች /methods/ ነበሩ ፤ እንጂ ተአምራቱ በራሳቸው መዳረሻ /ዓላማዎች/ አልነበሩም። ጌታችንና ተአምራቱን የሚመለከተው ርዕሰ ጉዳይ ራሱን የቻለ ሰፊ ጉዳይ ነው። ጌታችን ተአምር አላማው እንዳልሆነና ተአምሩን የሚፈጽምባቸው ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉት የሚከተሉትን ሦስት ምክንያቶች እንደ ምሳሌ እንመልከት።

ጌታችን ተአምር የሚያደርግበት የመጀመሪያው ምክንያት እርሱ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ የተላከው ወልደ መሆኑን ፣ በሕልውና ከአባቱ ጋር አንድ መሆኑን እና ነቢያት የተናገሩለት መሲሁ እሱ መሆኑን ለማስረዳት ምልክት እንዲሆን ነው።[60] ቃሉ እንዲህ ይላል ፡- ‹‹ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራል›› «የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠው ሰው ነበረ» ፤ «እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ ፤ ባደርገው ግን፥ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ» የሚሉት ቃላት ይህንን ያስረዳሉ። (ዮሐ.፭፥፴፮፤ ሐዋ.፳፪፥፳፪፤ዮሐ.፲፥፴፯)

ተአምራቱ እርሱ የሚመጣው መሲህ /ክርስቶስ/ ለመሆኑም ማስረጃዎች ነበሩ። መጥምቁ ዮሐንስ በወኅኒ ቤት ሆኖ እያለ «የምትመጣው

[60] በሌሎች ወንጌላውያን ዘንድ ጌታ የሚያደርጋቸው ድንቅ ሥራዎች ‹ተአምር› ‹ተአምራት› /miracles/ ተብለው የተገለጡ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ግን አንድም ቦታ ተአምር የሚለውን ቃል አናገኘውም። ቅዱስ ዮሐንስ ተአምር በሚለው ፈንታ ‹ምልክት› /Sign/ በማለት ጠቅሶታል።



Scanned by CamScanner

አንተ ነህ ወይንስ ሌላ እንጠብቅ?» በማለት በደቀመዛሙርቱ ወደ ጌታችን ሲልክበት ጌታችን የመለሰው «ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ ደንቆሮችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ» በማለት ተአምራቱን እንደ ማስረጃ በመጥቀስ ነበር፡፡ (ማቴ. ፲፩፥፬) ጌታችን በውኃ ላይ ሲሔድና ነፋስን ሲገሥፅ ያዩ ደቀመዛሙርቱም ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን በተአምሩ ተረድተው «በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብለው ሰግደውለት ነበር፡፡ (ማቴ. ፲፬፥፴፫)

ጌታችን ተአምራትን የሚፈጽምበት ሌላው ምክንያት ለሚያስተምረው ትምህርት መንገድን ለመክፈት ነበር፡፡ ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ዓሣና እንጀራን አበርክቶ ከመገባቸው በኋላ ‹ለሚጠፋ መብል አትሥሩ› ብሎ ስለ ሕይወት እንጀራ ስለሥጋ ወደሙ በሰፊው ያስተማረበት ተአምር ነው፡፡ (ዮሐ. ፮፥፳፯)

ተአምር የሚደርግበት ሦስተኛው ምክንያት ከአምላካዊ ቸርነቱና ርኅራኄው የተነሣ ነው፡፡ ይህን የምንረዳው ያደረጋቸውን ተአምራት አንድ በአንድ እየነጠልን በዚህ መነጽር ከተመለከትናቸው ነው፡፡ ሕዝቡን የመገበው ተርበው አይቶ ስለራራላቸው ፣ ወይን ጠጅን የሠጠው በሰርጋቸው ዕለት እንዳያዝኑ አስቦላቸው ፣ ድውያኑን የፈወሰው ‹ብዙ ዘመን እንዲህ እንደነበሩ አውቆ ፣ ሙታንን ያስነሣው የቤተሰቦቻቸውን መራር ኀዘን ተመልክቶ እያልን ማለት ነው፡፡ ይህም ተአምራቱን መፍቀሬ ሰብእ /ሰውን ወዳጅ/ የመሆኑ ማሳያ ያደርገዋል፡፡



Scanned by CamScanner

[61]አንዳንዶች ክብር ይግባውና ጌታችን ተአምራትን የሚያደርገው ‹በተአምር እየደለለ ተከታይ ለማፍራት› እንደነበር አድርገው በድፍረት ይናገራሉ፡፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ስንሔድ ግን ከላይ ከተመለከትናቸው መንፈሳዊ ዓላማዎች ውጪ ጌታችን ‹በተአምር አምናችሁ ተከተሉኝ› ሲል አናገኘውም፡፡ እንዲያውም ያዩአቸው ተአምራት አልበቃ ብለዋቸው ከሰማይ ተአምራትን እንዲያሳያቸው ፈልገው ያስልማዳቸው «መምህር ሆይ» ብለው ጠርተው የለመኑትን ጻፎችና ፈሪሳውያንን እንደ ፍላጎታቸው ከመፈጸም ይልቅ «ከፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል» በማለት ገሥፆአቸዋል፡፡ (ማቴ. ፲፪፥ ፴፱፤ሉቃ.፲፩፥፲፮)

ከዚህም በተጨማሪ ተአምር አይተው ብዙ ሰዎች በስሙ በማመናቸው አልተደሰተም፡፡ ‹‹በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ፥ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ፤ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰከር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና፡፡›› (ዮሐ. ፪፥፳፫-፳፭) ለዚህም ምክንያቱ ተአምር አይቶ ያመነ ሰው እምነቱ ጊዜያዊ እንደሆነ ልብና ኩላሊትን የሚመረምረው አምላክ በመሆኑ ስለሚያውቅ ነው፡፡ ተአምርም የእምነት መነሻ እንጂ መድረሻ ግብ አይደለም፡፡ ተአምር አይተው የሚነዱ ሰዎችም በመጨረሻው ዘመን ሐሳዊ መሲህ

[61] አሾ የተባለ በእግዚአብሔር የማያምን «ፈላስፋ» የቃና ዘገሊላን ተአምር በተመለከተ በሚሠጠው የራሱ ትንታኔ ላይ ክብር ይግባውና ጌታችንን በተአምራቱ ተከታይ የሚሰበስብ እንደሆነ አድርጎ እየተቸ ተከታዮቹን ሰብስቦ ሲያስቅ በአንድ ቪድዮ ላይ ተመልከቼ ነበር፡፡ የሚገርመው የትምህርቱ ርዕስ ‹ያለ ፈቃድ ተአምር መፈጸም› /performing miracle without permission/ የሚል መሆኑ ነው፡፡ ሙሽሮች በተጨነቁበት ሰርግ ቤት ወይንን መሥጠቱን ‹ያለ ፈቃድ አደረገው› ብሎ መንቀፉ ነው እንግዲህ ፍልስፍናው፡፡ ለፍልስፍና መሥፈርቱ እግዚአብሔር የለም ማለት የሆነ ይመስል ያለ ምንም አመክንዮ በቀልድ ላይ ሳይቀር ‹የፈጣሪን ሕልውና ተጠራጠርሁ› ማለት የሚያስጨበጭብበት የድንቁርና ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡



Scanned by CamScanner

ሲመጣ ‹‹የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል›› የሚለው ትንቢት መፈጸሚያ ይሆናሉ:: (፪ተሰ.፪፥፱-፲)

## ○ የጌታ ተአምራት አምላክነቱን ሲያሳዩ ይችላሉ?

ጌታችን ያደረጋቸው ተአምራት አብዛኞቹ ሌሎች ቅዱሳን ሲያደርጓቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ እናገኛለን:: እርሱ ሙት እንዳስነሣ ሙት ያስነሡ ፤ እሱ ለምጻሙን እንዳነጻ ለምጽ ያነጹ ፤ እሱ ዓይን እንዳበራ ዓይን ያበሩ ፤ እሱ በባሕር ላይ እንደሔደ በባሕር ላይ የሔዱ ሰዎች በዚያው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመዝግበዋል:: ራሱም በቃሉ «በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ያደርጋል ፤ ከዚያም የሚበልጥ ያደርጋል» በማለት ተናግሯል:: (ዮሐ. ፲፬፥፲፪) ታዲያ የጌታችን ተአምራት አምላክ መሆኑን እንዴት ሊያሳይ ይችላል? ለኒቆዲሞስ እንደመሰለው ይህን የሚያገናዝብ ሰው ‹እርሱ እግዚአብሔር ረድቶት የሠራ ነው እንጂ ራሱ አምላክ አይደለም ማለት ነው?› ብሎ ቢጠይቀን ሌሎች ያደረጉትን ተአምራት ከጌታ ተአምራት በምን መለየት እንችላለን? የሚለውን እንመልከት::

ጌታችን ያደረጋቸው ተአምራት አምላክነቱንም የሚያስረዱ ናቸው:: ሌሎች ቅዱሳን ብዙ ድንቅ ነገርን ቢያደርጉ ግን ማድረግ የቻሉት በራሳቸው

አይደለም። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ በኩል ተአምር ማድረግ ይችላል ፣ ያለ ቅዱሳኑም ተአምርን ሊያደርግ ይችላል። ቅዱሳን ግን ያለ እግዚአብሔር ምንም ማድረግ አይችሉም። «ያለ እኔ ምንም ማድረግ አትችሉም» በማለት በቃሉ እንደተናገረ የትኛውም ፍጡር በእጁ ታላላቅ ነገሮችን ቢያደርግ [62]ከእግዚአብሔር ባገኘው ጸጋ እንጂ በራሱ ሊሆን አይችልም። /ዮሐ. ፲፭፥፲፭/ የጌታችን ተአምራት ግን በገዛ ሥልጣኑ ያደረጋቸው ናቸው።

የጌታችን ተአምራት ሌሎች ቅዱሳን ካደረጓቸው ተአምራት የሚለየው በራሱ ሥልጣን በማድረጉ ብቻ አይደለም። የተአምራቱ አፈጻጸምም አምላክነቱን የሚያሳይ ነበር። እሱ አስችሏቸው ሙትን ያስነሡ ቅዱሳን ሰዎች አሉ። በሥልጣን ንግግር «አልዓዛር ሆይ ወደ ውጪ ና» ብሎ የአራት ቀን ሬሳ ከሞት እንቅልፍ የቀሰቀሰ ግን ማንም የለም። (ዮሐ.፲፩፥፵፫) ለምጻምን አስጠምቆ የፈወሰ አለ በገዛ ፈቃዱ «እወዳለሁ ንጻ» ብሎ ያነጻ ግን ማንም የለም። (ማቴ.፰፥፫) ዓይንን ያበሩ ነበሩ በደረቅ ግንባር ላይ በጭቃ ዓይን ሠርቶ ያበራ ግን ማንም አልተገኘም። ‹‹ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኖች ማንም እንደ ከፈተ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አልተሰማም›› ይላል ወንጌሉም (ዮሐ.፱፥፴፪) ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታ አስችሎት በባሕር ላይ ሔዷል ነገር ግን ካላስቻለው በራሱ

---

62 በቤተ ክርስቲያናችን በሰንከሳርና በገድላት በአብዛኛው የቅዱሳን ተአምራት ሲነበብ ለእግዚአብሔር ሥራ ቦታ ያልተሠጠ የሚመስላቸው ሰዎች ይህንን ነጥብ የዘነጉ ናቸው። የቅዱሳን ተአምር ሁሉ የራሱ የእግዚአብሔር ተአምር ነው። ተአምረ ማርያም ያልኑ ያካማወን የሰው ልጅ አበርትቶ መሣሪያ አድርጎት የሚሠራው ሥራ የበለጠ ስለሚያስደንቀን ነው። የቅዱሳኑን ተአምር አብዝተን የምናነበው ሁሉን ቻዩ አምላክ በራሱ ከሠራው ቅዱሳ የብንሰ በአንድ ዐረፍተ ነገር «ሁሉ በእርሱ ሆነ ፤ ከሆነውም አንዳችስ አንኳን ያ እርሱ አልሆነም» አንጠቀልለዋለን። /ዮሐ. ፩፥፫/

እንደማይሆንለት እዚያው ሠጥሞ አድነኝ ብሎ ጮኸ አሳይቶናል። (ማቴ.፲፬፥፴)

ሙትን ያነሡ ይኖራሉ ፤ በገዛ ሥልጣኑ ከነቱም መቃብር የተነሣ ፣ መቅደስ ሰውነቱን በፈረሰ በሦስት ቀኑ የሠራ ግን ከመድኃኒታችን በቀር ማንም የለም። በቅዳሴያችን መካከል «መኑ ይመስለከ አምነ አማልክት እግዚኦ ፤ አንተ ውእቱ ዘትገብር መንክረ ፤ አርአይኮሙ ለሕዝብከ ኃይለከ ወአድኃንኮሙ ለሕዝብከ በመዝራዕትከ» «አቤቱ ከአማልከት መካከል ማን ይመስልሃል? ድንቅ ነገር የምታደርግ አንተ ነህ። ለሕዝብህ ኃይልህን አሳየሃቸው። ሕዝብህንም በክንድህ አዳንካቸው» እያልን የምናመሰግነውም በጸጋ አማልክት ከተባሉ «የእግዚአብሔር ቃል ከመጣላቸው» ቅዱሳን ሁሉ ተአምራቱ ድንቅ ስለሆነ ነው። (ቅዳ.ሐዋ.፤መዝ.፹፱፥፮፤ዮሐ.፲፥፴፭) ስለዚህ ተአምራቱና ምልክቶቹ ሁሉ የአምላክነቱም ማስረጃዎች ነበሩ።

አንዳንዶች ጌታችን አንዳንዶቹን ተአምራቱን ሲያደርግ መጸለዩን አይተው «አምላክ ተአምር ለመሥራት እንዴት ይጸልያል?» ይላሉ። በእርግጥ ጌታችን ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው እንደመሆኑ ‹ለአጽድቆተ ትስብእት› /ሰው መሆኑን ለማስረገጥ/ እና ለአርኣያ ሲጸልይ እናገኛለን። ይህ ማለት ግን በመለኮትነቱ ሁሉን ማድረግ የማይቻለው ሆኖ እርዳታን ሽቶ አይደለም። ይልቁንም እርሱ ከአብ ዘንድ እንደመጣ የሚያስረዳበት አንዱ መንገድ ነበር። አልዓዛርን ከሞት ከማስነሣቱ በፊት እንዲህ አድርጎ ነበር ‹‹ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ። አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላከኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ።›› (ዮሐ. ፲፩፥፵፩-፵፪)

## ○ ጌታችን ከቃና በፊት ተአምር አላደረገም?

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደ ዓይን ምስክርም ጭምር ነበርና የቃናውን ታሪክ በወንጌሉ መዝግቦልናል። የዚህ ሰርግ ቤት ተአምርም በዮሐንስ ወንጌል ከተጻፉ የጌታችን ሰባት ተአምራት ቀዳሚው ነው።

ሰባት ነገሮች በሚበዙበት በዮሐንስ ወንጌል በጠቅላላው ጌታችን ያደረጋቸው ሰባት ተአምራት ተጽፈዋል። እነዚህም ውኃን ወይን እንዳደረገ (ዮሐ.፪፥፩-፲፩) የንጉሥ ቤት ሹምን ልጅ እንደፈወሰ (ዮሐ.፬፥፵፯) መጻጉዕን እንደፈወሰ (ዮሐ.፭፥፩-፲፭) አምስት ሺህ ወንዶች እንደመገበ (ዮሐ.፮፥፩-፲፬) በውኃ ላይ እንደሔደ (ዮሐ.፮፥፲፮-፳፩) የዕውሩ ዘተወልደን ዓይን በጭቃ ለውሶ እንዳበራ (ዮሐ.፱፥፩-፵፩) አልዓዛርን ከሞት እንዳስነሣ ናቸው። (ዮሐ.፲፩፥፴፰-፵፬)

በእኛ ቤተ ክርስቲያን ተአምረ ኢየሱስ በምንለው መጽሐፍ እና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ አፖክሪፋል ጎስፐልስ ተብለው በሚጠሩት መጻሕፍት ላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕጻንነቱ ወራት ባደገበት መንደር ስላደረጋቸው ተአምራት ተጽፎ እናገኛለን። እንዲሁም ጌታችን ወደ ግብፅ በተሰደደበት ወቅት ብዙ ተአምራትን እንዳደረገ በተአምረ ማርያምና በተሰደደባት ግብፅ ቤተ ክርስቲያን መዛግብት ላይ ተጽፎ እናገኛለን። /The Holy Family in Egypt p.31 ; The Lost Books of the Bible pp.45-46፤ ተአምረ ማርያም/ የቃና ዘገሊላው ተአምር የመጀመሪያ ነው ተብሎ ከተጻፈ «ታዲያ እነዚህ ሁሉ ተአምራት አልተፈጸሙም ማለት ነው?» የሚል ጥያቄ ያስነሣል።

በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በዚህ ጉዳይ ሁለት ዓይነት ሃሳቦች ተጽፈው እናገኛለን፡፡ የመጀመሪያው ሃሳብ ‹ጌታ ከቃና ዘገሊላ በፊት በተለይም ከመጠመቁ በፊት ተአምር ስለማድረጉ ለመናገር የሚያስችል ማስረጃ የለም› የሚለው የሃሳብ ወገን ነው፡፡ /John Chrysostom Homily John ii:Xi/ ሁለተኛው የሃሳብ ወገን ደግሞ ወንጌሉ ላይ «ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ» የሚለውን ቃል በማብራራት ላይ የተመሠረተ ሃሳብ ነው፡፡ ቃሉ የሚለው ‹የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ› ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተአምሩ የመጀመሪያነቱ ‹ለቃና ዘገሊላ› ሊሆንም እንደሚችል ያሳያል የሚል ነው፡፡ በእርግጥም ጌታ በቃና ዘገሊላ ለሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ተአምር ፈጽሟል፡፡ /ዮሐ.፬፥፵፮/ ትርጓሜ ወንጌልም «መጀመሪያ› የሚለውን ቃል «ደገኛ ተአምር ፣ ታላቅ ተአምር› ማለት ነው፡፡» በማለት የሚያብራራው ሲሆን ይህ ተአምር ጌታ ‹በአደባባይ የፈጸመው› የመጀመሪያ ተአምር ነው በማለት የዚህ ሃሳብ ወገንተኞች ይደመድማሉ፡፡ (ትር.ወን.ዮሐ.፪)

በእርግጥም ‹‹ጌታችን ከቃና በፊት ምንም ዓይነት ተአምር አልፈጸመም» የሚለው ሃሳብ ከአዋልድ መጻሕፍት ጋር ብቻ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችና ከብዙኃን አበው ትርጓሜያት ጋር ሊጋጭ የሚችል ይመስላል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ «እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ተጭኖ ወደ ግብፅ ይመጣል ፤ የግብፅም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ ፤ የግብፅም ልብ በውስጧ ይቀልጣል፡፡» በማለት ጌታችን በግብፅ በተሰደደ ጊዜ ጣዖታትን ስለማጥፋቱ ትንቢት ተናግሯል፡፡ (ኢሳ.፲፱፥፩) ሌላው ይቅርና ያለ ወንድ ዘር በድንግል ማኅጸን መጸነሱ ፣ ማኅተመ ድንግልናዋን ሳይፈታ ከእርስዋ መወለዱስ ድንቅ ምልክት አይባልም ወይ? ያስብላል፡፡ መጽሐፉም «ጌታ ራሱ ምልክትን ይሠጣችኋል ፤ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ብሏል፡፡ (ኢሳ. ፯፥፲፬)



Scanned by CamScanner

## ○ ይህ ድንቅ ተአምር ተአምርነቱ ለእኛ ነው

በቃና ዘገሊላ ጌታችን ውኃን ወይን ማድረጉ ዕፁብ ድንቅ ተብሎ ሲነገር አንድ ነገር ሊዘነጋ አይገባም። ይኸውም ውኃን ወደ ወይን መለወጥ ሰማይን ያለ ባላ ምድርን ያለ ካስማ ለዘረጋ ፈጣሪ ትልቅ ነገር ሠራ ተብሎ የሚነገር አለመሆኑ ነው። ውኃውንም ወይኑንም ካለመኖር አምጥቶ የፈጠራቸው እርሱ ነው። ካለመኖር ያመጣቸውን ሁለት ነገሮች አንዱን ወደ ሌላኛው መለወጥ ለእርሱ እጅግ ቀላል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ‹ሁሉ በእርሱ ሆነ› ብሎ ተናግሯልና ያየነውና የተደነቅንበት ነገር ሁሉ የእሱ ድንቅ ሥራ ነው። ሌላው ቀርቶ ሰው የሠራውን ነገር እንኳን ብቻ ብናደንቅ የሰውን ብሩሕ አእምሮ የሠራውን እርሱን እያደነቅን ነው።

ቅዱስ አውግስጢኖስ «በእርግጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃውን ወይን በማድረግ የፈጸመው ተአምር ይህን ያደረገው እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ለሚያውቁ ሰዎች አይደንቃቸውም» ብሏል።[63] በየወቅቱ ዝናም ከሰማይ እንዲወርድ የሚያደርገው እርሱ ነው። የተተከለውን የወይን አትክልት የሚያበቅለው እና እንዲያፈራ የሚያደርገውም እርሱ ነው። ሆኖም እነዚህ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች ከመደጋገማቸው የተነሣ በሰፋፊ የአትክልት ሥፍራ ወይንን ማብቀሉ ፣ ከሰማይ እጅግ ብዙ

[63] ቅዱስ አውግስጢኖስ የጌታችንን ድንቅ ሥራዎች ‹ይህ ምን ይደንቃል?› በሚል የአጻጻፍ መንገድ ሲጽፍ ይታያል። ለምሳሌ ‹ጌታ በቃና ሰርግ ቤት ታደመ› የሚለውን ‹ምን ይደንቃል ወደዚህ ዓለም የመጣውስ ለሰርግ አይደል?› በማለት የሥጋዌን ነገር ያብራራበታል። ጌታ የሐዋርያቱን እግር አጠበ የሚለውን ደግሞ ‹ምን ይደንቃል? በደሙ አጥቦን የለ?› ሲል እናገኘዋለን።

ውኃን ማዝነሙ ሳይደንቀን በስድስት ጋኖች ውስጥ የተሠራው ሥራ ብቻ የሚደንቀን ስለማናስተውለው ነው። (St. Augstine Homiles on John Soliloquies)

በመጽሐፈ ስንክሳር መጨረሻ ተጽፈው የምናገኛቸውን አርኬዎች እንደደረሱ የሚነገርላቸው ኢትዮጵያዊው አባ አርከ ሥሉስም በጥር ፲፪ ከሚነበበው ስንክሳር በስተመጨረሻ በጻፉት አርኬ ይህንን የቅዱስ አውግስጢኖስ ሃሳብ እንዲህ አብራርተውታል።

ሰላም ለሑረትከ ውስተ ቤተ ከብካብ በፍቅር
ከመ ታውይን ማየ እግዚአብሔር
ዝንቱ ኃይልከ ዘበኅቤነ መንክር
ለከሰ አልቦ ዘይሰአነከ ግብር
እስመ ገባሪሆሙ አንተ ለሰማይ ወምድር

«እግዚአብሔር ሆይ ውኃን ወይን ታደርገው ዘንድ በፍቅር ወደ ሰርግ ቤት ለመሔድህ ሰላምታ ይገባል። ይህ ኃይልህ በእኛ ዘንድ ድንቅ ነው። ለአንተስ የሚሳንህ ሥራ የለም። ሰማይና ምድርንም የሠራኃቸው አንተ ነህና።» ብለዋል። (አባ አርከ ሥሉስ ፤ ስንክሳር ጥር ፲፪ አርኬ)

በዚህ አርኬም የቃና ዘገሊላው ተአምር ‹በእኛ ዘንድ ድንቅ› ነገር መሆኑን እና ሰማይና ምድርን ለሠራ አምላክ ግን ከዚህ የሚበልጠውን ተአምር ሁሉ ለማድረግ የሚሳነው እንደሌለ አስረድተዋል።



Scanned by CamScanner

○ ደቀ መዛሙርቱ እስከ ቃናው ተአምር ድረስ የተከተሉት ሳያምኑበት ነበር?

የቃና ዘገሊላውን ተአምር ታሪክ የመጨረሻ ዐረፍተ ነገር ስናነብ የምናገኘው ቀሪ ሃሳብ «ክብሩን ገለጠ ደቀመዛሙርቱም በእሱ አመኑ» የሚለው ነው፡፡ ጌታችን ክብሩን ገለጠ የሚለውን ‹ጌትነቱን› በማለት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያብራሩታል፡፡ ይህም ውኃውን ወደ ወይን በኃልዮ ብቻ በመለወጡ በፍጥረቱ ላይ ያለውን ሥልጣንና ጌትነት በማስረዳቱ ነው እንጂ በደብረ ታቦር እንዳሳየው ክብሩ ፣ ዳግም በክብሩ ሲመጣ በሚታየው ግርማው ተገለጠ ማለት አይደለም፡፡ የክብሩም መገለጥ ለጊዜው ተአምራቱን ላወቁ ጥቂት ሰዎች ሲሆን በኋላ ደግሞ ዝናውን በሚሰሙ ሁሉ ዘንድ ነው፡፡

ደቀ መዛሙርቱ በእሱ አመኑ የሚለውን የሚያነብ ሰው «እስካሁን አላመኑም ነበር ማለት ነው?» የሚል ጥያቄ በልቡ ሳይመላለስ አይቀርም፡፡ በእርግጥ በሰርግ ቤቱ ከጌታ ጋር የመጡት ቅዱሳን ሐዋርያት በምዕራፍ አንድ ላይ እንደምናነበው ጌታን አምነው የተከተሉ ደቀመዛሙርት ነበሩ፡፡ ሆኖም የአሁን እምነታቸው ቀድሞ ካመኑት ይለያል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዳብራራው ደቀመዛሙርቱ አስቀድመው በጌታ ያመኑት በትምህርቱ ብቻ ነበር አሁን ደግሞ በተአምራቱም ጭምር አመኑ፡፡ የተከተሉትም ተአምር አይተው ሳይሆን የተናገረውን ሰምተው ነበር፡፡

በሌላ ክፍል እንደተመለከትነው ተአምር አይቶ ብቻ ማመን ከእምነት አይቆጠርም፡፡ ደቀመዛሙርቱ አስቀድመው በቃሉ ማመናቸው ለሐዋርያነት ክብር አበቃቸው እንጂ ተአምር አይተው ብቻ ቢከተሉት እንደ ብዙዎች



Scanned by CamScanner

የመጥፋት ዕድላቸው ይሰፋ ነበር፡፡ ጌታችንም «አይተማመንባቸው ነበር» (ዮሐ. ፪፥ ፳፫)

‹‹እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ይችላል›› ብሎ ለሚያምንና ለሚከተል ክርስቲያን ተአምር አያስደንቀውም፡፡ ተአምር እንዲያውም ለማያምኑ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም» በማለት እንዳስረዳን ካመኑ በኋላ ተአምር ፈላጊ መሆን አይገባም፡፡ (፩ቆሮ.፲፬፥ ፩) ሐዋርያቱም ያስተማሩን ይህንን ነው፡፡ እነርሱ ተከትለውት ተአምር አዩ እንጂ ፤ ተአምር አይተው አልተከተሉትም፡፡ «ሳያዩ ያመኑ» እነርሱ «ብፁዓን ናቸው» እኛም እንደነሱ «በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም፡፡» (ዮሐ.፳፥፳፱ ፤፪ቆሮ.፭፥፯)

የቅዱሳን ሐዋርያት እምነት ከቃናም በኋላ በወንጌል ታሪኮች ላይ በብዙ ውጣ ውረድ ከፍ ዝቅ ሲል እናያለን፡፡ ራሳቸውም «እምነት ጨምርልን» እስከማለት ደርሰው ነበር፡፡ (ሉቃ.፲፯፥፭) ጌታችንም በተደጋጋሚ «እምነት የጎደላችሁ» ብሎ እስኪገሥጻቸው ድረስ ኃይሉን ፤ አመጣጡን ፤ ትንሣኤውን ለማመንና ለመረዳት ብዙ ተቸግረው እንደነበር በወንጌላቱ ላይ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹን ታሪኮች የሚያነብ ሰው «ታዲያ በቃና ዘገሊላ በስሙ አመኑ የተባለው ለምን ነበር?» ማለቱ የማይቀር ነው፡፡

ወንጌሉ የሚያሳየው እምነት ቀስ በቀስ እያደገ የሚሔድ ነገር መሆኑን ነው፡፡ ጌታችን በትምህርቱ ወቅት ‹ትንሽ እምነት› ‹ጎዶሎ እምነት› ‹ታላቅ እምነት› ብሎ የእምነትን ደረጃ ከፋፍሎ አስተምሯል፡፡ (ማቴ.፮፥፴፤፲፭፥፳፰፤፲፯፥፳) ስለዚህ ቅዱሳን ሐዋርያት እምነታቸው ሙሉ የሆነው በሒደት ነው፡፡ የክርስቶስን ወልደ እግዚአብሔርነት በሙሉ ልብ ያመኑት ፤ ያለ ፍርሃት ያለ

ጥርጥር ማገልገል የቻሉት ጌታችን በተነሣ በሃምሳኛው ቀን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ነው።

## ○ የቃናው ወይን እና የባለ ትዳሮች ሕይወት

የቃና ዘገሊላዎቹ ሙሽራና ሙሽሪት እንደማንኛውም ሙሽሮች ሁሉ አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ለሰርጋቸው ሲዘጋጁ ሰንብተዋል። እንደባሕላቸው ስለሚለብሱት ልብስ ፣ ስለሚደግሱት ድግስ ፣ ስለሚጠሩአቸው እንግዶች ብዛት ፣ ስለሚቀርበው ምግብ ፣ ስለሚጠጣው የወይን ጠጅ ከዘመድ ወዳጆቻቸው ጋር ሲደክሙ ከርመዋል። በሰርግ ዕለት ግን የሚያጋጥም ነገር አይታወቅምና ብዙ እንግዳ ይሸኛል የተባለው የወይን ጠጅ ሳይታሰብ አለቀ።

የማይሽር ቁስል የሚጥልባቸውን ፣ የሰው መተረቻ የሚያደርጋቸውን ይህን ክስተት ግን እነርሱ ሳይሰሙ በሰርጉ ቤት የነበረችው እመቤታችን በምልጃዋ ፈታችው። ለተወደደ ልጅዋ ነግራ የጎደለውን አስሞልታ ባማረ ሁኔታ ዳረቻቸው። የጠሩት የሰማይና የምድር ንጉሥ መድኃኒዓለም ክርስቶስ ውኃን ወይን ጠጅ አድርጎ አከበራቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውኃና የወይን ጠጅ ከጠብና ከፍቅር ጋር ተያይዘው ሲነገሩ እናገኛለን። ጠቢቡ ሰሎሞን ስለ ፍቅር ሲናገር ወይን ጠጅን በንጽጽር ያነሣል «ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ መልካም ነው!» «ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እንዴት ያምራል!» ‹‹ከወይን ጠጅ ይልቅ ፍቅርህን እናስባለን›› ‹‹ወደ ወይን ጠጁም ቤት አገባኝ፥ በእኔ ላይ ያለው ዓላማውም ፍቅር ነው።›› እያለ ማለት ነው። (መኃ.፩፥፪ ፤ ፬ ፤ ፬፥፬ ፤ ፬፥፲) በአንጻሩ ስለ ጠብ ሲያነሣ ደግሞ ውኃን ያነሣል። «ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም»



Scanned by CamScanner

«የጠብ መጀመሪያ እንደ ውኃ አፈሳሰስ ነው» «በዝናብ ቀን የሚያንጠባጥብ ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው» ብሏል። (መኃ.፳፥፲፬፤ምሳ.፲፯፥፲፬፤፳፯፥፲፭) በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም ውኃ የጠብ ምሳሌ ሲሆን ወይን ጠጅ ደግሞ የፍቅር ምሳሌ ነው።

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት በመጀመሪያ የወይን ጠጅ ተጠምቆ ዝግጁ ሆኖ ነበረ። ይህ የወይን ጠጅ የጠማቂ ባለሙያ እጅ የተጠበበት ነበር። ሙሽሮቹ ያላቸው ወይን ጠጅ ሰርጉን እንደሚያዘልቃቸው ተማምነው የነበረ ቢሆንም ወይኑ ግን ባልጠበቁት ፍጥነት አለቀ። ከዚያ በኋላ በዚያ ሰርግ ቤት ለሚመጣ እንግዳ ሊቀርብ የሚችለው ብቸኛ መጠጥ ውኃ ብቻ ነበር። ለሙሽሮቹ የተሻለ የሚሆንላቸው ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ሌላ እንግዳ ጨርሶ ባይመጣ ነው። ወይን ጠጅ በሚጠጣበት ሰርግ ቤት ውኃ ከሚጠጣ ለእንግዳውም ባይመጣ ይሻለዋል።

በሁሉም የትዳር ሕይወት ውስጥ በወይን ጠጅ የተመሰለው ፍቅር መጀመሪያ ይኖራል። መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉም ማለት ባይቻልም ባለትዳሮች በአመዛኙ ከጋብቻ በፊት ቢያንስ ወደ ጋብቻ እንዲያመሩ ምክንያት ሊሆን የቻለ ፍቅር ይኖራቸዋል። ብዙዎች የቃና ሙሽሮች በወይን ጠጃቸው እንደተማመኑ ሁሉ በፍቅራቸው ዘላቂነት እርግጠኞች ነበሩ። ከጋብቻ በፊት የነበራቸው ፍቅር ከጋብቻ በኋላ አብሯቸው እንደሚዘልቅ ተማምነው ነበር። አንዳንድ ጥንዶች እንደውም በፍቅራቸው ዘላቂነት ላይ ካላቸው እርግጠኝነት የተነሣ ሌሎች ባለትዳሮች ሲጣሉ ሲያዩና ሲሰሙ ‹ሰው እንዴት ይጣላል? እንደኛ ስላልተፋቀሩ ነው!› ብለው ይፈርዳሉ። ‹የፈለገ ነገር ቢከሰት እኛ መቼም እንዲህ አንሆንም!› ብለው ይገዛታሉ።

በሰርግ ሰሞንና በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ወራት ባልና ሚስት በፍቅር ወይን የተሞሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጫጉላ እርከን (Honeymoon stage) ላይ እያሉ ሁሉም ነገር ደስታና ሰላምን የተሞላ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደቃናው ሰርግ ቤትም ይህ የፍቅር ወይን በልበ ሙሉነት ሲቀዳ ይቆያል፡፡ ሆኖም ሰው የጠመቀው ወይን ማለቁ እንደማይቀር በጋብቻ ሕይወትም እንዲሁ በወይን የተመሰለው ፍቅር እያለቀ እያለቀ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ከዚያ በኋላ በዚያ ጋብቻ ላይ ሊገኝ የሚችለው ውኃ ይሆናል፡፡ ባል ለሚስቱ ፍቅር የተባለውን ወይን ማቅረብ ሲሳነው ፣ ሚስትም እንዲሁ ወይን ማምጣት ሲያቅታት አንዳቸው በአንዳቸው ሁኔታ እየተበሳጩ ይሔዳሉ፡፡ ወይን ከሌለ ደግሞ እንደ መፍትሔ ቆጥረው አንዳቸው ለአንዳቸው የሚያቀርቡት ውኃን ይሆናል፡፡ ውኃ ደግሞ ከላይ በመጽሐፉ እንዳየነው የማያቋርጥ ጠብ ነው፡፡

ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ እንደ ውኃ የቀዘቀዙ ይሆናሉ፡፡ እርስዋ «አውነት ግን ይኼንን ሰው ነበር ባል ብዬ የተቀበልሁት?» ብላ ትብከነከናለች፡፡ እርሱም «ምን ነክቶኝ ነበር?» እያለ ይቆጫል፡፡ ወደ ቤታቸው የሚመጣ ሰውም ፊት ሊያቀርቡት የሚችሉት ወይን የላቸውም፡፡ የመጣ ሰው የሚያየው ጠባቸውን ብቻ ስለሚሆን የእንግዳ አለመምጣት ለሁለቱም የተሻለ ይሆናል፡፡ ያያቸው ሰው እርስ በእርሳቸው ያላቸውን ጥላቻ ሲመለከት «እነዚህ ሰዎች አስቀድሞስ እንዴት ተፋቅረው ሊጋቡ ቻሉ? የለም ቀድሞውኑም ፍቅር ባይኖራቸው ነው!» ብሎ ይደመድማል፡፡ ልክ ነው ወይን አልቆ ውኃ ሲቀርብ በዚያ ቤት ወይን ኖሮ የሚያውቅ አይመስልም፡፡



Scanned by CamScanner

በእንዲህ ዓይነት ኑሮ የሚሠቃዩ ብዙዎች ናቸው። ባልጠበቁት ሁኔታ የፍቅር ወይን አልቆባቸው የጠብ ውኃን መጋት የለመዱ ፣ የተጋቡበትን ቀን የሚራገሙ ፣ ጋብቻን ለማንም ሰው የማይመክሩ ፣ ባላገቡ ሰዎች ዕድል የሚቀኑ ፣ ፍቺ እንዳይፈጽሙ ፈርተው ልጆቻቸውን ላለመበተን ብለው አብረው የሚኖሩ ፣ ባልና ሚስት ሆነው አልጋ ለይተው የሚተኙ ፣ ሰላምታ እንኳን የማይሠጣጡ ወይን ጠጅ አልቆባቸው ቤታቸው በጠብ ውኃ ጎርፍ የተሞላባቸው እጅግ ብዙ ሰዎች አሉ።

ለዚህ ችግር መፍትሔ ፍለጋ ብዙዎች ይደክማሉ። ችግራቸውን ሊፈቱላቸው ለማይችሉ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው የወይናቸውን ማለቅ ተናግረው መዘባበቻ ሆነው የቀሩ ብዙዎች ናቸው። መፍትሔ ይሆናል ብለው በራሳቸው መንገድ ሔደው ሌላ ድጋሚ ሊያልቅ የሚችል በሰው ጥበብ የተጠመቀ የወይን ጠጅ ሊያመጡ ሞክረው ባጭር ጊዜ ያለቀባቸውም ብዙዎች ናቸው።

መፍትሔው ግን በዚሁ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ታሪክ ላይ ተቀምጧል። ችግሩ መፈታት የሚችለው በዚያ ሰርግ ቤት በተፈታበት መንገድ ብቻ ነው። የቃና ወይን ጠጅ ሲያልቅ አይታ «ወይን እኮ የላቸውም» ብላ ለምና ያስሞላችው ወላዲተ አምላክ በባለ ትዳሮች መካከል ካለች ችግሩ ያለጥርጥር ይፈታል። ስም ለሚያጠሩ ለሰዎች በመንገር ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም። በቃና ዘገሊላ እንዳደረገችው ድንግል ማርያም በባለ ትዳሮችም ቤት ገብታ «ፍቅር እኮ የላቸውም» ትላለች።

አንዳንድ ባለ ትዳሮች በጋብቻቸው ውስጥ ወይን መጉደሉን እንደ ቃና ዘገሊላዎቹ ሙሽሮች ፈጽመው አያውቁም። በየጊዜው አስታራቂ ከመካከላቸው



Scanned by CamScanner

እየገባ ሊያስማማቸው ሲሞክር የጠባቸው መንሥኤ ከድሮም አብሯቸው የኖረ ተራ ምክንያት ይሆናል፡፡ የማያጣላው አጣልቷቸው በውኃ ቀጠነ ሲነታረኩ ይገኛሉ፡፡ በተደጋጋሚ ሽምግልና እየታረቁም እንኳን ሰላም አያገኙም፡፡ «እስቲ ምን አዲስ ነገር ተገኘና ነው ዛሬ ተነሥተሽ እንዲህ የምትዪኝ» «ዛሬ ነው ወይ ይኼ ነገር የታየህ» እየተባባሉ በማያጠግብ ምክንያት መናቆራቸው ለሁለቱም ግራ ይገባቸዋል፡፡ ያልተረዱት ነገር ግን አለ፡፡ በየሰበቡ እንዲጣሉ የሚያደርጋቸው ፍቅራቸው ማለቁ ነው፡፡ የፍቅር ወይን እንዳለቀ ከእነርሱ ቀድማ የምታውቀው ድንግል ማርያም ግን «ፍቅርኬ አልቦሙ» «ፍቅር እኮ የላቸውም» ትላለች፡፡ ልጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ በጠብ ውኃ የተሞላውን ቤት ዳግመኛ በወይን ጠጅ ፍቅር ይሞላዋል፡፡ ይኼኛው የወይን ጠጅ ደግሞ እንደበፊቱ ሰው ሠራሽ ወይን የሚያልቅ አይደለም፡፡ ያለፈውን የሚያስንቅ ‹ቀድሞም የፍቅር ወይን አልነበረንም ፤ መናኛ ነበር የያዝነው!› የሚያሰኝ ነው፡፡

ይህን ስንል ግን ባልና ሚስት ራሳቸው ሊያስተካክሏቸው የሚገቡ ጉድለቶቻቸውን ሳያስተካክሉ የእመቤታችንን ምልጃና ተአምር ብቻ ይጠባበቁ ማለታችን አይደለም፡፡ በቃና ምልጃዋ ችግር እንዲፈታ ለአገልጋዮቹ ‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ› ብላ ድርሻ ሠጥታ እንደነበር ባለትዳሮችም ሊያደርጉት የሚገባ ነገር አለ፡፡ ትዳራቸው በፍቅር ወይን እንዲሞላ ‹የእኔስ ችግር ምንድር ነው?› ‹የእናቱን አማላጅነት ከጠየቅሁ ከእኔ ምን ማድረግ ይጠበቃል?› ብለው በትሕትና በመታዘዝና ድክመታቸውን በማስተካከል ትዳራቸውን መታደግ አለባቸው፡፡

መድኃኔዓለም ክርስቶስን ወደ ጋብቻ ሕይወት መጥራት የሚቻለው ሥጋና ደሙን በመቀበል ነው፡፡ በደቀመዛሙርት የተመሰሉት ካህናትን በንስሓ

አባትነት ይዞ ጋብቻን በሥጋ ወደሙ ወሰኖ ዘወትር በመንፈሳዊ ሕይወት መንገድ በእግዚአብሔር ቃል ለሚገዛ ሰው የወይን ጠጁ ዳግም ሳያልቅ ይሞላል፡፡

በጋብቻ ሕይወት መንገድ ላይ ላላችሁ ሁሉ የቃናዋ እንግዳ እመቤታችን በአማላጅነቷ ፤ የተወደደ ልጅዋ ደግሞ በአምላካዊ ሥራው በቤታችሁ ተገኝቶ መንፈሳዊውን የፍቅር ወይን ይሙላላችሁ አሜን!



Scanned by CamScanner


## ክፍል ሁለት

# ሰማያዊው ሰርግ

‹‹ኢየሱስ ሰርግ ቢጠሩት በቃና ዘገሊላ ውኃውን ጠጅ አድርጎ አጠጣ:: በሰው ሰርግ እንደዚህ የሆነ በራሱ ሰርግ እንዴት ይሆን? የእግዚአብሔርን ልጅ ሰርግ አይቼ አድግሱም በልቼ ጠጥቼ እዚያ ወዲያ ምነው በሞትሁ››

መጽሐፈ ጨዋታ መንፈሳዊ
/አስቃ ዘነብ ኢትዮጵያዊ ፲፰፻፵፯ ዓ.ም

# ምዕራፍ ስድስት




«በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥
የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች
...የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት
ወይን እኮ የላቸውም አለችው
ኢየሱስም አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?
ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት፡፡
... አሳዳሪውም ሙሽራውን ጠርቶ ..
አንተ መልካሙን የወይን ጠጅ
እስካሁን አቆይተሃል አለው፡፡ »
ዮሐ. ፪፥፩-፲

## ፩. የመስኮትና የሥጋን ተዋሕዶ አንደ ጋብቻ

### ○ ሦስተኛው ቀን

በምሥጢራዊው መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ‹ቀን› የሚለው ቃል ብዙ ትርጉምን የያዘ ምሥጢራዊ ቃል ነው፡፡ የመጀመሪያው ‹ቀን› የሚለው ቃል ትርጉም የፀሐይን ዑደት የተከተለው ‹[64]ሃያ አራት ሰዓት› ነው፡፡ ሁለተኛው

[64] አንዳንድ ጸሐፊዎች ፀሐይ እስከተፈጠረች እና የፀሐይ ዑደት እስከተጀመረበት እስከ አራተኛው ቀን /ዕለተ ረቡዕ/ ያለውን የሥነ ፍጥረት ዕለት በሃያ አራት ሰዓት ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነ እና ሳይንስ የሚለው

ትርጓሜ ደግሞ አምላካዊው አቆጣጠር ነው፡፡ ‹‹ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፥ እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና›› ‹‹እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት ፤ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።›› የሚሉት ቃላት ይህንን ያስረዳሉ፡፡ (መዝ. ፹፱፥፬ ፤ ፪ጴጥ.፫፥፰) ከዚህም ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ‹ቀን› የሚለው ቃል እንደየአገባቡ ‹ሕይወትን› ‹ዘመንን› የመሳሰሉ የተለያዩ ትርጉሞችን ይዞ እናገኘዋለን፡፡ (ዮሐ.፱፥፬፤ኤፌ.፭፥፲፮፤መዝ.፻፴፰፥፲፮)

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ‹በሦስተኛው ቀን ሰርግ ነበረ› የሚለውን ዐረፍተ ነገር በምሥጢር ሲተረጉሙ ሦስቱን ቀናት ‹ሦስቱ ዘመናት ናቸው› ይላሉ፡፡ ሦስቱ ዘመናት የተባሉት ዘመነ አበው ፤ ዘመነ ኦሪት እና ዘመነ ወንጌል ናቸው፡፡ ‹በሦስተኛው ቀን› ሲል በሦስተኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ ወንጌል ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ስለ ‹ሦስተኛው ቀን› ሲያስተምር ነቢዩ ሆሴዕን ይጠቅሳል፡፡ ‹‹ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ እርሱ ሰብሮናልና፥ እርሱም ይፈውሰናል እርሱ መትቶናል፥ እርሱም ይጠግነናል።ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል፤ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን።›› በማለት ትንቢት የተናገረለት ሦስተኛ ቀን አምላክ ሰው የሆነበት የዘመኑ ፍጻሜ ዘመነ ወንጌል መሆኑን አስረድቷል፡፡ (Cyril *Archbishop of Alexandria* On The Gospel of John. BOOK II.)

በቃናው ሰርግ ቤት ከልጅዋ አስቀድማ መታደሟን በሚገልጥ መንገድ ወንጌሉ ‹የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች› ይላል፡፡ ይህም እመቤታችን ከጌታ ድንግላዊ ልደት በፊት አስቀድማ መታወቋን አንድም [65]በአምላክ ኅሊናም አስቀድማ

በሚልዮን የሚቆጠር ዘመን ሊሆንም እንደሚችል ይጠቅሳሉ፡፡ /Many years with peoples's Questions I; Pope Shenouda III ; Creation Fr. Athanasius Iskandar ; etc/

[65] እመቤታችን በአምላክ ኅሊና ታስባ ትኖር ነበር የሚለው አነጋገር የአምላክን አዋቂነት መሠረት አድርጎ የሚነገር ነው፡፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንኳን ድንግል ማርያም ሁሉም ሰው በአዋቂው እግዚአብሔር አስቀድሞ የታሰበ ነበር፡፡

ታስባ ትኖር እንደነበር ያስተረጉማል፡፡ አንድም ‹ጥበቡ ከሥጋዌ አስቀድማ ነበረች› ይላል፡፡

## ○ ሰርግ ቤት ውስጥ የተገኘችው ሰርግ ቤት

በሦስተኛው ዘመን በዘመነ ወንጌል መጀመሪያ የተደረገው ታላቁ ሰርግ ምንድን ነው? ሰርግ ቤቱስ የት ነው? ሙሽራው ማን ነው? ሙሽራይቱስ? የሚሉት ጥያቄዎች ደግሞ በማስከተል ምላሽ የምናገኝባቸው ናቸው፡፡

የሐዲስ ኪዳኑ ታላቅ ሰርግ የተፈጸመባት ሰርግ ቤት በቃና ዘገሊላ የታደመችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ይህችን የሰርግ ቤት ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም «ሙሽራዋ ንጹሕ የሆነ ንጽሕት የሰርግ ቤት ናት» በማለት ሲያመሰግናት አባ ሕርያቆስ ደግሞ በቅዳሴው «የሚልከያስ ንጹሕ አዳራሽ» በማለት በ‹ታላቅ አዳራሽ› መስሎ ይገልጿታል፡፡ ቅዱስ ዳዊትም ስለጌታችን «እርሱም እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል» በማለት እልፍኝ ከተባለችው እናቱ እንደሚወለድ ትንቢትን ተናግሮ ነበር፡፡ (ውዳ.ማር.ዘረ.፤ቅዳ.ማር.፤መዝ.፲፰፥፭)

ቅዱስ አውግስጢኖስ ይህንን ሃሳብ እንዲህ ያብራራዋል፡-

‹‹ሙሽራው (የእግዚአብሔር) ቃል ነበርና የሰው ልጅ ሥጋ ደግሞ ሙሽራዪቱን ሆነ፡፡ ሁለቱም አንድ ሆኑ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆነ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ራስ (ክርስቶስ ሰው)

---

ቅዱስ ዳዊት ‹ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ፡፡› በማለት እንደተናገረ፡፡ (መዝ. ፻፴፰፥፲፮) መቅድመ ወንጌልም ‹ሐም ቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ› ‹አዳምን ሳይፈጥረው በፊት ሥራውን ያውቃል› ይላል፡፡



Scanned by CamScanner

የሆነበት የድንግል ማርያም ማኅጸን ደግሞ የሙሽራ እልፍኙ ሆነ፡፡ እርሱ እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ወጥቷልና መጽሐፍ እንደተነበየ ‹እርሱም እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል እንደ አርበኛ በመንገዱ ለመሮጥ ደስ ይለዋል፡፡›[66]

‹ሰርግ ቤት› በተሰኘችው እመቤታችን በሰርግ ቤት ውስጥ የሚከናወኑ አራት ነገሮች ተፈጽመዋል፡፡ በሰርግ ቤት ውስጥ ሙሽራውና ሙሽሪቱ አንድ አካል ሆነው እንደሚዋሐዱ በእመቤታችን ውስጥም መለኮትና ሥጋ አንድ ሆነዋል፡፡ በሰርግ ቤት የሙሽራውና የሙሽሪት ዘመዶች አንድ ቤተሰብ እንደሚሆኑ በእመቤታችን ማኅጸን በተፈጸመው የአምላክና ሰው ተዋሕዶ ምክንያት ሰውና መላእክት ፣ ነፍስና ሥጋ ፣ ሕዝብና አሕዛብ አንድ ሆነዋል፡፡ በሰርግ ቤት መብልና መጠጥ እንደሚቀርብ በእርስዋ በተደረገው ተዋሕዶ ምክንያት ሥጋ ወደሙ ለሁላችን ማዕድ ሆኖ ተሰጥቷል፡፡ በሰርግ ቤት ዘፈንና ጨዋታ እንዳለ ደግሞ ሁሉን የሚያስደስቱ ታላላቅ ተአምራት በአምላክ ሰው መሆን ምክንያት ታይተዋል፡፡ /ውዳ.ማር.ትር.ገጽ ፺፪/

በእመቤታችን ማኅጸን የሃይማኖታችን መጠሪያ የሆነው ‹ተዋሕዶ› በማይመረመር አምላካዊ ጥበብ በመለኮትና በሥጋ መካከል ተፈጽሟል፡፡ ይህ ተዋሕዶም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስጠንቅቀው እንደሚያስተምሩት መለኮት ወደ ሥጋ ፣ ሥጋ ወደ መለኮት ሳይለወጥ /እንበለ ውላጤ/ ፣ መለኮት ከሥጋ ፣ ሥጋ ከመለኮት እንደ ሁለት ሳይለይ /እንበለ ምንታዌ/ ፣ ከተዋሐዱም በኋላ ዳግም ወደ ሁለትነት ላይመለሱ /እንበለ ሚጠት/ ተዋሕደዋል፡፡ በአጠቃላይ በእመቤታችን ውስጥ የተፈጸመው ፍጹም ተዋሕዶ መለኮት መለኮትነቱን ሥጋም ሥጋነቱን ሳያጣ ፣ አንዱ አንዱን

---

[66] For the Word was the Bridegroom, and human flesh the bride; and both one, the Son of God, the same also being Son of man. The womb of the Virgin Mary, in which He became head of the Church, was His bridal chamber: thence He came forth, as a bridegroom from his chamber, as the Scripture foretold, "And rejoiced as a giant to run his way." /NPNF1-07. St. Augustin: Homilies on the Gospel of JohnTractate VIII.Chapter II. 1–4/



Scanned by CamScanner

ሳይውጠው ፣ የመለኮት የሆነ ሁሉ የሥጋ የሥጋ የሆነ ሁሉ ደግሞ ለመለኮት ሆኖ በመጣባበት /በተዓቅቦ/ አንድ ሆነዋል። ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ በዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜው ላይ «ራሱ እንደተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ከሰማያት ወረደ አንደ ሙሽራም (ሆኖ) የሰውን ባሕርይ የራሱ ባሕርይ አደረገው›› በማለት የአምላክና የሰውን ባሕርይ ተዋሕዶ በሰርግ መስሎ ተናግሯል። (Cyril *Archbishop of Alexandria* On The Gospel of John. BOOK IL)

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የአምላክ እና የሰውን ፍጹም ተዋሕዶ በሰርግ መስለው የሚያስተምሩት በሰርጉ ዕለት ብቻ ሳይሆን እንደ ቀድሞው ባሕል ሽማግሌ ከሚላክበት ሒደት ጀምሮ ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ጠቅሰው በማብራራት ነው። የሚከተለው የዘመነ አበው ታሪክና ምሥጢራዊ ትርጓሜው ይህን አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

በዘመነ ብሉይ የነበሩት ሦስቱ ታላላቅ አባቶች አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በማድረግ ምሥጢረ ሥላሴን ያስተምሩባቸዋል። የሚወደው ልጁን ይስሐቅን ለመሠዋት የፈቀደውን አብርሃም ‹የሚወደውን አንድያ ልጁን እስኪሠጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ የወደደው› የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ነው።

አባቱ ሊሠዋው በወደደ ጊዜ በሙሉ ፈቃደኝነት የታዘዘው ይስሐቅ ደግሞ ‹ለመስቀል ሞት እንኳን በታዘዘው› በእግዚአብሔር ወልድ ይመስላል። አብርሃም ልጁን ሊሠዋ ከወሰነበት ዕለት አንሥቶ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ በልቡ ልጁን ሠውቶ የነበረ ሲሆን እግዚአብሔር ተው ሲለው በሦስተኛው ቀን እንደሞተ የቆጠረውን ልጁን ዳግመኛ አግኝቷል። በአብርሃም ኅሊና ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት የሞተው ይስሐቅ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በመቃብር ያደረው የእግዚአብሔር

ወልድ ምሳሌ ነው። የነገደ እስራኤል አባት የሆኑትን ዐሥራ ሁለት ልጆች የወለደው ያዕቆብ ደግሞ የእስራኤል ዘነፍስ (የክርስቲያኖች) አባት የሆኑትን ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት በጸጋ የወለደው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።

አብርሃም በስተርጅና ለወለደው ለልጁ ለይስሐቅ ከሚኖርበት ሀገር ከከነዓን ሚስትን ሊድርለት አልወደደም ነበር። ለልጁ የምትሆነዋን ሙሽራ ማምጣት የፈለገው ከሶርያ ነበር። ስለዚህ ታማኝ አገልጋዩን ኢያውብርን ጠርቶ ለልጁ የምትሆነዋን ቆንጆ ይዞ እንዲመጣ ላከው። ይህ የአብርሃም ሎሌም ‹ጌታዬ ሆይ ውኃ አጠጪኝ ስላት ለአንተ ጠጣ ግመሎችህንም አጠጣልሃለሁ የምትለኝ እርስዋ ለጌታዬ ልጅ ሚስት የምትሆነዋ ትሁን› ብሎ ምልክት እንዲሠጠው ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ወደ ውኃ መቅጃ ሥፍራ ሲደርስም አንዲት ወንድ የማያውቃት ድንግል ውኃ ልትቀዳ መጣች። ውኃ እንድታጠጣው ሲጠይቃት እንስራዋን አውርዳ አጠጣችው። ለግመሎቹም አጠጣችለት። ደስ ብሎት የወርቅ ጌጥ ሸለማት። ወደ ቤተሰቧ ሔዶ እንዲሠጡት ሲጠይቅ ተቀበሉት። ርብቃን ጠርተው የይስሐቅ ሚስት ለመሆን ፈቃደኝነቷን ጠየቋት «ከዚህ ሰው ጋር ትሔጃለሽ?» አሏት። ርብቃም «አዎን እሔዳለሁ» አለች። (ዘፍ. ፳፬፥፩-፶፰)

ከላይ እንደተመለከትነው አብርሃም የእግዚአብሔር አብ ይስሐቅ የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ ናቸው። ይስሐቅ ከርብቃ ጋር ያደረገው ጋብቻ ደግሞ እግዚአብሔር ወልድ ከሰው ሥጋ ጋር ያደረገው ተዋሕዶ ምሳሌ ነው። አብርሃም የነበረበት ሀገር ከነዓን የሰማይ ፤ የርብቃ አገር ሶርያ የምድር ምሳሌ ናቸው። አብርሃም ልጁ ከከነዓን ሳይሆን ከሶርያ ሚስት እንዲያገኝ እንደወደደ

እግዚአብሔር አብም አንድያ ልጁ ወልድ የሰማያውያን መላእክትን ዘር ያይደለ የምድርን /የሰውን/ ዘር እንዲዋሐድ ወድዷል። /ዕብ. ፪፥፲፯/

አብርሃም ሎሌው ኢያውብርን ወደ ሶርያ እንደላከ እግዚአብሔር አብም ሎሌውን ቅዱስ ገብርኤልን ወደ ምድር ልኳል። ኢያውብር ውኃ ልትቀዳ የመጣችውን ርብቃን እሺ እንዳሰኘ ፣ ቅዱስ ገብርኤልም ውኃ ቀድታ ስትመለስ ያገኛትን እመቤታችንን በታላቅ ትሕትና ዜናውን ነግሯት ‹ይሁንልኝ› አሰኝቷታል። በሰርግ የተመሰለው የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶም በእርስዋ ተፈጽሟል። /ወንጌል ትርጓሜ ዘሉቃስ ፩፥፴፰/ በአጠቃላይ ምሥጢረ ሥጋዌ በሰርግና በጋብቻ መመሰሉ ብሉያት ፣ ሐዲሳትና ሊቃውንት የተባበሩበት እውነታ ነው።

○ ንስጥሮሳዊና ስውጤኪሳዊ ጋብቻ

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ በመጣባበቅ የተፈጸመ ሁለትነት የሌለበት ፣ አንዱ አንዱን ያላጠፋበት ፣ [67]የአንዱ ገንዘብ የሌላው የሆነበት ፍጹም ተዋሕዶ ነው። በጋብቻ የተመሰለው ይህ የአምላክና ሰው ተዋሕዶ ከምሳሌነት ባሻገር ለጋብቻ ትምህርት የሚሆን ተዋሕዶ ነው።

መለኮት ሁሉ የርሱ የሆነ ባዕል ነው ፤ ሥጋ ደግሞ አንዳች የሌለው ነዳይ ነው። ሆኖም መለኮት የሥጋን ባሕርይ ሲዋሐድ የሥጋን ንዴት /ማጣት/ የራሱ አደረገ ፤ ሥጋም ከመለኮት ባሕርይ ጋር በመዋሐዱ የመለኮትን ብዕል /ሀብት/ የራሱ አድርጓል። መለኮት ሥጋን አላቃለለውም ፤

[67] እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል



Scanned by CamScanner

አከበረው ከፍ ከፍ አደረገው እንጂ፡፡ በጋብቻ የሚዋሐዱ ሁሉም ከዚህ ተዋሕዶ አንዱ የአንዱን ጉድለት መሙላትን መማር ይገባቸዋል፡፡

የመለኮት የሥጋን ተዋሕዶ አስመልክቶ የሐሰት ትምህርት ያስተማሩ መናፍቃን ነበሩ፡፡ ከእነዚህ አንዱ በጉባኤ ኤፌሶን የተወገዘው የንስጥሮስ ክህደት /Nestorianism/ አንዱ ነው፡፡ ንስጥሮስ የመለኮትና የሥጋን ፍጹም ተዋሕዶ ባለማመን ‹መለኮት እና ሥጋን በሁለትነት አብረው ሆኑ እንጂ አልተዋሐዱም› በማለት ክዷል፡፡ በወቅቱ የነበሩ ሊቃውንትም ‹ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ› የሚለውን ምሥጢር በማብራራት መልስ ሠጥተው አልሰማ ሲል አውግዘው ለይተውታል፡፡ በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት በመንፈስ ፣ በሃሳብ ፣ በአኗኗር አንድ ሳይሆኑ ተጋብተው እንደ ደባል አብረው ከኖሩ ጋብቻቸው የተዋሕዶ ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ ንስጥሮሳዊ ጋብቻ ይሆናል፡፡

‹እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው› የሚለውን የመጽሐፍ ትእዛዝ ጥሰው የተዋሕዶ ምሳሌ በሆነው በባልና ሚስት አንድነት መካከል ገብተው ነገር የሚሠሩ ፣ አንድ የሆኑት ባልና ሚስት ሊለያዩ የሚሞክሩ ፣ የሐሰት ወሬን እየነዙ ባልና ሚስትን የሚያለያዩ ሰዎች ስላልታወቀባቸው ያልተወገዙ የዘመናችን ንስጥሮሶች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በተዋሕዶ ላይ የተነሣው ኑፋቄ ደግሞ የአውጣኬ ክህደት /Eutychianism/ ነው፡፡[68] በዚህ ሰው የክህደት ትምህርት ደግሞ ‹መለኮት ሥጋን

[68] አንዳንድ መጻሕፍት ከታሪክ አንጻር ይህን ክህደት አውጤኪስ አልተናገረውም የሚል ሃሳብ ያነሳሉ፡፡ ሆኖም እሱ ተናግሮትም ባይሆን እንኳን ሃሳቡ ልክ እንዳልሆነ ሁሉም ስለሚስማማበትና ይህ ጽንሰ ሃሳብም (Theory) በእርሱ ስም ኤውቲኪሳዊነት ተብሎ ስለሚታወቅ በአሰያየሙ ላይ የተለየ ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ በሚታወቅበት ተጠቅሜአለሁ፡፡ N.C. Samuel ; The Council of Chalcedon Re-examined ppg. 201/

ቀጠው መጠጠው› የሚል ሲሆን አምላክ የሥጋን ባሕርይ እንዳሸነፈው እንደሠለጠነበት› የሚያስተምር ነው።[69] በጋብቻ ሕይወት ባል የሚስትን ማንነት በሚያጠፋ የበላይነትን ካሳየ ፣ ሚስት የባልዋን ማንነት የሚያጠፋ ገዥነት ካሳየች ጋብቻው ለተዋሕዶ ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ አውጣኪያዊ ጋብቻ ይሆናል። በትዳር ምክንያት ማንነታቸው የተለወጠ ፣ እንደ ከዋክብት ያበሩ እንዳልነበር ድንገት ተውጠው የቀሩ ብዙዎች ናቸው። ይህ ግን የመንፈሳዊ ጋብቻ ጠባይ አይደለም። ለመለኮትና ሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌ የሆነው እውነተኛው ጋብቻ ባልና ሚስት በተዓቅቦ /በመጠባበቅ/ ማንነታቸውን ሳያጡ የሚዋሐዱበት ሲሆን ነው።

የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ የተደረገው አንድ ጊዜ ሲሆን ይህ ተዋሕዶ በምንም ምክንያት ዳግመኛ ወደ መለያየት የማይመጣ ‹ሚጠት› የሌለበት ነው። ለዚህ ተዋሕዶ ምሳሌ የሆነው ጋብቻም እንዲሁ ከተፈጸመና ባልና ሚስት አንድ ከሆኑ በኋላ ወደ መፋታትና መለያየት መመለስ የለባቸውም። «መፋታትን እጠላለሁ» ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። (ሚልክ. ፪፥፲፮)

## ○ ወይን እኮ የላቸውም... ጊዜዬ ገና አልደረሰም

የቃና ዘገሊላ ታሪክ ምሥጢራዊ ትርጓሜ እንዳለው ከሚያስረዱ ክፍሎች አንዱ የእናትና ልጅዋ ጥያቄና መልስና ከዚያ በኋላ የተከናወነው

[69] "The Divine nature absorbed human nature"

ነገር ነው። ጌታችን እናቱ ‹ወይን የላቸውም› ብላ ስትለምነው ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ካለ በኋላ ወዲያው ጋኖቹን ውኃ ሙሉ ብሎ ውኃን ወይን አድርጓል። በእርግጥ ጊዜዬ አልደረሰም ያለው ተአምር ለማድረግ ከሆነ ለምን ወዲያው ተአምሩን ፈጸመ? ወይስ የምኑ ጊዜ ነው ያልደረሰው? ማድረጉ ካልቀረስ ለምን ጊዜዬ አልደረሰም አለ? ያስብላል።

መጽሐፍ ቅዱስን ከብሉይ እስከ ሐዲስ ስንመረምር ስለ ወይን ጠጅ ከተነገሩት ቃላት ብዙዎቹ ስለ መጠጥ ብቻ የተነገሩ አይደሉም። በመጽሐፈ መሳፍንት በሰውኛ ዘይቤ የወይን ጠጅ ስለራሱ የተናገረበት ታሪክ እንዲህ ይላል። ‹‹ዛፎችም ወይኑን፦ መጥተህ በላያችን ንገሥ አሉት።ወይኑም። እግዚአብሔርንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው።›› (መሳ.፱፥፲፫) በዚህ ቃልም ወይን ጠጅ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለሰዎች ትፍስሕት /ደስታ/ እንደሆነ እንረዳለን። ቅዱስ ዳዊትም ‹ወይን የሰውን ልብ ያስደስታል› ሲል ልጁ ሰሎሞን ደግሞ «ነፍሱን ለመረረው የወይን ጠጅ ሥጡት ፤ ይጠጣ ድህነቱን ይርሳ ጉስቁልናውን ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ» ብሏል። (መዝ. ፻፫፥፲፭ ፤ ምሳ.፴፩፥፯) ማኅሌተ ጽጌ ደግሞ «ወይን የማይጠጣ ሰው ሕይወቱ ምንድር ነው? ሲራክ የልብ ደስታ ነው ብሏልና!» (ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንትኑ ሕይወቱ ፤ ሲራክ ይቤ እስመ ትፍስሕተ ልብ ውእቱ) ይላል። እነዚህ ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ወይን ጠጅ ብቻ ቢነገሩ ኖሮ እጅግ አስደንጋጭ ይሆን ነበር። ትርጓሜው ግን ከሥጋዊው መጠጥ የላቀ ነው።

በምሥጢር የወይን ጠጅ ተብሎ የተጠራው ነፍሱ በኃጢአት ለተመረረ ሰው ሊሠጥ የሚገባው እውነተኛ መጠጥ ‹ከኃጢአት ሁሉ የሚያነጻ›ን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። (የሐ.፮፥፶፭ ፤ ፩ዮሐ. ፩፥፯) ከወይን የሚገኘው ደስታ

ደግሞ በክርስቶስ በደሙ ፈሳሽነት የሚገኘው የመዳን ደስታ ምሳሌ ነው። ይህንን ደስታ የፈለገው ቅዱስ ዳዊት ‹‹የማዳንህን ደስታ ስጠኝ›› ሲል ልጁ ድንግል ማርያም ደግሞ «መንፈሴም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል» በማለት ጸልያለች። /መዝ. ፶፥፲፪ ፤ ሉቃ. ፩፥፵፯/

ስለዚህ ‹ወይን እኮ የላቸውም› የሚለው ልመና መዳንን ለሚሹ ለሰው ልጆች ሁሉ ‹አድናቸው የሕይወት መጠጥ የሆነ ሥጋህን ደምህን ሥጣቸው› ማለት ነበር። ጌታችንም ‹ጊዜ ገና አልደረሰም› ማለቱ ‹በመስቀል ላይ ተሰቅዬ የመድኃኒት መጠጥ የሆነ ደሜን የምሠጥበት ፣ የማድንበት ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ሲል ነበር። /ወን.ትር.ዘዮሐ./ ሊቃውንቱ እንደሚከተለው ተባብረው ይተረጉሙታል።

«ይህንን የሚለው ከሦስት ዓመታት በኋላ ስለሚፈስሰውና በእርሱ ለሚያምኑ ለአዳም ልጆች ሁሉ ይሠጠው ዘንድ ስላለው ስለ ደሙ ወይን ነው ፤ ለእናቱ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ጊዜዬ ገና አልደረሰም ያላት ለዚህ ነው» «ዘንተኒ ዘይቤ በእንተ ወይነ ደሙ ዘይትከዓው በጊዜ ሕማሙ እምድኅረ ሠለስቱ ዓመት ዘሀለዎ ይሁቦሙ ለኩሎሙ ውሉደ አዳም እለየአምኑ ቦቱ ወበእንተዝ ኢበጽሐ ጊዜየ ይቤላ ለእሙ እግዝእትነ ማርያም ድንግል» (ስንከሳር ጥር ፲፪ ቁ.፴፬)

አባ ጊዮርጊስ ደግሞ እንዲህ ይላል «ጊዜዬ አልደረሰም ያለው የአባቴን ድንቅ ተአምራት በምድር ላይ የምገልጥበት ፣ ካንቺም በነሣሁት ሥጋ ረሃብንና ጥምን ጭንቁንም ሁሉ የምቀበልበት ፣ በአመንዝሮች የምዳሰስበት ሦስት ዓመታት ቀርተውኛልና ከኃኔ በፊሰስ የምሥጢር ወይን ምእመናንን የማረካበት ጊዜዬ ገና አልደረሰም ተብሎ ይተረጎማል» (መጽ.ምሥ.፯፥፬)

በዮሐንስ ወንጌልም በተደጋጋሚ ‹ጊዜዬ/ጊዜው አልደረሰም› ተብሎ የተነገረው ጌታችን ስለሚሰቀልበት ጊዜ ነበር። «ስለዚህ ሊይዙት ይፈልጉ ነበር፤ ነገር

ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አልጫነበትም።» «ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር በግምጃ ቤት አጠገብ ይህን ነገር ተናገረ፤ ጊዜው ገና አልደረሰምና ማንም አልያዘውም።» (ዮሐ.፯፥፴ ፤ ፰፥፳) ጊዜዬው ሲደርስ ደግሞ «አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ።» «ኢየሱስም ከፋሲካ በዓል በፊት፥ ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ ደረሰ አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው።» «አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል» ይላል:: (ዮሐ.፲፪፥፳፯ ፤ ፲፫፥፩ ፤፲፯፥፩)

ይህ ምሥጢራዊ ትርጓሜ እንዳለ ሆኖ የወንጌሉን ታሪክ በማስተዋል ብቻ እንኳን ጌታችን ጊዜዬ ገና አልደረሰም ያለው ስለሚሰቀልበት ጊዜ መሆኑን መረዳት እንችላለን:: ጌታችን እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስ በአደባባይ ተአምራትን እንዳላደረገ ቀደም ባሉት ምእራፎች ተመልክተናል:: የቃናው ተአምር የመጀመሪያው የአደባባይ ተአምር ነው:: በዚህ ተአምር ተሰውሮ የቆየውን ‹ክብሩን ገልጦአል› በዚህም ምክንያት ዝናው በሁሉ ዘንድ ተሰምቷል:: ይህ ዝናው በተሰማ መጠንም የአይሁድ በምቀኝነት መነሣሣት ተከትሎ በመጨረሻ ለመስቀል ሞት አድርሶታል:: እመቤታችን ልጅዋ ተአምር እንዲያደርግ ስትጠይቀው በተዘዋዋሪ ወደ መስቀል የሚያደርገውን ጉዞ እያስጀመረች ነበር:: በሁለቱም መንገድ የእመቤታችን ጥያቄ ወደ መስቀል የሚያመለክት በመሆኑ ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› የሚያሰኝ ነበር::

እመቤታችን በቃና ዘገሊላ ‹ወይን እኮ የላቸውም› በሚለው ንግግሯ በምሥጢር ‹ደምህን ሥጣቸው› ብላ እንደለመነች ሁሉ በዕለተ አርብ ደግሞ ከመስቀሉ ሥር ቆማ እንደ ቃናው ወይን ጠጅ የልጅዋ ደም ለዓለም ድኅነት ሲፈስስ ተመልክታለች:: ልጅዋም በቃና ዘገሊላ የለመነችው ልመና



Scanned by CamScanner

እንደተፈጸመ በሚያስታውስ ሁኔታ በዚያ ሰርግ ቤት በጠራበት አጠራር መስቀል ላይ ሆኖ «አንቺ ሴት» ብሎ ጠርቷታል፡፡ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ወይኑ ሲቀዳ ከጌታ ጋር የነበሩት ደቀመዛሙርት በዕለተ አርብ ደሙ ሲቀዳ ግን አልተገኙም፡፡ ጌታችን ተላልፎ በተሠጠባት ምሽት ደቀመዛሙርቱን «ለአንዲት ሰዓት እንኳን ከእኔ ጋር ልትተጉ አልቻላችሁም?» ብሎ እንደተናገራቸው በመከራው ጊዜ አብረውት ሊተጉ አልቻሉም፡፡ እመቤታችን ግን እስከመጨረሻው ሰዓት አብራው ልትተጋ ችላለች፡፡ የልጅዋን ሥቃይ እያየች ተሠቃይታለች፡፡ እናት[70]የልጅዋን ሥቃይ ስታይ የሚሰማት ሁሉ ተሰምቷታል፡፡



ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ከሁሉ ተለይቶ ጌታውን ተከተለ፡፡ በዚህም ትልቅ ሥጦታን ይህችውም ‹ጾጋ ወሀብት› የምትባል እመቤታችንን ተቀበለ፡፡ ሳታውቀው ለልጆችዋ ሞትን በምትለምነዋ እናቱ በማርያም ባውፍልያ ፈንታ ‹ለነፍሳችን ሕይወትን የምትለምነዋን› እናት ተቀበለ፡፡ (‹ሰአሊት ለነፍሳቲነ ሕይወተ› እንዲል) በምድር ላይ ሲመላለስ መኖሪያ ቤት ፣ ገንዘብ ፣ ሀብት ንብረት ያልነበረው እና ልብሱን እንኳን በወታደሮች የተገፈፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለወዳጁ ለዮሐንስ ኑዛዜ ሲናዘዝ ፈልጎ የቀረችው ሀብቱን ፣ ገንዘቡን ፣ ቤቱን ድንግል ማርያምን ተናዘዘለት፡፡

---

[70] ‹ሑሱ ተሰቀለ እንጂ እስዋ ምን ሆነች?› የሚሉ ሰዎች አስተሳሰባቸው የዲያቢሎስን ይመስላል፡፡ ኢዮብ ዐሥር ልጆቹ ሲሞቱበት ‹እግዚአብሔር ሠጠ እግዚአብሔር ነሣ› ባለ ጊዜ ዲያቢሎስ «ቁርበት ስለ ቁርበት ነው» ብሏል፡፡ በዲያቢሎስ አስተሳሰብ ወላጅ ልጁ ቢሞትም እሱ እስካልተነካ ድረስ አይሰማውም፡፡ ኢዮብስ ልጆቹ ሲሞቱ አላየም ! እመቤታችን ግን ሥቃዩን አይታለች፡፡ የእሱ ሥቃይ እስዋን አይነካም የሚሉ ሰዎች ሃሳቡን ከየት እንዳገኙት ግልጽ ነው፡፡

ለዓለም ሁሉ የተሠጠው ‹ወይን› የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በዕለተ አርብ ከተሠጠ በኋላ አልቆመም፡፡ ዛሬም ድረስ ወደ እኛ እየፈሰሰ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንጠጣዋለን። ውኃውን ወይን ያደረገው አምላካችን ዛሬም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወይኑን ደም እያደረገ ዕለት ዕለት ይሠጠናል። ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም እንዲህ ይላል ‹‹እርሱ አንድ ጊዜ በቃና ዘገሊላ ውኃውን ወይን አድርጎ ነበር፡፡ ይህም የደሙ ምሳሌ ነው፡፡ ታዲያ ወይኑን ወደ ደም ቢለውጥ ምን ይደንቃል? ወደ ሥጋዊው ሰርግ ቤት ተጠርቶ እንዲህ ያለ ድንቅ ሥራ ከፈጸመ ወደ ሙሽርነቱ እልፍኝ ልጆች ወደ እኛ በጠራነው ጊዜ ምን ያህል የሥጋና ደሙን ፍሬ ይመግበን ይሆን? ›› (St. Cyril of Jerusalem, *Catechetical Discourses*, XXII, 2)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትም ቅዳሴ የሚጀምሩት እንዲህ እያሉ ነው ፡-

«ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን እግዚእነ ዘሖርከ ውስተ ከብካብ አመ ጸውዑከ በቃና ዘገሊላ ወባረከ ሎሙ ወረሰይኮ ለማይ ወይነ ከማሁ ረስዮ ለዝንቱ ወይን ዘንቡር በቅድሜከ

ወይእዜኒ ባርኮ ወቀድሶ ወአንጽሖ ይኩን ለሕይወተ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ በኵሉ ጊዜ፤ ሀሉ ምስሌነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወምላእ ወይነ ትፍስሕት ወሐሴት ለሠናይ ወለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለልቡና ወለፈውስ ወለምክረ መንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን»

«እውነተኛ አምላካችን ጌታችን ክርስቶስ ሆይ የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና በጠሩህ ጊዜ ወደ ሰርግ የሔድህ ውኃውንም ባርከህ ጠጅ ያደረግህላቸው በፊትህ የተቀመጠ ይህንን ወይን እንደርሱ አድርገው፡፡ አሁንም ባርከው አከብረው አንጻው ሁልጊዜ የሥጋችንና የነፍሳችን የልቡናችንም ሕይወት ይሆን ዘንድ፡፡



Scanned by CamScanner

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ከእኛ ጋር ኑር፡፡ ለተድላና ለደስታ የሚሆን ወይኑንም ለበጎ ነገር ምላው፡፡ ለሕይወትና ለመድኃኒት ለኃጢአትም ማስተሥረያ ለማስተዋል ለደኅንነት ለመንፈስ ቅዱስም ምክር ዛሬ ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን!!» /መጽሐፈ ቅዳሴ ፫፥፲፮/

## ○ ሁለቱ የቃና ሰርግ ቤት ወይን ጠጆች

ከላይ እንደተመለከትነው ‹ወይን እኮ የላቸውም› የሚለው የእመቤታችን ልመና ምሥጢራዊ ትርጓሜው በዕለተ አርብ ስለተሠጠው ስለ እውነተኛው መጠጥ ስለ ደመ ክርስቶስ ነው፡፡ በቃና ሰርግ ቤት ጌታችን ስለ ምሥጢራዊው ወይን ‹ጊዜዬ ገና አልደረሰም› ቢልም በሰርግ ቤት የሚጠጣውን ወይን ግን እዚያው ሠጥቷል፡፡ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ እውነተኛው ወይን ደመ ክርስቶስ ከመሠጠቱ በፊት የተሠጠው የቃና ዘገሊላ ወይን ጠጅም የራሱ የሆነ ምሥጢራዊ ትርጓሜ አለው፡፡

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት በአጠቃላይ ሁለት ዓይነት የወይን ጠጅ ቀርቦ ነበረ፡፡ የመጀመሪያው የወይን ጠጅ አስቀድሞ የቀረበውና በኋላ መናኛ የተባለው ጠጅ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ጠጅ ደግሞ የበፊቱን ያስናቀው መልካም የወይን ጠጅ ነው፡፡ የመጀመሪያው ወይን ጠጅ አስቀድሞ ለሰው ልጅ የተሠጠችው የኦሪት ሕግ ምሳሌ ሲሆን ሁለተኛው መልካም የወይን ጠጅ ደግሞ የሕገ ወንጌል ምሳሌ ነው፡፡ ሙሽራ የተባለው ደግሞ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

አባ ጊዮርጊስ እንዲህ ይላል ‹‹የቃና ወይን በኦሪት ሕግ ተመሰለች ፤ የጠጡአትን አላጸደቀቻቸውምና፡፡ ነገር ግን በመዓዛዋ ጣፋጭነት ልባቸውን ደስ አሰኘች፡፡ /ግአሰከረቻቸው/ ኦሪትም ቀድመው የተቀበሏትን አላጸደቀቻቸውም ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ናትና እርስዋን በመስማት ልባቸውን ደስ አሰኘች፡፡›› ‹‹ወይነ ቃናሰ ተመሰለት በሕገ ኦሪት እስመ ኢያጽደቀቶሙ ለእለ ሰተይዋ ወባሕቱ አስተፍስሐት በጣዕመ መዓዛሃ ፤ ወከማሁ ኦሪትኒ ኢያጽደቀቶሙ ለእለ ተወከፍዋ ቀዲሙ ፤ ባሕቱ አስተፍስሐት አልባቢሆሙ በአጽምኦታ እስመ ቃለ እግዚአብሔር ይእቲ››/ (አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፥፩)

በኋላ የተሠጠችው መልካም የወይን ጠጅ አዲሲቱ ሕግ ወንጌል ናት፡ ፡ ስድስት ጋኖች በዚህ ሰርግ ቤት ውኃ ተሞልተው ወይን እንደተሞላባቸው በስድስተኛው ሺህ ‹እንደ ድንጋይ በፈዘዘው› በሰው ልጅ ልብ ውስጥ የተሞላችው አዲሲቱ ወይን ጠጅ ሕገ ወንጌል ነበረች፡፡ አሳዳሪው ደግሞ በሰማያዊው ሰርግ ቤት ሁሉን በእቅፉ የሚያስተናግደው እንግዳ ተቀባዩ አብርሃም ነው፡፡ የቃናው አሳዳሪ ወይኑን ቀምሶ ደስ ሲለው «ሰው አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል ፤ ከሰከሩ በኋላ መናኛውን ፤ አንተ ግን መልካሙን የወይን ጠጅ እስካሁን አቆይተሃል!» ብሎ ለሙሽራው ተናግሮ ነበር፡፡ አብርሃምም አዲሲቱን የክርስቶስ ወንጌል ባየ ጊዜ ተደስቶ ለሙሽራው ክርስቶስ «መልካሚቱን ሕግ እስካሁን አቆይተሃል!» ብሎ አድንቋል፡፡ «አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴትን አደረገ ፤ አየም ደስም አለው»

[71] ‹‹ስኩራነ መንፈስ ነቢያት›› «በመንፈስ የሰከሩ ነቢያት» እንዲል /ሰዓታት ዘሰሎሞን/

እንዳለ ጌታ። (ዮሐ. ፳፥፺፮) ቅዱስ አውግስጢኖስም «[72]መልካሙን የወይን ጠጅ እስካሁን አቆይተሃል ተብሎ የተነገረው ሙሽራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ አዲቱን ወይን ወንጌልን እስከ አሁን አቆይቷታልና።» ብሏል።

## ፪. የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደ ጋብቻ

### ○ የአዳምና ሔዋን ጋብቻ

ልዑል እግዚአብሔር በስድስቱ ዕለታት ፍጥረታትን እንደፈጠረ በተጻፈበት አንቀጽ ሁሉ «እግዚአብሔርም የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ» ይላል። ለእግዚአብሔር መልካም ሆኖ ያልታየው አንድ ነገር ብቻ ነበር- የሰው ብቻውን መሆን። ስለዚህ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» በማለት ለመጀመሪያው ሰው አዳም ረዳትን ሔዋንን ፈጠረለት።

እግዚአብሔር ሔዋንን ሲፈጥር አዳምን ለመፍጠር እንዳደረገው ከምድር አፈር አላነሣም። ከአዳም ጎን አንዲትን አጥንት ብቻ ወስዶ ሴት አድርጎ ሠራት። (ዘፍ. ፪፥፳፩) ኦሪት ዘፍጥረት የሴትን መፈጠር የሚናገረው ግን ከአዳም ጎን ስትፈጠር የነበረውን ሁኔታ ሲተርክ ብቻ አይደለም። ከዚህ አስቀድሞ ‹‹እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው

[72] "The Bridegroom who was told 'thou hast kept the good wine until now.' is The Lord Jesus Christ who has preserved the New wine - that is the Gospel - until now" St. Augstine /Commentary On the Gospel According to John ii/



Scanned by CamScanner

ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡›› ተብሎ ተጽፎአል፡፡ (ዘፍ. ፩፥፳፯) ‹ወንድና ሴት› ተብሎ የተነገረው ሔዋን አዳም ሲፈጠር ከጎኑ ተፈጥራ ስለነበር ነው፡፡[73]

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ስለዚህ ሲናገር «አዳም አንድም ሁለትም ነበረ፡፡ ወንድ እንደመሆኑ አንድ ነው፡፡ ወንድና ሴት እንደመሆኑ ሁለት ነው፡፡» ይላል፡፡ አክሎም «ሙሴ ሔዋን ከጎኑ ባለው አጥንት ምክንያት በአዳም ውስጥ ስለነበረች ‹ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው› ብሎ ጻፈ፡፡ ምንም እንኳን በኅሊናው ውስጥ ባትኖርም በአካሉ ውስጥ ነበረች፡፡ ከእርሱ ጋር የነበረችው በአካሉ ብቻ አልነበረም፡፡ በነፍስና በመንፈስም ከእርሱ ጋር ነበረች፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር [74]ከአዳም ጎን የወሰደውን አጥንት አበጃጅቶና አሳመረው እንጂ ምንም አልጨመረበትም፡፡ ለሔዋን የሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ በአጥንቱ ውስጥ ተሟልቶላት ነበር፡፡ ለዚህም ነው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ያለው፡፡» በማለት ያብራራል፡፡ (St. Ephraim the Syrian, *Commentary on Genesis,*1.29) ከዚህ የምንረዳው የአዳምና ሔዋን ጋብቻ የባዕዳን ጋብቻ ሳይሆን አብረው የተፈጠሩ አካላት ዳግም ተዋሕዶ /reunion/ መሆኑን ነው፡፡

ቅዱስ ሄሬኔዎስ ‹በእንተ ስብከት ሐዋርያዊት› በሚለው ስብከቱ ላይ እንደገለጸው «የሰው ልጅ በገነት ሲኖር እንቅልፍ የሚባል ነገር አያውቅም ነበር፡፡» ሆኖም «ግርማንና ውበትን የተጎናጸፈው እና እስካሁን እንቅልፍን የማያውቀው ሰው በመሬት ላይ ዕርቃኑን ተኝቶ አንቀላፋ ...» ይላል ቅዱስ ኤፍሬም (St. Irenaeus On the Apostolic Preaching 13 ; St. Ephrem Commentary On Genesis 2:12)

---

[73] ፈረንጆቹ የሔዋን የልደት ቀን ሁለት ነው እያሉ በቀልድ መልክ ይህንን ሃሳብ ያብራራሉ፡፡
[74] "The first case of human cloning!' /Creation , Fr. Athanasius Iskander : ppg 82/



Scanned by CamScanner

እግዚአብሔር ሔዋንን ሊፈጥር በወደደበት ሰዓት በመጀመሪያ በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ትርጓሜው የአዳምን ሁኔታ ‹‹እኔ ተኝቻለሁ፥ ልቤ ግን ነቅቶአል›› ከሚለው ጥቅስ አገናኝቶ አብራርቶታል፡፡ /መኃ. ፭፥፪/ አዳም ምንም በሥጋው ቢተኛ ነፍሱ ከሥጋው ስላልተለየች እግዚአብሔር ከጎኑ አጥንት እንደወሰደ ይታወቀው ነበር፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ለአዳም ሁሉ ነገር ይታየው የነበረው በሕልሙ ነው ብሎ ተርጉሞታል፡፡ (*Commentary on Genesis*,2.12) ጠርጡለስም «እንቅልፍ ዕረፍትን የሚሠጠው ለሥጋ ብቻ ነው ፤ በአዳም ላይ የተጣለው ከባድ ሰመመን ግን ነፍስን ከዕረፍት የሚያነቃ ዓይነት ነው፡፡ ይህ ሁኔታም በተፈጥሮ ሕልም የሚታይበትን ከስተት ይፈጥራል» ብሏል፡፡ ( Tertullian *On the Soul*, 45.1-3 ; The Theology Of Eros ; Vladmir Moss)

አዳም ሔዋን ከእርሱ በሚወሰድ አጥንት ስትፈጠር ነቅቶ እያየ ቢሆን ኖሮ ምንም ቢሆን አጥንትን ያህል ነገር ከጎኑ ሲወሰድ ሕመም መሰማቱ ስለማይቀር በእርስዋ ምክንያት የደረሰበትን ሥቃይ ሲያስታውስ ጥላቻ ሊያድርበት ይችል ነበር፡፡ ስለዚህ ሒደቱ አዳም አንዳች ሕመም ሳይሰማው ተከናወነ፡፡ (መጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ ዘፍ. ፪፥፳፪ ፤ St. John chrysostom, To Genesis, Homily 15) ‹ከባድ እንቅልፍ› የሚለውን ቃል በሰባው ሊቃናት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በግሪኩ ‹ኤካስታሲ› / ecstasy/ የሚል ሲሆን በዕብራይስጡ ደግሞ ‹አናስቴዥያ› /anaesthesia/ ይላል፡፡ ‹አናስቴዥያ› ዛሬም ድረስ የቀዶ ሕክምናን ያለ ሕመም ስሜት ለማከናወን የሚደረገው ዘመኑ የደረሰበት የሕክምና አጋዥ የሆነው የ‹ማደንዘዣ› ሳይንሳዊ መንገድ የሚጠራበት ስያሜ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ



Scanned by CamScanner

ግን በመጀመሪያው ሰው ላይ የተከናወነው አጥንትን አውጥቶ ሥፍራውን በሥጋ የመዝጋት ሥራ በዚህ ጥበብ የተከናወነ ነበር።

ሔዋን ለአዳም ምን ናት? ብንል አብራው በመፈጠርዋ እኅቱ ፣ ከጎኑ በመውጣትዋ ልጁ ፣ ረዳት እንድትሆነው በመሠጠትዋ ሚስቱ ፣ ከእርሱ በመገኘትዋ አካሉ ናት። ሔዋን ከአፈር ተፈጥራ ቢሆን ኖሮ አዳም ‹አጥንቴና ሥጋዬ ናት› ብሎ አይቀበላትም ነበር። ባዕድ ያደርጋትም ነበር። ምናልባትም አንድ አባት እንዳሉት እግዚአብሔር ሔዋንን ከመሬት ፈጥሮ ወደ አዳም ቢያመጣት ኖሮ ፤ ለአዳም ሔዋን ስም ከሚያወጣላቸው ሌሎች እንስሳት አንዷ መስላው በለመደ አንደበቱ ስም አውጥቶ ይተዋትም ይሆናል።[75] ስለዚህ አዳም በተኛበት ከጎኑ አንዷትን አጽም በመውሰድ የሰው ልጆች እናት የሆነች ሔዋንን ፈጠራት።

አዳም ከጎኑ የተፈጠረችውን ሔዋንን እግዚአብሔር ወደ እርሱ ባመጣለት ጊዜ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ይህች ሥጋም ከሥጋዬ ናት ፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።» አለ። አስከትሎም «ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» አለ። ምዕራፉ የሚያበቃው ‹አዳምና ሔዋን ዕርቃናቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር› በማለት ነው።

በዚህ የአዳም ንግግር ውስጥ ስለጋብቻ እጅግ ብዙ ቁምነገሮች ተቀምጠዋል። የመጀመሪያው ሃሳብ ጋብቻ ሰው እናትና አባቱን የሚተውበት እና ከሚስቱ ጋር የሚተባበርበት መሆኑን ነው።

[75] Creation ; Fr. Athanasius Iskander , ppg 82



Scanned by CamScanner

*ይህም ባል ወደ ትዳር ሲመጣ ከቤተሰባዊ ትስስሩ ተላቅቆ ወደ ትዳሩ ማዘንበል እንዳለበት ያሳያል። ይህ ትእዛዝ ‹ሰው ... ከሚስቱ ጋር› ስለሚል ሴቶችን አይመለከትም ማለት አይደለም። የቅዱስ ዳዊት መዝሙር ትርጓሜውን ትተን በጥሬ ንባቡ ብቻ ስንመለከተው ለአንዲት ሙሽሪት «ልጄ ሆይ ስሚ አዩም ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽንና የአባትሽን ቤት ርሺ ፤ ንጉሥ /ባልሽ/ ውበትሽን ወድዷልና» ሲል እናገኘዋለን። በዚህም ቤተሰብን ትቶ ለትዳር ቅድሚያ መሥጠት ሚስትንም የሚመለከት ትእዛዝ መሆኑን እንረዳበታለን። /መዝ.፵፬፥፲/*[76]

‹ከሚስቱም ጋር ይተባበራል› የሚለው ቃል በአማርኛውም መጽሐፍ ቅዱስ ሆነ በሌሎች ትርጉሞች ‹ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል› (he shall cling')ተብሎ እናገኘዋለን። ይጣበቃል የሚለው አገላለጽ የባልና ሚስትን ፍጹም አንድነት የሚገልጽ ነው። ሁለት የተጣበቁ ነገሮችን ለመለየት ሲሞከር ሁለቱም መጎዳታቸው የማይቀር ነው። ጋብቻም በፍቺ የሚለይ ከሆነ ሁለቱም ተጋቢዎች መቁሰላቸው የማይቀር ነው። የተጋቡ ሰዎች መለያየት የሚችሉት በሞት ብቻ ነው።

ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ አስተውሎታል «አንድ ሥጋ ይሆናሉ አለ እንጂ አንድ ነፍስ ወይም አንድ መንፈስ ይሆናሉ አላለም። የነፍስ ወይም የመንፈስ አንድነት ለማንኛውም ሰው የሚቻል ነው። (ያመኑትም አንዲት ነፍስ አንዲት ልብ ነበራቸው እንደሚል ሐዋ. ፬፥፴፪) ‹ሥጋ› እና ‹ይጣበቃል› የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ፍቅርን ነው።» / St. John Chrysostom, *Homily 20 on Ephesians*/

---

[76] ABC of Marriage ; Fr. Dawood Lemai ppg 3



Scanned by CamScanner

## ○ ክርስቶስ እንደ አዳም ፤ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሔዋን

አዳም በብሉይ ኪዳን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች ከሆኑ ሰዎች አንዱ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።›› በማለት ክርስቶስን ‹ኋለኛው አዳም› በማለት ሲጠራው ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ደግሞ «የነቢያት ሀገራቸው ቤተልሔም ሆይ ደስ ይበልሽ ፤ ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ በአንቺ ተወልዷልና» በማለት ‹ሁለተኛው አዳም› ይለዋል፡፡ /፩ቆሮ. ፲፭፥፵፭ ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሰኑይ ቁ. ፯/

አዳምና ክርስቶስ በምን ተነጻጽረው ነው ጌታ ‹ሁለተኛ አዳም› የተሰኘው ቢባል በሁለት መልኩ ነው። አዳም ሳይበድል በፊት በገነት ሳለ የነበረውን ንጽሕና ጠባይዕ ይዞ በመወለዱ ክርስቶስ ዳግማዊ አዳም ተብሏል። በተቃራኒ ንጽጽር ደግሞ አዳም በኃጢአቱ የጎዳውን ሰው ሁሉ ጌታችን በትሩፋቱ አድኗል ፤ አዳም ለሞት ምክንያት ሆነ ክርስቶስ ግን ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ሕይወትን የሚሠጥ መንፈስ ሆነ፡፡ /ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ ፳፬/

የማይተኛው አዳም የሁላችን እናት የሆነችውን ሙሽራው ሔዋንን ለማስገኘት እንቅልፍ እንደተኛ ፤ የማይሞተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሁላችን እናት የሆነችውን ሙሽራው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከነምሥጢራትዋ ለማስገኘት በዕለተ አርብ የሞትን እንቅልፍ ተኝቶ ነበር። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ያስገኘውም በጦር በተወጋ ጊዜ ከጎኑ በፈሰሰው ደምና ውኃ ነው። በዚህ የጎን ውኃ ጥምቀትን ፣ በዚህ የጎኑ ደም ደግሞ ምሥጢረ ቁርባንን ሠጥቶ የሁላችን እናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አስገኝቷል። /መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት ፤ ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ/

አዳም በተኛበት ወቅት ከእርሱ ጎን የሚወጣው ነገር ይታወቀው ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዕለተ አርብ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ከጎኑ የሚፈስሰው ሁሉ በመለኮቱ ይታወቀው ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስ ስለዚህ ‹በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ› ሲል ተናግሯል ፤ እኛ ደግሞ በዕለተ አርብ ስቅለት «አ ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ» «በሥጋ ሞትን የቀመስከው ሆይ» እያልን እንሰግዳለን። /፩ጴጥ. ፫፥፲፰ ፤ ሥርዓተ ሕማማት/

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይተርከዋል። ‹‹ሔዋን ከራሱ ከአዳም ጎን እንደተገኘች ሁላችንም እናውቃለን። እግዚአብሔር በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍን እንደጣለበት ፣ ከአጥንቶቹ አንድ እንደወሰደና ሴት አድርጎ እንደሠራት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል። ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጎን እንደተገኘችስ እንዴት አድርገን ማሳየት እንችላለን? መጽሐፍ ቅዱስ ይህንንም ይገልጻል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ፣ በዚያ ላይ በተቸነከረና በሞተ ጊዜ ከወታደሮች አንዱ ጎኑን ሲወጋው ውኃና ደም ወጣ። ከዚያ ደምና ውኃ ቤተ ክርስቲያን ተገኘች። ስለዚህም ራሱ መስክሮ ነበር። «ሰው ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም።» መንፈስ ብሎ የጠራው ደሙን ነበር። በጥምቀት ውኃ እንወለዳለን። ደሙን እየጠጣን እናድጋለን። ተወልደን ያደግነው በውኃና በደሙ ስለሆነ ከሥጋውና ከአጥንቱ እንደተገኘን አያችሁ? አዳም ተኝቶ ሴት ከጎኑ እንደተሠራች ፤ ክርስቶስም ሲሞት ቤተ ክርስቲያን ከጎኑ ተመሠረተች።» /St.John Chrysostom, *Third Discourse on Marriage*/ ኢትዮጵያዊው ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስም ስለ ጌታችን የዕለተ አርብ ባስተማሩበት ድንቅ ትምህርታቸው «ከጎኑ በፈሰሰው ውኃ ዓለምን አጠመቀ ፤ ከጎኑ በፈሰሰው ደም ዓለሙን አቆረበ» በማለት ገልጸውታል። /www.youtube.com /Eotc television program/



Scanned by CamScanner

‹ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ› የሚለው ቃልም ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ክርስቶስ ጋብቻ የሚያስረዳ ነው፡፡ ሰው እናትና አባቱን ይተዋል እንደሚል እግዚአብሔር ወልድ ከባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ በተለየ አካሉ ፣ በትስብእቱ እናቱ ከምትሆን ከወላዲተ አምላክ እመቤታችን ተለይቶ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሚስቱ ከተባለች ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ሆኗል፡፡ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ እንደተባለም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ «አካሉና ሁሉን በሁሉ ለሚሞላ ለእርሱ ሙላቱ ናት፡፡» (ኤፌ. ፩፥፳፫) [77]አንድ ግሪካዊ ካህን «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ» የሚለውን የጌታችን የመስቀል ላይ ንግግር አንሥተው ሲያስተምሩም «ለምን ተውከኝ ለሚለው ንግግር እግዚአብሔር አብ ቢመልስ ኖሮ መልሱ ሙሽራ ስለሆንህ የሚል ይሆን ነበር» ብለዋል፡፡ ይህን ያሉበትም ምክንያት «ሰው እናትና አባቱን ይተዋል» የሚለው ቃል የተፈጸመው እግዚአብሔር አብን ትቶ ሙሽራው ክርስቶስ ከሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያን አንድ የሆነው በመስቀል ላይ ስለሆነ ነው፡፡ በእርግጥም መልሱን በዚህ አገባብ ስናየው ‹ሙሽራ ስለሆንክ› ብቻ ሳይሆን ‹እናትና አባቱን ይተዋል› ከሚለው አንጻር ‹የተውከኝ አንተም ነህ› የሚልም ሊሆን ይችላል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱም ራሱን እንደ ሙሽራ አድርጎ አስተምሯል፡፡ ደቀመዛሙርትህ ለምን አይጾሙም ተብሎ ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ «ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ አይጾሙም» በማለት መልሶአል፡፡ (ማቴ. ፱፥፲፭) ስለ ምጽአቱ ሲያስተምርም አመጣጡን በሙሽራ መምጣት ምሳሌ

[77] Fr. Thomas Hopko

አድርጎ አስተምሯል። (ማቴ.፳፭፥፩-፲፫) መጥምቁ ዮሐንስም «ሙሽራዪቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው» በማለት ምእመናንን /ቤተ ክርስቲያንን/ በሙሽራይቱ ክርስቶስን በሙሽራ መስሎ ተናግሯል (ዮሐ. ፫፥፳፱)

ይህ የክርስቶስ እና የቤተ ክርስቲያን አንድነት የተፈጸመው የሰርግ ዕለት በተባለው በዕለተ አርብ ነው። «እናንተ የጽዮን ቈነጃጅት፥ ውጡ እናቱ በሰርጉ ቀንና በልቡ ደስታ ቀን ያደረገችለትን አክሊል ደፍቶ ንጉሥ ሰሎሞንን እዩ።›› የሚለውን የትንቢት ቃልም ሊቃውንት ለዕለተ አርብ ይተረጉሙታል። ሰሎሞን የሰላማዊው ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። የጌታችን የሰርጉ ቀንና የልቡ ደስታ ቀን የተባለው ዓለምን ያዳነበት ዕለተ አርብ ነው። እናቱ ያደረገችለት አክሊል የተባለው ደግሞ እናቱ ቤተ አይሁድ የደፉለት የእሾህ አክሊል ነው። (መኃ.፫፥፲፩)

በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ጋብቻ እንደ ሚዜ የተመሰሉት ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው። ‹ጌታ ይመጣል› ብሎ በማስተማሩ ነቢይ ፤ ‹የእግዚአብሔር በግ እነሆ› በማለቱ ደግሞ ሐዋርያ የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ ‹‹ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምጽ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ።›› በማለት እርሱ ‹አርኩ ለመርዓዊ› /የሙሽራው ሚዜ/ መባሉን ተናግሯል። ጌታችን ደግሞ ስለ ጾመ ሐዋርያት ሲናገር ‹‹ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።›› በማለት የሐዋርያትን ሚዜነት ተናግሯል። ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ምእመናንን ለሙሽራው ክርስቶስ የማቅረብ ሓላፊነቱ አስጨንቆት ‹‹እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ



Scanned by CamScanner

ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና›› ካለ በኋላ ሚዜ ሙሽራዪቱን ወደ ሙሽራው ከነ ንጽሕናዋ ማድረስ ሓላፊነት እንዳለበት ሁሉም ‹‹ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።›› እያለ *ሥጋቱን* ይነግረናል:: (፪ቆሮ.፲፩፥፫)

አዳም ‹አጥንትሽ ከአጥንቴ *ሥጋሽም* ከ*ሥጋዬ*› ነው በማለት የተናገረው ሲተረጎም የቤተ ክርስቲያን *ሥጋዎ*ቿና አጥንቶቿ የሆንን እኛ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል ስትሆን አብረን አካል መሆናችንን የሚያስረዳ ነው:: ከቤተ ክርስቲያን በጥምቀት በመወለዳችንም የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎች ሆነናል:: ስለዚህ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ጋብቻ ተመልካቾች ብቻ ሳንሆን የክርስቶስ አካል ነን::

ንዋይ ኅሩይ ቅዱስ ጳውሎስ «ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ *ሥጋቸው* አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል:: ማንም የገዛ *ሥጋውን* የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይንከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ *ሥጋ* ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።» በማለት የጋብቻን ምሥጢር ከክርስቶስና ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ጋር አመሥጥሮ



Scanned by CamScanner

ተናግሯል፡፡ (ኤፌ. ፭፥፳፮-፴) በዚህ ጉዳይ ብዙ ሊቃውንት ሰፊ ትምህርት የሠጡበት ሲሆን ራሱን የቻለ ሌላ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ቤተ ክርስቲያን ከሙሽራዋ ክርስቶስ ጋር በሰማያዊው ኅብረት ለዘላለም እንድትኖር እድፍና የፊት መጨማደድ ሳይኖርባት መገኘት አለባት፡፡ አካላችን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አካል ነው፡፡ ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ‹ንጽሕት› መሆን አለባትና አካልዋም ንጹሕ ነው፡፡ የእርስዋ አካል ለመሆን እኛም ንጹሕ መሆን አለብን፡፡ ልብስዋና ጌጥዋ ለመሆን ደግሞ በንጽሕና ላይ ቅድስናና የጽድቅ ሥራን መጨመር አለብን፡፡ ሐዋርያው እንዳየት «የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ። ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቶአታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።» /ራእ.፲፱፥፯/

ይህ ሰርግ የሚደረገው ጌታችን ከአእላፋት መላእክቱ ጋር በሚመጣበት በዕለተ ምጽአት ነው፡፡ ዕለተ ምጽአት ሙሽራዪቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ምግባር አጊጣ የምትታይበት ፣ የጽድቅ ዘይት ይዘው መገኘት የቻሉ ልባሞች ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሰርጉን የሚታደሙበት ፣ እንደ ቃናው ደስታ በ‹‹ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች» የምንደርስበት ዕለት ነው፡፡ /ዕብ.፲፪፥፳፪/

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ የቃናን ሰርግ ከሰማያዊው ሰርግ ጋር አሰናስሎ ሲያመሰግን እንዲህ ይላል፡፡ «ወደ ሰርግ በዓልዋ ዕለት ደስታን ይዘህላት

ስለመጣህ ቃና ታመስግንህ! አከብረኸዋልና ሙሽራው የደፋው ዘውድ አንተን ያከብርሃል:: የሙሽራዋ አክሊልም የአንተን ድንቅ ሥራ ያደንቃል:: ቤተ ክርስቲያንህን በሙሽራዋ መስለሃታልና በቃና መስታወትነት ምሳሌዎች ሁሉ ትርጉማቸውን አገኙ:: የቃናዎቹ እንግዶች ደግሞ አንተ የመረጥሃቸው (ወደ ሰማያዊው ራት) የጠራሃቸው ናቸው:: ምጽአትህንም በሰርግ ቤቱ ደስታ መሰልከው::[78]» /The Harp of siprit/

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደ ሙሽራ አጊጣ ፣ ለበጉ ሰርግ ያለ እድፍና ያለ ነውር ውብ ሆና ተዘጋጅታ በምትቀርብበት በዚያ ሰማያዊ ሰርግ ለመገኘትና ወደ በጉ ሰርግ ራት ገብተን ፣ ካኄጡ ቅዱሳን ጋር ለመቀመጥና ለመብላት የበቃን ያድርገን::

«ያብአነ ቤተ መርዓሁ ውስተ ደብተራሁ ፤
አመ ይትጋብኡ ለምሳሕ ሥርግዋን ሐራሁ»
«ያኄጡት ወታደሮቹ ምሳ ሊበሉ ሲሰበሰቡ ፤
ወደ ሰርግ ቤቱ ድንኳን ውስጥ ያስገባን»

‹‹ሁልጊዜ ድል በመንሳቱ ለሚያዞረን በእኛም በየሥፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለእምላክ ምስጋና ይሁን!›› ፪ ቆሮ. ፪፥፲፬

[78] Let Cana thank You for bringing joy to her wedding feast. The bridegroom's crown honours You, since You honoured him, and the bride's crown shall adorn Your victory. In Cana's mirror parables find their explanation, for in the bride You depicted Your church, and in Cana's guests are those invited by You marked out, and in its festivity You depicted Your own coming.

## ዋቢ. መጻሕፍት


- ሃይማኖተ አበው ፤ 1982 ፤ አዲስ አበባ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው ፤ 1988 ዓ.ም. ፤ አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- ማኅሌተ ጽጌ ንባቡና ትርጓሜው ፤ 1998 ዓ.ም. ሊቀ ጠበብት አሰራደ ባያብል
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ፤ 1997 ዓ.ም አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ፤ 1948 ዓ.ም. አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት
- ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ፤ ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ
- መጽሐፈ ቅኔ /ዝክረ ሊቃውንት/ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ
- መርሐ ልቡና ፤ ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ
- መጽሐፈ ስንክሳር ፤ ማኅበረ ሐዋርያት ፤ አሥመራ
- መድሎተ አሚን መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ
- መዝገበ ሃይማኖት ነገረ ጉባኤያት
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
- ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው 1983 ዓ.ም. አዲስ አበባ ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- መጽሐፈ ምሥጢር ፤ 2001 ዓ.ም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ በአባ ጊዮርጊስና በአባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም
- መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው
- መጻሕፍተ ሐዲሳት ዘሠልስቱ ንባቡና ትርጓሜው 1989 ዓ.ም ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
- ድርሳነ ሚካኤል
- ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ፤ መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ 2002 ዓ.ም. አዲስ አበባ ፤ ካፍ ማተሚያ ቤት
- ትንቢተ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው ፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፤ 1916 ዓ.ም.
- መጽሐፈ ሰዓታት ንባቡና ትርጓሜው መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ
- ሕይወተ ወራዙት ቁ. ፪ ዲ/ን ኅብረት የሺጥላ
- ሦስቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ፤
- መጻሕፍተ ብሉያት ንባቡና ትርጓሜው
- መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት ፤ ምገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ
- ABC of Marriage ; Fr. Dawood Lemaie
- **Bible Dictionary** ; Paul j. Achtemeier ; 2009 Theological Publications In India Bangalore

- **Catholic Bible** , The king James version
- **Creation** ; Fr. Athanasius Iskander ; Kichner Ontario Canada
- **Commentary on the Gospel according to John** St. Cyril of Alexandria
- **Commentary On The Gospel according to John** ; St. Augstine
- **Commentary On The Gospel according to John** ; St. John Crysostom
- **Commentary On Genesis** St. Ephrem the Syrian
- **The Living God** /a catechism/ ; Volume 1 ; 1996 St. Vladmir Seminary Press
- **The Life of The Holy Virgin Mary** , The Theotokos ; 1989 Holy Apostles Convent
- **The Theology of Eros** ; 2011 , Vladimir Moss
- **The Early Years of Marriage** ; Peter M.Kalellis; Hellenic Community, Durban 1998
- **The Life of The Holy Virgin Mary;** Olga Moss
- **The Harp of The Spirit** ; Poems of St. Ephrem The Syrian
- **Oration on the Holy Baptism** ; St. Gregory the Theologian
- **On The Mother of God** ; St. Jacob of Serug
- **On the Apostolic preaching** ; St. Irenaeus
- **On the Soul**; Turtulin
- **Orthodox Study Bible** ; St. Athnasius Acadamy Septuagint 2008. St. Athnasius Acadamy of Theology
- **Parousia** Vol.Xvii ; On The Nicene and Post Nicene Fathers
- **Patrstic Commentary The Gospel According to John** Fr. Tadros Y.Malaty
- **Who is Christ to me?** Hegomen Matta Morgan of Alexandria




Scanned by CamScanner

ክብረ ክህነትና ታቦት በሐዲስ ኪዳን በሚሉ መጻሕፍቶቻቸው የምናውቃቸው መምህር ሄኖክ ኃይሌ ያዘጋጁት ይህ መጽሐፍ ለሁሉ በሚረዳ መልኩ ስብከትም ትምህርትም የሚገኝበት ነው፡፡ ባለማወቅ ለሳቱ መልስ የሚሰጥና ወደ ሃይማኖት የሚመልስ ፡ ለሚጠራጠሩ በሃይማኖት የሚያጸና ፤ በቃና ዘገሊላው ሰርግ ቤት የኢትዮጵያንም ሆነ የሌሎች ሀገራት ሊቃውንትን ሀሳብ በሰፊው የሚያሳይ ግሩምና ድንቅ መጽሐፍ ነው፡፡

መልአከ ሰላም ቆሞስ አባ ሰይፈ ገብርኤል ኦብሰን
የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ሓላፊ

ቃላት ከሚወክሉት ሃሳብ ጋር ተፈጥሮአዊ ዝምድና የሌላቸው መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል "የእግዚአብሔር ቃል" የምንለው ሰዎች ተግባብተን በምንጠቀምባቸው ቃላት በመገለጹ እንጂ መለኮታዊው መልእክት ሃሳቡን ወክለው በተቀመጡት ቃላት የሚወሰን ሆኖ አይደለም፡፡ የአንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ትርጉምም በአንድ መልእክት ብቻ የማይወሰነውም መለኮታዊ መልእክቱ ሁልጊዜም ከቃላቱ የሚያልፍ በመሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር በየጊዜው ለተነሡ ሊቃውንት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ተቀድተው የማያልቁ ምሥጢራትን ሲሠጥ መኖሩም ለዚህ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር ቀርቶ የውኃ ጉድጓድን ውሃ ቀድቶ መጨረስ እንዳይቻል ግልጽ ነው፡፡ የዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ «ቃና ዘገሊላ» መጽሐፍም የዚህ ሃሳብ አስረጅ ሆኖ አግኝቻታለሁ፡፡ ስለዚህም ወይነ ቃናን በዚህ መጽሐፍ የትርጉምና የመልእክት ስድስት ጋኖች (ምዕራፎች) ውስጥ እንድትጎነጩና መለኮታዊ መልእክት ተቀድቶ የማያልቅ መሆኑን እንድትመሰክሩ እጋብዛለሁ፡፡ የጌታ ወይነ ትምህርት የዶኪማስ (የዚህ ዓለም) ዕላቂ ወይን (ሃሳበ ሰብእ) ያልነካው ነውና፡፡

ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ

ቅዱስ ጴጥሮስ በስም መጥቀሱ ሳያንስ ‹የተወደደ ወንድማችን› ብሎ በመጥራት ስለ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ጥልቀትና ምጥቀት ምስክርነት ሰጥቷል፡፡ /፪ኛ ጴጥ. ፫፥፲፭/ ስለዚህ ሥራውን እና አገልግሎቱን በቅርብ ስለሚያውቁት ሰው የሚሰጥ ምስክርነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያለው ነው፡‹የተወደደ ወንድማችን› ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ በአገር ቤትና ከአገር ውጭ በመዘዋወር የተወደደ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ቀደም የራሱን ወጥ መንፈሳዊ መጻሕፍት በመጻፍና በመተርጎም ለንባብ አብቅቷል፡፡ አሁን ደግሞ እንደ ጊደር ወተት እንደ ገነትም ወይን እየጣፈጠ የሚነበበውን «ቃና ዘገሊላ»ን አዘጋጅቶ አቀረበልን፡፡ መጽሐፉ በአጭር ንባብ ብዙ ምሥጢር የሚገኝበት ነው፡፡ ጠንካራ የዶግማ ሐሳቦችን በቀላሉ ከማስረዳቱ በተጨማሪ ሕይወትን በበጎ ምግባር የሚያንጹ ስብከቶች ሰፍረውበታል፡፡ በእውነቱ በውስጡ ያሉት ቁም ነገሮች የሚገኙባቸውን የቅርብና የሩቅ ዋቢዎች ያለ አንዳች ድካም አሰባስቦ የሚያቀርብልን ቢኖር እንኳን በዚህ መጽሐፍ እንደተጻፈው ጨምቆ ለማውጣትና ለመጠቀም ብዙ መቸገራችን አይቀርም ነበር፡፡

‹የተወደደ ወንድማችንን› እያመሰገንን ነፍሳችንን በንባብ እንመግባት፡፡

ቀሲስ ኀብረት የሺጥላ

የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ፈጣሪያችንና መድኃኒታችንን ጨምሮ ሁሉም በየወገኑ የታደመባት ሁነት እንደነበረች ሁሉ ፤ በዚህም በ‹ቃና ዘገሊላ› መጽሐፍ በርካታ መንፈሳዊ ትምህርቶች ተካተውበታል፡፡ አዘጋጁ ዲያቆን ሄኖክ የመጻሕፍትን ትርጓሜ አራቅቆበታል፡፡ ነገረ መለኮትንና ነገረ ማርያምን አትቶበታል፡፡ የጋብቻንም ምሥጢር ታላቅነትም መስክሮበታል፡፡ እንደ ሰርጉ ማዕድም እጅግ የላመ የጣመ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጽሐፉ የተነሡት ነጥቦች ከዚህ በፊት በተለያዩ ወገኖች የተነሡ ቢሆንም በዚህ ደረጃ አምልቶ ፤ አስፍቶ ማቅረብ ላይ እጥረት ነበረ፡፡ በመሆኑም ለዲያቆን ሄኖክ «አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል...» ለማለት እወዳለሁ፡፡

ዲያቆን ማለደ ዋስይሁን

ህትመት ጃጃው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃ.የተ.የግ.ማ.

ዋጋ ብር 65.00

Scanned by CamScanner